telegram: - @Holy_scriptures

# መስቀል-አልባ ክርስትና



ዶክተር መለሰ ወጉ

## በዶ/ር መለሰ ወጉ ተጽፈው የቀረቡ ሌሎች መጻሕፍት

- ስሜት ያለቦታው
- በጸሎት፥ የማይቻለው ይቻላል
- የአዕምሮ ጭንቀት
- ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ማድረግ
- ጋብቻ፥ እስከ ሞት ወይስ እስከ መፋታት?
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም
- እስቲ ምላስህ!
- የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ - ክፍል አንድ
- የዘመናችን ቤተ የመሪዎቿ መሠረታዊ የአመራር ስልት - ክፍል ሁለት
- ከአስቸጋሪ ሰው ጋር አብሮ መኖር፣ መኅራብት፣ መሥራት፣ማምለክ ይቻላል?
- አሥርቱ ትእዛዛትና የዘመኑ የሞራል ውድቀት
- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፥ በቅድስና ኑሮ እግዚአብሔርን መምሰል
- እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?
- ስንካከስ እንዳንጠፋፋ
- መንፈሳዊ ውጊያ
- ባንስማማ፥ ላለመስማማት እንስማማ

**መስቀል-አልባ ክርስትና**
*"Meskel Alba Kiristina"*
*Crossless Christianity*

የመጀመሪያ እትም፤ መስከረም 2004 ዓ.ም.
First Edition, October 2011

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች፥ እንዲሁም በኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ከታተመው 'አዲሱ መደበኛ' መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ፥ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት፥ በቅድሚያ ከኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ዋና ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright © 2011 by Ethiopian Outreach Ministry
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any manner without written permission from Ethiopian Outreach Ministry except in the case of brief quotations in critical articles and reviews.

Produced by:

Ethiopian Outreach Ministry
P.O. Box 2241
York, PA 17405
United States of America

**Ethiopia Office Address:**
P.O. Box 7888
Addis Ababa, Ethiopia
Phone: 011-251-1-156-4268

http://www.eomusa.org
E-mail: eom@eomusa.org

Printed in Ethiopia

# ማውጫ

መግቢያ .......................................................... 3

1. ያለመስቀል ክርስትና ..........................................11
2. ያለመስቀል ደቀ መዝሙርነት ...............................40
3. በመቀሉ ታማኝነታችን ይፈተሻል ..........................71
4. በመስቀሉ ሙሉ መሰጠታችን ይመዘናል ..................101
5. በመስቀሉ የእምነታችን ጽኑነት ይለካል ..................131
6. በመስቀሉ ታዛዥነታችን ይረጋገጣል ........................150
7. በመስቀሉ ኃይል አለ ............................................171
8. ያለመስቀል ዘውድ የለም ......................................192

   በመታዘዝ ውስጥ መስቀል አለ (ማጠቃለያ ሃሳብ).......222

ዋቢ ጽሁፎች ..........................................................227

# *መግቢያ*

*"ክርስትና"* ኢየሱስን መከተል ከሆነ፣ ምርጥ የሆኑ ጥቂት መንፈሳዊ ሰዎችን ብቻ የሚያቅፍ፣ *"ኃጢአተኛና ደካማ ናቸው"* የሚባሉትን ግን የሚንቅና የሚገፋ ሊመስል ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት የተገለጠው ለጥቂት ቅዱሳን ብቻ ሳይሆን ለኃጢያተኞች፣ ለደካሞችና ተስፋ ላጡ ሁሉ እንደሆነ ቃሉ ይመሰክራል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ መራራ የሆነውን የሞት ጽዋ ሲቀምስ፣ የራሱ የሆኑት ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ብቻውን ሆኖ ነው። አብረውት የተሰቀሉትም፣ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ተመርጠው ሳይሆን፣ ሁለት ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ። ከመስቀሉ ዙሪያ የተገኙትም ልባቸው ካዘነባቸው ጥቂት አማኞች፣ ጥርጣሬና ፍርሃት ከተጠናወታቸው ጥቂት ደቀ መዛሙርቱ በስተቀር፣ አብዛኞዎቹ ጠላቶቹና ተሳዳቢዎች ነበሩ።

በዚያች መራራና አስፈሪ የጨለማ ሰዓት መስቀል ላይ ሆኖ *"የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"* ብሎ ሲጸልይ፣ ለተወሰኑ ጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ ለኃጢያተኞች ሁሉ እንደሆነ እርግጠኞች ነን። በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት በጠላቶቹ መካከል እንኳን እንዳለ ተገልጾ እናያለን። ይሄ በጸጋ የተሞላው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባረፈበት ጊዜ ያፌዘበትን ነፍሰ ገዳይ *"ይቅር"* ያለ አምላክ፣ እኛንም ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ብሎ ደቀ መዛሙርቱ እንድንሆን፣ መስቀሉንም ተሸክመን እንድንከተለው ይጠራናል። ጥሪውን ተቀብለን ብንከተለው ወዴት እንደሚመራን፣ ምን ዓይነት ውሳኔ ማድረግ እንዳለብን፣ እንዲሁም ምን መያዝና ምን መልቀቅ እንዳለብን ይነግረናል። እንድንከተለው ሲጠራን እውነቱን ደብቆ መንገዳችን መስቀል የሌለበት፣ የአበባ ምንጣፍ የተነጠፈበት እንደሆነ አድርጎ በማሳየት አባብሎ እንደ ማይወስደን እርግጠኞች ነን።

*ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቼ እንዳወጣ ምክንያት የሆነኝ፣ በማወቅም* ሆነ ባለማወቅ ክርስትና ርካሽ *ጸጋ* (Cheap grace) *ያለበት እንደሆነ፣*



*መንገዱ ሰፊና መስቀል መሸከምን የማይጠይቅ አድርገው በማቅረብ* እውነት መሳይ ወንጌልን ከሚያስተምሩ አስተማሪዎች ለማስጠንቀቅ ነው። ክርስትና *ርካሽ ጸጋ ያለበት* እንደሆነ አድርጎ ከማቅረብ የበለጠ ቤተ ክርስቲያንን የሚገድል ሌላ አደገኛ ጠላት የለም። *"ርካሽ ጸጋ"* ማለት *ጸጋን እንደ አሮጌ ዕቃ ያለዋጋ እንደተገኘ መቁጠር*፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ውሎ *ያስገኘልንን ደህንነት፣ ያለዋጋ እንደተገኘ* አድርጎ *መቁጠር*፣ ክርስቶስ ስለ እኛ የከፈለውን *ዋጋ አቃሎ* እንደ *መቁጠር* ይሆናል።

ክርስቶስ እኛን ለማዳን የከፈለውን *ዋጋ* ለማሳየት ዮሐንስ፣ *"እርሱም የራሱን መስቀል ተሸክሞ በአራማይክ 'ጎልጎታ' ተብሎ ወደሚጠራው 'የራስ ቅል' ወደ ተባለው ቦታ መጣ"* ይላል (ዮሐ. 19፥17)። ይሄ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ የከፈለውን *ዋጋ* ለማሰብ፣ ለአዕምሯችን በጣም ይተል ቅብናል። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ *መሞት*፣ ስቃዩን እጅግ *መራራ* የሚያደርገው፤ የተሰቀለውን ሰው ቶሎ የማይገድለው *መሆኑ* ነው። በመስቀል ላይ እንዲሞት የተፈረደበት ሰው ቀላል ሞት እንዲሞት ሳይሆን በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ በጸሀይ፤ በብርድ፤ በረሀብና በውሃ ጥም ለረጅም ጊዜ ተሰቃይቶ እንዲሞት ነው። በስቅላት እንዲሞቱ የተፈረደባቸው ወንጀለኞች፣ አንዳንዶቹ ነፍሳቸው የሚወጣው አንድ ሳምንት ያህል *መስቀሉ* ላይ ከተሰቀሉ በኋላ ነው። ኢየሱስ ግን ለመሞት ያን ያህል ጊዜ አልፈጀበትም። የዚህም ዋናው ምክንያት ከመስቀሉ በፊት ብዙ ግርፋትና ድብደባ ስለደረሰበት እንደሆነ የነገረ መለኮት ምሁራን ይገልጻሉ።

ኢየሱስ የሞተው የውርደት ሞት ነው። የለበሰውን ከላዩ ገፍፈው *ዕጣ ተጣጣሉበት*። ምራቃቸውን ተፉበት። ቀለዱበት፤ በጥፊ እየመቱ አንገላቱት። ሰውነቱ እስኪተለተል ድረስ በጅራፍ ገርፉት። ዘውድ ሲገባው የሾህ አክሊል በራሱ ላይ ደፉበት። ራስ ራሱን በመቃ ደበደቡት። እጆቹንና እግሮቹን በሚስማር ጠረቀቁት። የሚሰቀልበትን፣ ከአቅሙ በላይ የሆነውን ትልቅ የእንጨት *መስቀል* አሸከሙት። እየወደቀ እየተነሳ የጎልጎታን ተራራ እንዲወጣ አደረጉት። በመጨረሻም በሰማይና በምድር *መካከል* አንጠለጠሉት፤ በጦር ጎኑን ወጉት። ከጎኑም ደምና ውሃ ፈሰሰ።

ክርስቶስ የቀመሰው የመስቀሉ ስቃይ በከፊል ይህን ይመስል ነበር። በዚህ ዓይነት የተዘረጋልንን ጸጋ ርካሽ አድርጎ መቁጠር፣ ምሕረት ያሳየንን ጌታ ማሳዘን አይሆንብንም?

የክርስትና እምነት መስቀል መሸከም የሌለበት አለመሆኑን የበለጠ የምንረዳው፣ *"መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"* (የማቴ. 10፥38) የሚለውን፣ ራሱ የተናገረውን ቃል ስንሰማ ነው። ሁላችንም የራሳችን የሆነ መስቀል አለን። ይህን እውነት ስንረዳ፣ "መስቀሌ ምን ዓይነት ይሆን?" ብለን እንጠይቃለን እንጂ፣ መስቀል ሳንሸከም ክርስቲያን መሆን ስለማንችል፣ ከመስቀሉ ሸሽተን ለመኖር ሙከራ አናደርግም። ይህን እውነት የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስም ከመስቀል ሕይወት ለማምለጥ ከመሞከር ይልቅ፣ *"...የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ..."* (ፊልጵ. 3፥11) አለ። ጳውሎስ ይህን ሲል፣ *"... እርሱ የተሸከመውን ዓይነት መስቀል መሸከም እፈልጋለሁ"* ማለቱ ነው። ይሄም ከልቡ ተጨምቆ የወጣ እንጂ፣ ለማለት ያህል ብቻ የተናገረው እንዳልሆነ በሕይወቱ አስመስክሯል። እኔና እናንተስ የልባችን ምኞት ምን ይሆን? *"ኢየሱስ የቀመሰውን መከራ ለመቅመስ፥ የጠጣውን መራራ ጽዋ ለመጠጣት፥ እርሱ የሞተውን ዓይነት የመስቀል ሞት ለመሞት ይሆን?"*

እኔና እናንተ *"መስቀል"* የምንለው ክርስቶስ የተሸከመውን ዓይነት ይሆን? ወይስ በወርቅ፥ በነሀስ ወይም በብር የተሠራ፥ አንገታችን ላይ የምናንጠለጥለውን ዓይነት ጌጥ ይሆን? ወይስ ሮማውያን ከፍተኛ ወንጀል የፈጸመውን ሰው በሰማይና በምድር መካከል በማንጠለጠል በሞት የሚቀጡበት እንጨት ይሆን? ይህ ቢሆን ኖሮ በተለይ በአሁኑ ዘመን ያለነው ክርስቲያኖች ምንም ዓይነት ስደት ቢደርስብን በመስቀል ላይ ተሰቅለን *ስለማንሞት፣ "መስቀሉ እኛን አይመለከተንም"* በማለት ችላ እንለው ነበር።



*"መስቀል"፥* እኔና እናንተ በራሳችን ኃጢአት ምክንያት የምንቀምሰው የመከራ ጽዋ ቢሆን ኖሮ፣ መስቀል ተሸካሚዎች ወንበዴዎችና ነፍሰ ገዳዮች ብቻ ይሆኑ ነበር። እውነተኛው መስቀል ግን፣ *አማኝ ክርስቶስን በማወቁና በመከተሉ፥ ፍጹም ታዛዥ በመሆኑ፥ ሕይወቱን ስለ ክርስቶስ ሲል በቅድስና በመኖሩ ምክንያት የሚቀምሰው ስቃይ፥ ያ "መስቀል" ነው። "በመታዘዝ ጎዳና ላይ ሁልጊዜ መስቀል አለ"* የሚባለው ለዚህ ነው። *"በሕይወቴ መስቀል አጋጥሞኝ አያውቅም"* የሚል ክርስቲያን ቢኖር፥ ያለመስቀል ክርስትና ስለሌለ፣ ያ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን መሆኑ ያጠራጥራል። መስቀላችን ምን ዓይነት ይሆን?

- *የአንዳንዶቻችን መስቀል ስለ ክርስቶስ ስንል የሚደርስብን መጠላት፥ መገፋት፥ ወይም በኃጢአት ከሚገኝ ብልጽግና ይልቅ ድህነትን በመምረጣችን የሚደርስብን የኑሮ ጉስቁልና ሊሆን ይችላል።*
- *የሌሎቻችን መስቀል ደግሞ ስለ ክርስቶስ ስንል የሚደርስብን ስደትና መከራ ይሆናል።*
- *የሁላችንም መስቀል መጠኑና ዓይነቱ የተለያየ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ማናችንም ብንሆን ልንሸከመው ከምንችለው በላይ መስቀል የማንሸከም መሆናችን ነው።*

ምናልባት የተሰጠን መስቀል ከባድና አስጨናቂ ቢሆንብን፣ ለመሸከም የሚያስችለንን ጸጋ ያበዛልናል እንጂ መስቀል ከመሸከም ነጻ አያደርገንም። ስለዚህ በማጉረምረም ፈንታ "ምን ያህል ቢታመንብኝ ነው?" በማለት በደስታ መስቀላችንን መሸከም ይገባናል። በሌላ በኩል ደግሞ እንድንሸከመው የተሰጠን መስቀል ትንሽ መስሎ ከታየን፥ የተሰጠንን ንቀን፥ ያልተሰጠንን መስቀል እንዳንሸከም መጠንቀቅ አለብን። ከሁሉ የበለጠ የሚያሳዝነው፥ በአሁኑ ዘመን ክርስትና መስቀል የሌለበት እምነት እንደሆነ፣ ወይም "መስቀል የሌለበት የክርስትና ሕይወት መኖር ይቻላል" ብለው የሚያስተምሩ አስተማሪዎች

በብዛት መኖራቸው ነው። ምድራዊ (ሥጋዊ) አባት *"አልፈልግህም"* ብሎ የካደውን፣ በጠላትነት ተነስቶበት ኮብልሎ የጠፋውን ልጁን ቢወድደው፣ ቢፈልገው፣ *"በአንተ ምትክ እኔ ልሙትልህ"* ቢለው፣ ያ አባት ምን ያህል የሚደነቅና የሚወደድ አባት ይሆን ነበር?

ሰማያዊው አባታችን እግዚአብሔር፣ ለእኔና ለእናንተ ከሥጋዊው አባታችን የበለጠ ያሳየንን ፍቅር ለመረዳት ከአዕምሯችን በላይ ይሆንብናል። የራሳችንን ፈቃድ ተከትለን፣ "በሕጉ አንመራም፣ ለእርሱ አንገዛም" ብለን በምንገዝበት ጊዜ እንኳን ፍቅሩን አልቀነሰብንም። ስለ ኃጢአታችን ከፍተኛ ዋጋ በመክፈል ለእኛ ያለውን ፍቅር ገለጸልን። ዮሐንስ *"ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለ ሰጠ፤ ፍቅር ምን እንደሆነ በዚህ እናውቃለን" (1 ዮሐ. 3፥16)* ይላል። ኃጢአተኛ በመሆናችን ሲኦል ተዘጋጅቶ ይጠብቀን ነበር። ነገር ግን፣ ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር ግድ ብሎት፣ እኛን ከሞት ፍርድ ለማዳን፣ በእኛ ምትክ ሆኖ በሰማይና በምድር መካከል ተንጠልጥሎ፣ የውርደት ሞት ሞተልን። ከዚህ የበለጠ ፍቅር የት ይገኛል?

ኢየሱስ ያለፈበት መከራና ስቃይ ከላይ የገለጽነው ብቻ አይደለም። የሚወዳቸው፤ *"የቅርቤ ናቸው፤ ሕይወታቸውን ስለ እኔ አሳልፈው ይሰጣሉ"* ብሎ የሚያምንባቸው ሰዎች ሲከዱት የተሰማው የልብ ስብራት ከፍተኛ እንደነበረ እናምናለን። በዚህ አቅጣጫ ኢየሱስ ሊሰማው የሚችለውን የስሜት መጎዳት በመጠኑም ቢሆን መረዳት የምንችለው፤ በግል ሕይወታችን የደረሰብንን ሁኔታ ስንመለከት ብቻ ነው። የእኛ ናቸው የምንላቸው፤ በሕይወታቸው ከፍተኛ ሚና የተጫወትን፤ የረዳናቸው፤ የደገፍናቸው፤ በችግራቸው ጊዜ እጃችንን የዘረጋንላቸው፤ ልባችንና ቤታችንን ከፍተን የተቀበልናቸው፤ ያጽናናናቸው ሰዎች በምክንያትም ሆነ ያለምክንያት ሲሸሹን፤ ፊታቸውን ሲመልሱብን፤ አንዳንዶችም ይባስ ብለው ጠላት ሲሆኑብን ልባችን ያዝናል። በዚህ ዓይነት የሚሰማንን የስሜት መጎዳት ሊረዱልን የሚችሉት በውስጡ ያለፉ ሰዎች ብቻ እንደሆኑ እናውቃለን። ክርስቶስ የራሱ የሆኑ



ደቀ መዛሙርት ትተውት ሲሸሹ፤ አንዳንዶችም ሲከዱት ምን ያህል የስሜት ጉዳት እንደደረሰበት መረዳት እንችላለን። በእጆቹ ላይ ሚስማር ከመቱት ወታደሮች ያላነሰ፤ ደቀ መዛሙርቱ በክህደታቸው ያደረሱበት ጉዳት ይበልጣል።

ኢየሱስን የሰቀሉት፤ የገረፉት፤ ልብሱን ገፍፈው ራቁቱን በሰማይና በምድር መካከል ያንጠለጠሉት አይሁዶች፤ የሮማ ወታደሮች ብቻ አይደሉም። እኔና እናንተም ጭምር ነን። በመከራው ጊዜ ከአጠገቡ የሸሹት፤ በገንዘብ የሸጡት፤ የካዱት ይሁዳ አስቆሮቱና ጴጥሮስ ብቻ ሳይሆኑ እኛም በክህደቱ ውስጥ አለንበት። ኢየሱስን በመስቀሉ ላይ አጣብቆ የያዘው በእጆቹ ላይ የጠረቀቋቸው ሚስማሮች ሳይሆኑ፤ ከመስቀሉ እንዳይወርድ የከለከሉት በወቅቱ ይጠብቁት የነበሩት የሮማ ወታደሮች ሳይሆኑ ለእኔና ለእናንተ ያለው ፍቅር ነው።

መከራውን መቀበል አቅቶት፣ እንዲሁም *"አምላክ ከሆንክ ከመስቀሉ ውረድ"* ሲሉት ኃይሉን ለማሳየት ሲል ብቻ፣ በሰይጣን ተገፍቶ ከመስቀሉ ቢወርድ ኖሮ፤ እኔና እናንተ የደህንነታችን መንገድ ለዘለዓለም የተዘጋ ይሆን ነበር። ይህን ለመሰለው ፍቅር ትክክለኛውን መልስ አለመስጠት፤ መጀመሪያ ከሰቀሉት ሰዎች ያላነሰ በደል በእርሱ ላይ መፈጸም ይሆናል። *"ስለ እኔ ነው የተሰቃየኸው፤ ስለ እኔ ነው ደምህ የፈሰሰው፤ ስለ እኔ ነው በጦር የተወጋኸው፤ ስለ እኔ ነው የደም ላብ ያላበህ፤ ስለ እኔ ነው ራቁትህን በሰማይና በምድር መካከል የተንጠለጠልከው"* በማለት ይህን ጌታ ወድደንና አክብረን አለመቀበል፤ በዚህ ጌታ ላይ ትልቅ በደል መፈጸም ይሆናል። ደቀ መዛሙርቱና እንዲሁም ከዳተኛው ጴጥሮስ ያገኙትን ሁለተኛ ዕድል፤ የተዘረጋላቸውን ምሕረትና ይቅርታ እንደተቀበሉት፤ እኛም በተደጋጋሚ የተዘረጋልንን ዕድል ባንቀበል ኖሮ ለዘላለም በጠፋን ነበር።

የሚያስደንቀው ነገር ኢየሱስ የሞት ፍርድ ሲፈረድበት፣ *"ይህ ሰው የተከሰሰው ያለአግባብ ነው"* የሚል፣ እንዲሁም እርሱን የሚደግፍ፣ ወይም ምንም ዓይነት ወንጀል ያልፈጸመ መሆኑን የሚና

ገርለት፣ ምስክር ሆኖ የሚቀርብ አንድም ሰው አለመገኘቱ ነው። ከሳሾቹን *"የምታደርጉት ከሕግ ውጪ ነው"* ብሎ በድፍረት ለክርስቶስ የቆመ ባለሥልጣን አንድም አልነበረም። ተርበው የመገባቸው፥ ከልዩ ልዩ ደዌ የፈወሳቸው ሰዎችም እንኳን መሞቱን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ አላደረጉም። ሌላው ቀርቶ ኢየሱስ ራሱ እንኳን "ሞት አይገባኝም" ብሎ አልተከራከረም። እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱ ልጁን ከመስቀል ሞት ለማዳን "ተዉት አትንኩት" በማለት አንድም ቃል አልተናገረም። እንዲሁም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሲሞት፣ "በእርሱ ምትክ እኔ ልሙትለት" በማለት ራሱን ለመስጠት የቀረበ አንድም ሰው አልነበረም። ሌላው ቀርቶ በሀሰት ከሰሰው በሮማውያን ባለሥልጣናት ፊት ያቀረቡት አይሁዳውያን የሃይማኖት መሪዎች እንኳን ኃላፊነቱን ለመውሰድ አልደፈሩም። እንዲያውም *"ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን"* አሉ። ጲላጦስም "ከደሙ ንጹህ ነኝ" ብሎ እጁን ታጥቦ አሳልፎ ሰጣቸው። ሁሉም መሞቱን ወይም መወገዱን ይፈልጉ ነበር። *"ሮማውያንም ሆኑ አይሁዶች፥ ኢየሱስን በመስቀል ላይ ለመሞቱ ምክንያቶቹ እኛ አይደለንም"* ብለው ካዱ። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞት የብዙዎች አስተዋጽኦ አለበት። የሞተው ስለ እኛ ኃጢአት በመሆኑ፣ በዚያን ዘመን ባንኖርም፣ የእኛም አስተዋጽኦ አለበት።

*መለሰ ወት*



# 1

# ያለመስቀል ክርስትና

***"ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፤ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም"***

***(ዕብ. 9፡22)***

***"...የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ በል ከመስቀል ውረድ ይሉት ነበር"***

***(ማቴ 27፡40)***

እውነተኛዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ኃይሏን ያገኘችው፣ መከራዋን ታግሳ ያለፈች በመሆኗ ነው። መሠረቷን ሳትለቅ ጸንታ ለመቆም የቻለችው፣ ብዙ ነገር ለመተው ፈቃደኛ በመሆኗ ነው። መሠረቷ ብርቱና ጽኑ በመሆኑ፣ ደሟን እንደ ውሃ ለማፍሰስ ፈቃደኛነቷን አሳይታለች። የሰናፍጭ ዘር የሚያክለው እምነቷ በዕንባዋና በፈሰሰው ደሟ የረሰረሰ በመሆኑ፣ አጥፊ የሆነ ኃይለኛ ማዕበል ቢነሳባትም፣ ሥሮቿ በሰፊው ተዘርግተው አለቱን አንቀው በመያዛቸው እስከ ዛሬ ጸንታ ቆመች እንጂ፣ አልወደቀችም። ክርስቶስ ዳግመኛ እስከሚመጣበት ጊዜም ድረስ ጸንታ ትቆማለች። በዚህም ውስጥ እኛም ወንጌሉን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ የራሳችንን ድርሻ ለመፈጸም፣ የሚያስከፍለውን ማንኛውንም ዓይነት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለብን። የዚህም መጽሐፍ አንዱ ዓላማ ይህንኑ እውነት አማኞች እንዲያውቁት ለማድረግ ነው።

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጽኑ በሆነው የመሠረት ድንጋይ ላይ የታነጸች ነች። አመጽን የምታሸንፈውም የሚነሱባትን ጠላቶቿን መልሶ በማጥቃት ሳይሆን በፍቅር ነው። ኃይለኛውን ጠላት ድል የምትመታው በሌላ ኃይል ሳይሆን፣ በትዕግሥቷ ነው። ይህንን እውነት የተረዱት ልጆቿ

በየቀኑ ለመሞት ዝግጁ መሆን አለባቸው። በእግራቸው ቢሮጡም፣ ከፌረስ ጋር መወዳደር የሚችሉ ናቸው። የተጠሩት ክርስቶስን እንዲያምኑ ብቻ ሳይሆን፣ በእርሱ ምክንያት ወይም ስለ እርሱ ተሰቃ ይተው እንዲሞቱም ጭምር ነው። የሚያሳድዷቸው ጠላቶቻቸው "ንፋስ እንደሚወስደው ገለባ ጠፉ" ብለው ሲጠብቋቸው፣ በሰፌ መሬት እንደተዘራ ዘር ሆነው በዘመናት ሲያድጉና ሲያብቡ እንዲሁም ሲበዙ ይታ ያሉ።

የታወቀው ጸሀፊ፣ ኤ. ደብዩ ቶዘር *(A. W. Tozer)* ሐዋርያው ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬ ሞቻለሁ"* ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ለማስረዳት፣ በመስቀል ላይ የተሰቀለ ሰው ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነጥቦች በመዘርዘር ይገልጻል። ይኸውም፥

*"1ኛ፣ በመስቀል ላይ የተሰቀለ ሰው የሚመለከተው ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ እንደሆነ፣*

*2ኛ፣ የተሰቀለ ሰው ወደ ኋላ መመለስ የማይችል መሆኑን፣*

*3ኛ፣ የተሰቀለ ሰው ስለ ወደፊት ሕይወቱ ዕቅድ የማያወጣ መሆኑን"* ገለጸ።[1]

በዚህ ዓይነት ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለ ክርስቲያንም፣ ወደፊት እንዴት መኖር እንዳለበት ዕቅድ ስለማያወጣ፣ ከማንም ጋር አይጋጭም። የራሱ የሆነ ክብርና ዝና የሌለው ስለሆነ፣ የሚኩራበት ምክንያት የለውም። ባለው ሀብት መጠቀም ስለማይችል፣ *"ሌባ ይሰርቅብኝ ይሆን?"* ብሎ አይጨነቅም። እንዲሁም *"የእኔ ነው"* የሚለው ነገር ስለሌለው፣ የሚቀናበት ምክንያት የለውም። ሞቶ ያለቀለት ስለሆነ፣ *"እሞት ይሆን?"* ብሎ አይፈራም። ይህንን ዓይነት አቋሙን ለመግለጽ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ያለው።

[1] Paul Erb, ed. From the Mennonite Pulpit, Herald Press, Scottdale, PA 1965.



## 1. በብዙዎች ዘንድ ችላ የተባለ የመስቀሉ ኃይል

ሐዋርያው ጳውሎስ *"ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ተሰቅሎ ሞተ፤ የሚለው ቃል ለሚጠፉት ሰዎች እንደ ሞኝነት ይቆጠራል፤ ለምንድን ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው"* (1 ቆሮ 1፡18-25) ይላል። እዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ቁጥር 23 ላይ ደግሞ *"...ለአይሁዳውያን መሰናከያ ነው፤ ለግሪካውያንም ሞኝነት ነው"* ይላል። በዚህ ዓይነት የመስቀሉ ኃይል በብዙዎች ዘንድ ችላ እንደተባለ እናያለን።

- *(1) ለአይሁዶች የመስቀሉ ነገር መሰናከያ የሆነበት ምክንያት ሕጋቸው "በመስቀል ላይ የሚሞት የተረገመ ነው" ስለሚል ነው። እንደ አይሁዶች እምነት ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተሰቀለ በመሆኑ፣ የተረገመ ነው። ስለዚህ አይሁዶች የተረገመ መሲህ ስለማይፈልጉ፣ ኢየሱስን እንደ መሲህ መቀበል አልዋጥ ም ብሏቸው ነበር። ያልተረዱት ነገር ግን የተረገመ የሆነበት ምክንያት ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ እነርሱ ኃጢአት ብሎ እንደሆነ፣ ወይም እነርሱን ከእርግማን ለማዳን ሲል የእነርሱን እርግማን የተሸከመ መሆኑን ነው።*
- *(2) ለግሪካውያን ደግሞ የመስቀሉ ነገር ሞኝነት ነው። ኢየሱስ ኃያል አምላክ ከሆነ፣ እንዴት ደካማ በሆነው በሰው እጅ ይሰቃያል? ብለው ይጠይቃሉ። እግዚአብሔር የሚሰቃይ አምላክ ነው ብሎ ማሰብ ከአዕምሯቸው በላይ ስለሚሆንባቸው፣ የመስቀሉ ነገር ለግሪኮች ሞኝነት ሆኖባቸዋል። ግሪኮች እግዚአብሔር "አፓትያ" ነው ይላሉ። ይህም ማለት እግዚአብሔር ስሜት የለውም ማለት ነው። እግዚአብሔር ስሜት የሌለው ከሆነ ሀዘን፣ ደስታ፣ ወይም ቁጣ እንደማያውቀው፣ እንዲሁም ከእርሱ ውጪ የሆነ ሌላ ነገር የእርሱን ስሜት ሊነካ ወይም ሊለውጥ የሚችል ኃይል ፈጽሞ እንደሌለ ያምናሉ። ስለዚህ ደካማ በሆነው በሰው እጅ የሚሰቃይ አምላክ ከሆነ፣ ለግሪኮች የመስቀሉ ነገር ሞኝነት ይሆንባቸዋል።*

ግሪኮችም ሆኑ አይሁዶች የመስቀሉን ነገር ችላ ያሉት ከላይ በጠቀስነው ምክንያት ነው። በዘመናችንም ያሉ አንዳንድ ሰዎች ከሁለት ሺ ዓመት በፊት በመስቀል ላይ የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዛሬ ከእነርሱ ሕይወት ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት ከአዕምሯቸው በላይ ስለሚሆንባቸው፣ መስቀሉን መቀበል ያስቸገራቸው ይመስላሉ። የመስቀሉ ምስጢር በትክክል ከገባቸው ሰዎች መካከል አንደኛው ሐዋርያው ጳውሎስ የመስቀሉ ተካፋይ ለመሆን ያለውን ምኞት ሲገልጽ፣ *"...የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ" ይላል (ፊልጵ. 3፥11)።* እኛም ስለ መስቀሉ ትክክለኛ የሆነ መረዳት ሲኖረን በመስቀሉ ውስጥ ያለውን ኃይልና ጥበብ ለማግኘት የመስቀሉ ተካፋይ ለመሆን እንናፍቃለን።

በዓለም ውስጥ ኃጢአትን ሊደመስስ ወይም ሊያጠፋ የሚችል ከመስቀሉ በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት ኃይል የለም። በመስቀሉ ዙሪያ በተፈጠሩት ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ምክንያት፣ በመስቀሉ ላይ ስላረፈው ክርስቶስ የተለያዩ ሰዎች የተለያየ አስተያየት ሰንዝረዋል። ሮማዊው የመቶ አለቃ፣

> *"በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ነው"* በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል።
>
> በሌላ በኩል ደግሞ ቅናት እንደ እሳት ያቃጠላቸው የካህናት አለቆች፣ የኦሪት ሕግ መምሕራንና ሽማግሌዎች ደግሞ "የእግዚአብሔር ልጅ ነው" በማለት ፈንታ፣
>
> *"...የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እስቲ ከመስቀል ውረድ፤ ...ራስህንም አድን"*እያሉ ከመስቀሉ ሊያወርዱት ሞክረዋል።

በየትኛውም ዘመን *"ክፋት"* ወይም ኃጢአት ብርቱ ኃይል ያለው ስለሆነ፣ የሰውን ሕይወት ዛሬም ቢሆን ጨምድዶ ይዟል። ከመስቀሉ በስተቀር ሊያሸንፈው የሚችል ሌላ ምንም ዓይነት ኃይል እንደሌለ እናውቃለን። የክርስትና ሕይወት ደስታና ሰላም የሞላበት ሕይወት ይሁን



እንጂ፣ መስቀል የሌለበት ሕይወት አይደለም። እኔና እናንተ እውነተኛ ክርስቲያኖች ከሆንን ከመስቀል ሕይወት ሸሽተን መኖር ፈጽሞ እንደ ማንችል ማወቅ አለብን። ወደ ክርስትና እምነት ከመጣንበት ቀን ጀምሮ በምድር ላይ የተወሰነልንን ዘመን ጨርሰን እስከምንሄድበት ጊዜ ድረስ የመስቀሉ ተካፋዮች ነን። ጳውሎስ፥

- *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ እኔም አሁን ህያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ ከወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" ይላል (ገላት. 2፥20)።*

ሐዋርያው ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ሲል፣ *"የተሰቀለ ክርስቲያን ሆኛለሁ"* ማለቱ ነው። የተሰቀለውን ክርስቲያን ከማየታችን በፊት በቅድሚያ ስለ ተሰቀለው፣ የራሱን መስቀል ስለ ተሸከመው ኢየሱስ እንመልከት። ስለ መስቀሉ ስቃይ ብዙ ጸሀፊዎችና ምሁራን ምን ያህል አስከፊና መራራ እንደሆነ ጽፈዋል። የታወቀው አይሁዳዊው ጸሀፊ *ክላውስነር፥* የመስቀል ሞት ምን ያህል የከፋ መሆኑን ሲገልጽ፣

- *"ወንጀል ፈጽሟል የተባለውን ሰው ለመቅጣት በመስቀል ላይ ማንጠልጠልን የመሰለ የሚዘገንን፣ አስከፊና ጭካኔ የሞላበት ድርጊት ሌላ አይገኝም" አለ።*

ሰውን በመስቀል ላይ አንጠልጥሎ እንዲሞት ማድረግ የተጀመረው በጥንት ዘመን *"ፐርሺያ"* ውስጥ ሲሆን፣ ታሪካዊ የሆነ ምክንያት ነበራቸው።

- *መሬት (ምድር) ጣዖታቸው ሲሆን፣ አርመዙድ ብለው ይጠሩት ነበር። ይሄ አርመዙድ እየተባለ የሚጠራው አምላካቸው የተቀደሰ በመሆኑ ማንኛውም ወንጀለኛ በምድር ላይ ቢገደል ምድሪቷን ወይም አምላካቸውን ያረክሳል (ያጎድፋል) ብለው ስለሚገምቱ ወንጀለኛው መሬት እንዳይነካ በሰማይና በምድር መካከል በመስቀል ላይ ያንጠለጥሉት ነበር። ቀጥሎ ይህን ዓይነት ልምምድ ከፐርሺያ ወደ ሰሜን አፍሪቃ መጣ። ሮማውያንም ሀሳቡን*

*ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙት ከሰሜን አፍሪካ እንደሆነ ታሪክ ይመሰክራል። ሮማውያን ይህን ዓይነቱን ቅጣት ይፈጽሙበት የነበረው፣ በጣም ኃይለኛ በሆኑ ወንጀለኞች፣ ጠፍተው በሚሸሹት ባሪያዎች፣ ወይም በጣም ልክስክስና ወራዳ በሆኑ ወንጀለኞች ላይ ነበር። በወቅቱ ኢየሱስን ያዩት ከላይ በገለጽነው ዓይነት ነው።*

*ክላውስነር የተባለ አይሁዳዊ ጸሀፊ፣ ስለ መስቀል ሞት ሁኔታ ቀጥሎ ሲያብራራ እንዲህ ይላል፥*

- *"በስቅላት እንዲሞት የተፈረደበት ወንጀለኛ ቀደም ሲል በደረሰበት ግርፋትና ድብደባ ደሙን እያንጠባጠበ፣ እጆቹ በእንጨት ላይ በሚስማር ይጣበቅና ወደ ላይ ከፍ ተደርጎ ይንጠለጠላል። በረሀብና በውሃ ጥም ተንገላትቶ እንዲሞት በመስቀል ላይ ለብዙ ሰዓት፣ አንዳንዴም ለብዙ ቀናት ይተዋል። በመስቀል ላይ የሚንጠለጠለው ወንጀለኛ ራቁቱን በመሆኑ በደምና በቁስል የተለወሰውን አካሉን ዝንቦች ቢበጠብጡትም የመከላከል አቅም ወይም ችሎታ" አይኖረውም።*

በጥንት ዘመን ሮማውያን በመስቀል ላይ እንዲሞት የፈረዱበትን ወንጀለኛ ወደ ሚሰቀልበት ስፍራ ሲወስዱት፣ የሚሰቀልበትን የእንጨት መስቀል እንዲሸከም ያስገድዱት ነበር። የሞት ፍርድ ለምን እንደተፈረደበት ወይም የወንጀሉን ዓይነት ጽፈው አንገቱ ላይ ያንጠለጥሉታል፤ ወይም አንድ ወታደር ጽሁፉን ይዞ ከፊቱ እየቀደመ እንዲሄድ ያደርጉ ነበር። ወንጀለኛውን መስቀሉ ላይ ከሰቀሉት በኋላ፣ ከመስቀሉ ጫፍ ላይ ጽሁፉን ያደርጉት ነበር። ያ የእኛ አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት መስቀል ጫፍ ላይም የወንጀሉን ዓይነት ለመግለጽ *"የአይሁድ ንጉሥ"* የሚል ጽሁፍ ተደርጎበት ነበር። ያልተረዱት ነገር "የአይሁድ ንጉሥ" ብቻ ሳይሆን፣ የዓለም ንጉሥ መሆኑን ነው።

ሮማውያን በስቅላት የሚቀጡትን ወንጀለኛ ወደ መሰቀያው ሥፍራ ሲወስዱት የበለጠ ለማሰቃየትና ለማዳከም ሲሉ የሚወስዱት በአቋራጭ



መንገድ ሳይሆን በረጅሙ ነው። ይህን የሚያደርጉበት ሌላው ምክንያት፣ ብዙዎች በወንጀለኛው ላይ የደረሰውን አይተው ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ለማስጠንቀቅ ነው። ኢየሱስም ከመስቀሉ ላይ ከማረፉ በፊት እየወደቀ፣ እየተነሳ የቀራንዮን ተራራ የራሱን መስቀል ተሸክሞ መውጣት ነበረበት። ክርስቶስ የመስቀልን ሞት ወደሚቀምስበት ጎልጎታ እየተባለ ወደሚጠራው ሥፍራ ተወስዶ እጆቹ በሚስማር ከእንጨቱ ጋር ሲጣበቁ፣ እግሮቹ ግን በሚስማር ሳይሆን በገመድ መታሠራቸውን አንዳንድ ምሁራን ይገልጻሉ። በመስቀል ላይ ተሰቅለው በሞት እንዲቀጡ የሚደረጉ ወንጀለኞች ስቃያቸው ከፍተኛ ስለሚሆን፣ አንዳንድ በጎ አድራጊ ሰዎች በሥፍራው ተገኝተው፣ ስቃዩ እንዳይሰማቸው ለማድረግ ከሀሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ ያጠጧቸው ነበር። ኢየሱስ ግን የቀረበለትን የስቃይ ማስታገሻ "እምቢ!" አለ። ምክንያቱም የሞትን ስቃይ፣ እንዲሁም መራራነቱን አንዳችም ሳያስቀር እስከ መጨረሻው ድረስ ያለአንዳች ማደንዘዣ መቀበልን ስለ መረጠ ነው። ክርስቶስ የቀመሰው የመስቀል ስቃይና ሞቱ የሰው አዕምሮ ከሚገምተው በላይ ነው። የሰቀሉት ባለሥልጣናት፣ የሮማ ወታደሮች፣ እንዲሁም ሁኔታውን ለመመልከት የተሰበሰበው ሕዝብ ክርስቶስ ብቸኛና ረዳት የሌለው መሆኑን እንደተገነዘቡ እርግጠኞች ነን። ነፍሰ ገዳዩ በርባን እንኳን፣ "ይለቀቅ!" የሚል ጩኸት የሚያሰሙለት ሰዎች ነበሩት። ኢየሱስ ግን ብቸኛ ነበር። ሁላችንም በመስቀሉ ዙሪያ፣ በአዕምሯችን የሚመላለሱ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉን፥

- *"የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ መሞት ለምን አስፈላጊ ሆነ?*
  - *ሰው ደህንነትን እንዲያገኝ ከሆነ፣ የሚድንበትን ሌላ መንገድ እግዚአብሔር ለምን አላዘጋጀም?*
    - *ኢየሱስ ከመስቀል ላይ መውረድ የሚያስችለው ኃይል እያለው ለምን አልወረደም? በመስቀል ላይ መራራ የሆነ የመከራ ጽዋ መጠጣቱ ለምን አስፈላጊ ሆነ?*

⊙ *የሰው ልጅ ደህንነት የእግዚአብሔርን ልጅ በመስቀል ላይ መሞትን ለምን የሚጠይቅ ሆነ?"*

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች በብዙዎቻችን አዕምሮ ውስጥ የሚመላለሱና አጥጋቢ መልስ ያላገኘንላቸው ናቸው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከተሰቀለበት ቀን አንስቶ አሁን እኛ እስካለንበት ዘመን ድረስ፣ *"የመስቀሉን ምስጢር"* ሰው ውስን በሆነው አዕምሮው ሊረዳው ያልቻለው፣ ወይም ትርጉም ያላገኘለት ነገር ነው። ፈጣሪው በተፈጣሪው እጅ በመስቀል ተሰቅሎ መሞት፣ የሰው አዕምሮ ሊረዳውና ሊቀበለው ከሚችለው በላይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለብዙዎች ፍጹም ሞኝነት መስሎ የሚታይ ነገር ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ፣

⊙ *"ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ የሚለው ቃል ለሚጠፉት ሰዎች እንደ ሞኝነት ይቆጠራል..." ያለው (1 ቆሮ.1፡18)።*

የሚያስደንቀን የእርሱ መስቀል መሸከምና በመስቀል ላይ መሞት ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን መከተል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው መስቀሉን መሸከም ያለበት መሆኑ ነው። *"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከ ተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ስላለ (የማቴ. 10፡38)፣* መስቀሉን ሸሽተን መኖር አንችልም። እንዲሁም ከመስቀሉ ውጪ ደህንነትን የምናገኝበት ሌላ መንገድ ስለሌለ፣ መስቀሉን ችላ ማለት አይሆንልንም። የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን የግድ መስቀሉን መሸከም አስፈላጊ ስለሆነ፣ ራሳችንን ክደተን፣ መስቀሉን ተሸክመን *(ማር. 8፡34)* እንድንከተለው ቀጥተኛና ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ሰጠን እንጂ፣ *"መስቀሉን ለመሸከም ፈቃዳችሁ ነው ወይ?"* በማለት በሀሳቡ እንስማማ እንደሆን አልጠየቀንም።

## 2. እግዚአብሔር የኢየሱስን በመስቀል መሞት ሲፈቅድ፣ ምን ያህል ኃጢአትን እንደሚጠላ ያሳያል

ኢየሱስ የመስቀል ሞት እንዲሞት ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በእግዚ አብሔር የታቀደ ነው። ኢየሱስ በምድር ያሳለፈው ሰላሳ ሶስት ዓመት



ያከተመው፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሲሞት ነው። ኢየሱስ እንደገና በእኛ ዘመን ቢወለድ፣ በአሁኑ ዘመን ያለነው ሰዎች ስለ ኢየሱስ የተለየ አመለ ካከት ይኖረን ይሆን? ምርጫ ቢሰጠን ከሞት ፍርድ ነጻ እንዲሆን የምንመ ርጠው በርባንን ይሆን ወይስ ክርስቶስን? ሕዝቡ በአንድ ድምጽ *"ይሰቀል!"* ብለው በኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ እንደፈረዱበት እኛም እንፈ ርድበት ይሆን? የምናስተላልፈው ፍርድ ከእነርሱ የተለየ ይሆናል ብዬ አላምንም። በሌላ ዓይነት ሞት እንዲሞት ሳይሆን፣ በክርስቶስ ዘመን እን ደነበሩት ሰዎች እኛም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት እንፈርድበት ነበር።

የኢየሱስ ሞት ድንገት የተፈጸመ ሳይሆን፣ በዚህ ዓይነት ሞት እንደሚሞት አስቀድሞ የተወሰነ ነው። ከብዙ መቶ ዓመት በፊት ነብዩ ኢሳያስ ስለ መከራውና ስለ ስቃዩ ሲተነብይ፣ *"እኛ ልንሸከመው የሚገባ ንን መከራና ሕማም እርሱ ተሸከመ፤ ይህም በእርሱ ላይ የደረሰበት ግርፋ ትና መከራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተላከ ቅጣት እንደሆነ አድርገን አሰ ብን። ይሁን እንጂ እርሱ ተወግቶ የቆሰለው ስለ ኃጢአታችን ሲሆን፣ በመ ገረፍ የደቀቀውም እኛ ስለ ፈጸምነው በደል ነው" አለ (ኢሳ. 53፡4-5)።* ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ሲሆን፣ ብሉይ ኪዳን ላይ በምሳሌ የተጠ ቀሰው፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ግልጽ ሆኖ ታይቷል።

*"እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ" (ዮሐ. 1፡29)፣* እንዲሁም፣

*"መልካሙ እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ሰጠ" (ዮሐ. 10፡11)፣*

*የተባለለት፣ በመስቀል ላይ የሞተው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።* ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ለብዙዎቹ በዘመናት *"የመስቀሉ ሀሳብ"* ምስጢር እንደሆነባቸው ነው። አንዳንዶች እርሱ የመስቀልን ሞት የሞተው ስለ እነርሱ ኃጢአት ዋጋ ለመክፈል እንደሆነ ሳይሆን፣ ለአንድ ዓይነት እውነት የቆመ ጀግና ሰማዕት አድርገው ይመለከቱታል። ሌሎች ደግሞ *"ክርስቶስ ሁሉን ነገር የከፈለልን በመሆኑ እኛ ምንም ማድረግ የለብንም"* ብለው የሚያምኑ ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ኢየሱስ

የሰዎችን ሞራል ለመለወጥ ብቻ እንደመጣ አድርገው የሚመለከቱት፣ የሰው ኃጢአት ምን ያህል ጥልቀት እንዳለው ፈጽሞ ያልተረዱ ናቸው። የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት እግዚአብሔር ኃጢአትን ምን ያህል እንደሚጠላ ያሳየናል። በኃጢአት ምክንያት ተለይቶ የነበረውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ኢየሱስ የመስቀል ሞት መሞት አስፈለገው። ይህን በማድረግ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙነት ለማስተካከል በሩን የከፈተ ይሁን እንጂ፣ ሰው የግድ የራሱን ድርሻ መፈጸም አለበት። ድርሻውም ኃጢአቱን ተናዝዞ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ነው። በዚህ ዓይነት ሰው ድርሻውን ሲፈጽም እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ራሱን ከዓለም ጋር ያስታርቃል።

### 3. መስቀሉ፣ ክርስቶስ ለእኛ የዋለልንን ውለታ ያሳያል

*ወቅቱ፣ ጦርነቱ አልቆ ግዳጃቸውን የጨረሱ ወታደሮች ወደ አገራቸው የሚገቡበት ቀን ነው። ከመርከብ ሲወርዱ ሊቀበሏቸው ቤተሰቦቻቸው በናፍቆት እየጠበቋቸው ነው። የሚጠብቋቸው ወታደሮች ልክ ከመርከብ እንደ ወረዱ፣ ቤተሰቦቻቸው እየሮጡ ሄደው አንገታቸው ላይ ይጠመጠሙ ነበር። በዚያ ግርግር ውስጥ በሕይወት መኖሩን እርግጠኛ ያልሆነች አንዲት እናት ልጇን ለማግኘት በዓይኗ ትፈልግ ነበር። ጥቂት ከፈለገች በኋላ ልጇን ከሩቅ ስታየው ደስታ ውስጧን ፈንቅሏት "ያውና! በሕይወት አለ ልጄ'" ብላ እየሮጠች አንገቱ ላይ ተጠመጠመች። እራሱን ከእናቱ እያላቀቀ፣ "ቆይ የእኔ እናት!" ብሎ እየሮጠ ሄዶ አንድ ወታደር ይዞ ወደ እናቱ አመጣና፣ "የእኔ እናት ይሄ ልጅ በጣም ጥሩ ጓደኛዬ ነው! ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ገጥመን ስንታኮስ፣ እኔ ያላየሁት አንድ የጠላት ወታደር ተኩሶ ሊገድለኝ ሲል፣ እየሮጠ መጥቶ እላዬ ላይ በመውደቅ፣ በእኔ ላይ ሊያርፍ የነበረው ጥይት እርሱን እንዲመታው አደረገ። እኔ ከሞት ዳንኩ፣ እርሱ ግን ለእኔ በተተኮሰችዋ ጥይት ተመትቶ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት። ይኸው እንደምታይው ዓይኑ ሥውር ሆነ" አላት። ይህን ያደረገው እኔን ከሞት ለማዳን ነው" አላት። እናትየውም ዓይኖቿ በዕንባ ተሞልተው፣ "ለእኔና ለልጄ ስላደረግኸው በጎ ነገር፣ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፣ አመሰግንሃለሁ" ለዘላለም ባለውለታዬ ነህ" አለችው።*

በዚህ አስደናቂ ታሪክ ውስጥ፣ ኢየሱስ ለእኔና ለእናንተ ከዚያ ወታደር የበለጠ ውለታ የዋለልን መሆኑን እንረዳለን። እኛ ከዘላለም ሞት እንድንድን፣ በቀራንዮ ተራራ ላይ ተሰቃይቶ ሞተልን። እኛ ልንሰቀል በት በሚገባው መስቀል ላይ እርሱ ተሰቅሎ፣ እኛ ልንጠጣው የሚገባንን መራራ የሞት ጽዋ ጠጥቶ እኛን ከዘላለም ሞት አዳነን። ብዙዎች እየቀለዱበት "*አምላክ ከሆንክ እስቲ ከመስቀል ውረድ*" እያሉ ሲፈትኑት ከመስቀሉ ወርዶ ቢሆን ኖሮ፣ ያለመስቀል ደኅንነት ስለሌለ እኔና እናንተ በኃጢአታችን ምክንያት ለዘለዓለም በጠፋን ነበር። ነገር ግን እኛ እንድንድን እርሱ ሞተልን። ስለዚህ፣ ለእኛ ስላደረገው ትልቅ ነገር፣ ውለታው ከብዶብን በእግሩ ሥር ተደፍተን ከልባችን ልናመሰግነው ይገባናል።

*እኛ የማንረባውን ለማዳን፣ የከበረው ጌታ ስለ እኛ ሞተልን። የእኛን ኃጢአት ይቅር ሊል፣ በደላችንን ሁሉ ተሸክሞ፣ የመስቀል ሞት ሊሞትልን ማንም ሳያስገድደው፣ ፈቅዶ ቀራንዮ ተራራን ወጣልን።*

*በኃጢአት የቆሸሸውን ሕይወታችንን ለማጽዳት ክቡር የሆነውን ደሙን አፈሰሰልን።*

*ኃጢአታችንን በመስቀሉ ላይ ስለ ተሸከመልን፣ በእርሱ የምናምን ልጆቹ ዛሬ ከኃጢአት ፍርድ ነጻ ሆንን።*

ደስ የሚለን፣ መስቀሉን አልፈን ወደ ፊት ስንሄድ፣ የሞተልን የእግዚአብሔር በግ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሳ በመሆኑ፣ የምናየው ባዶ መቃብሩን የምናየው ባዶ ሆኖ ነው። የእኛ ጌታ ሞቶ የተቀበረ አምላክ ሳይሆን፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሳ፣ ሕያው የሆነ አምላክ ነው።

- *ታላቁ እስክንድር ጦር ሠራዊቱን እየመራ ከፐርሺያ ጋር ጦር ለመግጠም ይጓዝ ነበር። ጊዜው ክረምት ስለ ነበረ በበረዶው ውስጥ ተራራውን መውጣት ወታደሮቹን በጣም አዳክሟቸው ስለነበረ፣ ተስፋ ወደ መቁረጥ ደረጃ ደርሰው ነበር። ታላቁ እስከንድር የወታደሮቹን መዳከምና ተስፋ መቁረጥ ሲያይ፣ ወዲያው ከተቀመጠበት ፈረስ ወርዶ መካከላቸው ገብቶ በእግሩ ተራራውን መውጣት ሲጀምር፣ መጀመሪያ የቅርብ ተከታዮቹ፣ ቀጥሎ የጦር ሠራዊቱ የበላይ አዛዦች፣ ቀጥሎም ተራ ወታደሮች በድካማቸውና ተስፋ በመቁረጣቸው ሀፍረት ተሰምቷቸው ተነቃቅተው መሪያቸውን፣ ታላቁን እስክንድርን ተከትለው መጓዝ እንደ ጀመሩ ታሪክ ይመሰክራል።*

ክርስቶስም ሰማያዊ ዙፋኑን ትቶ፣ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዶ፣ አስቀድሞ የራሱን መስቀል ተሸክሞ፣ የመስቀልን መራራ ጽዋ ለመጠጣት ወደ ቀራንዮ ተራራ በመውጣት ለእኛ ለተከታዮቹ ምሳሌ ሆኖልናል። ኢየሱስ፣ *“መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም” (የማቴ. 10፥38) ሲል*፣

- እርሱ ያልተሸከመውን መስቀል *“ተሸከሙ”*፣ እርሱ ያልቀመሰውን መራራ ጽዋ *“ጠጡ”* ማለቱ አይደለም። *“መስቀሉን ተሸክማችሁ ተከተሉኝ”* ሲል፣ እርሱ ራሱ የሰጠንን መስቀል እንጂ፣ በእኛ እጅ የተሰራውን መስቀል፣ ይኸውም በኃጢአታችን ምክንያት የሚደርስብንን መከራና ስቃይ ማለት አይደለም። መስቀሉን ተሸክመን የምንጓዘው ከእርሱ ጋር እንጂ ብቻችንን ሆነን አይደለም። ከእኛ ጋር አብሮን ይጓዛል እንጂ፣ *“መንገዱ ያውና”* በማለት የምንጓዝበትን መንገድ ከሩቅ አያሳየንም።
- *“መስቀሉን ይዤ ከፊታችሁ ቀድሜ ስለማልፍ ከኋላዬ ሆናችሁ ተከተሉኝ”* ነው የሚለን። የተሸከምነው መስቀል በጣም ከባድ መስሎ ከተሰማን፣ መረዳት ያለብን እውነት ቢኖር፣ ከምንችለው በላይ እንድንሸከም የማያደርግ መሆኑን ነው። እኛ የተሸከምነውን እርሱ ከተሸከመው መስቀል ጋር ስናወዳድረው፣ የእኛ መስቀል በጣም ቀላል መሆኑን እንዘንጋ። መስቀሉን መሸከም አስቸጋሪና ከባድ ሲሆንብን፣ እርሱ ስለ እኛ ከዚህ የበለጠ መከራና ስቃይ የተቀበለ መሆኑን ተገንዝበን፣ ከማጉረምረም ይልቅ ስለ ክርስቶስ ስንል መስቀሉን በመሸከማችን የበለጠ ደስ ሊያሰኘን ይገባል። ስለ እርሱ ስንል የምንከፍለው ዋጋ ያንሰበታል እንጂ አይበዛበትም።

ክርስቶስን መከተል ማለት ከክርስቶስ ጋር ሕብረት መፍጠር ማለት ነው። ከእርሱ ጋር ሕብረት ስንፈጥር፣ በመከራውም እንመስለዋለን። ይሁን እንጂ፣ የሚኖረን ደስታ ልንገልጸው ከምንችለው፣ ወይም አዕምሯችን ሊረዳው ከሚችለው በላይ ነው። ክርስቶስ መስቀሉን እንድንሸከም ሲያዝን፣ አጋዥ ሳይኖረን፣ ብቻችንን ሆነን አይደለም። አንዳንድ ጊዜ መስቀሉ ከብዶብን ከትከሻችን አውርደን ለመጣል ትንሽ ሲቀረን፣ በትክክለኛው ጊዜና ሰዓት ደርሶ ከነመስቀላችን ይሸከመናል። ብዙዎቻችን ስለ እኛ የመስቀልን ሞት የሞተልንን ጌታ አንድ ቀን ፊት ለፊት አግኝተነው በእግሩ ሥር ወድቀን፣ *“ስለ እኔ ሞተህ አዳንከኝ”* ብለን የምናመሰግንበትን ቀን እንናፍቃለን። *“እኔ ሄጄ ሥፍራ አዘጋጅላችኋለሁ፣ እኔ ባለሁበት እንድትሆኑ ልወስዳችሁ እመጣለሁ”* የሚል ተስፋ ስለሰጠን፣ ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን፣ ወይም እኛ ወደ እርሱ የምንሄድበትን ቀን በናፍቆት እንጠብቃለን።

*አንድ ጊዜ አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ዘመናን ሙሉ ከጌታ ጋር ያሳለፈችውን አንዲት የሰማንያ ስምንት ዓመት አሮጊት ለመጠየቅ እቤቷ ሄደ። አብረት ከጸለዩ በኋላ ሲሰናበታት፣ “እግዚአብሔር ብዙ ዕድሜ እንዲሰጥሽ እመኝልሻለሁ” አላት። ሴትዮዋም፣ “ብዙ ዕድሜ እንዲሰጠኝ አትመኝልኝ። ቶሎ ሄጄ ከኢየሱስ ጋር መሆን እፈልጋለሁ” አለችው። ቤቷን እያሳየችው፣ “ይህን ሊወድቅ የደረሰውን ቤቴን ተመልከት! ጣራው ያፈሳል። በረንዳው ሊፈርስ ትንሽ ነው የቀረው። ይህን የፈራረሰ ጎጆ ተሰናብቼ የሰው እጅ ወዳልሠራው ዘላለማዊ ቤቴ ቶሎ መሄድ እፈልጋለሁ” አለችው።*

ይህን ዓይነቱን የደህንነት በር የከፈተልን፣ በፍቅር የተሞላው፣ በመስቀል ላይ የሞተልን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያለመስቀል ደህንነት የለም።

## 4. ለአማኞች ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተበት ቀን ልዩ ነው

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በዓለም ውስጥ ብዙ አስደናቂ የሆኑ ሁኔታዎች የተከናወኑባቸው፣ ልዩ የታሪክ ምዕራፍ የተነደፈባቸው፣ ብዙ አስደናቂ የሆኑ ቀናት መጥተው አልፈዋል። ከእነዚህ ውስጥ አስደናቂው ቀን፣ እኔና እናንተ በሕይወታችን ልንረሳው የማንፈልገው ቀን የትኛው ይሆን?

- *ከእናታችን ማህጸን የወጣንበት ቀን፣ ወላጆቻችን "ልጅ ተወለደልን" ብለው "ዕልል!" ያሉበት ቀን ይሆን?*
- *በሕይወታችን ልንረሳው የማንፈልገው ቀን ትምህርታችንን ጨርሰን የተመረቅንበት ቀን ይሆን?*
- *ወይስ ትዳር የመሠረትንበት የጋብቻችን ቀን ይሆን? ልጆቻችን የተወለዱባቸው ቀናት ይሆኑ?*
- *በሕይወታችን ልንረሳው የማንፈልገው ቀን የሰው ልጅ ታላላቅ ነገሮችን የፈለሰፈባቸው ቀናት ይሆኑ?*
- *ይኸውም፣ በዓይሮፕላን የበረረበት፣ ውሃ ላይ በመርከብ የተንሳፈፈበት፣ እንዲሁም እግሩን ለመጀመሪያ ጊዜ ጨረቃ ላይ ያሳረፈበት ቀን ይሆን?*
- *በሕይወታችን ልንረሳው የማንፈልገው የብዙዎች ደም እንደ ውሃ የፈሰሰበት፣ ሥጋቸው የተቆራረጠበት፣ አጥንቶቻቸው የተከሰከሰበት ያ የጨላማ ዘመን ይሆን? ....*



ከቀናት ሁሉ በታሪክ ውስጥ ደምቃና ጎልታ የምትታይ፣ በሕይወታችን ፈጽሞ ልንረሳት የማይገባን አንድ ቀን አለች። ያችም፣ ፍጹም አምላክ፥ ፍጹም ሰው የሆነው፥ በታላቅነቱ ፈጽሞ ተወዳዳሪ የሌለው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመክበር ፈንታ የተዋረደባት፥ የሚሰቀልበትን የራሱን መስቀል እንደ ክፉ ወንጀለኛ የተሸከመባት ቀን ናት። ያቺን ቀን በሕይወታችን ፈጽሞ ልንረሳት የማንችላት፥ ከልባችን የምንወዳት ልዩ ቀን ናት። የእኔና የእናንተ ፍጹምና ቅዱስ ጌታ፥ ምድርን እንዳያረክስ ተብሎ እንደ ክፉ ወንጀለኛ በሰማይና በምድር መካከል ሆኖ በመስቀል ላይ የተንጠለጠለባት፥ ያቺ ቀን ከቀናት ሁሉ ተለይታ የተባረከች እንጂ ተራ ቀን አይደለችም።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማይና ምድር የተገናኙባት፥ የሰው ልጅ ከአምላኩ ጋር የታረቀባት፥ በቅዱሱና በቅዱሰ-ቅዱሳን መካከል የነበረው መጋረጃ፣ ከላይ እስከታች ለሁለት ተሰንጥቆ ወደ ቅዱሰ-ቅዱሳን መግባት እንዲቻል በሩ ክፍት የሆነበት ቀን ነው። ድንቅ ሥራ የተሠራባት፥ ያቺ ቀን ልዩ ቀን ናት። ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶት የነበረው የኃጢአት ግድግዳ የፈረሰባት፥ እግዚአብሔር አብ ፍቅሩን በሙላት ለሰው ልጅ የገለጸባት ያቺ ቀን፥ ከቀናት ሁሉ የተለየች ቀን ናት። ያቺ ቀን በተለይ የደህንነት ብርሃን በርቶልን ለተቀበልነው ሰዎች ልዩ ቀን ናት። ያቺ ቀን ከቀናት ሁሉ የበለጠ የተባረከች ናት። ፍጹም የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሲል መስቀሉን የተሸከመባት፥ መራራ ጽዋ የጠጣባት፥ በሰማይና በምድር መካከል የተንጠለጠለባት፥ በጦር ተወግቶ ከጎኑ ደምና ውሃ እንዲፈልቅ የሆነበት፥ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ *"ኤሎሄ! ኤሎሄ! ለማሰብቅታኒ፥ አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውኸኝ?"* ብሎ የጮኸባት፥ መጨረሻ ላይ *"ተፈጸመ"* ብሎ በመጮኽ የመጨረሻውን እስትንፋስ ተንፍሶ ሕይወቱን ስለ እኔና ስለ እናንተ የሰጠባት ያቺ ቀን ልዩ ቀን ናት።

## 5. እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር አስደናቂ ነው

ሁላችንም በመስቀሉ አማካኝነት የሚገኘውን መልካም ነገር ለመቀበል ፈቃደኞች ነን። መስቀሉ ከሚያስገኛቸው መልካም ነገሮች መካከል አንደኛው *"የሕይወታችን ደህንነት"* ነው። ስለሆነም፣ አምነን ለተቀበልነው፣ በመስቀሉ አማካኝነት ደህንነትን ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንዶቻችን መስቀሉን ለመሸከም፣ መስቀሉ የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈል ግን ፈቃደኞች አይደለንም። *ጀርመናዊው ዲትሪች ባንሆፈር፣* በእምነቱ ምክንያት ተሰቅሎ የሞተው፣ *"ዘ ኮስት ኦፍ ዲሳይፕልሺፕ"* *(The Cost of Discipleship)* *(ደቀመዛሙርትነት የሚያስከፈለው ዋጋ)* በሚለው መጽሐፉ ክርስቲያኖች "ጸጋውን" እንዴት ርካሽ እንዳደረጉት ገልጿል። ባንሆፈር፣ መስቀል የሌለበት፣ እንዲሁም *ደቀ መዝሙርነት የሌለበት ጸጋ፣ "ርካሽ ጸጋ ነው" ይላል።*[2] የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን፣ በክርስቶስ መንፈስ መሞላትን፣ ክርስቶስ በተጓዘበት መንገድ መጓዝን ይጠይቃል። ክርስቶስ የተጓዘበትም መንገድ የመስቀል መንገድ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። ስለዚህ ያለመስቀል፣ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን አይቻልም። ኢየሱስም *"ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ"* ብሏል (የማቴ. 16፤24)።

ለእኔና ለእናንተ ሲል ስለ ተሰቃየው፤ ራሱን አሳልፎ ስለ ሰጠው ጌታ ምን እንበል? ለእኛ ለአመጸኞች፣ ለኃጢአተኞችና ለበደለኞች ራሱን አሳልፎ መስጠቱ፤ የመስቀሉን ውርደት መቅመሱ፤ ስለ እኛ ሲል የክቡር ዙፋኑን ትቶ ወደ ምድር ወርዶ የመከራን ጽዋ መጠጣቱ፤ እግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ ያለውን አስደናቂ ፍቅር ያሳያል። ፍጹም የሆነው ጌታ ስለ እኛ ሲል ተወነጀለ፤ ተናቀ፤ ተቀለደበት፤ ተተፋበት፤ ተገረፈ፤ በመጨረሻም ተፈርዶበት በሰማይና በምድር ተንጠልጥሎ እንዲሞት ተደረገ። ለእኛ ለከፉዎች፣ በጎ ነገር

---

[2] Dietrich Bonhoeffer. The Cost of Discipleship, The Macmillan co. New York c1959.



ለማይገባን፣ ለእኛ ለበደለኞች ሲል ተሰቃይቶ ሞተ። በእኛ ምትክ ሆኖ እግዚአብሔር የሚፈልገውን የጽድቅ ዋጋ ከፈለልን። ሕይወት እንድናገኝ፣ ለእኛ ሲል መቃብርን ፈንቅሎ ከሞት ተነሳልን። ይህን ጌታ እንዴት እንውደደው? አንዳንዶቻችን *"የሚበቃውን፣ ወይም የሚገባውን ያህል እወደው ይሆን?"* ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን። ደስ የሚለን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁኔታዎች የማይለዋውጡት፤ *"እናንተ ከወደዳችሁኝ ብቻ መልሼ እወዳችኋለሁ"* የማይለን መሆኑ ነው።

*አንድ ጊዜ፣ ዘመኑን ሙሉ ከጌታ ጋር ያሳለፈ አንድ ክርስቲያን ታሞ ይሰቃይ ነበር። የዚህ ሰው ስቃይ በሰውነት ውስጥ የሚሰማው ህመም ሳይሆን በአዕምሮው የሚመላለስ አሳብ እያስጨነቀው ነበር። ክርስቲያን መሆኑ አጠራጥሮት፣ መንግሥተ ሰማይ አልገባም ይሆን? በማለት ፍርሃትና ጥርጣሬ አዕምሮውን ሞልቶት አይደለም። ያስጨነቀው ግን "ለጌታ በቂ የሆነ ፍቅር አይኖረኝም ይሆናል" ብሎ በማሰብ ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አንድ ክርስቲያን ሰው ሊጠይቀው መጣ። ለዚያም ወዳጁ የሚሰማውን ጭንቀት ነገረው።*

*ያም በጌታ ጥበብ የተሞላ ሰው፤ የዚያን ሕመምተኛ ሰው ጭንቀት ለማሳረፍ እንዲህ አለው። "አሁን ከአንተ ተለይቼ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ። እቤቴ ስደርስ ገና አንድ ዓመት ያልሞላትን ሕጻን ልጄን ከተኛችበት አንስቼ ጉልበቴ ላይ አስቀምጬ የሚያማምሩ ዓይኖቿን አያለሁ። የምታሰማውንም ድምጽ ትርጉሙ ባይገባኝም እንኳ ጆሮዎቼ ተከፍተው በደስታ ያዳምጧታል። ምንም ያህል ደክሞኝ ብገባም የእርሷ አጠገቤ መሆን ድካሜን ሁሉ ያስረሳኛል። በቃላት መግለጽ ከምችለው በላይ እጅግ በጣም እወዳታለሁ። እርሷ ግን እኔ የምወዳትን ያህል አትወደኝም። እንደምትወደኝም አላውቅም። በአንድ ምክንያት ልቤ ቢያዝን፣ ልቤ ቢሰበር "አባቴ ምን ሆነ?" ብላ ስለ እኔ በመጨነቅ ያለ እንቅልፍ አታድርልኝም። እኔ ብሞት በጥቂት ቀናት ውስጥ ትረሳኛለች። ይህቺ ልጄ እኔን ወጪ ከማስወጣቷ በቀር፣ አን*

*ድም ሳንቲም ገቢ አታስገኝልኝም። ሀብታም ሰው አይደለሁም። ይሁን እንጂ፥ እርሷን በገንዘብ የምገዛት ቢሆን ኖሮ ምንም ያህል ገንዘብ ከፍዬ እገዛት ነበር። ታዲያ እኔ እንደምወዳት ትወደኛለች? ከመውደዴ በፊት እንድትወደኝ፥ አንድ ነገር እንድታደርግልኝ እጠብቃለሁ? የእግዚአብሔርም ፍቅር ልክ እንደዚሁ ነው። አንተ ለመውደድህ እርግጠኛ ባትሆንም፥ እርሱ ይወድሃል" በማለት አጽናናው። ያም ሰው በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ለልጆቹ ስላለው እውነተኛ ፍቅር ሲሰማ ዕንባዎቹ በጉንጮቹ ላይ ይፈሱ ነበር። "አሁን ገባኝ። ቁም ነገሩ ያለው እኔ ለእግዚአብሔር ያለኝ ፍቅር ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለእኔ ያለው ፍቅር ነው" አለ።*

"እግዚአብሔር የደህንነትን መንገድ ከባድና ጠባብ ለምን አደረገው?" ብለን ብዙዎቻችን መጠየቃችን አይቀርም። ይህን መንገድ የመረጠው፣ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ትልቅ ፍቅር የሚገልጽበት፣ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚያየውን አንድያ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ወይም የተሻለ ሌላ መንገድ እንደሌለ ስላወቀ ነው። በዚህም የሰው ልጅ ደህንነት በርካሽ የተገኘ እንዳልሆነ መግለጹ ነው። ስለ ሰው ደህንነት እግዚአብሔር ከፍተኛ ዋጋ ከፍሏል። ያም እንደ ዓይኑ ብሌን የሚወደውን አንድያ ልጁን መስዋዕት አድርጎ በመስጠት ነው።

- *"...እግዚአብሔር አንድ፡የ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" ይላል (ዮሐ. 3፥16)።*

ለሰዎች ደህንነት ሲል መላእክትን መስጠት ሲችል፣ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚያየውን አንድያ ልጁን ምንም ሳይሳሳ አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ሌላ የፍቅር መግለጫ የለም። እግዚአብሔር ስለ ሰዎች ደህንነት ሲል ከፍተኛ ዋጋ የከፈለበትን እኛ *"ርካሽ"፣ ወይም መስቀል የሌለበት* ስናደርገው ደስ አይለውም። ሰው ለዘላለም የሚጠፋው ኃጢአት ስለ ሠራ ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ ዋጋ ከፍሎ እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን ደህንነት ረግጦ ወይም ችላ ብሎ በመሄዱ ነው። በጣም ቅርቡ የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ



እንኳን ስለ መስቀል ሞቱ መስማት አይፈልጉም ነበር። ደጋግሞ ቢነግራቸውም፣ *መስቀል የሌለበት ደህንነት ይጠብቁ ነበር።* ኢየሱስ አልፎ እንደሚሰጥና እንደሚሞት ሲናገር፣ ይህን መስማት የማይፈልገው ጴጥሮስ አንድ ጊዜ ኢየሱስን ወደ ጎን ወስዶ *"እንዲህ አትበል"* በማለት ሊገስጸው እንደሞከረ እናውቃለን። ኢየሱስን ያስቆጣው ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዋና ምክንያት ወይም ዓላማ ጴጥሮስ ያልተረዳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ተልዕኮውን እንዳይፈጽም ሊያደናቅፈው በመሞከሩ ነበር። ለዚህ ነው ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ *"አንተ ሰይጣን! ወዲያ ሂድ"* በማለት የገሰጸው።

ዛሬም ስለ ክርስቶስ መስቀል፣ ስለ ቀመሰው ስቃይ፣ እንዲሁም ስለ መከራው፣ በሚያሳዝን ሁኔታ በሰዎች እጅ በጭካኔ ተሰቅሎ መሞቱ ሲሰበክ መስማት የማይፈልጉ ብዙዎች አሉ። ከድንግል ማርያም መወለዱን፣ ፈዋሽነቱን፣ ተአምር ሠሪ አምላክ መሆኑን ብቻ እንጂ ስለ መስቀሉ እንድንሰብክ የማይፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ። *አሜሪካዊው ሜል ጊብሰን "ዘ ፓሽን ኦፍ ክራይስት" (The Passion of Christ)* የሚለውን በዓለም ዙሪያ ተደናቂነትን ያስገኘውን ፊልም ብዙዎቹን እንዳስለቀሰ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ፣ ፊልሙ ያበሳጫቸውም ሰዎች እንደ ነበሩ ይታወቃል።

የዘመኗ ቤተ ክርስቲያን፣ የአንዳንዶቹን ፍላጎት ለማሟላት ስትል መስቀል የሌለበትን ወንጌል በመስበክ፣ መስቀሉን ከቤተ ክርስቲያን ለማስወጣት የምትሞክር ትመስላለች። ስለ ፈውስ፣ ስለ ብልጽግና ትሰብካለች፤ ስለ መስቀሉ መስበኳን ግን ያቆመች ትመስላለች። ይህ እንዲህ ሊሆን የቻለው፣ የሕዝቡን ፍላጎት እያየች የምትሰብክ በመሆኗ ነው። ዛሬ ሕዝቡ መስማት የሚፈልገው የሚያስጨበጭብ፣ ሃሌሉያ የሚያሰኝ፣ አፍን በሳቅ የሚሞላውን ነው። አገልጋዮቹም ይህንን በመረዳት *"ይሄ ይሆንልሃል፣ ያንን ታገኛለህ..."* እያሉ ያባብሏቸዋል እንጂ፣ *"መስቀል ትሸከማላችሁ፣ የምትጓዙበት መንገድ ጠባብና አስቸጋሪ ነው..."* ብለው አይነግሯቸውም። ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን ያሉት ሰዎች ምን ዓይነት ትምህርት መስማት እንደሚፈልጉ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፣

- *"…ሰዎች ትክክለኛውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል፤ ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን የሚያሳክክ ጆሯቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ። እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረትም ዘወር ይላሉ"* አለ (2 ጢሞ. 4፡3-4)።

በአሁኑ ዘመን ስብከታችን ብቻ ሳይሆን አምልኮታችን፣ እንዲሁም የምንዘምራቸው መዝሙሮቻችንም በጣም ተለውጠዋል። ቀደም ሲል እንዘምራቸው የነበሩት መዝሙሮቻችን፥

- *"…መስቀሉ ማማሩ… መስቀል ከፊቴ ዓለም ከኋላ…"*
- *"ትዝ ይለኛል ያ መድኅኔ በእንጨት ላይ የሞተው ስለ እኔ። ትውስ ይለኛል የመስቀል ፍቅሩ፣ ያደረገልኝ ውለታው ሁሉ።"*
- *"የጌታዬን ፍቅር ሳስበው፣ በመስቀል ለእኔ ሲል የሞተው። የደም ላብ በሲቃ ያላበው፣ በመስቀል ላይ የሞተው። ጌታዬ ተዋርዶ የቆሰለው፣ መርገሜን ለመውሰድ የታገሰው፣ የጌታዬን ፍቅር ሳስበው፣ አመሰግኘ፣ አመሰግነው ይለኛል፣ ፍቅሩ ያስገድደኛል"* የሚል ነበር።

በአሁኑ ጊዜ ግን ዝማሬያችን፣ *"…አደረግኸልኝ… ድሃ ነበርኩ፣ አበለጸግኸኝ…"* የሚል፣ በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን፣ በሰው ፍላጎት ላይ ያተከረ፣ ሰማያዊው ላይ ሳይሆን ምድራዊ ብልጽግና ላይ ያረፈ ሆኗል። እኛ ወንጌሉን ለመስበክ ተጠርተናል የምንል አገልጋዮች፣ በወንጌል ያፈራናቸውን ነፍሳት አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ይዘን ስንቀርብ፣ ሕይወት ያላቸውን ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሬሳ የሆኑትን ከሆነ፣ ባፈራነው ፍሬ የምናፍር መሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዘንድም ተጠያቂዎች መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። የዚህም መጽሐፍ ዋና ዓላማ የጻፍኳቸውን መጽሐፍት ቁጥር ለማብዛት ሳይሆን፣ ይህንን እውነት ለማሳየት ነው።



## 6. ኢየሱስ "ይለፈኝ" ያለው ጽዋ ምንን ያጠቃልላል?

ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ሲጸልይ፣ *"አባት ሆይ! የሚቻልህ ከሆነ ይህ የመከራ ጽዋ ከእኔ ወዲያ ይለፍ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን"* አለ (ማቴ. 26፡39)። ኢየሱስ ሊጠጣው ስላለው *"የመከራ ጽዋ"* በእኛ ኃጢአት ምክንያት እንጂ ስለራሱ ኃጢአት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ሊጠጣው የተዘጋጀው ትልቁና አስደንጋጭ የሆነው የዓለም ኃጢአት ከመጠን በላይ በነፍሱ ላይ ከፍተኛ ጭነት፣ በሕሊናው ላይ ውጋት ሆኖበት ነበር። ሰዎች ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ታዛዦች አልነበሩም። መተላለፋቸውና ግዴለሽነትታቸው ቅዱስ የሆነውን እግዚአብሔርን መስደባቸውና ማዋረዳቸውን ይገልጽ ነበር። ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ሊጠጣው የተዘጋጀው፣ ከላይ የገለጽነውንና የከፋውን የዓለም ኃጢአት የሞላበትን ጽዋ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ዓለማውያን፣ ስለ ኃጢአት ግድ የሌላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ክርስቲያኖችም፣ "እግዚአብሔርን እናውቃለን" የሚሉትም፣ ኃጢአትን አቃልለውና አሳንሰው ያዩታል። ኢየሱስ ግን የተመለከተው እንዲህ አልነበረም። ነፍሱን ስላስጨነቀው፣ እግዚአብሔር አብን *"የሚቻልና ፈቃድህ ቢሆን ከእኔ ይህ ጽዋ ይለፍ"* ብሎ ጸልዮ ነበር። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት ያለው አመለካከት በግልጽ በጌቴሴማኒ ውስጥ ታይቷል። በጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ የምናየው የሰው ልጅ በቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስን የመከራ ጣር ነው። ጌቴሴማኒ የሰው ልጅ ኃጢአት ምን ያህል ትልቅና አስከፊ፣ እንዲሁም የሚዘገንን መሆኑን ያሳየናል።

## 7. የጌቴሴማኔው ጽዋ

ኢየሱስ የመጨረሻውን ዕራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከበላ በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባለው ሥፍራ ሄደ። በቅርብ አብረውት ለነበሩት ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ለዮሐንስ፣ ለጴጥሮስና ለያዕቆብ፣ *"ለመሞት እስከደርስ ድረስ አዝኛለሁ፤…እኔ እዚያ ሄጄ እስክጸልይ፣ እናንተ እዚህ ቆዩ"* አላቸው (ማቴ. 26፡38)። ለብቻውም ሆኖ *"አባት ሆይ! የሚቻልህ ከሆነ ይህ*

*የመከራ ጽዋ ከእኔ ወዲያ ይለፍ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን" ብሎ ጸለየ (ማቴ. 26፡39)።* ከጸሎት ሲመለስ አብረውት እንዲተጉ፣ መከራውን ብቻውን እንዳይሸከም፣ እንዲያግዙት ደጋግሞ ጠይቋቸው ነበር። እነርሱ ግን በዕንቅልፍ ተሸንፈው አብረውት ሊታገሉ አልቻሉም። ኢየሱስ ያንን የመሰለ የመቃተት ጸሎት እንዲጸልይ ያደረገው ጽዋ ከመጠን በላይ መራራ በመሆኑ እንደሆነ እንገምታለን። የደም ላብ እስኪያልበው ድረስ ነፍሱ ተጨንቃ ነበር።

ክርስቶስ ካለፈባቸው ልዩ ልዩ ትግሎች ውስጥ አንደኛው *በጌቴሴማኔ የአትክልት ሥፍራ* ውስጥ የነበረው ብርቱ *መንፈሳዊ* ትግል ነው። *"ጌቴሴማኔ" ማለት ተጨምቆ የወጣ ዘይት ማለት ነው።*[3] በዚህ ስፍራ የወይራ ዘይት እየተጨመቀ መድኃኒትነት ያለው ዘይት ይመረት ስለ ነበረ፣ *"ጌቴሴማኔ"*የሚል ስም ተሰጠው። ክርስቶስ የዓለም ኃጢአት ተጭኖት የደም ላብ ያላበው በዚህ *ሥፍራ* ስለሆነ፣ *"ጌታሴማኔ"* ተብሎ መጠራቱ ተገቢ ነው። ጌቴሴማኔ፣ ኢየሱስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዛዥ ለመሆን፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን ሙሉ በሙሉ የሰጠበት *ሥፍራ* ነው። የጌቴሴማኔን ትርጉም እንደሚገባው ባናውቅም፣ ለኃጢአታችን ተገቢ የሆነውን መስዋዕት ለማቅረብ ኢየሱስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ መሄዱን፣ እንዲሁም ብቸኛ ሆኖ የእግዚአብሔርን ቁጣ ቀምሶ ያለፈ መሆኑን ግን እናውቃለን።

## *7-ሀ መከራ የሞላበት ጽዋ*

*"ጽዋው"* ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሚጠብቀውን ከባድ መከራ የሚያሳይ ነበር። የመከራውን ጥልቀትና ስፋት ለመረዳት ኢየሱስ ፍጹም ሰው ብቻ ሳይሆን ፍጹም አምላክ መሆኑንም ማወቅ ይጠቅማል። ኢየሱስ አምላክ ከሆነ፣ የአምላክነት ባሕሪ እንዳለው ግልጽ ነው። ይህንንም በሚያስተምረው ትምህርት፣ በሚፈጽማቸው ታምራት፣ እንዲሁም ሁሉን በማ

[3] Theodore W. Engstrom, ed. Great Sermon by Great American Preachers, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI.



ድረግ ችሎታው አስመስክሯል። በሌላ በኩል ደግሞ ፍጹም ሰው ነበር። እንደ እኔና እንደ እናንተ ሥጋ የለበሰ፣ ነፍስ ያለው ነበረ። ከሌላው ሰው የሚለይበት ነገር ቢኖር ኃጢአት የሌለበት ፍጹም ሰው መሆኑ ነው። እንደ እኛ ተርቧል፤ እንደ እኛ ተጠምቷል። እንደ እኛ በስጋው ድካም ይሰማው ነበር። እንዲሁም የሾኽ አክሊል ሲደፋበት ቆስሎ ደሙ ፈሷል፤ በመገረፍ ቆስሏል፤ በሚስማር ከእንጨት ጋር አጣብቀውታል፤ በጦር ወርውረው ጎኑን ወግተውታል። ኢየሱስ በስጋው የቀመሰውን መከራ መዝሙረኛው ሲገልጽ፣ *"ጉልበቴ ደከመ እንደ ውሃ ፈሰስሁ፤ አጥንቶቼ ሁሉ ከመገጣጠሚያቸው ተለያዩ፤ ልቤም እንደ ሰም በውስጤ ቀለጠ። ጉሮሮዬ እንደ ሸክላ ደረቀ፤ ምላሴም ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ፤ እንደ ሞተ ሰውም በትቢያ ላይ ጣልኸኝ። ክፉ ሰዎች እንደ ውሻ መንጋ ከበቡኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ። አጥንቶቼ ተቆጠሩ፤ ጠላቶቼም በጥላቻ ዐይን ተመለከቱኝ። ልብሶቼን ተከፋፈሉ፤ በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ" አለ (መዝ. 22፡14-19)።* ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የቀመሰው ጽዋ፣ ሥጋዊ ስቃዩና መከራው በከፊል ነው። ሌሎችም ይህን ዓይነቱን መከራ በመስቀል ላይ ተሰቅለው አልፈዋል። ከሥጋዊ መከራ የበለጠው ኢየሱስ የቀመሰው ሌላ መከራ፣ ከዚያ እጅግ በጣም የከፋ ነው።

ከሁሉም የከፋው ኢየሱስ በነፍሱ ውስጥ የቀመሰው መራራ ጽዋ ነው። ኢየሱስ እንደ ሥጋዊ ሰው ነፍስ ነበረው። ከሰው የሚለየው ግን የእርሱ ነፍስ ከኃጢአት ፍጹም ንጹህ መሆኑ ነው። እንደ ሰው ነፍሱ ትጨነቅ ነበር። የሚያሳዝን ነገር ሲያጋጥመን እኛ ሰዎች ከውስጥ ነፍሳችን ትጨነቅብናለች። ልክ እንደ እኛ የእርሱም ነፍስ ትጨነቃለች። አግባብ ያልሆነ ነገር በሌላውም ሆነ በእኛ ላይ ሲፈጸም ነፍሳችን ትታወካለች። የክርስቶስም ነፍስ ከእኛ የበለጠ ትታወካለች። ጠላቶቻችን እኛን ለማጥፋት የተንኮል ሥራ ሲፈጽሙብን ውስጣችን እንደሚታወከው ሁሉ፣ የእርሱም ከዚያ የበለጠ ይታወካል። የረዳናቸው፣ ያገዝናቸው፣ በጎ ያደረግንላቸው ሰዎች በምስጋና ፈንታ ጠላቶች ሲሆኑብን ነፍሳችን እንደምታዝን፣ የእርሱም ከዚያ የበለጠ ያዝናል። በራሱ ላይ የደፋበት የሾኽ አክሊል፣ ሥጋውን ወግቶ አቆሰለው፤ ሲሰድቡትና ሲቀልዱበት ግን ነፍ

ሱን ወጋው። ሚስማር ሥጋው ውስጥ ሰርጉዶ በመግባት ካሰቃየው የበ ለጠ፣ የራሱ የሆኑት ጥለውት ሲሸሹ፣ ቅርቤ ናቸው ያላቸው ሲከዱት ሕመሙ የበለጠ እንደተሰማው፤ ውስጡን ከመጠን በላይ እንዳቆሰለው እርግጠኛ ነን። ጠቢቡ ሰሎሞን *"በሕይወት ለመኖር ያለህ ተስፋ ሕመም ሆን እንድትታገስ ይረዳሃል፤ ይህ ተስፋ ከሌለህ ግን የተሰበረውን መንፈስ ሆን ማንም ሊጠግነው አይችልም"* አለ (ምሳሌ 18፡14)።

በጌቴሴማኒ ክርስቶስን ፊት ለፊት የገጠመው በነፍሱ ውስጥ የተሰ ማው ስቃይ ነው። ይህን ዓይነቱ ሥቃይ ሲሰማው ነው ኢየሱስ *"አባት ሆይ! የሚቻልህ ከሆን ይህ የመከራ ጽዋ ከእኔ ወዲያ ይለፍ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን" (ማቴ. 26፡39)* ብሎ እንዲጮኽ ያደረገው። በነፍሱ ውስጥ ከተሰማው ስቃይ የከፋ ሌላ ጌታ ችን የቀመሰው መራራ ጽዋ አለ። የደም ላብ እስኪያልበው ድረስ የተጨነ ቀው ምን እንደሆን ነብዩ ኢሳያስ ይህ ሁኔታ ከመፈጠሩ ከብዙ መቶ ዓመ ታት በፊት በትንቢቱ ገልጾታል። *"እኛ እያንዳንዳችን ከመንገድ ወጥተው በመባዘን፣ እንደ ጠፉ በጎች ሆነን ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እኛ ልንቀ በለው የሚገባንን ቅጣት ሁሉ በእርሱ ላይ አኖረ" ይላል (ኢሳ. 53፡6)።*

## *7-ለ ኃጢአት የሞላበት ጽዋ*

ኢየሱስን ያንገሸገሸው በሥጋው የተሰቃየው ሥቃይ ብቻ ሳይሆን፣ የዓለምን ክፉ ኃጢአት በመጠጣቱ ነው። ያ ጽዋ፣ በዚያን ዘመን የነበሩት የዓለም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት በሚወለዱትም ሰዎች ክፉ ኃጢአ ትና በደል የተሞላ ነበር። በዚያ ጽዋ ውስጥ በአጠቃላይ የኃጢአትን መር ዛምነቱን፣ ስፋቱና ጥልቀቱን ያይ ነበር። ኃጢአት ሰንል የሰዎችን ሞራል የጎደለውን ተግባር ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወታቸው ጭካኔ የሞላባቸው፣ የሰ ዎችን ደም እንደ ውሃ ያፈሰሱትን ሰዎች ተግባር ስናይ፣ የኃጢአት ጥል ቀቱና ስፋቱን መረዳት እንችላለን።

- *ስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያንን ያስፈጀው የሂትለር ኃጢአት፣*
- *የብዙዎችን ደም ያፈሰሰ የእስታንሊን ኃጢአት፣*



- *"ከዳዳሉ ይልቅ እኔን ለምን አሳከበራችሁኝም?" በማለት መቶ ሃምሳ ሺ ሰዎች በአንድ ቀን ያስፈጀው የፈረንሳዩ የቻርለስ ዘጠነኛው ኃጢአት፣*
- *በዓለም ዙሪያ ያሉት የሴተኛ አዳሪዎች ኃጢአት፣*
- *በዓለም ዙሪያ ያሉት የነፍሰ ገዳዮች ኃጢአት፣ የከሃዲዎች፣ የዘራ ፊዎች፣ በሃሰት ከሳሾች ኃጢአት የተሞላ ነበር።*

ኢየሱስ ከላይ በዘረዘርናቸው ክፉና መራራ ኃጢአቶች የተሞላውን ጽዋ መጠጣት ነበረበት።

ሰው የራሱ ኃጢአት፤ በደልና መተላለፍ ሊከብደው ይችላል። እስቲ እናስብ የዓለም ኃጢአት ሁሉ በእኛ ላይ ቢጫን ምን ያህል ክብደቱ ይሰማን ይሆን? ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የተሰማው ጭንቀት በሥጋው ላይ ስለሚደርስበት መከራና ስቃይ ብቻ ሳይሆን፣ የዓለም ኃጢአት ሁሉ በእ ርሱ ላይ ስለተጫነበት ነበር። የዓለም ኃጢአት በእርሱ ላይ ሲጫን እየከበ ደው ሲመጣ ነው ኢየሱ ወደ አባቱ *"አባት ሆይ! የሚቻልህ ከሆን ይህ የመ ከራ ጽዋ ከእኔ ወዲያ ይለፍ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን" ሲል የጮኸው (ማቴ. 26፡39)።* እግዚአብ ሔርም ኢየሱስ ጽዋውን ሳይጠጣው እንዳያልፍ ያላደረገው፣ ዓለም ከኃ ጢአቱ እንዳይጠፋ ስለ ፈለገ ነው። ጽዋውን ልዩ የሚያደርገው የእኛን የክፉዎችንና መዳን የማይገባንን ሰዎች ኃጢአት ጭምር የያዘ በመሆኑ ነው። ነብዩ ኢይሳያስ በመከራ ውስጥ ስለሚያልፈው ኢየሱስ ሲናገር፣ *"እኛ ልንሸከመው የሚገባንን መከራና ሕማም እርሱ ተሸከመ፤ ይሆም በእ ርሱ ላይ የደረሰበት ግርፋትና መከራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተላከ ቅጣት እንደሆነ አድርገን አሰብን። ይሁን እንጂ እርሱ ተወግቶ የቆሰለው ስለ ኃጢአታችን ሲሆን፣ በመገረፍ የደቀቀውም እኛ ስለፈጸምነው በደል ነው፤ እርሱ በተቀበለው ቅጣት እኛ ሰላምን አገኘን፤ እርሱም በመቁሰሉ እኛ ተፈወስን" ይላል (ኢሳ. 53፡4-5)።* ሐዋርያው ጳውሎስም *"ክርስቶስ ስለ እኛ እንደ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማንዎጀን..." ይላል (ገላት. 3፡13)።*

## *7-ለ በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞላ ጽዋ፥*

በመስቀሉ ላይ የተንጠለጠለውን ክርስቶስ እግዚአብሔር ያየው እንደ ልጁ ሳይሆን፣ የእኛን እርግማን በሥጋው እንደተሸከመ ነው። ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ስለ ዓለም ኃጢአት የሚከፍለውን ዋጋ ኢየሱስ ለብቻው እንዲወጣው ፊቱን ከእርሱ አዞረበት። *"ኤሎሄ! ኤሎሄ ለማ ሰብቀተኒ... አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውከኝ"* ብሎ የጮኸው ለዚህ ነው። በኃጢአት ላይ ከፍተኛ ቁጣ ስለነበረው፣ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት በሥጋው በመሸከሙ እግዚአብሔር ከልጁ ፊቱን አዙሮ ነበር። በጌቴሴማኔ ሊጠጣው የተዘጋጀው ጽዋ በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞላ ነበር። በጌቴሴማኔም ሆነ በመስቀል ላይ ክርስቶስን ትቶት ያልሄደው የጨለማው ገዢ የሆነው ሰይጣን ብቻ ነው። ከመስቀሉ እንዲወርድ በመፈተን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ከመስቀል ውረድና ራስህን አድን" ብሎ ሀሳብ አቅርቦለት እንደነበረ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ይሁን እንጂ፣ ያለመስቀል ደኅንነት እንደሌለ የሚያውቀው ጌታ፣ የዓለም ሕዝብ ከኃጢአቱ ለዘላለም እንዳይጠፋ አልተሸነፈለትም።

## *7-መ በምሕረት የተሞላ ጽዋ፥*

በጌቴሴማኔም ሆነ በመስቀሉ ላይ የነበረውን፣ ለመሞት የተዘጋጀውን አዳኛችንን ነፍሱን የሞላው አንድ ነገር ነበር። ያም እግዚአብሔር አብ ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን የነበረው ሀሳብ ነው። ኢየሱስ *"የአንተ እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን"* ብሎ ወደ አባቱ ሲጸልይ፣ የሰዎች ከኃጢአት መዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ያውቅ ነበር። በኃጢአት፣ በመከራ የተሞላውን ጽዋ ሲመለከት የሚዘገንን ቢሆንም፣ ለመጠጣት እንዲወስን ያስቻለው ክርስቶስ ለኃጢአተኞች የነበረው ፍቅር ነው። ቅዱሱ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር የሚለው በልጁ የመስቀል ሞት ብቻ እንደሆነ ያውቃል። ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ በመስጠት፣ ለኃጢአተኞች ያለውን ፍቅር ገለጸ። ጽዋው ልጁን እስከ ሞት ድረስ ያስጨንቀው መሆኑን ቢያውቅም፣ እግዚአብሔር ጽዋውን እንዳይጠጣ አላስወገደለትም። ጽዋው በውርደት፣ በኃጢአት፣ በመከራ፣ በበደለኛነት



ስሜትና በቁጣ የተሞላ እንደሆነ ያውቃል። እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች ካለው ፍቅር፣ እንዲሁም ኃጢአትን እጅግ በጣም በመጥላቱ ምክንያት፣ ጽዋውን እስከ መጨረሻው ጭልጥ አድርጎ እንዲጠጣው ፈቀደ።

እኔና እናንተ ስለ ኃጢአታችን ያለን አመለካከት ምን ዓይነት ይሆን? ወደ ጌታ ቀርበን *"ጌታ ሆይ! ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በልልኝ"* ብለን ስንጮኽ *"እሺ!"* እንደሚለን በምን እናውቃለን? ልጁ በስቃይ ላይ ሆኖ *"ይህን ጽዋ እንዳልጠጣው ገለል አድርግልኝ"* ብሎ ሲጠይቀው፣ *"እሺ!"* ካላለው፣ እኛን እንዴት *"እሺ!"* ይለናል? እኛ ከልጁ እንበልጥበታለን እንዴ? ልጁ የደም ላብ ሲያልበው እያየ ውስጡ ካልተንቀሳቀሰ የእኛን ጩኸት ይሰማል ብለን እንዴት መገመት እንችላለን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ታላቅ ፍቅር ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም። ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት መራራ የሆነውን ጽዋ የጠጣ መሆኑን አምነን ከተቀበልን፣ በትህትና ተሞልተን በመስቀሉ ሥር ተንበርክከን ከጸለይን፣ ኃጢአታችንን ለዘላለም ይቅር እንደሚለን በቃሉ ውስጥ አረጋግጦልናል። የእግዚአብሔር ቅድስና፣ በመስቀሉ እኛን ከኃጢአታችን ነጻ ለማውጣት ብቃት እንዳለው እናውቃለን። ሀቀኝነቱና ለትክክለኛ ፈራጅነቱ የሚጠይቀውን ሁሉ ያሟላል። ለዚህ ነው ያለመስቀል ደህንነት የለም ያልነው።

ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት ሲል በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዕዳችንን የከፈለልን መሆኑን በሰፊው ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ሀሳቡን የበለጠ ለመረዳት ለየት ባለ መልክ እንመልከተው። ለምሳሌ፣ አንድ ዓይነት ወንጀል ብንሠራ ተይዘን ወህኒ ቤት መጣላችን አይቀርም። ወህኒ ቤት የምንገባው በሠራነው ወንጀል ምክንያት ነጻነታችንን ተገፍፈን፣ በሀፍረትና በውርደት ተሞልተን ነው። ወንጀለኞች በመሆናችን ምክንያት በር ተዘግቶብን፣ ነጻነታችንን አጥተን አንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ እንቆያለን። የተወሰነብንን የእስራት ዘመን ሳንጨርስ አንወጣም። ልክ እንደዚሁ ኃጢአት አስሮ፣ በመከራና በሀፍረት ውስጥ ይጥለናል። ከኃጢአት እስራት ነጻ መሆን የምንችለው፣ የተወሰነብንን ቅጣት ስንጨርስ ብቻ ነው። ቅጣ

ቱም፣ *"የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው" (ሮሜ 6፡23)* ስለሚል፣ ቅጣታችን ሌላ ነገር ሳይሆን ሞት ነው።

ስለዚህ የተወሰነብንን ቅጣት ለመፈጸም፣ እኛ ወይም ከእግዚአብሔር የተላከ ሌላ ሰው በእኛ ምትክ ሆኖ የግድ መሞት አለበት። ያለሞት ከእስራታችን ነጻ መሆን አንችልም። ለዚህ ነው የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ሰው *"ደም ሳይፈስ ስርየት የለም"* ያለው። ስለሆነም፣ ኢየሱስ ዙፋኑንና ክብሩን ሁሉ ጥሎ፣ ከሞት ቅጣት ነጻ እንድንሆን፣ በእኛ ምትክ በመሞት፣ የሞት ዕዳችንን ከፍሎ ነጻ አወጣን። ክርስቶስ ስለ እኛ ስለ ሞተ፣ ከእርሱ ጋር ሕብረት ከፈጠርን፣ አሮጌው እኛነታችንም ለኃጢአት አብሮ ይሞታል። ያንን ለማሟላት ነው ኢየሱስ በቀራንዮ ተራራ ላይ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሞተው። ኢየሱስ ሲሞት፣ እኛም ለኃጢአት የሞትን ሆንን። ከዚህ በኋላ ከእርሱ ጋር ሕብረት ከፈጠርን፣ በክርስቶስ አማካኝነት ነጻነታችንን እናገኛለን።

ጳውሎስ ከሕይወቱ መጨረሻ ላይ ደርሶ፣ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ያለፈበትን ሕይወት ለመመርመር ዕድል አገኘ። በኖረው ኑሮ፣ ባሳለፈው ሕይወት ቅር አልተሰኘም። የሚሰማውን ሲገልጽ፣ *"ጦርነትን በመልካም ተዋግቻለሁ"* ይላል። የክርስትና ሕይወት ጦርነት ያለበት መሆኑና እርሱም ጥሩ አድርጎ የተዋጋ መሆኑን አልሸሸገም። ጦርነቱም ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣ ከሰይጣንና ከክፉ መናፍስት ጋር ነበር። ጳውሎስ ከወንጌል ጠላቶች ጋር መዋጋት ነበረበት። ጠላቶቹ ለክርስቶስ ያለውን ታማኝነት ያውቃሉ። ስለዚህ ባላቸው ኃይል፣ ባላቸው ዘዴ ሁሉ እየተጠቀሙ የወንጌሉን ሥራ ለማደናቀፍ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር። ይሁን እንጂ፣ አልተሸነፈላቸውም። የእኛስ ሕይወት ምን ይመስላል? ዋጋ ያስከፍለናል ብለን በመፍራት ክርስቲያን መሆናችን እንዳይታወቅብን የድብብቆሽ ሕይወት እንኖር ይሆን? በውጊያ ውስጥ፣ በጦርነት ውስጥ ስላላፍን፣ ጳውሎስ "ጦርነትን በመልካም ተዋግቻለሁ" እንዳለው እኛም ማለት እንችል ይሆን? ጦርነትን በመልካም ያልተዋጋን እንደሆነ ደግሞ "የጽድቅ አክሊል ይጠብቀኛል" ማለት አንችልም። ዛሬ የክርስትና ሃይማኖት፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ ዋጋ የማያስከፍል፣ ርካሽ አድርገን እንዳንወስ



ደው፣ ለሌሎችም "የክርስትና ሃይማኖት" በሳቅና በጨዋታ እንደሚገኝ አድርገን እንዳናስተምር መጠንቀቅ አለብን።

አንዳንድ የዘመኑ ክርስቲያኖች ከጌታ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት እንዳላቸው፣ የቅድስና ሕይወት የመኖር ምልክታቸው፣ ስለ ክርስቶስ ሲሉ መከራ መቀበላቸው፣ የመስቀል ሞት መሞታቸው አይደለም። እንደነዚህ ዓይነቶቹ በእነርሱ አስተያየትና እምነት የተባረኩ ሳይሆኑ፣ የተረገሙ ናቸው። እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ብልጽግና የሚሰጥ፣ አመቻችቶ የሚያስቀምጥ እንጂ፣ የመከራ፣ የስደትና መራራ የሆነ የሞት ጽዋ እንድንጠጣ የሚፈቅድ ነው የሚለውን እምነት መቀበል የሚያቅታቸው ናቸው። በዕድሜያቸው ገና ወጣት የሆኑት እንኳን ሳይቀሩ ብዙዎች ደማቸውን እንደ ውሃ አፍስሰው ያስተላለፉልንን ወንጌል፣ ከእነርሱ የተቀበልነውን ንጹህ ወንጌል ሳንሸቃቅጥ ለሚቀጥለው ትውልድ ልናስተላልፍ ሲገባን፣ ለክርስትና እምነት ሲሉ ብዙዎች እንደሞቱለት እኔና እናንተም ልንሞትለት ሲገባ፣ ሸቃቅጠን ዋጋውን አርክሰነው ይሆን? በብር፣ በምቾት፣ በቆሳቁሳዊ ነገር ሸቃቅጠነው ይሆን? ወደድንም ጠላንም፣ በዚህ ምድር ላይ ዘለዓለም ስለማንኖር፣ አንድ ቀን የሕይወታችን ዘመን ማክተሙ አይቀርም። ወንጌሉን መጠቀሚያ አድርገን ምንም ያህል በምቾት ብንኖርም፣ አንድ ቀን ሰውነታችን መጨማደዱ፣ መበስበሱና መድከሙ የማይቀር ነው። የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው ስላዳናቸው ጌታ ሲሉ፣ ሥጋቸው በእሳት እንዲቃጠል፣ በአንበሶች እንዲቦጫጨቅ ራሳቸውን አሳልፈው መስጠታቸውን እየሰማን ነው። እኔና እናንተ ግን፣ ለሚበሰብሰው ምድራዊ ነገር ስንል ራሳችንን አሳልፈን መስጠታችን፣ እንዴት ያሳዝናል? ለመሆኑ እርሱ ፊት ስንቀርብ ምን ይዘን እንቀርብ ይሆን? እርሱስ ምን ይለን ይሆን? እኛስ ምን እንለው ይሆን? ደህንነት እርግጥ ነው እኛ በምንከፍለው ዋጋ የሚገኝ ሳይሆን፣ ጌታችን ራሱ በከፈለልን ዋጋ እንደሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፣ *"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"* ስለሚል፣ መስቀል የሌለበት የክርስትና ሕይወት ለመኖር አንሞክር።

2

# ያለመስቀል ደቀ መዝሙርነት

*“መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም”*

*(የማቴ. 10፡38)*

ኢየሱስ እንዲከተሉት ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራ፣ *“የአበባ ምንጣፍ አነጥፍላችኋለሁ፣ የጠየቃችሁኝን ሁሉ አደርግላችኋለሁ”* ብሎ ሳይሆን፣ *“ኑና መስቀሌን ተሸክማችሁ ተከተሉኝ”* በማለት ነበር። እርሱን መከተል መስቀል መሸከምን፣ የመስቀል ሞት መሞትን፣ በመከራ ውስጥ ማለፍን የሚጠይቅ መሆኑን ከማንም አልሸሸገም። ኢየሱስ ተከታዮቹን ለማብዛት ሲል እርሱን መከተል ትልቅ መስዋዕት የሚጠይቅ መሆኑን ሳይናገር፣ የሚያስከፍለውን ከፍተኛ ዋጋ ሳይገልጽ እውነቱን ሸፍኖ፣ ወይም ደብቆ ማንንም አባብሎ አይጠራም። እንዲከተሉት አባብሎ በመጥራት ፈንታ በግልጽ *“ከእኔ ጋር መሄድ የሚፈልግ፣ በመጨረሻ ከብሬን መካፈል የሚወድ ሰው፣ መጀመሪያ የሞቴ ወይም የመስቀሌ ተካፋይ መሆን አለበት”* በማለት በቅድሚያ በግልጽ ተናግሮ ነው። ጴጥሮስና እንድርያስን (ማቴ. 4፡18-10)፣ እንዲሁም ያዕቆብና ዮሐንስን (ማቴ. 4፡21) ሲጠራ፣ *“ፈቃዳችሁ ነው ወይ?”* ብሎ ሳይሆን፣ “ተከተሉኝ” የሚል ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ሰጥቷቸው ነበር (ዮሐ. 1፡43)። ኢየሱስ እንዲከተሉት ማንንም ተለማምጦ አልጠራም። ለምሳሌ፥

*በወንዙ ዳር ያገኛት ያቺ አመንዝራዋ ሳምራዊቷን፣*

*በሊቅነቱ ትዕቢት ይታይበት የነበረው ኒቆዲሞስን፣*

*እንዲሁም በሃይማኖታቸው ይመጻደቁ የነበሩትን ፈሪሳውያንን፣*



*“የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ”* ብሎ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንጂ አባብሎ ሲጠራቸው አናይም። ኢየሱስ ባለጸጋውን ወጣት *“...ያለህን ሸጠህ ተከተለኝ”* ሲለው፣ ባለጸጋው ፈቃደኛ አለመሆኑን ሲገልጽ፣ *“እንግዲያውስ ሁሉን ሸጠኽ ለድሃ ሰጥተህ እኔን መከተል ከብድ ከሆነብህ፣ ግድ የለም ግማሹን ለራስህ አስቀርና ግማሹን ሸጠህ ለድሆች አከፋፍልና ና!”* በማለት ኢየሱስ ከዚያ ወጣት ባለጸጋ ጋር አልተደራደረም።

## 1. ደቀ መዝሙርነት መስቀሉን መሸከም ይጠይቃል

ግሪክ በነበራት ፈላስፋዎቿ የምትደነቅበት ዘመን ነበር። ወጣቱ *ፕሉቶ በአቴንስ* ከተማ ብሩህ አዕምሮ የነበረውን *ሶቅራጥስን* በገባበት ቦታ ሁሉ እየገባ፣ በየአደባባዩ ሁሉ እየዞረ በቅርብ ሆኖ ይከተለው ነበር። የደቀ መዝሙርነት ጅማሬ በዚህ ዓይነት ነው። *ሶቅራጥስ* መጽሐፍ አልጻፈም። ደቀ መዛሙርቱ (ተከታዮቹ) ሁልጊዜ አብረውት ስለሚሆኑ፣ ከአፉ የሚፈልቀውን የፍልስፍና ቃል አንድም ሳያመልጣቸው በጥንቃቄ ያዳምጡ ነበር። በቅርብ ሆነው የሚያደርገውን ያዩ፣ የሚናገረውን ይሰሙ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የሶቅራጥስ ተማሪ (ደቀ መዝሙር) የሆነው ፕሉቶ፣ ሳይንስና ፍልስፍና ለቀጣዩ 900 ዓመታት ብዙዎች ሊማሩ የሚችሉበትን አካዳሚ አቋቋመ።

ኢየሱስም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ደቀ መዛሙርቱን ከላይ ባየነው ሁኔታ ያሰለጥን ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል በቅርብ ሆነው ይከተሉት ነበር። የሚሰብከውን ይሰሙ፣ የሚያስተምረውን በቃላቸው ያጠኑ ነበር። እንዲሁም የሚያስተምረውንና የሚሰብከውን በዕለታዊ ሕይወቱ ሲኖርበት በቅርብ ሆነው ያዩ ነበር። ወደ አባቱ ከሄደ በኋላ ደቀ መዛሙርቱም ክርስቶስ ያስተማራቸውን ትምህርት ለሌሎች ማስተላለፍ ጀመሩ፤ እርሱ እንደኖረው እንዲኖሩ፣ እርሱ ያስተማረውን እየታዘዙ እንዲኖሩ ብዙዎቹን ያደፋፍሩ ነበር። ደቀ መዝሙርነት፣ በመምህሩና በተማሪዎቹ መካከል ቅርብ ግንኙ

ነትን ይጠይቃል። ተራርቆ በመኖር ደቀ መዝሙር መሆን አይቻልም። ደቀ መዝሙሩ ከመምህሩ ያገኘውን ዕውቀት (ፍልስፍና)፣ ለሌሎች ተማሪዎቹ በማስተላለፍ ራሱን ማባዛት አለበት።

ደቀ መዝሙርነት "ለራስ መሞትን"፣ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ መኖርን ይጠይቃል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፥

- *"በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ምክንያቱም ነፍሱን ሊያድናት የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱን ስለ እኔ ብሎ የሚያጠፋት ግን ያድናታል" አላቸው (ሉቃ. 9፡23-24)።*

## 2. እኔና እናንተ መስቀል የምንለው ምን ይሆን?

ኢየሱስ ተከታዮቹ ምን ማድረግና ምን መሆን እንዳለባቸው ሲገልጽ፣ *"መስቀሉንም የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"* አለ። ለመሆኑ "መስቀል" ምንድነው?

- ❖ *ሮማውያን ከፍተኛ ወንጀል የፈጸመውን ሰው በሞት የሚቀጡበት በእንጨት የተሠራ ይሆን?*
- ❖ *በወርቅ፣ በነሀስ ወይም በብር የተሠራ አንገታችን ላይ የምናንጠለጥለው ጌጥ ይሆን?*
- ❖ *"መስቀል" ሰው በራሱ ኃጢአት ምክንያት የሚቀምሰው የመከራ ጽዋ ይሆን? ለምሳሌ ከጋብቻ ክልል ውጪ ሆኖ ዝሙት በመፈጸም በአባለ ዘር በሽታ ተይዞ የሚሰቃይ ክርስቲያን፣ "ይሄ በሽታ መስቀሌ ነው" ማለት ይችላል?*
- ❖ *አማኝ ክርስቶስን በመከተሉ፣ ለጌታው ፍጹም ታዛዥ በመሆኑ፣ በቅድስና ሕይወቱን በመምራቱ ምክንያት የሚቀምሰው መከራና ስቃይ፣ ያ "መስቀል" ነው። 'በመታዘዝ ጎዳና ላይ ሁልጊዜ መስቀል እንዳለ' የታወቀ ነው።*



- ❖ *መስቀላችን ስለ ክርስቶስ ስንል የሚደርስብን መጠላት፣ መገፋት፣ ወይም በድህነት መሰቃየት፣ መንሳቆል ሊሆን ይችላል።*
- ❖ *መስቀላችን ስለ ክርስቶስ ስንል የሚደርስብን ስደትና መከራ ሊሆን ይችላል።*

## 3. መስቀላቸውን በደስታ የተሸከሙ፥

መስቀላቸውን ተሸክመው ጌታን በደስታ የሚከተሉ ቁጥራቸው ትንሽ ይሁን እንጂ፣ የሉም ማለት አይደለም። ዛሬ ወንጌል ለብዙዎች የሚደርሰው በታማኝነት መስቀላቸውን ተሸክመው በሚያገለግሉ ጥቂት አገልጋዮች ነው። ስለ እነርሱ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። መስቀሉን መሸከም መራራ ጽዋ የሚያስጠጣ ቢሆንም፣ ሳያጉረመርሙ መስቀላቸውን በአግባቡ ተሸክመው የክርስትና ሕይወታቸውን የሚኖሩ አሉ። አንድ ጊዜ ጆን ዌስሊ በጣም የታመመች አንዲት ሴት ለመጠየቅ ሄዶ ያጋጠመውን ሁኔታ ሲጽፍ እንዲህ አለ፥

> *"ዛሬ አንዲት በጣም የታመመች ሴት ለመጠየቅ ሄድኩ። ይህቺ በህመም አልጋ ላይ የነበረችው ሴት በብዙ መከራ ውስጥ ያለፈች ነች። ከቤተሰቧ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰባቱን በሞት ያጣች ሴት ናት። በቅርቡ ደግሞ በጣም የምትወደው ባሏ በባህር ላይ ሲጓዝ መርከቡ ባሕሩ ውስጥ ሰጥሞ ሞተ። የዚህችን ሴት ታሪክ፣ የደረሰባትን መከራ ሁሉ ስታወራ ከሰማሁ በኋላ፣ "ይህን በመሰለ ልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ስታልፊ በውስጥሽ በእግዚአብሔር ላይ ምሬት አልተፈጠረም?" ብዬ ጠየቅኋት። እርሷም ፈገግ ብላ እንዲህ አለችኝ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በሆነው ነገር እንዴት መራራ መሆን እችላለሁ? የእኔ ናቸው የምላቸውን ሁሉ ወስዶ አጠገቡ ቢያኖራቸው፣ ግድ የለም። ለእኔ እንደሆን ሁልጊዜ እርሱ ራሱ አለልኝ። በከፋውም ሆነ*

*በደጉ፣ ወይም ሁልጊዜ እንድወደውና እንዳመሰግነው አስተምሮኛል አለችኝ።"*

እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ እኛን በማሳለፍ ሊያስተምረን የሚፈልገውን ቁም ነገር ለመማር በፈቃደኝነት ራሳችንን ሙሉ በሙሉ መስጠት አለብን። ዓላማውን በሕይወታችን እንዳይፈጽም በመከልከል ፈንታ የፈቀደውን እንዲያደርግ፣ በማንኛውም ነገር ሁሉ እንተባበረው። ይህንን ስናደርግ የምናልፍበትን መከራና ችግር አቃለን ማየት አለብን ማለት አይደለም። ከእግዚአብሔር እጅ የሚሰነዘርልንን ክፉም ሆነ ደግ ነገር በመቀበል ሊያስተምረን የሚፈልገውን ሁሉ በደስታ መማር አለብን። ከላይ ታሪኳን የሰማናት ሴት በሕይወቷ ይህንን እውነት የተለማመደች ትመስላለች። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሕይወታችን ምን ለማድረግ እንዳሰበ በግልጽ የሚታየን ጊዜ አለ። በዚህ ወቅት፣ ሊያስተምረን የሚፈልገውን ነገር በትህትና ተቀብለን በተግባር ላይ ልናውለው ይገባል። በሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወታችን ምን ለመሥራት እንዳሰበ ፈጽሞ የማይታየንና የማይገባን፣ በውስጣችን አንዳንድ ጥያቄ የሚፈጠርበት ጊዜ አለ። በነዚህ ጊዜያትም እግዚአብሔር በጎ የሆነውን ነገር በሕይወታችን ይሠራል ብለን በማመን ሊያስተምረን የመረጠውን ነገር ለመማር ፈቃደኞች መሆን አለብን።

*ጊዜው 1967 ዓመተ ምህረት (እ.ኤ.አ.) ሲሆን፣ ሁኔታው የተፈጠረበት ሥፍራ፣ ቻይና ነው። ባለ ታሪክ የሆኑት ሴት የሰማንያ ዓመት ዕድሜ የሆናቸው አሮጊት ናቸው። እኚህ ብዙ የልጅ ልጆች ያሏቸው ሴት፣ ብዙ ዓመት ሽባ ሆነው የኖሩ፣ በእግራቸው የማይራመዱ አሮጊት ናቸው። ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱ ሰዎች አንድ ቀን እኚህን ሴት በሚገፋ ተሽከርካሪ ወንበር (wheel Chair) ላይ አድርገው እየገፉ ወደ ከተማው መሀል፣ ብዙ ሕዝብ ከሚተላለፍበት ትልቅ አደባባይ አመጧቸው። መሳቂያና መቀለጃ እንዲሆኑ ጸጉራቸውን በግማሽ ላጭተዋቸዋል፤ ፊታቸውን ቀለም ቀብተዋቸዋል። ኢየሱስ ሊሰቀል ሲወሰድ መስቀሉ ላይ "የአይሁድ ንጉሥ" የሚል ጽሁፍ እንደተደ*



*ረገበት፣ በእኝህም አሮጊት አንገት ላይ የጽህፈት ምልክት ተንጠልጥሏል። ደወል ሲደወልላቸው፣ "ክርስቲያን ነኝ..." ብለው በኃይል ጮኸው እንዲናገሩ ያስገድዱቸው ነበር።*

*የእኛ ሴት ወንጀል ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ክርስቲያን መሆናቸው ነበር። ለአሳዳጆቻቸው የወንጀለኛ መጠሪያ ስም ይምሰል እንጂ፣ ለእኛ ሴት ግን የማዕረግ ስማቸው ነበር። በዚህ ዓይነት እኛን አሮጊት ሴት በአደባባይ መሳቂያ ሲያደርጓቸው የተመለከቱ ትናንሽ ልጆች ለሴትዮዋ በጣም አዘኑ፣ ይህን የሚያደርገውን ወታደር እግር ላይ ተጠምጥመው፣ ይህን አስከፊ የሆነ የግፍ ሥራውን እንዲያቆም አጥብቀው ለመኑት። እኛ አሮጊት ግን ልጆቹን ተቆጥተው፣ "ምን ማድረጋችሁ ነው? ልመናችሁን አቁሙ፤ በዚህ ዓይነት በመንደሬ ላሉት ሰዎች ለመመስከር ዕድል አገኘሁ። ይህን ዓይነቱን ዕድል ለማግኘት በጣም ብዙ ዓመት ጠብቄአለሁ" አሉ።*

እንዴት የሚያስደንቅ ታሪክ ነው? እኛ እሮጊት ስለ ክርስቶስ ስም መቀለጃ መሆናቸው፣ "*እኔ ክርስቲያን ነኝ*" ብለው በአደባባይ መጮኻቸው እንደ ክብር እንጂ፣ እንደ ውርደት አድርገው አላዩትም። የመመስከሪያ ዕድል እንጂ፣ እንደ ውርደት አድርገው አልተቀበሉትም። እኛ አሮጊት ሴት ስለ ክርስቶስ መቀለጃ መሆን፣ ከዚህም የከፋ መከራ መቀበል፣ የክርስቶስ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ሆነላቸው። እንዲሁም ለጎረቤቶቻቸው የሚመሰክሩበት ምክንያት ስለሆናቸው፣ የተቀበሉት በማጉረምረም ሳይሆን በታላቅ ደስታ ነበር። እኛስ እንዲህ ዓይነቱ ዕድል ቢያጋጥመን የምንቀበለው እንዴት ይሆን? የሚሰማንስ ስሜት ምን ዓይነት ይሆን? በክርስትናችን እንኮራበታለን ወይስ እናፍርበታለን? በአደባባይ እናውጀዋለን? ወይስ አፍረንበት እንደብቀዋለን?

በጥንት ዘመን ኃይለኛና ገናናው የሮም ንጉሠ ነገሥት ቤተ ክርስቲያንን ከሥሯ ነቅሎ በመጣል ሊያጠፉት ቢሞክርም፣ እግዚአብሔር የመሠረታት በመሆኗ ሊያጠፉት አልቻለም። ክርስቲያኖች ለትግል የሚገቡ

በት የጦር ሜዳ፣ ሌሎች ታጋይ ወታደሮች የሚመለመሉበት እንጂ፣ ክር ስቲያኖች ጠላቶቻቸውን የሚዋጉበት ቦታ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን የሮምን ኃይለኛ መንግሥት የተቋቋመችበት በጦር ኃይል ሳይሆን፣ በመ ከራ ውስጥ በመታገሷ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን ለአንዴ ብቻ ሳይሆን፣ ...አሁንም፣ ...አሁንም፣ ለመሰቃየት ፈቃደኛ ነበረች። በመጨረሻ ግን አሸናፊነቷን ታረጋግጣለች። በመታገስ ነፍሷን ታድናለች። ወደ ድል ለመድረስ ዓለም ኃይልን፣ አምባገሮን፣ ሥልጣንን በመጠቀም ወይም በማሳየቷ ነው። ክርስቲያን ግን ራሱን የሚከላከልበት መልሶ በመውጋት ሳይሆን ታግሶ በማለፍ ብቻ ነው። ለዚህ ነው በታላቅ ስደት ዘመን ውስጥ የነበሩት ክርስቲያኖች ሊያጠፏቸው የተነሱባቸውን ጠላቶቻቸውን ለመቋ ቋም የፖለቲካ ድርጅት ሲያቋቁሙ፣ የወጓቸውን መልሰው ለመውጋት፣ ወይም መብታቸውን ለማስከበር ምንም ዓይነት ጥረት ሲያደርጉ ያላየና ቸው። አማኝ በዚህ ዓለም ውስጥ ሁሉን ነገር ቢያጣ፣ ነፍሱን ግን ያተር ፋል። መከራ ለገጸ ባሕሪው ጥሩ መሠረት ይሆንለታል። ወርቅ በእሳት እንደሚጠራ፣ መከራም የአማኞችን ልብ ያጠራል።

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ይኸውም ከ54 ዓ.ም እስከ 305 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ድረስ፣ የተለያዩ ትላላቅ ስደቶች በሮማ ግዛት ውስጥ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ ተነስቶ እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክ ራል።፣ እነዚህ ታሪክ ያደነቃቸው፣ በታላቅ መከራ ውስጥ ያለፉ አማኞች አብዛኛዎቹ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ተራ ምዕመ ናን ናቸው። ይህንን እውነት ስናውቅ፣ የእነዚህ ሰዎች ድፍረትና ቆራጥ ነት እጅግ በጣም ያስደንቀናል። እንደ እኔና እንደ እናንተ ሥጋና ደም የለበሱ ተራ ሰዎች ከሆኑ፣ *"ሕይወታቸውን አሳልፈው ለመስጠት ይህን ዓይነት ድፍረትና ቆራጥነት ማግኘት የቻሉበት ምክንያት ምንድነው?"* ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

ስለ እነዚህ ሰዎች በጣም እርግጠኞች የሆንበት አንድ ነገር ቢኖር፣ ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መስጠት ድረስ ጌታ ኢየሱስን እጅግ በጣም የሚወዱት መሆናቸውን ነው። ጌታ ኢየሱስ *"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"* ብሎ የተናገረውን



በሕይወታቸው ኖረው ያሳዩ ናቸው። መስቀላቸውን ተሸከመው፣ የመስ ቀሉን ባለቤት እስከ መጨረሻው ድረስ የተከተሉ ናቸው። እኛ እርሱን ለመከተል ውሳኔ ያደረግን፣ ጌታ ኢየሱስ የራሱን መስቀል አስቀድሞ እንደ ተሸከመ፣ እኛም የራሳችንን መስቀል የመሸከም አቅም ይኖረን ይሆን? የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ከወሰንን፣ በቅድስና ከእርሱ ጋር ተቀራርበን መኖርን ከመረጥን፣ ከመስቀል ነጻ ሆነን ልንከተለው እንደ ማንችል ማወቅ አለብን። ይህ የክርስትና ጉዞ መስቀል ያለበት ጉዞ ስለ ሆነ፣ የመጨረሻውን ትርፍ ተምነን፣ ራሳችንን በደንብ ማዘጋጀት አለብን።

የመጀመሪያውን የመስቀል ጽዋ የቀመሰው፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከእርሱ በኋላ በሮማ ግዛት ውስጥ፣ በተለያዩ የሮማ ነገሥታት አነሳሽነት ታላላቅ የክርስቲያኖች ስደቶች ተፈጽመዋል። በዚህ ምክንያት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ሕይወ ታቸውን በሞት አጥተዋል። የሁሉንም ታሪክ ለማቅረብ ጊዜም ሆነ ሥፍራ ስለማይበቃን፣ ለትምህርት እንዲሆነን የጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥሎ እናቀርባለን።

ማክሲመስ የተባለው አምባገነንና ጨካኝ የነበረ የሮማ ንጉሠ ነገ ሥት፣ ክርስቲያኖች እየታደኑ እንዲገደሉ በመላ ግዛቱ ውስጥ አዋጅ አወጣ። በዚህ ዘመን በጣም ብዙ የሆኑ ክርስቲያኖች ስለ ተገደሉ፣ እያንዳ ንዱን በግል ለመቅበር ቦታ ስላልበቃ፣ በጣም ትልቅ የሆነ አንድ ጉድጓድ ቆፍረው ሃምሣዎቹን፣ ስድሳዎቹን በአንድ ላይ ይቀብሩ ነበር።

- *በእምነታቸው ምክንያት ከተገደሉት ውስጥ ፖንታኒየስ የተባ ሉት የሮም ጳጳስ የነበሩ፣ ሳርዲኒያ ውስጥ በእምነታቸው ምክን ያት ስደተኛ ሆነው በሚኖሩበት ወቅት፣ የጣዖት አምልኮትን ተቃው መው በመስበካቸው ተይዘው ተገድለዋል።*

- *ከፖንታኒየስ በኋላ ተተክተው ያገለግሉ የነበሩ፣ አንጢሮስ እየተ ባሉ የሚጠሩ ጳጳስ የሰማዕታትን ታሪክ ዘርዝረው በመጻፋቸው፣*

*መንግሥትን በጣም በማስቆጣቱ፣ አገልግሎታቸውን ገና እንደ ጀመሩ፣ እርሳቸውም እንደ ጳጳሱ ፖንታኒየስ ተገድለዋል።*

- *ሮማዊ ሴኔቴር (የፓርላማ አባል)፣ ፓማቺየስ ከነቤተሰባቸው፣ እንዲሁም 42 ክርስቲያኖች በአንድ ቀን ውስጥ አንገታቸው በሰይፍ ተቆርጦ በከተማው መግቢያና መውጫ ላይ የተቆረጠውን ጭንቅላታቸውን በመደርደር እንደ ኤግዚቢሽን ሕዝቡ እንዲያየው ያደርጉ ነበር።*
- *እንዲሁም ካልፖድየስ የተባለ ክርስቲያን አገልጋይ በሮም ከተማ መሬት ለመሬት እየጎተቱ ካሰቃዩት በኋላ፣ በአንገቱ ላይ ትልቅ መጅ አስረው ጢብሮስ ወንዝ ውስጥ ወረወሩት።*
- *በቁንጅናዋ ተወዳዳሪ ያልነበራት ማርቲና እየተባለች የምትጠራ ልጃገረድ ደግሞ ክርስቲያን መሆኗን በግልጽ በመናገሯ አንገቷ በሰይፍ ተቆርጦ ሕይወቷ አልፏል።*
- *እንዲሁም በዚሁ ዘመን ሂፖሊተስ የተባለ ክርስቲያን አገልጋይ ደግሞ ተሰቃይቶ እንዲሞት፣ ከፈረስ ጋር አስረው መሬት ለመሬት እየጎተቱ አሰቃይተው ገድለውታል።*

"ከሞት ለመዳን ክርስቲያን መሆናቸውን ለምን አይደብቁም?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እምነታቸውን መደበቅ፣ በክርስቶስ ማፈር መስሎ ስለሚሰማቸው፣ በእርሱ ከሚያፍሩ ሞትን የሚመርጡ በመሆናቸው እንጂ፣ ሞኞች ሆነው አይደለም።

ከላይ የጠቀስናቸውን ስደቶች ያፋፋመው ማክሲመስ የተባለው ንጉሠ ነገሥት በ238 ዓመተ ምሕረት (እ.ኤ.አ.) ሲሞት፣ በምትኩ ጎርዲያን የተባለው ንጉሥ ነገሠ። ከጎርዲያን ቀጥሎ ደግሞ ፊሊፕ የተባለው ንጉሥ ነግሦ ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች በነገሡበት ዘመን ለአጭር ጊዜ ቢሆንም፣ ይኸውም ከስድስት እስከ አሥር ዓመት ያህል ክርስቲያኖች ከስደት ነጻ ሆነው ነበር። በ249 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ግን አሌክሳንደርያ ውስጥ፣ መንግሥት ወይም ንጉሠ ነገሥቱ ሳያውቅ፣



የጣዖት አምልኮት ቄስ የነበረ አንድ ክርስቲያኖችን በጣም የሚጠላ ጨካኝ ሰው፣ በክርስቲያኖች ላይ ታላቅና መራራ ይሆን ስደት ያካሂድ ነበር።

- *በዚህ ለክርስቲያኖች በጣም መራራ በሆነበት ዘመን፣ በዕድሜ ያቸው ጠና ያሉ ወይም ያረጁ፣ሜትሩስ የተባሉ አንድ ክርስቲያን ሰው፣ "እግዚአብሔርን እንጂ ጣዖትን አላመልክም" በማለታቸው፣ በዱላ ተቀጥቅጠው፣ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ።*
- *እንዲሁም ኪንታ የተባለች አንዲት ክርስቲያን ሴት፣ ሰውነቷ እስኪተለተል ድረስ በጉማሬ ከገረፏት በኋላ፣ ባልጩት ድንጋይ ካለበት መሬት ላይ እየጎተቱ ካሰቃዩዋት በኋላ በመጨረሻ በድንጋይ ተወግራ ሕይወቷ አልፏል።*
- *እንዲሁም አንዲት የሰባ ዓመት ሴት፣ ክርስቲያን መሆናቸውን በግልጽ በመናገራቸው፣ በእሳት ከነነፍሳቸው እንዲቃጠሉ ተፈርዶባቸው፣ ተቆልሎ ከቆመው እንጨት ጋር ጠፍረው ካሰሯቸው በኋላ፣ በተከመረው እንጨት ላይ እሳቱን ለኮሱበት። እኛም አሮጊት ምሕረት እንዲያደርጉላቸው ለመኗቸው። በዚህን ጊዜ ክርስቶስን ከድተው እምነታቸውን ይተው ይሆናል ብለው በማመን ሲፈቷቸው፣ ክርስቶስን በመካድ ፈንታ፣ እነርሱን እስኪደንቃቸው ድረስ ከዚያ በኃይል ከሚነደው እሳቱ ውስጥ ዘለው በመግባት ከነነፍሳቸው ተቃጥለው ሕይወታቸው አልፏል።*

እኔና እናንተ ይህን ታሪክ የምናነበው እየዘገነን፣ በአድንቆት ተሞልተን እንጂ፣ እንደ ተረት እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ። በበኩሌ የእነዚህን ታላላቅ የእምነት አርበኞችን ታሪክ ሳነብ፣ ሁለት ዓይነት ጥያቄ በውስጤ ይመላለስ ነበር። አንደኛው፣ እነዚህ አማኞች፣ ክርስቲያን መሆናቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው፣ ታድነው ከፍርድ ወንበር ወይም ከከሳሾቻቸው ፊት ሲቀርቡ፣ በእነርሱ ምትክ ራሴን አቀርብና፣ እነዚህ ሰዎች በቆራጥነት ለሚወዱት ታላቁ ጌታ ራሳቸውን እንደ ሰጡት፣ እኔም እራ

ሴን እሰጥ ይሆን? ብዬ ውስጤን እመረምራለሁ። አንዳንዶቻችሁ "ራሱን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል" ብላችሁ መገመታችሁ አይቀርም። ይሁን እንጂ፣ "ራሴን ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ" በማለት በድፍረት ከመናገር ይልቅ፣ ሁኔታው ሲፈጠር እግዚአብሔር በእምነቴ እንድጸና ጸጋውን ያበዛልኝ ይሆናል ማለቱ ይቀለኛል።

በውስጤ የሚመላለሰው ሁለተኛው ጥያቄዬ "የጥንት ክርስቲያኖችን፣ ከእኛ ከዘመኑ ክርስቲያኖች የበለጠ ቆራጥና ፍጹም ደፋር ያደረጋቸው ነገር ምንድነው?" የሚል ነው። ሁላችንም የምናምነው አንዱን ጌታ ከሆነ፣ እነርሱ መስቀሉን በአግባቡ ሲሸከሙ፣ እኛ ግን *"በክርስትና ሕይወት ውስጥ ዘውድ እንጂ መስቀል የለም፤ መጥገብ እንጂ መራብ የለም፣ መበልጸግ እንጂ፣ ድህነት የለም፣ መክበር እንጂ ስለ ኢየሱስ ሲሉ መዋረድ የለም"* የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የሌለውን ትምህርት አምነን የተቀበልን የምንመስለው ለምን ይሆን? አማኞች መስቀላቸውን በታማኝነትና በትዕግሥት እንዲሸከሙ በማደፋፈርና በማበረታታት ፈንታ፣ የክርስትና ሕይወት መስቀል የሌለበት አድርገን የምናቀርበው ለምን ይሆን?

## 4. ከመስቀሉ መሸሽ የሚሞክሩ አማኞች አሉ

በአሁኑ ጊዜ *"አማኝ በመከራ ውስጥ ማለፍ፣ መስቀል መሸከም አለበት"* የሚለውን እምነት መቀበል ያቃታቸው ሰዎች የበዙበት ዘመን ሆኗል። ኢየሱስ ***"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"*** በማለት የተናገረው ንግግር ጊዜ ያለፈበት፣ በአሁኑ ጊዜ በክርስትና እምነት ውስጥ አስፈላጊ ያልሆነ ነገር አድርገው የሚያስቡ፣ ይህንን በመናገሩ ክርስቶስን እንደ ሞኝ፣ ከጊዜው ጋር የማይሄድ አድርገው የሚቆጥሩትና የሚያስቆጥሩት ብዙዎች እንዳሉ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፣ አማኞች በመከራና በስቃይ ውስጥ የሚያልፉ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች በጻፈው መልዕክት፣



- *"...አሁን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች ብንሆን፣ በኋላ የክብሩ ተካፋዮች እንሆናለን"* ይላል (ሮሜ 8፡17)። እዚሁ መዕራፍ ውስጥ፣ ቁጥር 22 ላይ ደግሞ፣
- *"ፍጥረት ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ በምጥ ጭንቀት ተይዞ በመቃተት ላይ መኖሩን እናውቃለን"* ይላል።

እግዚአብሔር የመከራን፣ የመስቀልን መንገድ ለምን እንደመረጠ፣ ውስን አዕምሮ ስላለን፣ ወይም ያለን መረዳት ትንሽ በመሆኑ፣ ሙሉ በሙሉ ሊገባን እንደማንችል ከላይ ገልጸናል። ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ አንዳንድ ያልጠበቅናቸው ነገሮች በሕይወታችን ሲደርስብን "ለምን?" ብለን የምንጠይቀው። እግዚአብሔር አብ ዓለም ከተፈጠረበት ዘመን ጀምሮ መስዋዕት የሚሆነው አንድያ ልጁ የመስቀል ሞት እንደሚሞት ያውቅ ስለነበረ፣ ለረጅም ዘመን በልቡ ውስጥ ተሸክሞት ይኖር ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ በመስቀል ሕይወት ውስጥ አልፎ በመቤዠት ድርጊቱ ብዙዎቹን ከሞት የሚያድን መሆኑን ስለሚያውቅ ደስ ይለው ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር አብ ሀዘንና ደስታ የተፈራረቀበት አምላክ ነበረ። እግዚአብሔር ወልድ፣ ክብሩንና ማዕረጉን ትቶ፣ እንደ ሰው ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር በመምጣት በመካከላችን ተመላለሰ።

ዘመናችን *"ያለመስቀል የክርስትና ሕይወት መኖር ይቻላል"* ብለው የሚያምኑ ሰዎች የበዙበት ዘመን እንደሆነ ገልጸናል። ያለመስቀል ደቀ መዝሙር መሆን የሚቻል ከሆነ፣ *"መስቀሉንም የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"* የሚለውን ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰርዘን ማውጣት አለብን። መጽሐፍ ቅዱሳዊነት በሌለው ትምህርት የተወናበዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ ቃሉ በግልጽ ቢናገርም፣ *"መልካም ነገር እንጂ ክፉ ነገር ጌታ ስለማይሰጥ፣ መስቀሉን አንቀበልም..."* የሚሉ፣ ከመከራ ለመሸሽ የሚሞክሩ ብዙዎች ናቸው።

*አንድ ጊዜ አንዲት እናት ልጇ ታምባት የቤተ ክርስቲያን መጋቢው እንዲጸልይለት ይዛው መጣች። መጋቢውም በሞትና በሕይወት መካከል ያጣጥር ለነበረ ልጇ ሲጸልይ፣ "ጌታ ሆይ! ፈቃድህ ከሆነ*

ከሞት አድነው" አለ። እናትየው በመጋቢው ጸሎት ተበሳጨችና ጸሎቱን አቋርጣ "ፈቃድህ ከሆነ ብለህ አትጸልይ፤ ፈቃዱ መሆን አለበት። ፈቃድህ ከሆነ የሚለውን አባባል አልቀበልም" አለችው። አገልጋዩ ጸሎቱን እዚሁ ላይ አቆመ።

ይህን ዓይነቱን ጸሎት የተቃወመችበት ምክንያት፣ የዘመኑ የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች "ፈቃድህ ይሁን" ብሎ መጸለይ እለማ መንን ስለሚያሳይ ትክክል አይደለም" ብለው ስለሚያስተምሩ ነው። እንደ እነርሱ ከሆነ፣ "አባት ሆይ! ፈቃድህ ይሁን" ብሎ የጸለየውን ኢየሱስንም መንቀፋቸው ነው። የሚገርመው ነገር ያ ልጅ ከሞት ዳነ። ይሁን እንጂ፣ በጣም ክፉ ልጅ ሆኖ በማደጉ፣ እናትየው ከመጠን በላይ ተሰቃየች። 22 ዓመት ዕድሜ ላይ ሲደርስ በፈጸመው ወንጀል ምክንያት እናትየው ዓይኗ እያየ በስቅላት ሞተ። ያቺ ሴት ልጇ ወደ ፊት ምን ዓይነት ልጅ እንደሚሆን ብታውቅ ኖሮ "እንደ ፈቃድህ ይሆን" ማለት አይከብዳትም ነበር።

- ጊዜው 1987 ዓመተ ምህረት (እ.ኤ.አ.) ሲሆን፣ ሥፍራው አሜሪካን አገር ነው። በቴሌቪዥን ሰባኪነቱ በጣም የታወቀ የአንድ ሰባኪ ሚስት፣ በቴሌቪዥን ታስተምራለች። በትምህርቷ "ስለ ክርስቶስ መከራ መቀበል አስፈላጊ አይደለም…" በማለት አድማጮቿን ለማሳመን ጥረት ስታደርግ ትታያለች። በወቅቱ ያዳምጧት የነበሩ ሰዎች፣ ግማሾቹ የምታስተምረውን ትምህርት የተቀበሉ መሆናቸውን ራሳቸውን በመነቅነቅ ሲገልጹ፣ ሌሎች ደግሞ ያጨበጭቡላት ነበር። ክርስቲያኖች ከችግር፣ ከመስቀል ሕይወት ነጻ ሆነው መኖር አለባቸው ብላ የምታምን ነች።

እንዴት ያሳዝናል? ይህችን ሴት የሚመስሉ የዘመኑ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች፣ መስቀሉን ከሕይወታቸው ያስወጡ፣ ያለመስቀል የክርስትና ሕይወትን ለመኖር የሚሞክሩ፣ ራሳቸውን ግን "ክርስቲያን" ብለው የሚጥሩ፣ እነርሱ ስተው ሌሎቹን የሚያስቱ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የጠወለጉ፣ ማደግ የማይችሉ መሳይ ክርስቲያኖችን እያፈሩ



መሆናቸውን የተረዱት አይመስሉም። ለእነርሱ መከራ፣ ወይም መስቀል ማለት ምን ይሆን? ካላቸው ሁለት መርቼዲስ መኪናዎች ውስጥ የአንደኛው መርቼዲስ መኪና ጎማ መተንፈስ፣ ወይም ጌጣ ጌጥ ለመግዛት ሄደው ሰዓት ደርሶ ሳይገዙ ሱቁ ቢዘጋባቸው ያንን እንደ ትልቅ መከራ የሚቆጥሩ ናቸው።

የክርስትና ሕይወት የመስቀል ሕይወት መሆኑን ባለመረዳት አንዳንድ ሰዎች አንዳንድ ችግር በሕይወታቸው ሲያጋጥማቸው ልባቸው መራራ ሆኖ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተው፣ በእግዚአብሔር ላይ ቦክስ ጨብጠው የሚሞቱ አሉ። የእኔና የእናንተ መስቀል በሰይፍ መታረድ፣ በእሳት መቃጠል፣ በመጋዝ መሰንጠቅ፣ በአውሬዎች መበላት፣ ወህኒ በመጣል ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ማለፍ፣ መራራ የሕይወት ጽዋ መጠጣት ሊሆን ይችላል።

ለመሆኑ እኔና እናንተ እንድንሸከም የሚሰጠንን መስቀል መምረጥ ወይም "እምቢ!" ማለት እንችላለን ወይ? "ለጌታዬ ስል ምን ዓይነት ዋጋ ከፈልኩ? በወንጌል አተረፍኩ? ወይስ ከሰርኩ?" ብዬ ራሴን ስጠይቅ፣ ጎልቶ የሚታይ ነገር ባለማየቴ፣ በራሴ የማፍርበት ጊዜ አለ። ይህን ስል "መከራ እንዲደርስብኝ እፈልጋለሁ" ማለቴ አይደለም። የእውነትን ወንጌል ብቻ እንዲሰብኩበት በተሰጣቸው መድረክ ላይ እየወጡ ሳያፍሩ "የእኔ ጌታ በብልጽግና በሽበሽ አደረገኝ" በማለት ብልጽግናቸውን የሚያውጁ፣ የመኪናቸውን ቁልፍ የሚያወዛውዙ አሉ። ይህን ሲያደርጉ ለወንጌል ሲሉ በድህነት ውስጥ ሆነው ዋጋ የሚከፍሉትን፣ እግዚአብሔር የሚያዳላ አምላክ መስሎ እንዲታያቸው የሚያደርጉ መሆናቸውን የተረዱት አይመስሉም።

ክርስቶስ ከእኛ ጋር በመሆን፣ እኛ መቅመስ የሚገባንን መከራ ስለ እኛ ሲል ቀመሰ። የሰዎች ልጆች የሚያልፉበትን ሕይወት እያየ ልቡ በሀዘን ተሞላ፤ ከአልአዛር መቃብር አጠገብ ቆሞ አለቀሰ። የኢየሩሳሌምን ከተማ አይቶ፣ ያለችበትን አሳዛኝ ሁኔታ ተረድቶ ልቡ በርህራሄ ተሞልቶ ዕንባውን እያፈሰሰ፣ "ሰላምሽ የሚሆነውን ምነው አንቺ

*ዛሬ በተረዳሽ ኖሮ! አሁን ግን ከዐይንሽ ተሰውሮአል፤ ጠላቶችሽ ዙሪያሽን ቅጥር ሠርተው ከየአቅጣጫውም ከበው አንቺን የሚያስጨንቁበት ጊዜ ይመጣልና! አንቺና በቅጥርሽ ውስጥ የሚኖሩትንም ልጆችሽን ከዐፈር ይደባልቃሉ! ድንጋይም በድንጋይ ላይ አይተውም! የመጎብኛሽን ጊዜ አላወቅሽምና"* በማለት አለቀሰ (የሉቃ. 19፥41-44)።

ኢየሱስ እንባውን ያፈሰሰው ለራሱ ሳይሆን፣ ወደ ፊት በኢየሩሳሌም ላይ የሚደርሰውን አደጋ አስቀድሞ ስላወቀ ነው። በዚያን ጊዜ አይሁዶች በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ከፍተኛ ትግል ውስጥ ስለ ነበሩ፥ በ70 ዓመተ ምህረት ኢየሩሳሌም በጠላቶቿ ምክንያት ፍርስርሷ እንደ ወጣ፥ ታሪክ ይመሰክራል። በፖለቲካ ውስጥ ያለውን ኃይልና ስልጣን የመፈለግ ጥማቷን ትታ የክርስቶስን መንገድ ብትከተል ኖሮ፥ ያ ሁሉ ጥፋት ባልደረሰባትም ነበር። ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ያፈሰሰው ዕንባ፥ ሰዎች በሞኝነታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው፥ ወይም ከፈቃዱ ውጪ በመሆናቸው ሊደርስባቸው የሚችለውን መከራና ስቃይ የተረዳው እግዚአብሔር አምላክ የሚሰማውን ስሜት የሚገልጽ ነበር።

መስቀል፣ ወይም የመከራ ሕይወት ሁልጊዜ በዙሪያችን ያለ ነገር እንደሆነ ማወቅ ይገባናል። መስቀል እንደ ሌሎ ለማስመሰል መሞከር እውነትን መካድ ይሆናል። እግዚአብሔር ክርስትናን መከራና እንዲሁም አስቸጋሪ የመስቀል ሕይወት ያለበት እንዲሆን ያደረገበት ምክንያት ለምን ይሆን? ብለን ብዙ ጊዜ ጠይቀናል። ለጊዜው የምንመርጠው ነገር አይሁን እንጂ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ መከራና ሲቃይ ትልቅ ዋጋ እንዳለው የታወቀ ነው። ፍቅር፣ ከመከራ ጋር አብሮ ይሄዳል። ነጻነት ከመከራ ጋር የተያያዘ ነው። እንዲሁም የእውነት፣ የጥበብና የዕውቀት ሕልውና ከመከራ ጋር አብሮ ይሄዳል። ማንኛውም ነገር በራሱ ጠቃሚነት ያለው፣ በገንዘብ የማይገዛ፣ በመደራደር አሳልፎ የማይሰጥ ነገር ሁሉ ከመከራ ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ *"ነጻነት"* በገንዘብ የሚገዛ፣ በመደራደር የሚገኝ አይደለም። ለዚህ ነው ሰዎች ነጻነታቸውን እንደያዙ



ለመቆየት ደማቸውን የሚያፈሱት። ኢየሱስም ለእኛ መንፈሳዊ ነጻነት ለማስገኘት ሲል ደሙን አፈሰሰ።

## 5. በመከራው ክርስቶስን መምሰል ምርጫችን ይሆን?

ከዚህ በፊት ከማላውቃቸው አንዳንድ ሕጻናት ልጆች ጋር ለመቀራረብ መግቢያ እንዲሆነኝ ስማቸውን ጠይቄ ከተዋወቅኋቸው በኋላ፣ *"ትልቅ ስትሆን ምን መሆን ትፈልጋለህ?"* ብዬ እጠይቃቸዋለሁ። ከዚህ በፊት በሌሎች ሰዎች ተመሳሳይ ጥያቄ ተጠይቀው መልስ የሰጡ፣ ወይም መሆን የሚፈልጉትን የሚያውቁ ከሆነ ወዲያው *"ሀኪም፣ መሀንዲስ፣ ሳይንቲስት...."* የሚል መልስ ይሰጡኛል። አንዳንዶች ግን፣ *"እኔ እንጃ! አላውቅም..."* የሚል መልስ ይሰጡኛል። እኔም እየቀለድኩ *"አንተ የማታውቀው ከሆነ እኔ ልምረጥልህ! መንገድ ጠራጊ ብትሆንስ?"* እላቸዋለሁ። ማንም መንገድ ጠራጊ መሆን ስለማይፈልግ፣ *"አይ! መንገድ ጠራጊ መሆን አልፈልግም"* የሚል መልስ ይሰጡኛል። አብዛኛዎቹ ለማለት ያህል እንጂ፣ ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን በትክክል አውቀውት አይደለም። አንዳንዶቹ ግን ዝንባሌያቸውን በእርግጠኝነት ስለሚያውቁ፣ *"እንዲህ መሆን ነው የምፈለገው"* የሚል መልስ ይሰጡኛል።

ልጆች ብቻ ሳይሆኑ፣ በዕድሜ የገፉትም ሰዎች እንዲኖራቸውና እንዲሁም መሆን የሚፈልጉት የራሳቸው የሆነ ምኞት አላቸው። ሕጻናት ልጆችም ሆኑ በዕድሜ የገፉት፣ ሁለቱም የሚመሳሰሉበት አንድ ነገር አላቸው። ይኸውም፣ በጎ ነገር፣ ትልቅ ነገር እንጂ ከፉ ወይም አነስተኛ ነገር ለማግኘት የማይመኙ መሆናቸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም እንዲሆንለት ከልቡ የሚፈልገው ወይም የሚመኘው ነገር ነበረው። ምኞቱን ለፊልጵስዩስ አማኞች በደብዳቤ ሲገልጽ፣

- *"ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በስቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ"* አለ *(ፊልጵ. 3፡10)*።

ጳውሎስ ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? እንደ ዮሐንስና እንደ ያዕቆብ *"በጌታ ቀኝ መቀመጥ እመኛለሁ"* በማለት ፈንታ *"በመከራውና በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ ማለቱ ምን ነክቶት ነው? አሞታል እንዴ?"* ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አንዳንድ የዘመኑ የብልጽግና ትምህርት አስተማሪዎች ቢያገኙት፣ በቅድስናው እግዚአብሔር ያደነቀውን ኢዮብን እንደተቹት ጳውሎስንም ይተቹት ነበር። ኢዮብ በመከራ ውስጥ ያለፈው በእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን፣ *"የፈራሁት ደረሰብኝ ስላለ ነው"* ብለው እንደተቹት፣ "ጳውሎስም የተሰቃየው መከራና ስቃይ በመፈለጉ ነው" ብለው ማለታቸው አይቀርም።

የቴርሴሱ ጳውሎስ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስን ከመሞቱና ከትንሳኤው፣ እንዲሁም ወደ አብ ከመሄዱ በፊት በሥጋ ፊት ለፊት አይቶት እንደማ ያውቀው ግልጽ ነው። ጳውሎስ *"ክርስቶስን እንዳውቅ እመኛለሁ"* ሲል፣ ምን ማለቱ ይሆን? ሐዋርያው ጳውሎስ የመስቀሉ ምስጢር ስለገባው፣ የልቡን ምኞት ሲገልጽ፣ *"...የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ..."* (ፊልጵ. 3፡11) አለ። ይህን ያለው፣ መንፈሳዊ ለመምሰል ሳይሆን፣ ከልቡ ነው። ክርስቶስን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ አልፏል።

*5 ጊዜ 39 ጅራፍ (195) ተገርፏል።*

*3 ጊዜ የጀርባ አጥንቱ እስኪከሰከስ ድረስ በዱላ ተቀጥቅጧል።*

*1 ጊዜ በድንጋይ ተወግሯል።*

*3 ጊዜ በመርከብ ተገልብጧል። ብዙ ጊዜ ወህኒ ቤት ተጥሏል።*

ይሄ ሁሉ አልበቃም ብሎት *"በመከራው እንድካፈል በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ..."* ሲል እንሰማዋለን። ለማለት ያህል የተናገረው ሳይሆን ከልቡ የወጣ እንደሆነ እርግጠኞች ነን። እኔን *"መለሰ የልብህ ምኞት ምንድነው?"* ብላችሁ ብትጠይቁኝ፣ *"ኢየሱስ የቀመሰውን መከራ ለመቅመስ፣ ኢየሱስ የጠጣውን ዓይነት መራራ ጽዋ ለመጠጣት፣ ኢየሱስ የሞተውን ሞት ለመሞት እመኛለሁ"* ብዬ አልነግራችሁም። እውነቱን ልንገራችሁና እንኳን



እርሱ የቀመሰውን መከራ ለመቅመስ ቀርቶ፣ የራሴ መከራ፣ የራሴ መስቀል ከብዶብኝ ልጥለው ትንሽ የሚቀረኝ ጊዜ እንዳለ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

## 6. በመስቀሉ ውስጥ የምንቀምሰው መከራ፣ ለጥቅማችን ነው

*1ኛ፣ መከራና ስቃይ፣ ዘላለማዊ ስለሆነው ታላቅ ነገር በቂ የሆነ መረዳት እንዲኖረን ያስችለናል።*

በመከራና በስቃይ ወቅት ሰው ሊያየው የሚገባውን ዘለዓለማዊ የሆነውን እውነት፣ እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ጊዜያዊውና ዘለዓለማ ዊውን አወዳድሮ በማቅረብ (በማሳየት)፣ ማየት የሚገባንን ትልቁን ነገር ያሳየናል። በሕይወታችን የምንቀምሰው ወይም የምናልፍበት መከራ፣ በአሁኑ ወቅት እውነትነት ያለው ከባድ የህመም ስሜት ያለው ሲሆን፣ ይኸው መከራና ስቃይ በዘለዓለማዊ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሲታይ ግን፣ በጣም ትልቅ ዋጋ ላለው ነገር ወይም ለመንግሥተ ሰማይ ለማዘጋጀት የሚጠቀምበት መሣሪያ በመሆኑ፣ በመከራ ውስጥ የሚያልፈው ሰው ጊዜ ያዊነቱን ተረድቶ ጸንቶ እንዲቆም ይረዳዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ፣

- *"በየአቅጣጫው መከራ ይደርስብናል፤ ግን ተስፋ አንቆርጥም፤ ጠላቶች ያሳድዱናል፤ ግን ወዳጆች አጥተን አናውቅም፤ ተመትተን እንወድቃለን፤ ግን አንሞትም"* ይላል (2 ቆሮ. 4፡8-9)።
- እዚሁ ምዕራፍ ላይ ከ16 እስከ 18 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ *"ስለ ዚህ ተስፋ አንቆርጥም፤ ምንም እንኳ ውጫዊው ሰውነታችን ቢጠፋ፤ ውስጣዊው ሰውነታችን በየቀኑ ይታደሳል። ይህም ቀላ ልና ጊዜያዊ የሆነ መከራችን ወደር የሌለውን እጅግ ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል። እኛ የምንመለከተው የማይታየ ውን ነገር እንጂ የሚታየውን አይደለም፤ ምክንያቱም የሚታየው ነገር ጊዜያዊ ነው፤ የማታየው ግን ዘላለማዊ ነው"* ይላል። ቀላ ልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን፣ ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ክብር የሚያስገኝልን እንደሆነ በግልጽ ይናገራል።

*2ኛ፣ መከራና ስቃይ፣ የእግዚአብሔር ቃል በጅምላ የተጻፈ ብቻ እንዳልሆነ፣ ለግላችን (ለያንዳንዳችን) የተለየ ትርጉም ያለው መሆኑን እንድንረዳ (እንዲገባን) ያስችለናል።*

ለምሳሌ፣ ኢሳያስ 55፥1 ላይ፣ ባዶ እጃችንን ሆነን፣ ልባችን ተሰብሮ፣ በአዕምሯችን ግራ ተጋብተን ሰፊ የሆነውን ጸጋ እንድንቀበል፣

- *"… 'የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውሃ ኑ፤ የምትገዙበት ገንዘብ የሌላችሁ ኑ፤ ያለ ገንዘብና ያለ ዋጋ እህል ወስዳችሁ ብሉ፤ የወይን ጠጅና ወተትም በነጻ ጠጡ"* በማለት ይጠራናል።

በማጣት መነጽር ውስጥ ስናይ፣ ደስታን ለመፈለግ ጉልበታችንን በከንቱ ማባከናችን ይታየናል። ይሄ ሲሆን፣ ዘለቄታ ያለውን ደስታ ለማግኘት ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር እንመልሳለን። በደንብ ካዳመጥነው፣ ጥሩውን የበለጠ የመለየት ችሎታና ዕውቀት እናገኛለን።

- *"ለማይጠቅም ምግብ ገንዘብ የምታባክኑት ለምንድን ነው? ለማያጠግብ እንጀራ ስለምን በከንቱ ትደክማላችሁ? ይልቅስ ብታደምጡኝና እኔ የምላችሁንም ብታደርጉ፣ ከሁሉ የተሻለ ምግብ በማግኘት ትደሰታላችሁ"* ይላል (ኢ.ሳ. 55፥2)።

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር አሳብና መንገድ እኛ እንደምንፈልገውና እንደምናስበው የማይሆንበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ፣ *"በጥሩ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ጥሩ ያልሆነ ነገር ለምን ይደርስባቸዋል? ጥሩ ባልሆኑ ሰዎች ሕይወት ላይ ደግሞ ጥሩ ነገር ለምን ይሆንላቸዋል?"* በማለት የምንጠይቅበት ጊዜ አለ።

*ጥሩ በሆኑ ሰዎች ላይ ጥሩ ያልሆነ ነገር የሚደርስባቸው፣ ምናልባት በኃጢአት ምክንያት ሊሆን፣ ወይም ከዚያ በጎ ካልሆነ ነገር ውስጥ በጎ ነገር እንዲማሩበት ሊሆን ይችላል።*

*በሌላ በኩል ደግሞ ጥሩ ባልሆኑ ሰዎች ሕይወት ላይ ጥሩ ነገር የሚደርሰው፣ ጥሩ ነገር የሚገባቸው ሆነው ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ሰፊ በመሆኑ ይሆናል።*



*መልካም ነገር በክርስቲያኖች ላይ ብቻ የሚደርስ ቢሆን ኖሮ፣ ሁሉም "ክርስቲያን ነኝ" ማለት ይጀምር ነበር። በዚህ ዓይነት እምነት የእግዚአብሔርን እጅ መጠምዘዣ መንገድ ይሆን ነበር።*

መጥፎ በሚባሉ ሰዎች ውስጥ መልካም ነገር እንዳለ ሁሉ፣ ጥሩ በሚባሉ ሰዎችም ሕይወት ውስጥ መጥፎ ነገር ሊኖር እንደሚችል ማወቁ ይጠቅመናል። በፍጹምነቱ፣ በቅድስናው የተረጋገጠለት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ደግነቱና መልካምነቱ በኢሳያስ 53 ላይ እንደተጻፈው የእኛ ኃጢአት በርሱ ላይ የተጫነ እንደ ሆነው ሁሉ፣ የእርሱ ቅድስናም በእኛ ላይ ስለሚያርፍ፣ በእኛ ላይ የሚደርሰው ክፉ ነገር ሁሉ በኃጢአታችን ምክንያት በእኛ ላይ ለመፍረድ ሳይሆን፣ እኛን ዲሲፕሊን ለማድረግ ወይም እርሱን ወደ መምሰል ሕይወት የምንመጣበት ሂደት በመሆኑ ይሆናል።

*3ኛ፣ መከራና ስቃይ በሕይወታችን የሚደርሰው፣ በእምነት ከክርስቶስ ጋር እንድንያያዝ (እንድንጣመር) ነው።* በቀድሞው ቤተ ክርስቲያን ይተላለፍ የነበረው መልዕክት፣ *"በእምነት ከክርስቶስ ጋር ተለይተህ ለመታወቅ ከፈለግህ፣ መከራ እንደሚደርስብህ ጠብቅ"* የሚል ነበር።

በአሁኑ ወቅት አንዳንድ የሀሰት ትምህርት አስተማሪዎች የሚያስተምሩት የዚህ ተቃራኒ የሆነውን ነው። ይኸውም፣ *"በእምነት ክርስቶስን መምሰልን ከመረጥህ፣ እንደምትበለጽግ፣ ሁሉ ነገር እንደሚሳካልህ እወቅ (ጠብቅ)"* የሚል ነው። እውነተኛው የመጀመሪያው እንጂ ሁለተኛው አይደለም። በዘመናት በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኞች የክርስቶስ የመከራው ተካፋዮች ሆነው አልፈዋል። አሁንም በዓለም ዙሪያ የእርሱ በመሆናቸው ምክንያት ክርስቶስ የቀመሰውን የመከራ ጽዋ የሚቀምሱ አሉ። ሐዋርያው ጴጥሮስ፣

- *"ወዳጆች ሆይ! እንደ እሳት በሚፈትን መከራ ውስጥ ስትገኙ ያልተለመደ እንግዳ ነገር እንደ ደረሰባችሁ አድርጋችሁ አትደነቁ፤ ይልቅስ እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እጅግ ደስ እንዲላችሁ*

*የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በሆናችሁበት መጠን ደስ ይበላችሁ። ስለ ክርስቶስ ስም ብትሰደቡ ክቡር የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ ደስ ይበላችሁ። ከእናንተ ማንም መከራ ሲቀበል እንደ ነፍሰ ገዳይ፣ እንደ ሌባ፣ እንደ ወንጀለኛ በሰው ጉዳይ ጣልቃ እንደሚገባ አይሁን። ክርስቲያን በመሆኑ መከራ የሚደርስበት ቢኖር ግን ስለ ክርስቶስ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር"* እያለ ያጽናናናል (1 ጴጥ. 4፡12-16)።

እኔ እናንተ የክርስቶስ ነን? ከሆንን፣ እምነታችንን ካልደበቀን፣ ወይም አማኝነታችንን እንዳይታወቅ ካልሸፈንነው፣ በቅድስና መኖርን ከመረጥን በመከራ ውስጥ እንደምናልፍ ግልጽ ነው። ክፉው ጠላታችን ምስክርነታችንን ለማበላሸት፣ ወይም ዋጋ ለማሳጣት፣ እምነታችንን ለማዳከም፣ ደስታችንን ለማጥፋት ፈጽሞ አይተኛልንም። ይሁን እንጂ፣ ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች ልንሆን አይገባም። በሌሎች ቅዱሳን ላይ የደረሰው በእኔና በእናንተም ላይ እንደሚደርስ፣ እነርሱ ባለፉበት የመከራ መንገድ እንድናልፍ የሚፈቅድበት ጊዜ አለ። ዓላማው ሁልጊዜ ለበጎ ስለሆነ፣ ምንጊዜም ቢሆን በዚያ መንገድ ብቻችንን ሆነን እንድናልፍ አይፈቅድም። ጳውሎስ ይህንን እውነት በቅጡ ስለተረዳ፣ *"ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በስቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ፤ ለሙታን ትንሣኤም እንድደርስ እናፍቃለሁ"* ይላል (ፊልጵ. 3፡10-11)። በመከራውና በስቃዩ ክርስቶስን ስንመስል፣ እርሱ በመረጠልን መንገድ ብቻ ደስ ብሎን እንሄዳለን። እርሱን መስለን፣ እርሱ በሄደበት መንገድ ስንሄድ፣ የሚያስከፍለውም ዋጋ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን። ሕይወታችን ከእርሱ ጋር የተያያዘ እንዲሆን ከመረጥን፣ የእኛ መከራ የእርሱ፣ የእርሱ መከራ የእኛ ይሆናል። ስለዚህ መከራችን ከየት እንደሚመጣ፣ ወይም ምን ያህል ከባድ መሆን አለመሆኑን ማወቁ ይህን ያህል ግድ አይሰጠንም። ቁም ነገሩ ያለው እርሱ ሙሉ በሙሉ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠርና የዓላማው ወይም የክብሩ መግለጫ እንዲሆን መስጠቱ ላይ ነው።



❖ *ፒተር ክሬፍት የተባለ ክርስቲያን ጸሀፊ መከራና ስቃይ ምን እንደሆነ ሲገልጽ፣ "መከራ ክርስቶስ፣ እርሱን እንድንከተለው ያቀረበልን ጥሪ ወይም ግብዣ ነው። ክርስቶስ ምንም ሳያመነታ ወደ መስቀሉ ሄዷል፤ እኛም ተከትለነው ወደ መስቀሉ እንድንሄድ ይጠራናል። ወደ መስቀሉ የምንሄደው "መስቀል" ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣ የክርስቶስ መስቀል በመሆኑ ነው። መከራ ብጹዕ (የተባረከ) የሆነው፣ በረከት ስለሆነ ሳይሆን፣ የእርሱ መከራ በመሆኑ ነው። መከራ የክርስቶስን መስቀል የሚከሰትበት ሁኔታ መግለጫ አይደለም። መስቀል ግን መከራን ይገልጻል። መስቀል ለመከራ አዲስ ትርጉም የሚሰጥ ነው። በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ መካከልም ያለ ነው። ክርስቶስ የመስቀሉ ተካፋዮች እንድንሆን የመረጠበት ምክንያት፣ በስላሴዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕልውና እኛም ተካፋይነት እንዲኖረን ወይም ተካፋዮች እንድንሆን ነው" አለ።*

*4ኛ፣ መከራና ስቃይ በሕይወታችን የሚደርሰው፣ ለሌሎች ለመመስከር ልዩ ምክንያት ወይም መንገድ እንዲሆንን ነው።*

በምላሳችን ከምንሰጠው ምስክርነት ይልቅ፣ በሕይወታችን ኖረን የምንመሰክረው የበለጠ ኃይል እንዳለው የታወቀ ነው። በመከራና በስቃይ ውስጥ ያለ ሰው፣ በመከራ ውስጥ ያላለፈውን ሰው የሕይወት ምስክርነት ከመስማት ይልቅ፣ በመከራ ውስጥ ያለፈውን ሰው ሕይወት መስማት ይቀለዋል። አንዲት ክርስቲያን ሴት፣ ኤሽያ ውስጥ በፓስተርነት (በመጋቢነት) ያገለግል የነበረው ባሏ በእምነቱና በአገልግሎቱ ምክንያት ብዙ ዓመት ጨለማ ውስጥ ታስሮ በመቆየቱ ምክንያት ዓይነ ስውር ስለሆነው ባሏ እንዲህ አለች።

❖ *"ባሌ ጨለማ ውስጥ ለረጅም ጊዜ እስካሁን ታስሮ መቆየቱ በጣም ያሳዝናል። ይሁን እንጂ፣ በውስጡ ያለው መንፈስ አሁንም ጽኑና ብርቱ በመሆኑ፣ አሁንም ለጌታው ብዙ ፍሬ*

*እያፈራ ነው። እኔና ሁለት ልጆቼ ግን ቤተ ክርስቲያን ሰጥታን ከነበረው ቤታችን ከተባረርን ጊዜ ጀምሮ ሕይወታችንን ለማትረፍ ከቦታ ቦታ እየተንከራተትን ነው። ባለፉት ሁለት ወራት፣ ቤት አልባ የሆኑ ሰዎች ከሚያድሩበት በረንዳ እያደርን ነው። ቢሆንም ጌታን በጣም አመሰግነዋለሁ፣ እንድናልፍበት በሚፈልገው መንገድ በማለፋችን በጣም ደስ ይለኛል። ይህንን ሁሉ የምንታገስበት ትዕግስትና ጉልበት የሰጠን እርሱ እንደሆነ በጣም አምናለሁ። እግዚአብሔር ለሕይወታችን መልካም ዕቅድ እንዳለውም አውቃለሁ። በመከራና በስቃይ ውስጥ፣ እንዲሁም በፈተና ውስጥ አስደናቂ የሆነውን የእግዚአብሔርን በረከትና ደስታ ማየት እንችላለን። ኢሳያስ 25፡4 ላይ፣ "ድኾችና መጻተኞች ሸሽተው ወደ አንተ መጥተዋል፣ በችግራቸውም ጊዜ መጠጊያ ሆነሃቸዋል፣ ከዐውሎ ነፋስ የሚድኑበት ተገን ከፀሐይ ቃጠሎ የሚጠለሉበት ጥላ ሰጠሃቸው..." የሚለው ቃል ያጽናናኛል። በጌታ ላይ ባለኝ እምነት ጸንቼ እንድቆም ያጽናናኛል፣ ያበረታታኛል። ይሄም ባለሁበት እንድቆም ሳይሆን፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ስሆን፣ ወደፊት እንድራመድ ነው" አለች።*

*5ኛ፣ መከራና ስቃይ በሕይወታችን የሚደርሰው፣ በክርስቶስ መታመንን እንድንማር ዕድል እንዲሰጠን ነው።*

ይሄ ለብዙዎቻችን ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ነው ብለን ለመቀበል በጣም አስቸጋሪ የሚሆንብን ነው። በእግዚአብሔር ተማምኖ መቆየት ቀላል አይደለም። ሌላው ቀርቶ ትምህርት ቤት ተምረው እንዲመጡ የላክናቸው ልጆቻችን *"መኪና ገጭቶ ይገድላቸው ይሆን? ትምህርት ቤቱ ውስጥ አደጋ ደርሶ አንድ ነገር ሆነው ይሆን?"* ብለን በማሰብና በጭንቀት ውስጥ የምንቆይ ወላጆች ጥቂቶች አይደለንም። የታወቀው ክርስቲያን ጸሀፊ ኤ ደብልዩ ቶዘር እንዲህ አለ፡



- *ክርስቲያን መስቀልን የተሸከመ ሰውን ይመስላል። 'እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ' ይላል። መስቀል የተሸከመ ሰው፣ የራሱን መጨረሻ ወይም ዕጣ ፋንታ ወሳኝ አይደለም፣ ምርጫውን ያጣው መስቀሉን አንስቶ በተሸከመበት ቀን ነው። ያ የተሸከመው መስቀል የአማኙን ፍላጎት የሚቆጣጠር፣ በሁሉም ነገር ገልቃ የሚገባ ሆነ።"[4]*

እኔና እናንተ ራሳችንን መጠየቅ የሚገባን ጥያቄ ቢኖር፣

*[1ኛ] መስቀሉን አንስተን ስንሸከም፣ ዕጣ ፋንታችንን በሚወስነው ወይም በሚቆጣጠረው ጌታ እንታመናለን ወይ? የሚለው ይሆን፣*

*[2ኛ] በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን በሕይወታችን ገልቃ እንዲገባ እንፈቅድለታለን ወይ? የሚለውን ነው።*

እግዚአብሔርን መተማመን ያቃታቸው ሰዎች አንድ በጎ ያልሆነ ነገር ሲደርስባቸው፣ በእግዚአብሔር በመተማመንና ሁሉን ነገር ለእርሱ በመተው ፈንታ፣ *"እግዚአብሔር እንዳልንቀሳቀስ አድርጎ ማንቁርቴን ይዞ ይመራኛል"* ይላሉ። በመሠረቱ የሚመራን ጉሮሯችንን ይዞ በኃይል ሳይሆን በፍቅሩ ልባችንን ይዞ በመምራት ነው። አንዳንድ ጊዜ ቀላል ባይሆንልንም እንኳን እርሱን መተማመንን መለማመድ ይገባናል። በእርሱ ከታመንን፣ ለእኛ የማይታየው ለእርሱ ስለሚታየው፣ ክፉ ቢመስል እንኳን ለበጎ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል። ምን ያህል መሸከም እንደምንችል አቅማችንን ያውቃል። እርሱ ርህሩህና ደግ፣ በፍቅር የተሞላ በመሆኑ፣ ሌላው ቀርቶ አለማመናችንና ጥርጣሬያችንን ሁሉ ይቅር ይላል። ፍርሃታችንን ጸጥ ያደርጋል። በእምነታችን ደካማዎች ብንሆን እንኳን፣ ልክ እንዳለነው ይቀበለናል። ይህንን እውነት ተቀብለን በሕይወታችን ውስጥ መለማመድ ይገባናል።

---

[4] Gerald B. Smith ed. Men Who Met God. Christian Publications. Camp H[illegible]

የክርስትና እምነት ወደ መከራ፣ ወደ ችግርና ፈተና፣ በመጨረሻም ወደ ትንሳኤ የሚያደርስ ሃይማኖት ነው። ደስ የሚያሰኘው ግን፣ ሰው በግድ ሳይሆን በምርጫ የሚያደርገው መሆኑ ነው። አንዳንድ አማኞች የሚቀምሱት መስቀል ቀላል አይደለም። መስቀል ተወዳዳሪ የሌለውን ዓይነት ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች የሚያልፉበት ቅጣት እንደሆነ ተምረናል። በመስቀል የተንጠለጠለውን ሰው ቀስ በቀስ የሚገድል፣ ተወዳዳሪ የሌለው ጭካኔ የሞላበት አገዳደል ነው። ሚስማሩ እግርና እጁ ውስጥ በመዶሻ ተራ በተራ እየተመታ ሰውነቱን ሰርጉዶ ሲገባ መቁነጥነጥ ተፈጥሯዊ ነው። ሕመሙ ቶሎ እንዲያልፍልን እንፈልጋለን፤ ይሁን እንጂ፣ ቶሎ አያልፍም። ለመሆኑ ከሚሰማን መከራና ጭንቀት የተነሳ፣ እንድንሸከመው ከተሰጠን የመስቀል መከራ ቶሎ የሚያስጥለንን ነገር ብንፈልግ፣ ይህን ያህል ይፈረድብን ይሆን? በሌላ በኩል ደግሞ ለተቀበልነው እምነት ስንል፣ ሕይወታችንን እስከማጣት ድረስ መከራ መቀበልን መምረጥ የለብንም ወይ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የመጨረሻውን ሽልማታችንን ስናስብ፣ እንዲሁም ጌታችን የከፈለልንን ከፍተኛ ዋጋ ስናስብ፣ መስቀላችንን በአግባቡ ተሸክመን ወደ ፊት መጓዝ እንዳለብን እንረዳለን።

ስለ እምነታቸው ሲሉ ሕይወታቸውን ያጡ አማኞች፣ "ሞት ወይስ ሕይወት?" የሚል ምርጫ ተሰጥቷቸው ሞትን የመረጡ ናቸው። ይህን ዓይነቱን ምርጫ መርጠው ከውሳኔ የደረሱት፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምቾት ባለው ወንበር ላይ ተቀምጠው፣ መዘምራን ጣዕም ያለው መዝሙር እየዘመሩ፣ ሁሉም ሰላም በሆነበት ጊዜ ሳይሆን፣ ተቃዋሚዎቻቸው *"ሞኝ አትሁን! እምነትህን ካድና ሕይወትህን አድን"* እያሉ ሲሰድቧቸው፣ እንዲሁም የሚወዷቸው ዘመዶቻቸው ደግሞ *"ትተኸን አትሂድ! የእምነት አቋምህን በልብህ ያዝና ከሞት አምልጥ"* እያሉ እያለቀሱ ሲለምኗቸው፣ ከነፍሳቸው በእሳት ለመቃጠል ቀርበው፣ የእሳቱ ወላፈን እግሮቻቸውን እንደ ደረቅ እንጨት እያነደደው ባለበት ጊዜ፣ ሌላው ቀርቶ ኢየሱስ ራሱ ፈጽሞ የረሳቸው በሚመስላቸው ጊዜ መርጠው የወሰኑት ውሳኔ ነው።



በዚህ ዓይነት ስለ እነርሱ ሲል አስቀድሞ የሞተላቸውን ጌታ እስከ ሞት ድረስ ሊከተሉት ወሰኑ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ፍጹም ልዩ ሰዎች ሳይሆኑ፣ እንደ እኔና እንደ እናንተ ሥጋ የለበሱ ተራ ሰዎች ናቸው።

*መኖር የጠሉ፣ ኑሮ ሰልችቷቸው ሞት የሚፈልጉ አይደሉም።*

*ሞትን የመረጡት ትተዋቸው የሚሄዱ ዘመድ አዝማድ፣ ወላጆች፣ ልጆች የሌሏቸው ብቸኞች ሆነው አይደለም።*

*ሞትን የመረጡት ትተዋቸው ከሚሄዱት ሰዎች የበለጠ የመስቀልን ሞት የሞተላቸውን ጌታ አብልጠው የወደዱ በመሆናቸው ነው።*

*የተፈጥሮ ፍርሃት ስለሌላቸው፣ የጭንቀት ሕይወት፣ መከራ የበዛበት ሞት ስለማያስፈራቸው አይደለም።*

*ነገር ግን ከፍርሃት ስሜታቸው የበለጠ፣ ለጌታቸው ያላቸው የፍቅር ስሜት የበለጠ ብርቱ በመሆኑ ብቻ ነው።*

ከውጪ እኛን ይምሰሉ እንጂ፣ ከውስጣቸው ፍጹም የተለዩ ቆራጥና ደፋሮች ናቸው። ቆራጥና ደፋር ያደረጋቸውም ልዩ ፍጥረቶች በመሆናቸው ሳይሆን፣ *"እስከ ሞት ድረስ እከተልሃለሁ"* ብለው ለጌታቸው የገቡትን ቃል ኪዳን ለማክበር ቁርጥ ውሳኔ በማድረጋቸው ምክንያት ነው።

## 7. የክርስቶስ ፍቅር ከመስቀል እንድንሸሽ አያደርገንም

ኢየሱስን መከተል ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም፣ የሚያስደንቀው ብዙዎችን እንደ ማግኔት የመሳብ ኃይል ያለው መሆኑ ነው። ክርስቶስን በመከተላቸው ምክንያት በአደባባይ ከነፍሳቸው በእሳት ሲቃጠሉ ለማየት ከተሰበሰቡት መካከል፣ ፈርተው *"ኢየሱስ የሚባለውን ጌታ አልከተልም፣ ሞት ያስከትልብኛል"* በማለት ፈንታ፣ ከዚያው ክርስቲያኖች በእሳት ከሚቃጠሉበት አደባባይ ላይ ከማግኔት የበለጠ የመሳብ ኃይል ባለው የጌታ ፍቅር ተስበው ወደ እምነት የሚመጡ ነበሩ። የክርስቶስ ፍቅር መከራ፣ ስደት፣ ሞት ባለበት ወቅት እንኳን በዘመናት ብዙዎችን

ከማግኜት የበለጠ ይስብ እንደ ነበር ታሪክ ይመሰክራል። "ችግር ውስጥ ይጥለኛል፣ ሞት ያስከትልብኛል" ብለው በመፍራትና በመሸሽ ፈንታ፣ ብዙዎቹን እስኪያስደንቅ ድረስ በክርስቶስ ፍቅር ተስበዋል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ እንዲሆነን ከዚህ ቀጥሎ ያሰፈርናቸውን ሁለት አስደናቂ ታሪኮችን እንድታነቡ እንጋብዛችኋለን።

[1] ከብዙ ዓመት በፊት የሮማ ንጉሥ ነገሥት፣ በጣም የታወቀና የተመሰገነ የሕንጻ ነዳፊ (አርክቴክተር) የሆነውን፣ "ከዚህ በፊት ተሠርቶ የማያውቀውን፣ ተወዳዳሪ የሌለውን ልዩ ኮለሰየም ሥራልኝ፤ ሠርተህ ስትጨርስ፣ በዓለም ዙሪያ ታዋቂና ዝነኛ እንድትሆን ከፍ ያለ ማዕረግ እንድታገኝ አደርግሃለሁ" አለው። ንጉሡ በአዘዘው መሠረት ሥራውን ሠርቶ ጨረሰ። ንጉሠ ነገሥቱም፣ በተሠራው ኮለሰየም በጣም ተደስቶ "አሁን ሥራው ተጠናቆ አልቋል። ትልቅ የምረቃ በዓል አዘጋጅተን ይህን ኮለሰየምን በሚያስደንቅ ሁኔታ የሠራውን አርክቴክተር ማከበር አለብን" በማለት ትልቅ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ። በምረቃው ቀን በኮለሰየሙ ውስጥ ስፍራ እስከማይገኝ ድረስ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር። ሳቁ፣ ጨዋታው፣ ዕልልታው ፍጹም ሌላ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ በዙፋኑ ላይ፣ እንዲሁም ኮለሰየሙን የሠራው አርክቴክተር የክብር ቦታውን ይዞ ተቀምጦ ነበር። የምረቃው በዓል የተጀመረው በልዩ ሁኔታ ነበር። ክርስቲያን በመሆናቸው ምክንያት የሞት ፍርድ የተበየነባቸው ክርስቲያኖች በሰንሰለት ታስረው ኮለሰየሙ መሀል ሜዳ ላይ እንዲቆሙ ተደረገ።፣ እንዲሁም እነዚያን ክርስቲያኖች በጫጭቀው እንዲበሉ፣ በጣም የተራቡ አንበሶችም በሰንሰለት ተይዘው ቀረቡ።

በዓሉን ለማክበር ቁጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ በዚያ ኮለሰየም ውስጥ ተሰብስቦ ስለ ነበር፣ የሕዝቡ ጩኸትና ሁካታ ፍጹም ሌላ ነበር። ንጉሡ ከተቀመጠበት ዙፋን ብድግ ብሎ እንዲህ አለ። "እንደምታዩት ይሄ ኮለሰየም በሚያምር ሁኔታ ተገንብቷል። ዛሬ



ይህን ኮለሰየም ለመመረቅና እንዲሁም ይህን ተወዳዳሪ የሌለውን አስደናቂ ኮለሰየም በዚህ ሁኔታ የሠራውን ብልህ አርክቴክተር ለማክበር በዚህ ሥፍራ ተሰብስበናል። በዓሉን ለማክበር ክርስቲያኖችና፣ እንዲሁም የተራቡ አንበሶችም ስፍራቸውን ይዘው ይገኛሉ። በዓሉንም የምናከብረው እነዚህን ክርስቲያኖች ለአንበሶች አሳልፈን በመስጠት ነው" አለ። ግሪካዊው አርክቴክተር ይህን ሲሰማ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ፣ በታላቅ ድምጽ "ግርማዊ ሆይ! እኔም እኮ ክርስቲያን ነኝ" በማለት ክርስቲያንነቱን በዚያ ሕዝብ መካከል አወጀ። ከዚህ በኋላ አንበሶቹ የነበሩበት ክፍል በር ተከፈተና እነዚያ የተራቡ አንበሶች ተለቀቁ። ያ ግሪካዊው አርኪቴክተርም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በአንበሶች ተቦጫጭቆ፣ ደሙ እንደ ውሃ ፈሶ ሞተ።

ያ ሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ታላቅ ክብር ከማግኘት ይልቅ፣ ከክርስቲያኖች ጋር በአንበሶች ተቦጫጭቆ መሞት ከእግዚአብሔር ዘንድ የበለጠ ክብር እንደሚያስገኝለት ስላመነ፣ ክርስቲያን መሆኑን አልደበቀም። ያ ሰው ውሳኔውና ድርጊቱ ሞት እንደሚያስከትልበት ቢያውቅም፣ ከክርስቶስ ሕዝብ ጋር መከራ ተቀብሎ መሞትን መረጠ። እንዴት ዓይነት የሚያስደንቅ፣ ድፍረት የሞላበት እምነት ነው? በዓለም ዐይን ሲታይ ሞኝነት ይምሰል እንጂ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን የእምነት አርበኛነት ነው። ይህን የመሰለ ድፍረትና ቆራጥነትን ለመሆኑ ከየት ነው ያገኙት? ምስጢሩ ምንድነው?

[2] ሌላው አስደናቂ ታሪክ የቢሾፕ ሁፐር ታሪክ ነው። በእምነቱ ምክንያት በሞት እንዲቀጣ የተፈረደበት ቢሾፕ ሁፐር የተባለ ሰማዕት ከፈራጆቹ ፊት ቀርቦ፣ "ሕይወት ጣፋጭ ነው፤ ሞት ግን መራራ ነው" ብሎ ከተናገረ፣ እምነቱን ከካደ፣ ይቅርታ እንደሚደረግለት ተነገረው። ቢሾፕ ሁፐርም፣ "እርግጥ ነው፣ ሕይወት ጣፋጭ፣ ሞት ግን መራራ ቢሆንም፣ ሁለተኛው ሞት ከአሁኑ ሞት የበለጠ መራራ ነው፤ የወደፊቱ ሕይወት ግን፣ ከአሁነኛው ሕይወት የበለጠ ጣፋጭ ነው" ብሎ ተናግሮ የተመ

ደበለትን መራራ የሞት ጽዋ ቀምሶ አለፈ። ጌታውን ክዶ በሕይወት ከመኖር ይልቅ፣ ጌታውን ይዞ መሞትን መረጠ።

[3] ሌላው ሰማዕት ደግሞ በእምነቱ ምክንያት ክስ ቀርቦበት በሞት እንዲቀጣ የሚል ፍርድ ተፈርዶበት ፍርዱ ሲነበብለት፣ "ወይኔ!" ብሎ በማልቀስ ፈንታ ድምጹን ከፍ አድርጎ፣ "እግዚአ ብሔር ሆይ! ደስ ብሎህ ከዚህ ከታሠርኩበት ከሥጋዬ ሰንሰለት ነጻ ስላወጣኸኝ ከልቤ አመሰግንሃለሁ!" አለ። ይህን ዓይነቱ ድፍረትና ቆራጥነትን እንዴት አገኙት? ኢየሱስን መከተል ሕይወትን እስከማጣት ድረስ ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም፣ የሚ ያስደንቀው ብዙዎችን እንደ ማግኔት የመሳብ ኃይል እንዳለው አይተናል። ሌላው አስደናቂ ታሪክ ይሄ ነው፦

[4] ኔሮ የሮማ ንጉሠ ነገሥት በነበረበት ዘመን፣ "የንጉሠ ነገሥቱ ታጋዮች" የሚል ልዩ ስም የተሰጣቸው በጀግንነታቸው የታወቁ ወታደሮች ነበሩ። እነዚህ በድፍረታቸው፣ በጦር ውጊያ ችሎታ ቸው የሮማ ምድር ካፈራቻቸው ጀግኖች ወታደሮች መካከል የተመረጡ ናቸው። በሚደነቀው ክብ ጣራ አልባ ቲያትር ቤት የሚገዳደራቸውን ማንኛውንም ኃይል ለመግጠም የተዘጋጁ የንጉሠ ነገሥቱን እጅ የሚይዙ ናቸው። ሊገጥማቸው ከቀረበ ጀግና ጋር ከመግጠማቸው በፊት ከንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ፊት ቀርበው፣ "እኛ ኃያላን ታጋዮች ለአንተ ለንጉሠ ነገሥታችን እንታገላለን። ለአንተ ለንጉሣችን ተዋግተን ድልንና የድልን ዘውድ እናስገኝልሃለን" በማለት በኃይለኛ ጩኸት ይጮኻሉ። ታላቁ የሮማ ጦር ሠራዊት ለጦርነት ሲላክ፣ እነዚህ የንጉሠ ነገሥቱ ታላቅ ታጋዮች ግምባር ቀደም ሆነው በድፍረትና በቆራ ጥነት የሚዋጉ ናቸው። በአንድ ወቅት ከወታደሮች መካከል አንዳንዶቹ ወደ ክርስትና እምነት እንደመጡ ዜናው ለንጉሠ ነገሥቱ ለኔሮ ደረሰው። ንጉሠ ነገሥቱ ኔሮም ይህን ሲሰማ ተቆ ጥቶ ለጦር ሠራዊቱ አዛዥ ለነበረው፣ ለቪስፓሲያን "አንተ በም ትመራው ጦር ሠራዊት ውስጥ ክርስቲያን የሆነ ወታደር ከተ



ገኘ፣ ያ ሰው አሁኑኑ በሞት መቀጣት አለበት" የሚል መልዕክት ላከበት።

ይህን ዓይነቱ አዋጅ የወጣው ኃይለኛ ክረምት በነበረበት ወቅት ነበር። ወታደሮቹ የሰፈሩት በብርዱ ምክንያት ሀይቁ ወደ በረዶነት ወደተለወጠበት አካባቢ ነበር። የጦሩ መሪ ቪስፓሲያን ንጉሠ ነገሥቱ የላከውን ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ያነበበው እያዘነና ልቡ እየፈራ ነበር። ቪስፓሲያን ወታደሮቹን ሰብስቦ "ከእናንተ መካከል የክርስትናን እምነት የተቀበለ ሰው አለ ወይ? ካለ ወደ ፊት ይውጣ" በማለት ትዕዛዝ ሰጠ። በዚህ ጊዜ "የንጉሡ ታጋዮች" ከሚባሉት ውስጥ 40ዎቹ ተራ በተራ ለአዛዡ ሰላምታ እየሰጡ ወደ ፊት በመውጣት ተሰለፉ። ይህን ያህል ሰው ይኖራል ብሎ አልገመተም ነበር። ቪስፓሲያን እምነታቸውን ክደው ከሞት እንዲያመልጡ አጥብቆ ለመናቸው። ይሁን እንጂ፣ ከአርባዎች መካከል አንድም እምነቱን የሚክድ ወታደር አልተገኘም። "ሀሳ ቡን የሚለውጥ ሰው ካለ ጸሀይ እስከትጠልቅ ድረስ ጊዜ እሰጣ ችኋለሁና ከዚያ በፊት መልስ እንድትሰጡኝ አስቡበት" አላ ቸው። ጸሀይዋ እንደ ጠለቀች። ለሁለተኛ ጊዜ "ከእናንተ መካከል የክርስትና እምነት የተቀበለ ካለ ወደ ፊት ይውጣ" አለ። አሁንም እነዚያው 40 ወታደሮች ሰላምታ እየሰጡ በመውጣት በሁለት ረድፍ ተሰለፉ።

ቪስፓሲያን እንደ ገና አጥብቆ ቢለምናቸውም ከነዚያ መካከል አንድም ጌታውንና እምነቱን የሚክድ አልተገኘም። በመጨረሻም፣ "የንጉሡ ትዕዛዝ የግድ መከበር አለበት። እናንተ የተቀራችሁት ወታደሮች የጦር ባልደረቦቻችሁን ደም እንድ ታፈሱ አልፈልግም። በዚህ በረዶ በሆነው ሀይቅ ውስጥ ራቁታ ችሁን ሌሊቱን ሙሉ በመሰለፍ፣ ተፈጥሮ ራሱ በእናንተ ላይ ሥራውን እንዲሠራ እተዋችኋለሁ" አላቸው። ይኸውም፣ "በጦር ተወግታችሁ ከምትሞቱ ብርዱ ይግደላችሁ" ማለቱ ነበር። እነዚያ 40 ወታደሮች ልብሳቸውን አውልቀው በአራት ረድፍ

*ተሰልፈው ወደ በረዶነት ወደተለወጠው ሀይቅ እንዲሄዱ ትዕዛዝ ተሰጣቸው። በዚያ እንደ ጦር በሚዋጋ ብርድ ውስጥ ራቁታቸውን ቆመው "ክርስቶስ ጌታችን ሆይ! ለአንተ ድልን ለማስገኘት፣ የአሸናፊነት አክሊል ለማስገኘት እኛ 40 ታጋዮችህ ስለ አንተ እንታገላለን" እያሉ ይዘምሩ ነበር። በዚህ ጊዜ የጦር መሪው ቪስፓሲያን ትልቅ እሳት አንድዶ እነዚያን ወታደሮች ሌሊቱን ሙሉ ይጠብቅ ነበር። ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ የእነዚያ ታጋዮች ዝማሬ ድምጹ እየቀነሰ፣ እየቀነሰ ይመጣ ነበር።*

*ሌሊቱ እያለቀ ሲመጣ እንደ ጦር የሚዋጋውን ብርድ መቋቋም ያቃተው አንድ ወታደር፣ እምነቱንና ጌታውን ክዶ ከጨለማው ውስጥ ወጥቶ ወደሚነደው እሳት እየቀረበ ሲመጣ ቪስፓሲያን አየ። በዚህ ወቅት የተቀሩት፣ "ክርስቶስ ጌታችን ሆይ! ለአንተ ድልን ለማምጣት፣ የአሸናፊነት አክሊል ለማስገኘት እኛ 39 ታጋዮችህ ስለ አንተ እንታገላለን" የሚል ዝማሬ ያሰሙ ነበር። በዚህ ጊዜ ቪስፓሲያን ዘለዓለማዊ እሳት በሀይቁ መካከል ሲነድ ያየ ይመስል፣ ወዲያው የራስ ቁሩን ጥሎ፣ ልብሱን አውልቆ እራቁቱን ወደ ሀይቁ መካከል በኃይል ጮክ ብሎ "ክርስቶስ ጌታችን ሆይ! ለአንተ ሙሉ ድልን፣ ለማስገኘት እኛ 40 ታጋዮችህ ስለ አንተ እንታገላለን" የሚለውን መዝሙር እየዘመረ ከተቀሩት ወታደሮች ጋር ተቀላቀለ።*

ኢየሱስን መከተል ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም፣ መጨረሻ ላይ ከሚያስገኘው ክብርና ሽልማት ጋር ሲወዳደር ግን በጣም አነስተኛ ነው። ዛሬ የእኔና የእናንተ ምልክታችን "መስቀል" ነው? ወይስ ከመስቀል ሕይወት ነጻ ሆነን መኖራችን ነው? ኢየሱስ *"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"* ስላለ፣ ከመስቀል ነጻ የሆነ ሕይወት እንዳያጓጓን እግዚአብሔር ይርዳን።



# 3

# በመስቀሉ፥ ታማኝነታችን ይፈተሻል

***"ወደ ፊት የሚደርስብህን መከራ አትፍራ፤ እነሆ እንድትፈተኑ ከእናንተ አንዳንዶቹን ዲያብሎስ ወደ እስር ቤት ያስገባችኋል፤ ዐሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ፤ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን፤ የሕይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ" (ራዕይ 2፡10)***

ያለንበት ዘመን የክርስትና ሕይወትን መኖር አስቸጋሪ ሳይሆን ቀላል፣ ጠባብ ሳይሆን ሰፊ እንደሆነ፣ ሁልጊዜ ደስታ እንጂ ችግርና መከራ ፈጽሞ እንደሌለበት፣ ዘውድ እንጂ መስቀል መሸከም የሌለበት ሕይወት እንደሆነ አድርገው የሚያስተምሩ አስተማሪዎች በብዛት የሚታዩበት ዘመን ነው። አንዳንዶች የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ባሕሪ ባለማወቅ ያልሆነውን እንደሆነ አድርገው ለመሳል ስለሚሞክሩ፣ ልጆቹን በሥርዓት ሳይሆን እያሞላቀቀ እንደሚያሳድግ አባት አድርገው ይመለከቱታል። እውነቱን ካለማወቅ የሌለውን ዓይነት ስም፣ መልክና ባሕሪ ይሰጡት እንጂ፣ እግዚአብሔር ልጆቹን ምንም ያህል ቢወዳቸው፣ መስቀል የሌለበት ሕይወት ትኖራላችሁ ብሎ ተስፋ አልገባላቸውም። ከላይ ያየነው ጥቅስ ከመስቀል ነጻ ሆነን የማንኖር መሆናችንን በደንብ ይገልጻል። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔርን አባትነት ተቀብዬ ለረጅም ዘመን በእርሱ ቁጥጥር ውስጥ ኖሬአለሁ። ከግል

ልምምዴ እንደተረዳሁት፣ ይሄ ሰማያዊው አባቴ አንድ ጊዜም መስቀል የሌለበት ኑሮ አላኖረኝም። በዚህ ዘመን የተመደበልኝን ዘመን ጨርሼ እስከምሄድበት ጊዜ ድረስም፣ መስቀል ከመሸከም ነጻ ሆኜ እንደማልኖር አውቀዋለሁ።

ነፍሳትን ወደ ጌታ ለማምጣት በማደርገው ጥረት ማንንም አባብዬ *"የክርስትና ሕይወት ቀላል ነው፣ ችግር፣ መስቀል የለበትም፣ መንገዱ ሰፊ ነው፣ ሁልጊዜ አፋችሁ በሳቅ የተሞላ ይሆናል"* በማለት ሰዎችን ወደ ጌታ መሳብ አልፈልግም። ለእኔ ወንጌል የተነገረኝ፣ *"መንገዱ ጠባብ ነው...መስቀል ያለበት አስቸጋሪ ሕይወት ነው..."* ተብዬ ነው። የክርስትና ሕይወት የሚያስከፍለው ዋጋ ምን እንደሆነ ተነግሮኝ እንጂ፣ እውነቱን በትክክል ሳላውቅ አይደለም። ወደ ክርስትና የመጣሁት የሚያስከፍለውን ዋጋ አውቄ ነው። ከመጣሁና በክርስትና ሕይወት መኖር ከጀመርኩ በኋላ *"እንዲህ አልመሰለኝም ነበር"* ብዬ አላውቅም። እኔም በተራዬ ሰዎችን ወደ ጌታ እንዲመጡ ስጋብዝ፣ የክርስትና ሕይወት ምንም ዓይነት መከራ ወይም መስቀል የሌለበት፣ ሁልጊዜ *"ሃሌሉያ"* የሚባልበት አለመሆኑን ነግሬ ነው።

ኢየሱስ በማቴ. 16፥18 ላይ ደቀ መዛሙርቱን *"...በዚህች የመሠረት ድንጋይ ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ ይህቺንም ቤተ ክርስቲያን የሞት ኃይል እንኳ ሊያሸንፋትም"* ሲል ተናግሯል። በዚህ ኢየሱስ በተናገረው ንግግር ውስጥ ሦስት ፍሬ ነገሮችን እናያለን። ይኸውም፥

*1ኛ፣ ክርስቶስ በዓለም ውስጥ የራሱ የሆነችውን እውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚመሠርት፣*

*2ኛ፣ የምትመሠረተዋ እውነተኛዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተመችቷትና ተዝናንታ የምትኖር ሳትሆን፣ ሊያጠፏት በሚነሱ በአንዳንድ ጠላቶቿ ምክንያት ታላቅ መከራና ስደት እንደሚደርስባት፣*



*3ኛ፣ ጠላቶቿ ብዙ መከራና ስደት ያድርሱባት እንጂ፣ ፈጽሞ ሊያጠፏት እንደማይችሉ፣ "የሞት ኃይል እንኳ እንደማያሸንፏት በግልጽ ተናግሯል።*

በእርግጥ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተችና የወንጌል ብርሃንዋን በዘመናት ሁሉ እየፈነጠቀች እንደኖረች የማያጠራጥር እውነት ነው። በአሁኑ ዘመንም ክርስቶስ ራሱ የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን፣ ክርስቶስ እንደገና መጥቶ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እስኪወስዳት ድረስ በዓለም ትኖራለች። ክርስቶስ በተናገረው ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያን ጠላት አጥታ አታውቅም። በዘመናት ሁሉ ታላላቅ የዓለም መሪዎች፣ ለሃይማኖታቸው የሚቀረቀሩ የሃይማኖት መሪዎች፣ የክርስትና እምነት ጠላቶች ያላቸውን ኃይልና ጉልበት ሁሉ ተጠቅመው ፈጽሞ ሊያጠፏት ሞክረዋል። አሳደዋታል፤ በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ እንድታልፍ አድርገዋታል። አንዳንዶቹም *"አጠፋናት! ከዚህ በኋላ ተንሰራታ አትነሳም"* ብለው ያሰቡበትም ጊዜ ነበር። ይህም እውነት እንደሆን የዓለምም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሀፊዎች ይመሰክራሉ። እኛም በዚህ መጽሐፍ አማካኝነት ያለፈችበትን አስቸጋሪ መንገድ፣ የጠጣችውን መራራ ጽዋ በመጠኑም ቢሆን ለመግለጽ ወይም ለማሳየት ሞክረናል።

ጥንትም ሆነ ዛሬ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን፣ ሊያጠፏት በሚፈልጉ ጠላቶቿ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰባት፣ በታላቅ መከራና ስደት ውስጥ እያለፈች እንደሆነ የማያጠራጥር እውነት ነው። እንደ አንዳንዶች ፉከራና ዛቻ ቢሆን ኖሮ፣ ቤተ ክርስቲያን ገና ድሮ ጠፍታ በቀረች ነበር።

- *ፈረንሳዊ ጸሀፊ፣ ቮልቴር "12ቱ ሐዋርያት የመሠረቱት የክርስትና እምነት፣ በእኔ በቮልቴር ብዕር (ጽሁፍ) ይደመሰሳል" በማለት ፎክሮ ጽፎ ነበር። ይሁን እንጂ፣ የቮልቴር ጽሁፍ ሊደመስሳት አልቻለም። እርሱንና እርሱን የመሰሉትን የወንጌል ጠላቶችን ይግረማቸውና፣ ቮልቴር በሞተ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ እርሱ ራሱ ይኖርበት የነበረው መኖርያ ቤቱ መጽሐፍ ቅዱስ ማተሚያና ማሰራጫ እንደሆነ ታሪክ ይመሰክራል።*

ኢየሱስ *"የሞት ኃይል አንኳ አያሸንፋትም"* ባለው መሠረት፣ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረች ሆና በመጥፋት ፈንታ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ጸንታ ትቆማለች። ለዚህም ዋናውና ትልቁ ምክንያት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለመሠረታት ጌታ ከፍተኛ ፍቅር ስላላት ነው። ፍቅሯም የሚታየው ለጌታዋ በምታሳየው ሙሉ መሰጠትና ታማኝነት ነው።

## 1. *ታማኝነት ምን ማለት ነው?*

ታማኝነት የሰውን ባሕሪ የሚያንጸባርቅ ነው። ታማኝ የሆነ ሰው እምነት የሚጣልበት፣ ቃሉን የሚጠብቅ፣ የማይከዳ፣ ወሻወሼ ያልሆነ፣ አንዴ እዚህ፣ አንዴ እዚያ የማይል፣ ቃሉን የማይለዋውጥ፣ ለአመነበት ነገር ሕይወቱን እስከ መስጠት ድረስ የሚደርስ፣ ጽኑ የሆነ አቋም ያለው ሰው ማለት ነው። ታማኝነት በመከራ ውስጥ መታገስ፣ በዓላማ መጽናት፣ ግዴታን በቆራጥነት ማከናወን ወይም መፈጸም ማለት ነው። *"ታማኝነት"* ፈዝዞ መቆም፣ ምንም አለማድረግ፣ ፈንጠር ብሎ፣ ከሁኔታው ሸሽቶ ዳር መቆም፣ ቀላል በሆነ መንገድ መራመድ ማለት አይደለም። *"ታማኝነት"* ክፉትና ጭካኔ ባለበት መካከል ሳይደናገጡ፣ ሳያወላውሉ ጸንቶ መቆም ማለት ነው። እውነተኛ የሆነው ታማኝነት ምን እንደሆነ ለመረዳት፣ የክርስቶስን ታማኝነት መረዳት ይጠቅማል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሆነ።

በዓለም ውስጥ ብዙ ታማኞች፣ ብዙ ደፋሮች መጥተው ባመኑበት ነገር ጸንተው በመቆም፣ ታግለው፣ ሕይወታቸውን ሰጥተው አልፈዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ታሪክ በቀላሉ አይረሳቸውም። አንዳንዶቹ የአገር ፍቅር ያቃጠላቸው፣ አገሬን፣ ድንበሬን፣ ልጆቼን፣ ሚስቴን አላስነካም በማለት ሕይወታቸውን የሰጡ ናቸው። በአገራችንም ብዙ ታማኞች፣ ደፋሮች በቦምብና በመትረየስ፣ እንዲሁ በታንክ ሊወጋቸው የመጣውን ጠላት በመሸሽ ፈንታ፣ በጋሻቸው ለመመከት፣ በጦራቸው ለመውጋት በቆራጥነትና በታማኝነት በመታገል ላይ እያሉ ሕይወታቸውን የሰጡ



አሉ። ዛሬ የእኔና የእናንተ ታሪክ በእነርሱ ደም የተጻፈ የሚያኮራ ታሪክ ነው። በቀላሉ የማንረሳው፣ ከአዕምሯችን ፍቀን የምናወጣው ታሪክ አይደለም። ለአገራቸው የነበራቸውን ታማኝነት ያሳየናል። እነዚህ ታማኞች፣ ሕይወታቸውን ለሌሎች ሲሉ መስዋዕት በማድረጋቸው በአንዳንዶች ዓይን ስታዩ ዕብዶች ሊመስሉ ይችላሉ። እውነትነት ባላቸው ሰዎች ግን ሲደነቁ ይኖራሉ። ዓለማችን እነዚህን የመሳሰሉ ቆራጦች፣ ደፋሮችና ታማኞች ባይኖርባት ኖሮ ለመሆኑ ምን ትመስል ነበር?

- *በእስልምና እምነት ተከታዮችና በክርስቲያኖች መካከል በተደረገው "የመስቀል ጦርነት" ተካፋይ የነበረ አንድ ክርስቲያን ወታደር በእስላሞች ተማርኮ ተወሰደ። "በጣም የምወዳትና የምት ወደኝ ሚስት እንግሊዝ አገር አለችኝና እባካችሁን አትግደሉኝ" ብሎ ለመናቸው። "ሌላ ባል ታገባና ቶሎ ትረሳሃለች" አሉት። የጦር መሪው በጣም ጨካኝ ሰው ስለነበረ፣ "የፍቅር መግለጫ እንዲሆን አንድ እጇን ቆርጣ ከላከች፣ እንለቅሃለን" ብሎ ነገረው። ሚስቱም ይህ ዜና እንደደረሳት ያለአንዳች ማመንታት ቀኝ እጇን ቆርጣ ላከች። ያም ሰው በነጻ ተለቀቀና ከሚስቱ ጋር ተገናኘ። ለዚያች ታማኝ ሴት ማስታወሻ እንዲሆን፣ እንግሊዝ አገር ከአንደኛው ጥንታዊ ካቴድራል ውስጥ ሀውልት ተጸርጾ ቆመላት። ሀውልቱ ቆንጆ ሴት ሆና አንድ እጅ ግን እንዳል ነበራት ያሳያል።*

ለምድራዊ ነገር፣ ለሚጠፋውና ለሚረሳው ነገር ሰዎች ይህን ያህል ራሳቸውን በታማኝነት መስጠት ከቻሉ፣ እኔና እናንተማ ለሰማያዊው ነገር፣ ለሚወደንና ለምንወደው አምላካችን ምን ያህል ታማኝ መሆን ይኖርብን ይሆን? በታማኝነታቸው የሚደነቁ አማኞች ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ መጥተው አልፈዋል። ዛሬ ወንጌል ለእኔና ለእናንተ ሊደርስ የቻለው ብዙዎች በታማኝነት ዋጋ ስለከፈሉበት ነው። ሐዋርያት ታማኝነታቸው ዋጋ አስከፍሏቸዋል። የሚያስደንቀው ሁሉም የተፈጥሮ ሞት ሳይሞቱ፣ በአመኑበት ጸንተው በመቆማቸው በተለያየ መንገድ ሕይወታቸው ያለፈ መሆኑ ነው።

- ማቴዎስ፣ ትዮጴስ ከምትባል ከተማ ውስጥ በሰይፍ አንገቱ ተቆርጦ ሞቷል።
- ማርቆስ፣ አሌክሳንደርያ ውስጥ መሬት ለመሬት ተጎትቶ ሕይወቱ አልፏል።
- ሉቃስ፣ ግሪክ አገር ውስጥ በለስ ዛፍ ላይ ተሰቅሎ ሞቷል።
- ዮሐንስ፣ የፈላ ዘይት ውስጥ ተከትቶ ከዚያ አምልጦ ጳጢሞስ ደሴት ላይ ተገድሏል።
- ያዕቆብ (ትልቁ) ኢየሩሳሌም ውስጥ በሰይፍ ታርዶ ሞቷል።
- ያዕቆብ (ትንሹ) ከፎቅ ተወርውሮ ሳይሞት በመቅረቱ ተይዞ በዱላ ተቀጥቅጦ ሞቷል።
- ፊልጵስ፣ ግብጽ ውስጥ ምሰሶ ላይ ተሰቅሎ ሞቷል።
- በርጠለሜዎስ፣ ስጋውንና ቆዳውን እየገፈፉ አሰቃይተው ገድለውታል።
- እንድርያስ በመስቀል ተሰቅሎ ሕይወቱ አልፏል። ቶማስ፣ ኢስት ኢንዲስ ውስጥ በሰይፍ ተገድሏል።
- ይሁዳ፣ በቀስት ትወግቶ ሞቷል።
- ማትያስ በድንጋይ ተወግሮ ስላልሞተ፣ በመጨረሻ አንገቱ ታርዶ ሞቷል።
- በርናባስ፣ በአይሁድ እጅ በድንጋይ ተወግሮ ሞቷል።
- ጴጥሮስ ተዘቅዝቆ ሲሰቀል። ጳውሎስ በሰይፍ ታርዱ ምቷል።
- ከሐዋርያትም በኋላ በሚሊዮን የሚቆጠሩት በሰይፍ ታርደዋል።



## 2. ታማኝነት እውነተኛውን እኛነታችንን ያሳያል

ጳውሎስ የፍቅርን ባሕሪ ሲገልጽ፣ *"ፍቅር ሁልጊዜ ይታገሣል፣ ሁልጊዜ ያምናል፣ ሁልጊዜ ተስፋ ያደርጋል፣ ሁልጊዜ ጸንቶ ይቆማል" ይላል (1 ቆሮ. 13፡7)።* ታማኝነት፣ ላመነበት ነገር ሙሉ መስጠትን ይጠይቃል። ታማኝነት ዋጋ ስለሚያስከፍል በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚታይ ባሕሪ አይደለም። እንኳን ዋጋ የሚያስከፍል ቀርቶ፣ ምንም ዓይነት ዋጋ የማያስከፍል ቢሆንም በጎ ያደረግንላቸው ሰዎች እውነተኞች ሆነው አናገኛቸውም። እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆን ከፈለግን በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብናልፍ ለምንከተለው ጌታ ታማኞች መሆን አለብን። ታማኝነታችንም ተገልጦ የሚታየው በበጎ ጊዜ ሳይሆን በመከራ ሕይወት ውስጥ ስናልፍ ነው። ታማኝነትን፣ ሙሉ መስጠትን የማይጠይቅ መስቀል የለም። "እወድሃለሁ" ለምንለው ጌታ እውነተኛነታችንን በታማኝነታችን ገልጸን ማሳየት አለብን። ያም "ጸንተን እንቆምልሃለን" ላልነው ጌታ፣ መስቀሉን በአግባቡ በመሸከም ነው።

ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ መከራና ስቃይ ውስጥ ስታልፍ ታግሳ፣ ታማኝ ሆና በመቆም ለብዙ ዘመናት ሳትጠፋ ጸንታ ኖራለች። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሠረቷን እንደያዘች፣ ወደ ውስጥ ሥር ሰዳ በማደግ፣ ብርሃኗን ለዓለም ለመፈንጠቅ ስትል፣ ደሟን እንደ ውሃ እያፈሰሰች ለረጅም ጊዜ ኖራለች። ጦርን በጦር ሳይሆን በፍቅር ተዋግታ አሸናፊ ሆና ቆይታለች። ኃይልን በኃይል ሳይሆን ታግሶ በማለፍ አሸናፊነቷን አስመስክራለች። ልጆቿ የተጠሩት በክርስቶስ ለማመን ብቻ ሳይሆን ስለ ስሙ በየቀኑ ለመሰቃየትና ለመሞት ጭምር እንደሆነ አውቀው ብዙዎቹ በዘመናት ሰማዕታት ሆነው አልፈዋል። ጠላቶቿ ያላቸውን ኃይል ሁሉ ተጠቅመው ሊደመስሷት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። *"እንደ ገለባ በተንናቸው"* ሲሉ፣ በየቦታው እንደ ተዘራ ዘር ሆነው በያለበት በቅለውና ተስፋፍተው ተገኙ። ኃያሉ የሮም መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን እንዳልነበረች አድርጎ ሊያጠፋ ዝቶ ቢነሳም፣ ቆራጥ የሆኑ ታማኝ ልጆቿ ጸንተው በመቆማቸው ምክንያት ሊያጠፏቸው ወይም ሊደመስሷቸው አልቻለም። *የክርስቲያኖች ደም እንደ ውሃ የሚፈስበት የትግል ሜዳ፣ አዳዲስ የክርስ*

*ቶስ ወታደሮች የሚመለመሉበት ወይም የሚበቅሉበት ሥፍራ ሆነ እንጂ፣ ፈርተው የሚሸሸጉበት ሥፍራ አልሆነም። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ለመከራና ለስቃይ የተሰጠች ብትሆንም በመጨረሻ ድል አድራጊ ሆና በጌታዋ ፊት ለዘላለም ትቆማለች።*

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተከታታይ ያቀረብናቸው ባለታሪኮች፣ የመጀመሪያውን መስቀል የተሸከመውን ጌታ አርአያ በመከተል የራሳቸውን መስቀል ተሸክመው እስከ መጨረሻው ድረስ ዘልቀው የሄዱናቸው። ማንኛውም መስቀል የተሸከመ ሰው መጨረሻው በተሸከመው መስቀል ላይ መንጠልጠል ነው። እኛም የራሳችንን መስቀል ስንሸከም፣ እርሱን ተከትለን የምንሄደው ምቾት ወዳለበት ሕይወት ሳይሆን ወደ ስቅላት፣ ወይም ወደ ሞት ነው። እኛ፣ ከምንከተለው ከኃያሉና ከታላቁ ጌታ አንበልጥም። ይህ እውነት ከሆነ፣ በዚህ ዓለም ጌታ ኢየሱስ ያላገኘውን ዓይነት እንክብካቤ እናገኛለን ብለን ለምን እንጠብቃለን? እርሱን መከተልን ከመረጥን፣ እርሱ ከመስቀሉ ነጻ ካልሆነ፣ እኛም ከመስቀል ሞት ነጻ ሆነን መኖር አንችልም። የሚያስደንቀን የወንጌል ጠላቶች በዘመናት የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ዝተው ተነስተው፣ ያላቸውን ኃይልና ጉልበት ተጠቅመው ብዙ ሙከራ አድርገው ያልተሳካላቸው መሆናቸው ነው። የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ዝተው ተነስተው ሳይሳካላቸው መቅረቱን በእኛም ዕድሜ ውስጥ ያየነው ስለሆነ፣ ለዚህ እውነት ምስክሮች ነን።

በሮማ ግዛት፣ በተለያዩ የሮማ ንጉሠ ነገሥት አነሳሽነት የተካሄዱት አስር ታላላቅ የክርስቲያኖች ስደቶች ውስጥ፣ *ሰባተኛው የተፈጸመው፣ ከ249 እስከ 251 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለ ጊዜ ውስጥ ነው።* ይህን ሰባተኛውን ታላቅ የስደት እሳት በክርስቲያኖች ላይ ያቀጣጠለው *ዲሰየስ* የተባለው ንጉሠ ነገሥት ነበር። ከእርሱ በፊት የነገሠው ንጉሠ ነገሥት ፊልፕ ክርስቲያን ነበር ብሎ ይጠራጠር ስለ ነበረ፣ እንዲሁም ለእርሱ የነበረው ጥላቻ በጣም ከፍተኛ ስለነበረ፣ ክርስቲያኖችን ከሮማ ግዛት ውስጥ ፈጽሞ እንዳልነበሩ አድርጎ ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ ሰው ነበር። ሌላው የብስጭቱ ምክንያት በዚያን ወቅት ምንም ያህል ከፍተኛ ስደት ቢኖርም፣ የክርስቲ



ያኖች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ፣ በአገሪቱ የነበረው የጣዖት አምልኮት ግን እየተዳከመ የመጣ በመሆኑ ነበር። ስለሆነም፣ የክርስትናን እምነትንና ተከታዮችን ለማጥፋት ሲል አዋጅ አወጣ። የክርስቲያኖች ጠላት የነበሩት ሕዝቦችም ንጉሡ ያወጣውን አዋጅ ተግባራዊ ያደርግ እንደሆነ በጥብቅ ይከታተሉት ነበር። የክርስቲያኖች መጥፋት፣ እንዳልነበሩ ሆነው መደምሰሳቸው ለአገሪቱ ዕድገት ትልቅ አስተውጽኦ ያደርጋል ብለው ያምኑ ነበር። በዚህ ከባድ የስደት ዘመን በእምነታቸው ምክንያት የተገደሉት ክርስቲያኖች ቁጥር እጅግ በጣም ብዙ በመሆኑ፣ ትክክለኛውን ቁጥር ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ የአንዳንዶችን ታሪክ በአጭሩ እናቀርባለን።

በ398 ዓ.ም. *ክሪሶስተም* የተባሉት የኮኒስታንቲኖፕል ፓትሪያርክ ስለ ሰማዕታት የጻፉት ታሪክ እንደገለጸው፣

- *ጁሊያን የተባለ አንድ ወጣት፣ ክርስቲያን በመሆኑ ምክንያት በሞት እንዲቀጣ ተፈረደበት። በመርዘኛ እባቦች ተነድፎ እንዲሞት፣ አደገኛ የሆኑ እባቦች ካሉበት የቆዳ ከረጢት ውስጥ ከተቱት። በዚያ ብቻ አላበቃም። ከረጢቱን አስረው ባሕር ውስጥ ወረወሩት።*

- *ሌላው መከራ የበዛበት መራራ ጽዋ ጠጥቶ የሞተው፣ በዕድሜው በጣም ወጣት የነበረ፣ የሚደነቅ ብሩህ አዕምሮ፣ የሚያምር ቁመና የነበረው፣ መልከ መልካም ወጣት፣ ጴጥሮስ እየተባለ የሚጠራ አማኝ ነበር። ቬነስ እየተባለች ለምትጠራዋ የሴት ጣዖት መስዋዕት እንዲያቀርብ ተጠይቆ እምቢታውን ሲገልጽ እንዲህ አለ። "ይህቺ እንደ አምላክ የምታመልኳትና መስዋዕት የምታቀርቡላት የሴት አምላካችሁ በጣም የተበላሸ፣ ባለጌና ፍጹም ያደፈ ሕይወት የነበራት መሆኗን እናንተ ብትረሱ ታሪክ አይረሳትም። ይህንን እያወቃችሁ እርሷን ማምለካችሁና ለእርሷ መስዋዕት ማቅረባችሁ እኔን በጣም ያስደንቀኛል። እኔ ግን*

*እውነተኛ የሆነውን እግዚአብሔርን ብቻ አመልካለሁ፤ የማቀርብለትም የተቀደሰ መስዋዕት፣ ጸሎትና ምስጋና ነው" አላቸው።*

*አገረ ገዥው፣ በወቅቱ ስደቱን በክርስቲያኖች ላይ ያፋፍም የነበረው አፐቲመስ፣ ከላይ የሰማነውን ምላሽ ከወጣቱ ጴጥሮስ ሲሰማ፣ በንዴት ተሞልቶ በሁለት ተሽከርካሪዎች መካከል በኃይል ተጠፍሮ ታስሮ፣ ተሽከርካሪዎቹን በተቃራኒ አቅጣጫ እንዲነዱ በማድረግ፣ በኃይል ወጥረው ሰውነቱንና አጥንቱን ከበጣጠሱት በኋላ መጨረሻ ላይ አንገቱን በሰይፍ አርደው ገደሉት። እንዴት የሚዘገንን ታሪክ ነው?*

- *ይሄ ከላይ የገለጽነው ወጣት በአሳቃቂ ሁኔታ ሲገደል ከሚያዩት ሰዎች መካከል ዴኒሳ የምትባል የ16 ዓመት ዕድሜ የነበራት አንዲት ልጃገረድ ነበረች። የአገረ ገዢውን ጭካኔ ተመልክታ፣ "አንተ ደስታ የሸሸህ አሳዛኝና ጎስቋላ ሰው፣ ለጊዜያዊ ደስታ ስትል ዘላለማዊ የሆነውን መከራህን የምታጠብቀው ለምንድነው?" አለችው። አፐቲመስ ይህንን የድፍረት ቃል ሲሰማ፣ ልጅቷን አስረው ከፊቱ እንዲያቀርቧት ትዕዛዝ ሰጠ። እርሷም ክርስቲያን መሆኗን በግልጽ በመናገሯ እዚያው አንገቷን በሰይፍ ቆርጠው ገደሏት። ይህን ዓይነቱን ወኔና ድፍረት ከየት አገኘችው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም።*

በ251 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ዲሲየስ የተባለው ንጉሠ ነገሥት ኤፌሶን ከተማ ውስጥ የጣዖት አምላኪዎች መቅደስን ሠርቶ ካቆመ በኋላ የከተማው ነዋሪዎች ሁሉ ላቆመው ጣዖት መስዋዕት እንዲያቀርቡ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጠ። እርሱን በቅርብ ከሚጠብቁት ወታደሮች መካከል ሰባቱ ክርስቲያን በመሆናቸው "ላቆመው ጣዖት መስዋዕት አናቀርብም" በማለታቸው፣ ወህኒ ቤት ተጣሉ። ዲሲየስ ከተቀበሉት እምነት ሊመልሳቸው አስቦ፣ በሌሎች ላይ እንደሚያደርገው ፍርዱን አላጠበቀባቸውም። ከሚሄድበት ጉዞ እስኪመለስ ድረስ አስበውበት ወደ ውሳኔ እንዲመጡ በቂ ጊዜ ሰጣቸው። እርሱ በሄደበት ወቅት እነዚያ ሰባት ወታደሮች እምነታቸውን



ለመተው ስላልፈቀዱ፣ ሕይወታቸውን ለማትረፍ ኮረብታው ላይ ከነበረ አንድ ዋሻ ውስጥ ተደበቁ። ዲሲየስ ሲመለስ የተደበቁበት ዋሻ ስለታወቀ፣ በረሀብና በውሃ ጥም እንዲሞቱ የዋሻው አፍ እንዲደፈን ትዕዛዝ ሰጠ። በዚህ ዓይነት በረሃብና በውሃ ጥም ሕይወታቸው አለፈ። ምን ዓይነት ቆራጥነት ነው?

በሮማ ግዛት፣ በተለያዩ የሮማ ንጉሠ ነገሥት አነሳሽነት የተካሄዱት ከአስር ታላላቅ የክርስቲያኖች ስደቶች ውስጥ፣ *ስምንተኛው የተፈጸመው፣ ከ253 እስከ 260 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።* ስምንተኛው ስደት የጀመረው በ257 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) በአራተኛው ወር ሲሆን፣ ይኼኛውም ከአለፉት ሰባት ስደቶች፣ በመከራ ውስጥ ያለፉ ክርስቲያኖች ቁጥር፣ እንዲሁም ይቀምሱት ከነበረው ሥቃይና መከራ ያነሰ ወይም የተለየ አልነበረም።

ሩፊናና ሲኩንዳ የተባሉ ሁለት ወጣት ልጃገረዶች፣ በውበታቸው በጣም የተደነቁ፣ ከፍተኛ ትምህርት የነበራቸው፣ ወላጆቻቸው በሮም ከተማ ውስጥ በጣም ታዋቂነት የነበራቸው፣ በጣም ሀብታም የነበሩ ወጣት ወንዶችን ለማግባት ታጭተው ነበር። አራቱም ክርስቲያኖች ነበሩ። በክርስቲያኖች ላይ የተነሳው ስደት ገና ሲጀምር፣ ወጣቶቹ በጣም ሀብታም ስለነበሩ፣ ክርስቲያን በመሆናችን ንብረታችንን እናጣለን ብለው በመፍራት እምነታቸውን ካዱ። ያ ብቻ ሳይበቃቸው፣ እጮኞቻቸውም እንደ እነርሱ እምነታቸውን እንዲተው ማስጨነቅ ጀመሩ።

- *ሴቶቹ ግን እምነታቸውን ለመተው ፈቃደኞች አልነበሩም። እምቢተኝነታቸውን ሲያዩ፣ በእጮኞቻቸው ላይ ጥቆማ አድርገው ክርስቲያኖች በመሆናቸው አገረ ገዢው ፊት ቀርበው ሁለቱ ወጣቶች የሞት ፍርድ ተበይኖባቸው አንገታቸው በሰይፍ ተቆርጦ ሞቱ። የወጣትነት ዕድሜያቸው ሳያሳሳቸው፣ ትዳር መሥርተው በምቾት መኖራቸው ሳያጓጓቸው ስላመኑት ጌታ ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው መስጠታቸው እንዴት*

*የሚደነቅ ነው? ጊዜያዊ የሆነው ደስታ የቀረባቸው ይሁን እንጂ፣ ዘለዓለማዊው ደስታ ግን አልቀረባቸውም።*

በሮም ከተማ ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጣም የሚደነቅ፣ የተቀደሰ ሕይወት የሚኖር ሎረንስ ተብሎ የሚጠራ አገልጋይ፣ የቤተ ክርስቲያኒቷ ንብረት ጠባቂና ኃላፊ ነበር። በስግብግብነት መንፈስ የተሞላው አገረ ገዢው ማርሲያነስ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ንብረት ለመውሰድ ስለፈለገ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብትና ንብረት የት እንደደበቀው እንዲናገር አስጨነቀው። ሎረንስም የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብትና ንብረት ሰብስቦ ለማሳየት የሦስት ቀን ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀ። በተባለው በሦስተኛው ቀን፣ ምስኪኖችና ምንም ሀብት ያልነበራቸውን ድሃ ክርስቲያኖችን ሰብስቦ፣ አገረ ገዢውን አማኞችን እያሳየ፣ *"የቤተ ክርስቲያን ውድ የሆኑ ዕንቁዎችና ንብረቶች እነዚህ ናቸው። ክርስቶስ በሕይወታቸው መኖሪያ ያገኘበት፣ በክርስቶስ በማመናቸው ዕንቁ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶች እነዚህ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ከዚህ የበለጠ፣ ክርስቶስን በውስጣቸው ከያዙ ከእነዚህ ሰዎች የበለጠና የተሻለ ሌላ ምን ሌላ ሀብትና ንብረት ሊኖራት ይቻላል?"* አለው።

*ማርሲያነስ ይህን ሲሰማ እጅግ በጣም ተናዶ በጣም እየጮኸ ተከትዮቹን "እሳቱን በኃይል አንድዱት፣ ምንም እንጨት እንዳይቀር፣ ይሄ ባለጌና ተንኮለኛ አገረ ገዢውን ለማታለልና በእርሱ ለመቀለድ ሞክሯል። አስወግዱት! አስወግዱት! በጉማሬ አለንጋ ግረፉት፣ በሜንጠ መንጭቁት! በጡጫ አጥግቡት! በዱላ ደብድባችሁ አንጓሉን ፈጥፍጡት፣ ጠንካራ ሠንሰለት አምጡና ጥፍር አድርጋችሁ እሰሩት! በእሳት በጋለ መንሽ ውጉት! በብረት ፍቅፋቂ አልጋ ላይ አስተኙት! የብረት አልጋውን ፍም እስኪመስል ድረስ አግሉትና ይህን ከሀዲ እግርና እጁን አስራችሁ እዚያ ላይ አስተኙትና እያገላበጣችሁ ጥበሱት! እኔ ባዘዝኩት መሠረት አሰቃዩት! ካልሆነ ግን እናንተ እንድትሰቃዩ አደርጋለሁ" አላቸው። ንጉሡ ባዘዘው መሠረት ያንን ጻድቅ ሰው ማሰቃየት ጀመሩ። ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ብዙ ካሰቃዩት በኋላ ያንን የክርስቶስ አርበኛ፣ በእሳት በጋለው የብረት አልጋ ላይ አስተኙት። ይሁን እንጂ፣ በእግዚአ*



*ብሔር በጎነት ለዚያ ሰው ያ በእሳት የጋለው የብረት አልጋ የሆነለት፣ በለስላሳ የላባ ፍራሽ ላይ እንደተኛ ነበር። እዚያው አልጋ ላይ ሆኖ ሕይወቱ ሲያልፍ፣ እርግት ያለ እረፍት የሚያርፍ ይመስል ነበር።*

## *3. የደብረ ዘይቱ ስደት*

በ1959 ዓ.ም. (እ. ኢ. አ.)፣ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በአገራችን በተነሳበት ወቅት፣ የደብረ ዘይት ከተማ፣ አንዳንድ መጠጥ ቤትና ቡና ቤት የነበራቸው ሀብታሞች፣ ወጣቱ መጠጥ ቤት በመሄድ ፈንታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲጎርፍ ሲያዩ፣ በዚህ ዓይነት ገበያተኛ በማጣት ቡና ቤታችንና መጠጥ ቤታችንን የሚጎበኘው ሊጠፋና ልንከስር ነው ብለው በመፍራት፣ ለሃይማኖታቸው ተቆርቋሪ ከሚመስሉ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመተባበር፣ *"ይህን መጤ ሃይማኖት ፈጽሞ ከአካባቢያችን ማጥፋት አለብን"* በማለት ተማምለው ተነሱ። የተለያዩ የዕድር አባሎች የማጥፋት እርምጃቸውን በሚወስዱበት አንድ ዕሁድ፣ የብዙ ዕድሮች አባላት በሙሉ በተወሰነው ዕለት እንዲሰበሰቡ ጥሩምባ እየተነፋ ጥሪ ተደረገላቸው። ይህ ጥሪ ደርሷቸው በዚያን ዕለት ሳይገኙ ቢቀሩ ግን ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ጨምረው አወጁ። በአቀዱት መሠረት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችንን ከብበው፣ የቤተ ክርስቲያኑን የእንጨት አጥር እየመዘዙ፣ ሕዝቡን በአጠና መደብደብ ጀመሩ። ወንበሮቻችንን ሰባበሩ፣ መጽሐፍ ቅዱሶቻችንን አቃጠሉ። የሚችሉትን ያህል ሕዝቡን ቀጥቅጠው ደም በደም አደረጉት። ከአዲስ አበባ የመጣሁ የዕለቱ ሰባኪ እኔ ስለነበርኩ፣ "ሰባኪው ይሄ ነው" በማለት ተረባረቡብኝ፣ እንዳልሞት እንዳልሽር አድርገው ቀጠቀጡኝ። ራሴን ስቼ ካልጠበቅሁት ሥፍራ ወድቄ ራሴን አገኘሁት። የሚያሳዝነው፣ የቻሉትን ያህል ከደበደቡንና ደም በደም ካደረጉን በኋላ፣ ሆስፒታል በመውሰድ ፈንታ፣ ማምለጥ ያልቻሉትን ሁሉ ከነቁስላቸውና ከነደማቸው አንዳንዶቹን ይባስ ብለው ወህኒ ቤት ጣሏቸው። እኔም ራሴን ስቼ ከወደቅሁበት ስነቃ፣ የተደረገብንን ድብደባ ማስታወስ ስጀምር በመጸ

ጸት፣ "ሁለተኛ የትም ቦታ ሄጄ አልሰብክም! ከዛሬ ጀምሮ አርፌ እቀመጣ
ለሁ" የሚል ውሳኔ በማስተላለፍ ፈንታ፣ "እኔም እንደ ቀድሞ ሐዋርያት
ለዚህ ታላቅ ክብር ደረስኩ!" ብዬ ደስ አለኝ።

እኛን ከደበደቡንና ካሰሩን በኋላ፣ በማግሥቱ በወጣው አዲስ ዘመን
ጋዜጣ ላይ "የደብረ ዘይት ወላጆች ልጆቻቸውን ቀጡ" በሚል ርዕስ
ዜናው ተሰራጨ። "ከዚህ በኋላ መጤ ሃይማኖት በደብረ ዘይት አይኖ
ርም፤ አጠፋናቸው" በማለት ደስ ብሏቸው ወደ ቤታቸው ገቡ። የሚያስደ
ንቀው ነገር ይሄ ሁኔታ አማኞችን አስደንግጦ እምነታቸውን ክደው
ይሆን? መሰብሰባቸውን አቁመው ይሆን? የሚያስደንቀው አማኞች በመ
ድከምና ተስፋ በመቁረጥ ፈንታ ሁኔታው ከምንጊዜውም የበለጠ ጉልበት
ሰጣቸው። የአምልኮትና የጸሎት ፕሮግራማቸውን ለማካሄድ ማንም
ቤቱን የሚያከራያቸው ሰው እንደማይኖር ስለተረዱ፣ ተበታትነው በመቅ
ረት ፈንታ በየተራራው ላይ ቦታ እየቀያየሩ መሰብሰብ ጀመሩ። ጊዜያ
ችንን እንዳይሻማብን ታሪኩን ላሳጥረውና፣ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች
በደብረ ዘይት ከተማ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እንደዛቱት ማጥፋት
ችለው ይሆን? ደብረ ዘይት ከተማ በአሁኑ ጊዜ ያለውን የአማኞችንና
የቤተ ክርስቲያንን ቁጥር ስሰማ፣ ያቺ እንደ እባብ የተቀጠቀጥንባት ቀን
ትዝ አለችኝና ጌታዬን አመሰገንኩት። ደማችን በከንቱ እንዳልፈሰሰ
ተረዳሁ። ደማችን ምድሪቱን አረሰርሶ ትልቅ ፍሬ አስገኝቷል። ብዙ
ዎቹን ወደ ጌታ አምጥቷል። ኢየሱስ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ "*የሞት ኃይል
እንኳ አያሸንፋትም*" ያለው እውነት እንደሆነ በእኛም ዕድሜ ውስጥ
ስላየነው፣ እውነት መሆኑን ምስክሮች ነን።

በዘመናት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙዎች
ስለ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ሲሉ ተሰቃይተዋል፤ ሕይወታቸውን
አጥተዋል። ወንጌል ለእኔና ለእናንተ ሊደርሰን የቻለው፣ ብዙዎች ደማቸ
ውን አፍስሰው በታማኝነት በመቆማቸው ነው። ለዓለም ደህንነት ሲል
መከራ የተቀበለ፣ የተቀጠቀጠ፣ የቆሰለ፣ ደሙን ያፈሰሰ፣ የተገረፈ፣ የተ
ናቀ፣ በጥፊ የተመታ፣ ምራቅ የተተፋበት፣ መስቀል የተሸከመ የመጀመ
ሪያው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እኔና እናንተንም ሲጠራን፣ "*ኑና ተዝናኑ!*"



ብሎ ሳይሆን፣ "*ኑና መስቀል ተሸክማችሁ ሙቱልኝ፤ እኔ ስለ እናንተ
የተሸከምኩትን መስቀል ኑና ተሸከሙ። መስቀሌን ካልተሸከማችሁ ግን
ለእኔ ልትሆኑ አይገባችሁም*" ይለናል። ይህን እውነት አምነው ከተቀ
በሉት ውስጥ ከክርስቶስ ቀጥሎ የሞትን ጽዋ መጀመሪያ የጠጣው እስጢ
ፋኖስ ነው። በነገራችን ላይ "እስጢፋኖስ" ማለት "*አክሊል*" ማለት ነው።
እስጢፋኖስ ወንጌልን ሲሰብክ፣ አለሳልሶ፣ ችግር እንዳያመጣበት ተጠን
ቅቆ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በኃይልና በሥልጣን ተሞልቶ
ኢየሱስን አሰቃይተው የገደሉትን ሰዎች በድፍረትና በግልጽ ይናገ
ራቸው ነበር። የእስጢፋኖስን ኃይለኛ ስብከት ሲሰሙ በቁጣ ተሞልተው
ከከተማው አውጥተው በድንጋይ ወግረው ገደሉት። ስደቱ በእስጢፋኖስ
ላይ ብቻ አላቆመም።

"*...እስጢፋኖስ በሞተበት ቀን በኢየሩሳሌም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን
ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤ ከሐዋርያት በቀር አማኞች ሁሉ ወደ ይሁዳ
አገርና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ። አንዳንድ መንፈሳውያን ሰዎች
እስጢፋኖስን ቀበሩት፤ በታላቅ ድምጽም እየጮኹ አለቀሱለት*" ይላል
(የሐዋ. 8:1-2)።

በዚያን ወቅት ከ2 ሺ በላይ የሆኑ ክርስቲያኖች እንደተገደሉ ታሪክ
ይመሰክራል። ይሄ የክርስትና እምነት መከራ፣ ስቃይ፣ ስደት፣ መስቀል
ያለበት ሕይወት እንደሆነ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ የታየና የተረጋገጠ
ነው። እኔና እናንተም ወደዚህ እምነት ስንመጣ፣ ወንጌል በትክክለኛው
ተሰብኮልን ከሆነ፣ "*የአበባ ምንጣፍ ይዘረጋላችኋል...ትከብራላችሁ...
ይጨበጨብላችኋል... ሀብታሞችና ባለጸጋዎች ትሆናላችሁ... የምትፈል
ጉትን ሁሉ ታገኛላችሁ... መከራና ችግር አይነካችሁም...*" በማለት
ማንም ተስፋ የገባልን ሰው የለም። የእናንተን አላውቅም፤ ለእኔ ግን
"*መንገዱ ጠባብ ነው...መከራ፣ ስደት፣ መስቀል...አለበት...አውቀህ
ግባበት*" ተብሎ ተነግሮኝ፣ ተስማምቼ የገባሁበት ሕይወት ነው። "*መከራ
አይደርስብህም... ሁሉ ነገር ይሳካልሃል*" ብሎ አባብሎ ወደዚህ ሕይወት
ያመጣኝ ሰው የለም። መከራና ስደትን ባልወደውም፣ አንዳንዴ የጠበቅ
ሁትን ዓይነት፣ ሌሎች የቀመሱትን መራራ ጽዋ ባለመቅመሴ፣ በመደሰት

ፈንታ በራሴ የማፍርበት፣ *"የመስቀሉ አገልጋይ ነኝ ወይ? እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ነኝ ወይ?"* ብዬ በመጠራጠር ራሴን የምጠይቅበት ጊዜ አለ።

ኢየሱስ *"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" (የማቴ. 10፥38)* ባለው መሠረት የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርቱና ሐዋርያት ሕይወታቸውን አሳልፈው እንደ ሰጡ ታሪክ ይመሰክራል። ባመኑበት ጸንተው በመቆማቸው፣ ሁሉም የተፈጥሮ ሞት ሳይሆን፣ በተለያየ መንገድ ሕይወታቸውን እንዳጡ ቀደም ሲል ገልጸናል።

## 4. ቀደም ሲል በአማኞች ላይ የተፈጸሙ ስደቶች

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ይኸውም ከ54 ዓ.ም እስከ 305 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ድረስ፣ አስር የሚሆኑ ትላላቅ ስደቶች በክርስቲያኖች ላይ ተነስቶ እንደ ነበረ ታሪክ ይመሰክራል። አምስቶቹን ስደቶችና በእነዚህ ስደቶች ውስጥ ሰማዕት ሆነው ያለፉትን በዚህኛው ምዕራፍ ውስጥ ለማየት እንሞክራለን።

*[1] የመጀመሪያው ታላቅ የክርስቲያኖች ስደት፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፣ ከ54 እስከ 68 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ በንጉሠ ነገሥት ኔሮ ዘመን በክርስቲያኖች ላይ የተካሄደው ስደት ነው።*

ንጉሠ ነገሥት ኔሮ ተንኮለኛ፣ በጣም ክፉና ጭካኝ ሰው ነበር። የሮም ከተማ በእሳት እንድትቃጠል ሆን ብሎ ትዕዛዝ የሰጠው እርሱ ራሱ ሆኖ፣ የሮም ተወላጆች ቁጣ በክርስቲያኖች ላይ እንዲነድ፣ እንዲሁም ራሱን ነጻ ለማድረግ "ከተማዋን በእሳት ያቃጠሏት ክርስቲያኖች ናቸው" በማለት በክርስቲያኖች ላይ ስደትን አወጀ። ራሱ ኔሮ በጫረው እሳት የሮም ከተማ ዘጠኝ ቀን ሙሉ በእሳት ስትነድ ቆየች። በእነዚህ ዘጠኝ ቀናት፣ ክርስቲያኖች እየታደኑ ይያዙ ነበር። በክርስቲያኖች ላይ የተነ



ሳው ስደትና መከራ በኔሮ አገዛዝ ዘመን፣ ይኸውም 14 ዓመት ሙሉ ቆየ። በ14 ዓመት ውስጥ ምን ያህል ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን እንዳጡ መገመት ቀላል አይደለም። ከዚህ በፊት በክርስቲያኖች ላይ ከደረሰው ስደት የበለጠ የከፋና በጣም የሚዘገንን ነበር። እነዚህን የጭካኔና የግፍ ሥራዎችን ከሰይጣን ከራሱ በቀር ሥጋ የለበሰ ሰው ያካሄዳቸው ናቸው ብሎ መገመት በጣም ያስቸግር ነበር።

ክርስቲያኖችን እንደ ወንበዴ አሳድደው ከያዙ በኋላ፣ በልዩ ልዩ መንገድ አሰቃይተው ይገድሏቸው ነበር።

*(ሀ) አውሬዎችን ከጫካ አድነው ከገደሉ በኋላ፣ ቆዳቸውን ገፍፈው እንደ ልብስ ሰፍተው ክርስቲያኖችን ካለብሷቸው በኋላ ጫካ ወስደው በላያቸው ላይ ኃይለኛ የሆኑ ውሾችን ይለቁባቸ ነበር። ውሾችም አውሬ ያገኙ መስሏቸው የክርስቲያኖችን ሥጋ እየቦጫጨቁ በመብላት ያጠፏቸው ነበር። ይሄ ክርስቲያኖችን አሰቃይተው የሚገድሉበት አንደኛው መንገዳቸው ነበር።*

*(ለ) ሌላው መንገድ የክርስቲያኖችን ልብስ ነዳጅነት ያለው ሰም ውስጥ ነክረው ካለበሷቸው በኋላ፣ ኔሮ በአትክልቱ ውስጥ ለሹማምንቶቹ በሚያደርገው ግብዣ ላይ፣ ብርሃንና ድምቀት እንዲሰጡ ከምሰሶ ጋር አስረው በእሳት ይለኩሷቸ ነበር።*

በሮማ ግዛት ውስጥ ሁሉ ይህን ዓይነቱ ስደት በክርስቲያኖች ላይ በኃይል ይካሄድ ነበር። ይሁን እንጂ፣ የክርስቲያኖችን መንፈስ በማዳከም ፈንታ ይበልጥ ያጠናከረው ነበር። ጳውሎስና ጴጥሮስ እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወታቸውን ያጡት በዚህ ዘመን ነበር።

*[2] ሁለተኛው ታላቅ የክርስቲያኖች ስደት፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፣ ከ81 እስከ 96 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ በንጉሠ ነገሥት ዶሚትያን ዘመን የነበረ ነው።*

*ዶሚትያን* በጣም ጨካኝ የነበረ ሰው፣ ሌላው ቀርቶ የራሱን ወንድም የገደለና በክርስቲያኖች ላይ ሁለተኛውን ታላቅ ስደት ያካሄደ ንጉሥ ነበር። ክርስቲያኖችን በጣም ከመጥላቱ የተነሳ *"ክርስቲያን በመሆኑ ተከሶ ልዩ ፍርድ ቤት የቀረበ ማንኛውም ክርስቲያን፣ እምነቱን ካልካደ በስተቀር በሞት እንዲቀጣ"* የሚል አዋጅ አውጥቶ ነበር። በዚህ ዘመን ውስጥ፣ ብዙዎች የሰው አዕምሮ ሊያስበውና ሊገምተው ከሚችለው በላይ ኃይለኛ ጥላቻ በክርስቲያኖች ላይ ስለ ነበራቸው፣ እነርሱን ለማጥፋት ሲሉ ብዙ ሀሰተኛ ወሬዎችን እየፈጠሩ ያስወሩባቸው ነበር። በጠቅላላው በሮም ግዛት ውስጥ፣ በየትኛውም ሥፍራ ረሀብ፣ ተላላፊ በሽታ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ሲደርስ፣ ለደረሰው ችግር ሁሉ ምክንያት የሚያደርጉት ክርስቲያኖችን ነበር። በክርስቲያኖች ላይ በሀሰት እንዲመሰክሩ ለሕዝቡ ብዙ ገንዘብ ይከፍሉ ነበር። ብዙዎች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ፣ የብዙዎቹን ንጹህ ደም በከንቱ ያፈሱ ነበር።

ክርስቲያኖች ተይዘው በንጉሠ ነገሥት ዶሚትያን ልዩ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ፣ እምነታቸውን ክደው በዶሚትያን ስም መሃላ እንዲምሉ ይጠይቋቸው ነበር። "እምቢ!" ያሉትን ያለአንዳች ምሕረት፣ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ይገድሏቸው ነበር። በዚህ ዘመን በሰማዕትነት ከሞቱት ውስጥ፣ የሐዋርያው ጳውሎስ ደቀ መዝሙር የነበረው ጢሞቴዎስ ይገኝበታል። በ97 ዓ.ም. ኤፌሶን ውስጥ የጣዖት አምልኮ በዓል ሲከበር፣ ጢሞቴዎስ ኃይለኛ ተቃውሞ በማሰማቱ፣ በዱላ ከቀጠቀጡት በኋላ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት በሁለተኛው ቀን እንደ ሞተ ታሪክ ይመሰክራል።

*[3] ሦስተኛው ታላቅ የክርስቲያኖች ስደት፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፣ ከ98 እስከ 117 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በንጉሠ ነገሥት ትሮጃን ዘመን የነበረ ነው።*

*ፐሊኒ* የተባለው ታዋቂ ጸሀፊ በክርስቲያኖች ላይ ይደርስ የነበረውን ስደትና መከራ ተመልክቶ በጣም በማዘን፣ ብዙ ክርስቲያኖች ምንም ሳያጠፉ፣ የሮምን ሕግ ሳይተላለፉ እንዲሁ በከንቱ በየቀኑ ያለአግባብ



እንደሚገደሉ በመጥቀስ ለትሮጃን ደብዳቤ ጻፈለት። ደብዳቤው በከፊል እንዲህ ይላል፦

- *"ክርስቲያኖች አደረጉ ወይም ፈጸሙ የሚባለው ወንጀል ሌላ ነገር ሳይሆን ይሄ ነው። ቀን ወስነው በአንድነት ይሰበሰባሉ፤ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር ስለሚያምኑት ወደ እርሱ ይጸልያሉ። እምነታቸው የሚያዘውን ግዴታ ይፈጽማሉ። ክፉ ነገር ፈጽሞ አያደርጉም። ሌብነት፣ ዘረፋ ወይም ዝሙት አይፈጽሙም። ማንንም በሀሰት አይከሱም፤ ውሸት አይናገሩም። ማንንም አያጭበረብሩም፤ ማንንም አያታልሉም፤ ራሳቸውን ከሌላው መለየት ልማዳቸው ነው፤ በጋራ ማዕድ ይቀርባሉ"* የሚል ነበር።

ጸሀፊው ፐሊኒ ለንጉሠ ነገሥቱ ለትሮጃን የጻፈው ደብዳቤ የክርስቲያኖችን መከራ ለጊዜው በመጠኑም ቢሆን ቀነሰው እንጂ ፈጽሞ አላጠፋውም። በ110 ዓ.ም በነበረው የክርስቲያኖች ስደት፣ ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ "ክርስቲያን" ተብለው በተጠሩበት በአንጾክያ የቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው *ኢግናትየስ* የተባለው ሰው ክርስቲያን መሆኑን በማወጁና በማስተማሩ ምክንያት የሞት ቅጣት እንዲፈረድበት ወደ ሮም ተላከ። የሚያስደንቀው፣ በወታደሮች ተይዞ ሊገደል ወደ ሮም ሲወስዱት እንኳ፣ በሚያልፍበት ከተማ ሁሉ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት በድፍረት ይሰብክ፣ ክርስቲያኖችንም ያነቃቃ ነበር። ሲሚርና በደረሰበት ጊዜ፣ ሮም ላለችው ቤተ ክርስቲያን *"የሰማዕት ሞት እንዳልሞት ምንም ዓይነት ሙከራ እንዳታደርጉ፤ ይህንን ብታደርጉ ግን ብዙ ጊዜ ስመኘው የነበረውን ዕድል ታሳጡኛላችሁ"* ብሎ ደብዳቤ ጻፈላቸው። ደብዳቤው በከፊል እንዲህ ይላል፦

*"ደቀ መዝሙር ለመሆን ጀምሬአለሁ። ከዚህ በኋላ ከክርስቶስ በቀር፣ ለሚታየውም ሆነ፣ ለማይታየው ነገር ፍጹም ግድ የለኝም። እሳትም ይሁን መስቀል፣ አውሬዎችም ቢሆኑ ሥጋዬን ይቦጫጭቁት፣ አጥንቶቼን ይከስክሱት፣ የሰውነት ክፍሎቼን ይቆራርጡት፣ ሥጋዬን ይፍጩት፣*

የሰይጣን ተንኮልም ሆነ ክፉት በላይ ይረባረብብኝ፣ ክርስቶስን ብቻ እስካገኘሁ ድረስ ፍጹም ግድ የለኝም" ይላል።

በመጨረሻም ለአንበሶች ተጥሎ እንዲሞት ፈርደውበት፣ የአንበሶችን ማጓራት ቢሰማም፣ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ፈንታ፣ ለክርስቶስ መከራ መቀበልን በጣም ይናፍቅ ስለ ነበር እንዲህ አለ፣

"የክርስቶስ ስንዴ ነኝ፣ ንጹህ ዳቦ እንዲወጣኝ፣ በአናብስት ጥርስ ልፈጭ ነው።" አለ።

ንጉሠ ነገሥት ትራጃን ሲሞት፣ በምትኩ የተተካው ንጉሡ አድርያን ሦስተኛውን የክርስቲያኖችን ስደት የበለጠ ጭካኔውን እያከፋው መጣ። በአድርያን ዘመነ መንግሥት 10 ሺ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት እንደ ተገደሉ የሰማዕታት ታሪክ ጸሀፊዎች ይመሰክራሉ። አሟሟታቸው የክርስቶስን እንዲመስል ብዙዎቹ የሾህ አክሊል ተደፋባቸው፣ በመስቀል ተሰቀሉ፣ መስቀል ላይ እንደተንጠለጠሉ ጭካኔ በተሞላበት መንፈስ ጎናቸው በጦር ተወጋ።

እዩስታክዩስ የተባለ ደፋር የሮማ ወታደር ጦር መሪ የነበረው ባገኛቸው የጦር ድሎች ምክንያት የድል አድራጊነት መስዋዕት ለጣዖታት እንዲያቀርብ ተጠይቆ፣ ለክርስቶስ ሕይወቱን የሰጠ አማኝ ስለ ነበረ፣ ከምድራዊ ከንቱ ከሆነ ክብር ይልቅ፣ በልቡ የተቀበለው ክርስቶስ የሚበልጥ መሆኑን ስላመነ፣ "ለጣዖት መስዋዕት አላቀርብም" በማለት "እምቢ!" አለ። በዚህ ወቅት ንጉሠ ነገሥት አድርያንን፣ የእዩስታክዩስ ክርስቲያን መሆን በጣም ስላስቆጣው፣ እዩስታክዩስ ለአገሩ ያስገኛቸውን የጦር ድሎች ከምንም ባለመቁጠር፣ እርሱና መላው ቤተሰቡ በሞት እንዲቀጡ አደረገ።

በዚሁ በሦስተኛው የክርስቲያኖች ስደት ዘመን ፋሲነስና ጆቪታ የተባሉ ወንድማማቾች በእምነታቸው ምክንያት ሲሰቃዩ ኮለሲረስ የተባለ ጣዖት አምላኪ ያይ ነበር። እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች በነበራቸው ጽናት፣ ድፍረትና ቆራጥነት በጣም ከመደነቁ የተነሳ፣ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ "የክርስቲያኖች እግዚአብሔር፣ የክርስቲያኖች



አምላክ ታላቅ አምላክ ነው" ብሎ በኃይል ጮኸ። ይህን በማለቱ ወዲያው ተይዞ እነዚያ ሁለት ወንድማማቾች የቀመሱትን የመከራ ጽዋ ቀምሶ ሞተ። ምን ዓይነት የሚደነቅ ድፍረት ነው! የክርስትና እምነት በመከራና ሞት በበዛበትም ዙሪያም ሰዎችን ወደ ደህንነት የመሳብ ልዩ ኃይል እንዳለው እናያለን። በአማኞች መልካም ምስክርነት የተነሳ፣ ሰዎች ፈርተው በመሸሽ ፈንታ፣ የበለጠ ተስበው ወደ ደህንነት ይመጡ ነበር። በዚህ ዘመን ባለነው ክርስቲያኖች፣ ዓለማውያን የሚሰጡት ምስክርነት ምን ዓይነት ይሆን? ክርስቶስን እናስመሰግነዋለን? ወይስ ስሙን እናሰድባለን? ደማቸውን አፍስሰው፣ ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው ወንጌልን ላስተላለፉልን ሰዎች በመጨረሻው ቀን ምን እንላቸው ይሆን? "እናንተ የሞታችሁለትን ወንጌል ተቅብለን ዋጋ ከፍለን ለሚቀጥለው ትውልድ አስተላልፈናል"እንላቸው ይሆን? ይህን ለማለት ጌታ ይርዳን!

[4] አራተኛው ታላቅ የክርስቲያኖች ስደት፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፣ ከ162 እስከ 180 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በንጉሠ ነገሥት ማርከስ አውረሊየስ አንቶኒነስ ዘመን የነበረ ነው።

ማርከስ አውረሊየስ እጅግ በጣም ጨካኝ የነበረ ንጉሥ ሲሆን፣ የአራተኛውን ታላቅ የክርስቲያኖች ስደት ያፋፋመ ንጉሥ ነበር። ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው፣ እንዲሁም የሞት ቅጣት የተበየነባቸውን እንዲሞቱ ያደርግ የነበረው በጣም ጭካኔ በተሞላበትና በጣም በሚዘገንን ዓይነት በመሆኑ ተመልካቾቹን ሁሉ የሚሰቀጥጥ ነበር። ያ ብቻ ሳይሆን በዚህ ሁሉ መከራና ስቃይ ውስጥ ክርስቲያኖች ሲያልፉ ለእምነታቸውና ለአምላካቸው ያላቸውን ታማኝነት፣ ቆራጥነትና ድፍረት ብዙዎች እያዩ ክርስቲያኖችን እጅግ በጣም ያደንቋቸው ነበር። ሰማዕት ሆነው ከሞቱት ውስጥ አንዳንዶቹ እግሮቻቸው በዳመጠ ሲጨፈለቅ፣ ብዙዎቹ በሾህ ላይ፣ በሚስማር ላይ፣ እንዲሁም በጣም ሹል በሆኑ ጠርሙሶች ላይ እንዲራመዱ ያደርጓቸው ነበር። አንዳንዶቹን ደግሞ ቆዳቸውና ሥጋቸው እስኪተለተል፣ የውስጥ ሥሮቻቸው እስኪታዩ ድረስ ይገርፏቸው ነበር። የሰው አዕምሮ ሊቀበለውና ሊያስበው ከሚችለው በላይ ካሰቃዩዋቸው በኋላ፣ በመጨረሻ በሚዘገንን ሁኔታ ይገድሏቸው ነበር።

መከራውና ስቃዩ ሲበዛባቸው የሚያሰቃዩዋቸው ሰዎች መከራቸውን እንዲያቃልሉላቸው ወይም ቶሎ ገድለው ከመከራቸው እንዲያሳርፏቸው በመለመን ፈንታ፣ ጌታቸውን ከልብ እያመሰገኑ፣ የድል መዝሙር እየዘመሩ የሚሞቱ መሆናቸው ብዙዎቹን ከመጠን በላይ ያስደንቅ ነበር።

በዚሁ ክፉ ዘመን *ጀርመኒከስ* የተባለ አንድ ወጣት በእምነቱ ምክንያት ተይዞ ለተራቡ አንበሶች ሲጣል፣ ይህ ወጣት ያሳየው ድፍረትና ቆራጥነት ፍጹም ሌላ ነበር። በጠቅላላው ክርስቲያኖች ከላይ በገለጽነው ዓይነት ሲሰቃዩ ለማየት ከሚሰበሰቡት ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች መካከል ልባቸው በጣም ተነክቶ፣ በወቅቱ በክርስቲያኖች ላይ ይካሄድ የነበረው ስደትና መከራ ሳያስፈራቸው ብዙዎች ወደ ክርስትና እምነት ይመጡ እንደ ነበር ታሪክ ይመሰክራል።

በዚሁ ዘመን የሐዋርያው ዮሐንስ ተማሪ የነበረው፣ የስሚርና ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው *ፖሊካርፕ* በአንድ ወቅት ከተደበቀበት ሥፍራ ወታደሮች ሊወስዱት መጡ። ሊወስዱት የመጡትን ወታደሮች በብርድ ተቆራምደው፣ ደክመውና ተርበው ስላያቸው፣ ልቡ በርህራሄ ተሞልቶ በአስቸኳይ እሳት እንዲያነዱላቸው፣ ትኩስ ምግብ እንዲያቀርቡላቸው ሠራተኞቹን አዘዘ። ሠራተኞቹ ምግብ ከሠሩላቸው በኋላ ራሱ ፖሊካርፕ ምግቡን አቀረበላቸውና እስኪጠግቡ ድረስ በሉ። ፖሊካርፕ እነዚያ ይዘውት ለመሄድ ለመጡት ወታደሮች ባሳየው የጨዋነት ጠባይ፣ የርህራሄ መንፈስ እጅግ በጣም ተደነቁ። ወታደሮቹ በቁጣና በጥላቻ የተሞላ ሰው የሚጠብቃቸው መስሏቸው ነበር። ከወታደሮቹ አንደኛው "እንዲህ ዓይነቱን የተከበረና ጨዋ ሽማግሌ ለመያዝ ይህን ያህል የተደከመበት ምክንያቱ ምንድነው?" ብሎ ጠየቀ።

ወታደሮቹም ከበሉና ከተጠጡ በኋላ ፖሊካርፕን ይዘውት ለመሄድ ሲዘጋጁ፣ ለጸሎት የአንድ ሰዓት ጊዜ እንዲሰጡት ጠየቃቸው። ወታደሮቹ ፈቅደውለት የመጨረሻዋን አጭር ጊዜ ከጌታው ጋር በጸሎት በጥሩ ሁኔታ አሳለፈ። ሊወስዱት የመጡት ወታደሮች በተደረገላቸው መልካም አቀባበል በጣም ተደንቀው፣ ሞት የሚጠብቀው መሆኑን ስላወቁ ልባቸው



በሀዘን ተሞልቶ ነበር። *ፖሊካርፕን* ይዘው እንዲያመጡ ትዕዛዙን የተቀበሉት እነርሱ ባይሆኑ ደስ ይላቸው ነበር። ወታደሮቹም ለፍርድ አገረ ገዥው ፊት አቀረቡት፣ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈረደበት። አገረ ገዥው ፍርዱን ካሰማው በኋላ፣ ሀሳቡን እንዲቀይር *ፖሊካርፕን* ሊያባብለው ሞከረ። *"ዕድሜህን ተመልከት፤ ረጅም ዕድሜ፣ ጥሩ ኑሮ ኖረሃል፤ ለምን በዚህ ዓይነት ሕይወትህን ትጨርሳለህ? የተቀረውን ዘመንህን በሰላም ለምን አትጨርሰውም? ቄሳር ጌታ ነው ብለህ አንድ ጊዜ ብቻ ኢየሱስን ስደብና በነጻ እለቅሃለሁ"* አለው። ፖሊካርፕ የታሠረበት ሠንሠለት ቢከብደውም እንደምንም ራሱን ካመቻቸ በኋላ፣ *"ይህንን ጌታ 86 ዓመት አገልግዬዋለሁ። አንድ ጊዜም እንኳን ክፉ አላደረገብኝም። ታዲያ ይሄን ንጉሤንና ጌታዬን እንዴት ልሰደበው? ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ኑዛዜዬን ስማ! እኔ ክርስቲያን ነኝ"* ብሎ በኃይል ቃል ተናገረ። ይሄም ንግግሩ በስቴዲየሙ የተሰበሰበውን ሕዝብ በጣም አስቆጣው።

አገረ ገዥውም፣ *"የተራቡ አንበሶች ልለቅብህ ተዘጋጅቻለሁ"* አለው። ፖሊካርፕም *"እንግዲያውስ አምጣቸው፣ እኔ እንደሆንኩ፣ ከእምነቴ ትንሽም ፎቀቅ አልልም"* አለው። አገረ ገዢውም *"አንበሶች የማያስፈሩህ ከሆነ፣ በእሳት ተቃጥለህ እንድትሞት አደርጋለሁ"* አለው። ፖሊካርፕም *"የአንተ እሳት ለጥቂት ጊዜ ነዶ ወዲያው ይጠፋል፤ ለክፉዎች የተዘጋጀው የፍርድ እሳት ግን ለዘለዓለም አይጠፋም"* ብሎ መለሰለት። በዚህን ጊዜ አገረ ገዢው በጣም ተናዶ አዋጅ ነጋሪውን ጠራው። ጥሩምባው ተነፋ። በሕጉ መሠረት አዋጅ ነጋሪው ስቴዲየሙ መካከል ቆሞ ፖሊካርፕ በእሳት ተቃጥሎ ሲሞት ለማየት ለመጣው፣ በዚያ ስፍራ ለተሰበሰበው ብዙ ሕዝብ፣ *"ፖሊካርፕ ክርስቲያን መሆኑን ተናዝዟል"* ብሎ በኃይል ጮኸ። ሕዝቡም ይህንን ሲሰማ እሳቱ በኃይል እንዲነድ ያያዙትን እንጨት ሁሉ ሰብስበው አምጥተው ከመሩ። ፖሊካርፕ ይህንን ሁኔታ ሲያይ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ፈንታ፣ *"እግዚአብሔር ሆይ! እኔንም ከቁም ነገር ቆጥረህ ለዚህች ድንቅ ሰዓት ስላደረስከኝ ስምህን አከብረዋለሁ"* ብሎ ጸለየ።

*ፖሊካርፕ* ከነፍሱ በእሳት ተቃጥሎ ወደሚሞትበት ወደ ስታድየሙ ወስደው፣ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት ከግንድ ጋር በሚሥማር በማያያዝ ፈንታ፣ በገመድ ከተከሉት ግንድ ጋር ጠፍረው አሠሩት። ይህን ያደረጉበት ምክንያት ፖሊካርፕ እሳቱ በላዩ ላይ ሲነድ ነቅንቅ እንደማይልና እንደማያስቸግራቸው ቃል ስለገባላቸው ነበር። ሕዝቡ ሰብስቦ ያመጣውን ደረቅ እንጨት በዙሪያው ከከመሩ በኋላ እንጨቱን በእሳት አያያዙት። ብዙዎቹን እስኪያስደንቅ ድረስ እሳቱ እየነደደ ወደ ላይ ከፍ እያለ ሲመጣ፣ ፖሊካርፕን አይነካውም ነበር። በሁኔታው በመደነቅ ፈንታ፣ ቅጣቱን ለሚያስፈጽሙት ወታደሮች በሰይፍ እየወጉ እንዲያሰቃዩት ትዕዛዝ ተሰጣቸው። ሰውነቱን በጦር ሲወጉት ብዙ ደም እንደ ውሃ ፈስሶ ደሙ እሳቱን እንዳጠፋው የሚናገሩ አሉ። ክርስቲያን ወዳጆቹ እንዲቀብሩት ሬሳውን እንዲሰጧቸው ቢጠይቁም፣ የወንጌሉ ጠላቶች፣ አጥንቱ ሳይቀር በእሳት መቃጠል አለበት ብለው ከለከሏቸው። ፖሊካርፕ በዚህ ዓይነት የሰማዕትነትን ሞት ቀምሶ አለፈ።

በዚሁ በአራተኛው የክርስቲያኖች ታላቅ የስደት ዘመን፣ *ፍሊሲታቲስ* የተባለች አንዲት ሀብታም የሮማ ተወላጅ፣ በዚያ ከባድ የመከራ ዘመን ሕይወቷን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠች ታማኝ ሴት ነበረች። ይህቺ ሴት እንደ እርሷ ሕይወታቸውን ለጌታ የሰጡ ሰባት ወንዶች ልጆች ነበሯት። ሞት ተፈርዶባት በሰማዕትነት የሞተችው እርሷ ብቻ ሳትሆን፣ ሰባቱም ልጆቿ ናቸው።

- *የመጀመሪያው ልጇ፣ ጃንዋሪስ የተባለው ከተገረፈ በኋላ፣ ትልቅ ክብደት ባለው ነገር ተጨፍልቆ ተገደለ።*
- *ሁለቱ ልጆቿ ፌሊክስና ፊልፕ አንገላቸውን በዱላ ከስክሰው ገደሏቸው።*
- *አራተኛው ልጇ፣ ሲልቫነስ የተባለው ወደ ገደል ተወርውሮ ሞተ።*
- *ሦስቱ የመጨረሻዎቹ ልጆቿ፣ አሌክሳንደር፣ ቪታሊስና ማርቲያል በሰይፍ አንገታቸው ታርዶ ሞቱ።*



ልጆቿ በሙሉ ከተገደሉ በኋላ በመጨረሻ እናትየው፣ *ፍሊሲታቲስ* ሦስቱ ልጆቿ በታረዱበት በዚያው ሰይፍ ታርዳ ሞተች። እንዴት የሚያስደንቅና የሚዘገንን ታሪክ ነው! ይህን የመሰለ ታላቅ ጽናት ከላይ ካልሆነ በሰው ጉልበት የሚቻል እንዳልሆነ የታወቀ ነው።

በዚሁ በአራተኛ የክርስቲያኖች ታላቅ የስደት ዘመን *ብላንዲና* የተባለች አማኝ ነበረች። ይህቺ ሴት ደካማ የሆነ ሰውነት ስለ ነበራት የሚደርስባትን ስቃይ በትዕግሥት መቋቋም አትችልም ይባል ነበር። ነገር ግን ጽናቷም ሆነ ብርታቷ በጣም የሚደነቅ ከመሆኑ የተነሳ፣ አሰቃዮቿ የቻሉትን ያህል ክፉ ድርጊት ቢፈጽሙባትም እነርሱ ደከሙ እንጂ፣ መንፈሷን ትንሽም ቢሆን ሊሰብሩት አልቻሉም። በመጨረሻም ሀሳቧን ሊያስለውጧት እንዳልቻሉ ሲያዉቁ፣ ከሌሎች ሦስት ክርስቲያኖች ጋር ብዙ ሕዝብ ከተሰበሰበት ትልቅ የትያትር አዳራሽ፣ የተራቡ አንበሶች እየቦጫጨቁ ሥጋዋን እንዲበሉት፣ አንድ እንጨት ላይ አንጠለጠሏት። መከራውን ለመቀብል እየተጠባበቀች፣ አብረዋት የነበሩትን ሌሎች ክርስቲያኖችን እያደፋፈረች በኃይል ትጸልይላቸው ነበር። የሚያስደንቀው አንበሶቹ በጣም የተራቡ ቢሆንም፣ ብዙዎቹን እስኪገርማቸው ድረስ አንዳቸውም ሊነኳት አልፈለጉም። በዚህ ወቅት በጣም ተበሳጭተው ከአዳራሹ አውጥተው ወህኒ ቤት ጣሏት። ሁለት ጊዜም ለአንበሶች ተጥላ ሁለቱንም ጊዜ አንበሶች ሊበሏት አልፈለጉም።

ለመጨረሻ ጊዜ፣ *ፖንቲከስ* ከተባለ ከ15 ዓመት ወጣት ጋር እንደገና ወደ ቲያትሩ አዳራሽ አመጧት። የፖንቲከስ ወጣትነት፣ የብላንዲና ሴት መሆን የከሳሾቻቸውንና የሕዝቡን ልብ አላለሰለሰውም። የእነዚህ ሁለት ክርስቲያኖች ጽናትና ድፍረት ሕዝቡን በጣም ስለ አስቆጣው፣ በሰው አዕምሮ ሊገመት ከሚችለው በላይ የሆነ ስቃይ ያወርዱባቸው ጀመር። ብሊንዲና ሰውነቷ እስኪተለተል ድረስ በጉማሬ አለንጋ ተገርፋ፣ መረብ ውስጥ ተከታ ኃይለኛ በሆነ ኮርማ በሬ እንድትወረወር ካደረጓት በኋላ፣ ራቁቷን በኃይል በሚያቃጥል ወንበር ላይ አስቀመጧት። መናገር እስከ ቻለችበት ጊዜ ድረስ በአካባቢዋ አብረዋት የሚሰቃዩትን ክርስቲያኖች በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ታደፋፍራቸው ነበር። ያም

የ15 ዓመት ወጣት ልጅ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ ለአምላኩ ታማኝ ሆኖ ቆመ። ብሊንዲና ምንም ዓይነት ስቃይ ቢያደርሱባት ጌታዋን ለመካድ ያልፈለገች ሴት መሆኗን ተገንዝበው፣ መጨረሻ ላይ በሰይፍ ወግተው ገደሏት።

ይህንን ታሪክ ሳነብ እንባ እየተናነቀኝ በአዕምሮዬ ውስጥ የሚመላለስ ጥያቄ ነበር። *"እኔም፣ እነዚህም ሰዎች እኩል ክርስቲያኖች ተብለን እንጠራለን?"* ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር። አንድ ቀን እግዚአብሔር ጽናቱን ሰጥቶ ካቆመኝ፣ በላይ በመንግሥተ ሰማይ አያቸዋለሁ። ታዲያ እነርሱ የከፈሉትን ዋጋ አይቼ፣ እኔስ ለጌታዬ የከፈልኩት ዋጋ ምንድነው? ብዬ ደጋግሜ እርሴን እጠይቃለሁ። መጠየቅ ብቻ ሳይሆን በራሴም አፍራለሁ። እንኳን እነርሱ የቀመሱትን ዓይነት መከራ መቅመስ ቀርቶ፣ አንዳንድ ተራ የሆኑ ደካማ "የወንጌል ሰባኪዎች ነን" ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ፣ በአገልግሎቴ ላይ የሚያደርሱብኝን ጥቃትና ጠለፋ እያሰብኩ፣ ለምን በእኔ ላይ ይሄ ይሆናል ብዬ ማዘኔ ራሱ ያሳፍረኛል። "መከራ፣ ስደትና ስቃይ ይድረስብኝ" ብሎ የሚመኝና የሚናፍቅ የለም፤ ይሁን እንጂ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተከታታይ ታሪካቸውን ያቀረብኩላችሁ ሰዎች የጠጡትን ዓይነት መራራ ጽዋ እኔና እናንተ ባንጠጣም፣ የራሳችን የሆነ መስቀል አሁንም ሆነ ወደ ፊት ሊያጋጥመን እንደሚችል በማመን ራሳችንን ማዘጋጀት እንዳለብን ለማሳሰብ እፈልጋለሁ።

*[5]* አምስተኛው ታላቁ የክርስቲያኖች ስደት፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፣ ከ193 እስከ 211 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በንጉሠ ነገሥት *ሉስየስ ሴፕቲመስ ሲቪረስ* በነገሠበት ዘመን የተፈጸመ ነው።

ለጥቂት ጊዜ *ሲቪረስ* በክርስቲያኖች ላይ መልካም አስተሳሰብ ነበረው። ለዚህም ምክንያት የሆነው አንድ ጊዜ በጣም ታሞ አንድ ክርስቲያን ጸልዮለት ከበሽታው የዳነ በመሆኑ ነው። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሮማውያን በክርስቲያኖች ላይ የነበራቸው ጥላቻ እየከፋ ሲመጣ፣ በክርስቲያኖች ላይ የሚደረገው ስደትና መከራ እንደገና እያንሰራራ መጣ። በሮም ግዛት ውስጥ በተፈጥሮ ምክንያት ለሚደርሰው ችግር ሁሉ



ክርስቲያኖችን ምክንያት ማድረግ ተጀመረ። ስደቱ እያደገና እየጨመረ ይምጣ እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያንና የወንጌሉ ቃል ከምንጊዜውም ባላነሰ ሁኔታ ኃይሉ እየጨመረ፣ የአማኞችም ቁጥር በሮማ ግዛት ውስጥ ሁሉ በጣም እያደገ ይመጣ ነበር። በዚህ ሁሉ ስደት ውስጥ የክርስቲያኖች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ ለማሳየት፣ ከቀድሞ መንፈሳዊ አባቶች መካከል *ተርቱሊያን* የተባለ ሰው በ193 ዓ.ም. ወደ ጌታ የመጣ የሥነ መለኮት ሊቅ፣ "ከሮም ግዛት ውስጥ ክርስቲያኖች ይጥፉ፣ ይባረሩ ቢባል፣ የሮማ ግዛቶች ሁሉ፣ ሰው የሌለባቸው ባዶ ይሆኑ ነበር" አለ።

በዚህ በአምስተኛው ታላቅ የክርስቲያኖች የስደት ዘመን፣ ብዙዎች ስለ እምነታቸው ተሰውተዋል። የሮም ጳጳስ የነበረው *ቪክተር* በ201 ዓ.ም. በሰማዕትነት ሞቷል።

- *ሊኦኒደስ፣ የኦሪጅን* አባት፣ የብሉይ ኪዳንን ማብራሪያ የጻፈው፣ ታዋቂ ክርስቲያን ፈላስፋ የነበረ፣ በሰይፍ ታርዶ ሞቷል።
- ተማሪዎቹም *ፕሉታርከስ፣ ሴረነስ፣ ሄሮንና ሄራክላደስ* በሰይፍ አንገታቸው ተቆርጦ ሞተዋል።
- *ራሂስ* የተባለች አማኝ የፈላ እሬንጅ በላዩዋ ላይ ካፈሰሱባት በኋላ እሳት ለኩሰውባት ተቃጥላ ሞታለች።
- *ማርሲላ* የተባለችው እናትዋ፣ እንዲሁም *ፖቴይንየን* የተባለችው እህቷ በተመሳሳይ ሁኔታ ተገድለዋል።
- *ባሲላይደስ የተባለች ክርስቲያን በእምነቷ ምክንያት የሞት ፍርድ ሲፈጸምባት በዚያ ተገኝቶ እንዲጠብቅ የታዘዘው ወታደር፣ በዚያ መከራ ውስጥ ክርስቶስን አምኖ ክርስቲያን ሆነ። በሌላ ጊዜ በሮማውያን ጣዖት ስም መስዋዕት እንዲያቀርብ ተጠይቆ፣ ክርስቲያን በመሆኑ "እምቢ" አለ። መጀመሪያ ላይ አብረውት የነበሩት፣ ያ ወታደር "ክርስቲያን ነኝ" ማለቱን ማመን እስኪያቅታቸው ድረስ በጣም አስደንቋቸው ነበር።*

*ይሁን እንጂ፣ ወታደሩ ከልቡ የተናገረው መሆኑን ሲያውቁ ግን መሬት ለመሬት እየጎተቱ ከዳኛ ፊት አቀረቡት። ዳኛውም የሞት ፍርድ ፈርዶበት አንገቱ ተቆርጦ ሞተ።*

✪ *ኢረንየስ፣ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን አባት፣ የሊዮን ጳጳስ የተወለደው ግሪክ አገር ሲሆን፣ የዓለሙንም ሆነ የመንፈሳዊ ትምህርቱን የተማረው ግሪክ ውስጥ ነበር። ሊዮን ውስጥ በክርስቲያኖች ላይ ስለ ደረሰው ስደትና መከራ የጻፈው እርሱ ነው ይባላል። በ202 ዓ.ም. አንገቱ በሰይፍ ተቆርጦ ሞተ።*

የክርስቲያኖች ታላቅ ስደት በሮማ ግዛት አካባቢ ብቻ አላበቃም። ሰሜን አፍሪካ በሮማ አገዛዝ ሥር ስለነበረ ብዙዎች በእምነታቸው ምክንያት ታርደዋል። ከእነዚህ ውስጥ *ፐርፐታ* የተባለች ክርስቲያን ሴት ትገኛለች። በቅርብ ጊዜ የወለደች፣ ልጇን የምታጠባ ወጣት ሴት ነበረች። የምታጠባትን ልጅ ከእቅፏ ወስደው ምድር ቤት ውስጥ ከነበረው ወህኒ ቤት ጣሏት። ስለ እምነቷና ስለ ተጣለችበት ወህኒ ቤት ስትናገር፣ *"ወህኒ ቤቱ ለእኔ እንደ ቤተ መንግሥት ነው"* አለች። እርሷና እንደ እርሷ በእምነታቸው የተከሰሱ ሰዎች ፍርዳቸውን ለመቀበል ዳኛ ፊት ቀረቡ። *ፐርፐታ* እምነቷን ክዳ ለሮም ጣዖት መስዋዕት ካቀረበች በነጻ የምትለቀቅ መሆኑን ዳኛው ገለጸላት። የ*ፐርፐታ* አባት ሕጻን ልጇን ታቅፎ፣ ስለ ልጇ ስትል እንኳን የተጠየቀችውን አድርጋ ከሞት እንድትድን አጥብቆ ለመናት። እርሷ ግን "ፈጽሞ አላደርገውም። ለጣዖት መስዋዕት አላቀርብም" አለች። ዳኛው፣ "ክርስቲያን ነሽ?" ብሎ ሲጠይቃት፣ ፐርፐታ በድፍረትና በቆራጥነት "አዎን! ክርስቲያን ነኝ" ስትል መልስ ሰጠች። ሌሎችም እንደ እርሷ ተከሰው የቀረቡ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ጸንተው ቆሙ። በሚቀጥለው በጣዖት አምላኪዎች በዓል ላይ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ታላቅ አዳራሽ፣ ጣዖት አምላኪዎችን ደስ ለማሰኘት፣ ወንዶቹ በተራቡ አንበሶች ተበልተው እንዲሞቱ፣ ሴቶቹ ደግሞ በኃይለኛ ኮርማ በሬዎች ተወግተውና ተረጋግጠው እንዲሞቱ ተፈረደባቸው።



በዚያ በዓል ላይ እንዲሞቱ ከተበየነባቸው ሴቶች መካከል ፐርፐታና ሌላዋ ሴት ፍሊስታ ይገኙበታል። ፐርፐታና ፍሊስታ ልብሳቸውን አውልቀው መረብ ላይ አንጠለጠሏቸው። በዚያ የተሰበሰበው ሕዝቡ ራቁታቸውን ሆነው መቅረባቸውን ስለተቃወመ፣ አልብሰው እንደ ገና ወደ አዳራሹ አመጧቸው። ፐርፐታ ወደ አዳራሹ እንደገባች ኃይለኛ የሆነ ኮርማ በሬ በቀንዱ ወደ ሰማይ አውጥቶ ወረወራት። ለጊዜው ድንጋጤ ውስጥ ከተታት እንጂ፣ ከፍተኛ ጉዳት አላደረሰባትም ነበር። አብራት የነበረችው ፍሊስታ ግን በሬው በኃይል ስለወጋት፣ በጣም ቆስላ ከመሬት ላይ ተዘርራ ነበር። ፐርፐታ አብራት የምትሰቃየዋን ፍሊስታ ከወደቀችበት ስፍራ ሄዳ እቅፍ አድርጋ ይዛ፣ ኮርማ በሬው በድጋሚ እስኪመጣ ድረስ መጠባበቅ ጀመረች። ይሁን እንጂ፣ ያ ኮርማ በሬ እነርሱን ለመውጋት እምቢ ብሎ ቆመ። ኮርማ በሬው እነዚያን ሴቶች ለመውጋት እምቢ በማለቱ፣ በዚያ ስፍራ ያንን የመሰለ የጭካኔ ትዕይንት እንደ ቲያትር ለማየት የተሰበሰበው ሕዝብ የሚፈልጉትን የጭካኔ አገዳደል ማየት ባለመቻላቸው ተበሳጩ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለትግል በሰለጠኑ ጦረኞች (ግላድየተርስ)፣ እንዲገደሉ እነዚያን ሁለት ሴቶች ወደዚያ ታላቅ የትዕይንት አዳራሽ አመጧቸው። ፍሊስታ በጦር ተወግታ ወዲያው ሞተች። ፐርፐታን እንዲገድል የተወሰነው ሰው ግን እጆቹ በኃይል ይንቀጠቀጡ ስለነበረ፣ በጦሩ አቆሰላት እንጂ አልገደላትም። በመጨረሻም የእጁን መንቀጥቀጥ አይታ፣ ጦሩን በእጇ ይዛ እየመራች ሊገድላት ከሚችለው የሰውነት ክፍሏ ላይ አድርጋ ለገዳዩዋ ከአመቻቸችለት በኋላ በዚያ ጦር ተወግታ ሞተች። እነዚህ ከላይ የሰማናቸው ታሪኮች፣ በክርስቲያኖች ላይ ከደረሱት አሥር ታላላቅ ስደቶች ውስጥ፣ አምስቶቹ ብቻ ናቸው። በዚህ ሁሉ መከራና ስደት ውስጥ የክርስቲያኖች ቁጥር መጨመሩ፣ የአማኞች የእምነት ጽናት እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ነው።

እኔና እናንተ በጌታ ውስጥ ባገኘነው ደህንነት፣ በተቀበልነው የክርስትና እምነት፣ በክርስቶስ ውስጥ በሆነልን ሰላምና ደስታ እጅግ በጣም ደስ ይለናል። እግዚአብሔርንም ብዙ ጊዜ አመሰግነዋል። ይሁን

እንጂ፣ ለወንጌል ሙሉ መሰጠት የነበራቸው ደፋር፣ ቆራጥ፣ ለሕይወታቸው ያልሳሱ ብዙ ክርስቲያኖች በዘመናት ደማቸውን እንደ ውሃ አፍስሰው፣ ወንጌልን እየተቀባበሉ ለእኛ ያደረሱልን መሆናቸውን ብዙ ጊዜ እንዘነጋለን። ብዙዎች ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉበትን፣ ሕይወታቸውን ያጡበት ወንጌል ከእኛ እጅ ሲደርስ፣ እኛም በተራችን ዋጋ ከፍለን ለሌሎች በማስተላለፍ ፈንታ፣ መጠቀሚያ፣ መክበሪያ፣ መበልጸጊያ እናደርገው ይሆን? ብዬ እፈራለሁ።

ከክርስትና ሕይወት ውስጥ መስቀልን ለማስወጣት የሚሞክሩ በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች ናቸው። በማልቀስ ፈንታ ሳቅን፣ በማጣት ፈንታ ብልጽግናን፣ ዝቅ በማለት ፈንታ ክብርን፣ በመሰደድ ፈንታ ይቀድሙኛል ብለው የሚያስቡትን ማሳደድን፣ ወንጌልን ይዞ በረሃ ለበረሃ በመንከራተት ፈንታ፣ በየከተማው ያማረ፣ ዋጋው ውድ የሆነ ልብስ ለብሶ የወንጌል ሰባኪ መምሰል የበዛበት ዘመን ነው። በሕይወታቸው ተወራርደው፣ ደማቸውን አፍስሰው፣ ከቦታ ቦታ ተንከራትተው፣ አገራቸውን፣ ምቾታቸውን ጥለው ወንጌልን ያቀበሉን የእኛን የዘምኑን ክርስቲያኖች ሕይወት በአሁኑ ጊዜ ቢያዩ ምን ያህል ልባቸው ይሰበር ይሆን? ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቼ ለማቅረብ የመረጥኩበት ዋና ዓላማ፣ የክርስትናን እምነት ርካሽ ጸጋ፣ ዋጋ የማያስከፍል አድርገን እንዳናየው፣ በእምነታችን ምክንያት ለሚያጋጥመን መከራ፣ ችግርና ስደት የበለጠ እንዲያዘጋጀን ነው።



# 4

# በመስቀሉ፥ ሙሉ መሰጠታችን ይመዝናል

*"ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በሥቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ"*

*(ፊልጵ. 3፡10)*

የማንኛውም ሰው እውነተኛ ገጸ-ባሕሪ ተለይቶ የሚታወቀው ሁሉ ነገር ሰላም በሆነበት ወቅት ላይ ሳይሆን፣ በፈተናና በትግል ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ነው። ደቀ መዛሙርቱ በመከራና በችግር ውስጥ ሲያልፉ ያየናቸው፣ መንፈሳዊ ውበት እንዳላቸው ሆነው ሳይሆን ተጨናቂዎች፣ ፈሪዎች፣ ሳመኑበት ነገር ጸንተው የማይቆሙ፣ በቀላሉ የሚበረግጉ ሆነው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥ ባሕሪ የሌለው በመሆኑ፣ በመልካም ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ በፈተናም ሆነ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ሁልጊዜ ማንነቱ ሳይለዋወጥና፣ ውበቱ ሳይሸፈን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በስቃይና በመከራ፣ እንዲሁም በመናቅና በመገፋት ሕይወት ውስጥ ያለፈው እንደ ድንገት ወይም እንዳጋጣሚ ሳይሆን፣ ከብዙ ዓመት በፊት የተለያዩ ነብያት በተነበዩት ትንቢት መሠረት ነው።

እንጂ፣ ለወንጌል ሙሉ መስጠት የነበራቸው ደፋር፣ ቆራጥ፣ ለሕይወታቸው ያልሳሱ ብዙ ክርስቲያኖች በዘመናት ደማቸውን እንደ ውሃ አፍስሰው፣ ወንጌልን እየተቀባበሉ ለእኛ ያደረሱልን መሆናቸውን ብዙ ጊዜ እንዘነጋለን። ብዙዎች ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉበትን፣ ሕይወታቸውን ያጡበት ወንጌል ከእኛ እጅ ሲደርስ፣ እኛም በተራችን ዋጋ ከፍለን ለሌሎች በማስተላለፍ ፈንታ፣ መጠቀሚያ፣ መክበሪያ፣ መበልጸጊያ እናደርገው ይሆን? ብዬ እፈራለሁ።

ከክርስትና ሕይወት ውስጥ መስቀልን ለማስወጣት የሚሞክሩ በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች ናቸው። በማልቀስ ፈንታ ሳቅን፣ በማጣት ፈንታ ብልጽግናን፣ ዝቅ በማለት ፈንታ ክብርን፣ በመሰደድ ፈንታ ይቀድሙኛል ብለው የሚያስቡትን ማሳደድን፣ ወንጌልን ይዞ በረሃ ለበረሃ በመንከራተት ፈንታ፣ በየከተማው ያማረ፣ ዋጋው ውድ የሆነ ልብስ ለብሶ የወንጌል ሰባኪ መምሰል የበዛበት ዘመን ነው። በሕይወታቸው ተወራርደው፣ ደማቸውን አፍስሰው፣ ከቦታ ቦታ ተንከራትተው፣ አገራቸውን፣ ምቾታቸውን ጥለው ወንጌልን ያቀበሉን የእኛን የዘምኑን ክርስቲያኖች ሕይወት በአሁኑ ጊዜ ቢያዩ ምን ያህል ልባቸው ይሰበር ይሆን? ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቼ ለማቅረብ የመረጥኩበት ዋና ዓላማ፣ የክርስትናን እምነት ርካሽ ጸጋ፣ ዋጋ የማያስከፍል አድርገን እንዳናየው፣ በእምነታችን ምክንያት ለሚያጋጥመን መከራ፣ ችግርና ስደት የበለጠ እንዲያዘጋጀን ነው።



# 4

# በመስቀሉ፥ ሙሉ መስጠታችን ይመዝናል

*"ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በሥቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ"*

*(ፊልጵ. 3፡10)*

የማንኛውም ሰው እውነተኛ ገጸ-ባሕሪ ተለይቶ የሚታወቀው ሁሉ ነገር ሰላም በሆነበት ወቅት ላይ ሳይሆን፣ በፈተናና በትግል ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ነው። ደቀ መዛሙርቱ በመከራና በችግር ውስጥ ሲያልፉ ያየናቸው፣ መንፈሳዊ ውበት እንዳላቸው ሆነው ሳይሆን ተጨናቂዎች፣ ፈሪዎች፣ ላመኑበት ነገር ጸንተው የማይቆሙ፣ በቀላሉ የሚበረግጉ ሆነው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥ ባሕሪ የሌለው በመሆኑ፣ በመልካም ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ በፈተናም ሆነ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ሁልጊዜ ማንነቱ ሳይለዋወጥና፣ ውበቱ ሳይሸፈን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በስቃይና በመከራ፣ እንዲሁም በመናቅና በመገፋት ሕይወት ውስጥ ያለፈው እንደ ድንገት ወይም እንዳጋጣሚ ሳይሆን፣ ከብዙ ዓመት በፊት የተለያዩ ነብያት በተነበዩት ትንቢት መሠረት ነው።

ይህ ትንቢት የግድ መፈጸም ነበረበት። መገፋት ወይም ችላ መባል ከመከራ ውስጥ አንዱ ይሁን እንጂ፣ በሁለቱ መካከል ልዩነት እንዳለ ግልጽ ነው። ኢየሱስ መገፋትን ያላካተተ መከራ ውስጥ ብቻ የሚያልፍ ቢሆን ኖሮ፣ የኢየሱስን መሲህነት ብዙዎች በደስታ በተቀበሉት ነበር። የዓለም አድናቆትም ባለው ፍቅሩ ላይ ያተኮረ ይሆን ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ የተገፋ፣ በብዙዎች ዘንድ ያልተፈለገ መሲህ ነበር። ያልተፈለገ መሲህ በመሆኑ፣ የሚገባውን ክብሩንና ማዕረጉን ያጣ ሆነ። ስለዚህ የክርስቶስ መስቀል ስቃይና መከራ ብቻ ሳይሆን መገፋትን፣ ችላ መባልን፣ መናቅንና ተቀባይነት ማጣትንም ያጠቃለለ ነው። በብዙዎች ዘንድ ችላ መባሉ፣ የሚገባውን ክብር ያጣ መሆኑን ያሳየናል። ይህንን ሁሉ ታግሶ ማለፉ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጣበት ዓላማ ምን ያህል የተሰጠ እንደሆነ እናያለን።

## 1. ሙሉ መሰጠት ምን ማለት ነው?

ሙሉ መሰጠት (commitment) ምን ማለት እንደሆነ ትክክለኛ መረዳት እንዲኖረን ያስፈልጋል። ሙሉ መሰጠት ማለት ራሳችንን፣ ፍላጎታችንን፣ ፍርሃታችንና ተስፋ መቁረጣችንን መልቀቅ ወይም መተው ማለት ነው። ሙሉ መሰጠት (commitment) የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሲተረጎም "መንከባለል" ማለት ነው። ሸክማችንን ወደ ጌታ መንከባለል እንዳለበት ይገልጻል።[5] በጀርባችን የተሸከምነውን ሸክም በክርስቶስ ትከሻ ላይ ለመጣል ወይም ለማንከባለል እኔና እናንተ እንታመንበት ወይም እናምነው ይሆን? ሐዋርያው ጳውሎስ

- *"...ያመንሁትን እርሱን ስለማውቅ አላፍርበትም፤ የሰጠሁትንም ዐደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ" ይላል (2 ጢሞ. 1፡12)።*

---

[5] Lloyd John Ogilvie. Conversation with God, Harvest House Publishers, Eugene, Oregon, 1992.



ክርስቶስ ሲጠራን *"ለእኛነታችን እንድንሞትና"* ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ራሳችንን እንድናስረክብ ወይም ሙሉ መሰጠት እንዲኖረን ነው።

- *ኢየሱስ "...በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ምክንያቱም ነፍሱን ሊያድናት የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱን ስለ እኔ ብሎ የሚያጠፋት ግን ያድናታል" ይላል (ሉቃ. 9፡23-24)።*

በዓለም አስተሳሰብ ወይም አመለካከት *"ተከተሉኝ"* ብሎ ጥሪ ሲያደርግ፣ ከመጠን በላይ ግልጽ የሆነ ይመስላል። አንድ ሰው ሌላውን እንዲከተለው ሲጠራ፣ እርሱን በመከተሉ የሚያገኘውን ጥቅም በመንገር ለመሳብ እንደሚሞክር የታወቀ ነው። ኢየሱስ ግን እውነቱን ደብቆ፣ የሚያስከፍለውን ዋጋ፣ የሚጠይቀውን ሙሉ መሰጠት ሳይናገር፣ *"እኔን ብትከተሉኝ፣ ሁሉ ነገር በጎ ይሆንላችኋል"* አላለም። ኢየሱስ ያለው፣

- *"ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ..." ነው ያለው (ማር. 8፡34)።*

*መካድ ያለብን የዓለምን በጎ ነገር፣ ምቾቱን፣ ቆሳቁሳዊ የሆነውን ነገር ብቻ ሳይሆን፣ ራሳችንንም ጭምር መካድ አለብን። በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ለዕድገታችን ትልቅ እንቅፋት የሚሆንብን ነገር፣ ሌላ ሰው ሳይሆን፣ እኛው ራሳችን መሆናችንን ብዙዎቻችን አልተረዳነውም። አሸናፊ የሆነ የክርስትና ሕይወት መኖር የምንችለው፣ ምኞታችንን ወይም ሥጋዊ ፍላጎታችንን መግደል፣ እንዲሁም የራሳችንን ዕቅድና ምኞት መተው ስንችል ነው። የሞተ ሰው ተርቦ ምግብ እንደማይፈልግ፣ እንዲሁም ለምድራዊ ደስታ ስሜቱ እንደማይቀሰቀስ ግልጽ ነው። ከዚህ በፊት ይስበው የነበረው ነገር ከሞተ በኋላ ለእነዚያ ነገሮች አይሳብም። ይሁን እንጂ፣ በመሞት ውስጥ አዲስ ሕይወት እንዳለ ማወቅ አለብን። ይኸውም፣ ለሥጋዊ ነገር ስንሞት፣ ለመንፈሳዊ ነገር መኖር እንጀምራለን። ያለአንዳች ማመንታት ሕይወታችን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ የተሰጠ ከሆነ፣ አዲስ ፍጥረት እንሆናለን። አዲስ ፍጥረት ስንሆንም፣ ሕይወታችን ለእርሱ ሙሉ በሙሉ የተሰጠ እንጂ የራሳችን አይሆንም።*

*ለአሮጌው ሕይወታችን ሞተን፣ በአዲስ ሕይወት ውስጥ መኖር እንጀምራለን።*

## 2. ሙሉ መስጠት ራስን በመካድ ይጀምራል

ኢየሱስ *"እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" (ማቴ. 16፡24)* ይላል። መስቀሉን ለመሸከም በቅድሚያ ራሱን መካድ እንዳለበት ይናገራል። ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ስንክድ፣ ያኔ ስለ ስሙ መስቀሉን ለመሸከም ጉልበት (አቅም) ይኖረናል። እራሳችንን ክደን እርሱን ብቻ ስናስቀድም፣ በተሸከምነው መስቀል ምክንያት የሚደርስብን ስቃይ አይሰማንም። ኢየሱስ በጸጋው አስቀድሞ ካላዘጋጀን በስተቀር፣ በመስቀሉ ምክንያት የሚደርስብንን መከራ መታገስ ከአቅማችን በላይ ይሆንብናል። በመስቀሉ ውስጥ ያለውን መከራ መታገስ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን የታማኝነት ፍሬ ማፍራታችንን ያሳያል። በመስቀል ሕይወት ውስጥ ማለፍ እንዳጋጣሚ የሚደርስ ሳይሆን፣ ማንኛውም አማኝ የሚያልፍበት አስቀድሞ የተወሰነ የሕይወት ልምምድ ነው። ኢየሱስ በጌቴሴማኔ ውስጥ የቀመሰውን መራራ ጽዋ መረዳት ባንችልም፣ ፍጹም ኃጢአት የሌለበት ኢየሱስ ስለ ሰው "ኃጢአት" የተሰቃየ መሆኑን ግን እናውቃለን።

በመስቀል ላይ መሞት፣ በሰዎች ተንቆና ችላ ተብሎ የሞትን ጽዋ መቅመስ ነው። ኢየሱስ ተንቆና ተሰቃይቶ እንዲሞት አስቀድሞ የተወሰነ በመሆኑ፣ ይሄ እንዳይሆን መከላከል፣ የእግዚአብሔር ዓላማ ምን እንደሆነ አለመረዳት ነው። መከራውንና ሥቃዩን፣ እንዲሁም መገፋቱን መከላከል፣ ክርስቶስን መሲህ እንዳይሆን መከልከል ይሆናል። የቤተ ክርስቲያን ድንጋይ (አለት) የተባለው ጴጥሮስ፣ *"አንተ መሲሁ ነህ"* ብሎ ካለው በኋላ፣ ኢየሱስ ስለ መከራውና ስለ ስቃዩ ሲናገር፣ *"ይህ በአንተ ላይ አይድረስ"* ብሎ በመናገሩ ክርስቶስን ምን ያህል እንዳስቆጣው እናውቃለን። በዚህ ዓይነት ገና ከመጀመሪያው፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መስቀል የሌለበት ክርስትና ለመኖር ሙከራ ይደረግ እንደነበረ እንረዳለን። ጴጥሮስ



ኢየሱስን *"ይህ በአንተ ላይ አይድረስ"* ሲለው፣ ኢየሱስ በመስቀል ሕይወት ውስጥ እንዳያልፍ መከልከሉ፣ የክርስትና ሃይማኖት መስቀል የሌለበት ሃይማኖት እንዲሆን ማድረጉ እንደሆነ የተረዳው አይመስለንም።

ክርስቶስ እውነተኛ መሲህነቱ ተለይቶ የሚታወቀው የተገፋ፣ በመከራና በስቃይ ውስጥ አልፎ የመስቀልን ሞት በመሞቱ ነው። ኢየሱስ ራሱ ብቻ ሳይሆን፣ ደቀ መዛሙርቱም እርሱን ለመከተል ወይም ላለመከተል፣ እንዲሁም በመከራ ውስጥ እርሱ የቀመሰውን ለመቅመስ፣ እርሱ የጠጣውን መራራ ጽዋ ጠጥተው ማለፍ ምርጫው የራሳቸው እንደሆነ ገልጾላቸው ነበር። በፍቅር ይጠራል እንጂ ማንንም "ተከተሉኝ" ብሎ አያስገድድም። ማንም በፍቅሩ ተስቦ እንጂ ተገዶ እንዲከተለው አይፈልግም። ደቀ መዛሙርቱም የእርሱ ተከታዮች መሆን የሚችሉት በመከራው፣ በመስቀል ሞቱና በመገፋቱ እርሱን እንዲመስሉት አስቀድሞ ስለተነገራቸው በደንብ አውቀውታል።

ክርስቶስ ዙፋኑን ትቶ ወደ ዓለም የመጣው ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠት ዓለምን ለመቤዠት ስለሆነ፣ የመጣበትን ዓላማ ማንም እንዲያደናቅፍበት አይፈልግም ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ጥሪው ደርሷቸው ግማሽ መንገድ ድረስ ከሄዱ በኋላ፣ ሌላ መስቀልያ መንገድ ላይ ደረሱ። መስቀልያው መንገድ ላይ ሌላ ምርጫ መምረጥ ነበረባቸው። "እኔን መከተል የሚፈልግ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ" የሚል ጥሪ አደረገላቸው። ጴጥሮስ ኢየሱስን ሲክድ፣ "ይህን ሰው ፈጽሞ አላውቀውም" እንዳለ፣ የተቀሩትም ይህንኑ ብለው ሊክዱት ይችላሉ። ኢየሱስ *"ራሱን ይካድ"* ሲል ምን ማለቱ ይሆን? *ራስን መካድ ማለት ሥጋን መግደል ወይም አንድ ሥፍራ ተገልሎ መቀመጥ፣ ወይም የራስን ሕይወት በገዛ እጅ ማጥፋት (መግደል) ማለት አይደለም። ራሳችንን መካድ ማለት፣ ስለ ራሳችን ማሰብና መጨነቅን ትተን ከፊታችን ቀድሞ የሚሄደውን ኢየሱስን ማሰብና መከተል ማለት ነው።*

## 3. ክርስቲያን መሆን ሙሉ መሰጠትን ይጠይቃል

የክርስትና ሕይወት ደስታና ሰላም የሞላበት ሕይወት ነው። ይሁን እንጂ፣ ምቾት ያለበት፣ የአበባ ምንጣፍ የተዘረጋበት፣ ሁልጊዜ ፈንጠዝያ ያለበት ሕይወት ነው ማለት አይደለም። *"ጌታን እንደ ግል መድኃኒታችሁ አድርጋችሁ ብትቀበሉትና ክርስቲያን ብትሆኑ ሁሉ ነገር ይሰምርላችኋል፣ የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ ታገኛላችሁ፤ ፈተና፣ ችግርና መከራ ፈጽሞ አይደርስባችሁም"* ብላችሁ፣ ዋሽኋችሁ እንጂ እውነቱን አልነገርኳችሁም። ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ከተቀበልንበት ቀን ጀምሮ፣ በዚህ ዓለም የተወሰነልንን ዘመን ጨርሰን እስከምንሄድበት ጊዜ ድረስ የማያቋርጥ ጦርነት ይኖርብናል። *"የክርስትና ሕይወት ትግል፣ እንዲሁም ጦርነት ያለበት ሕይወት ከሆነ፣ ታዲያ በዚህ ዓይነት ኑሮ ውስጥ ለማለፍ ለምን እንመርጣለን?"* ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም። በኃጢአት ዓለም ውስጥ ለጊዜው ደስ ብሎን መጨረሻ ላይ ለዘላለም በሲዖል ውስጥ ከምንሰቃይ፣ ለጊዜው አስቸጋሪና ፈተና በበዛበት ሕይወት ውስጥ አልፈን መጨረሻ ላይ ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም በመንግሥተ ሰማይ ደስ ብሎን መኖር ስለሚሻለን ነው ይህንን መንገድ የመረጥነው።

አንዳንዶቻችን ወደ ጌታ ስንመጣ ቀደም ሲል የነበረን ችግር ሁሉ ይቃለላል ብለን እናስብ ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ብዙ ወደ ፊት ሳንገፋ ሁኔታዎች ሁሉ እንደጠበቅናቸው ሆነው አናገኛቸውም። መንፈሳዊ ሕይወት ፈተና፣ መደናገጥና ስጋት የሞላበት ሕይወት ሆኖ እናገኘዋለን። "ታዲያ ክርስቲያን መሆንን ለምን እንመርጣለን?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እርግጥ ነው የክርስትና ሕይወት ሰላምና ደስታ ያለበት ነው። ይሁን እንጂ ከፈተና፣ ከችግር፣ ከስጋትና ከጦርነት ሁሉ ነጻ ሆነን እንኖራለን ማለት አይደለም። ክርስትናም የራሱ የሆነ ትግል አለበት። በቅድስናና እንዲሁም በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር ሆኖ እስከ መጨረሻው ለመዝለቅ፣ መስቀሉን ተሸክመን ክርስቶስን ለመከተል፣ የተሰጠ ሕይወት (commitment) መኖር አለብን። ሙሉ መሰጠት በሂደት እንጂ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተምረን የምንደርስበት የሕይወት ደረጃ አይደለም።



ኢየሱስ በአንድ ወቅት ደቀ መዛሙርቱን *"ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ አለብኝ፣ እዚያም ከሽማግሌዎች፣ ከካህናት አለቆችና ከሙሴ ሕግ መምህራን መከራ እቀበላለሁ፤ ከሞትሁም በኋላ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ" (ማቴ 16፡22)* ሲላቸው፣ "ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻ ገለል አድርጎ *ጌታ ሆይ! ኩቶ አይሆንም! ይህ ነገር በአንተ ላይ አይድረስብህ' እያለ ይከለክለው ጀመር" (ማቴ. 16፡23)።* በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ *"ከእኔ ወዲያ ሂድ ሰይጣን! አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር ስለማታስብ መሰናከል ትሆንብኛለህ" አለው (ማቴ. 16፡23)።* ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ውስጥ ገና ብዙ ማደግ እንደነበረበት እናያለን። ኢየሱስ *"ከእኔ ወዲያ ሂድ ሰይጣን!"* ያለውን ጴጥሮስ፣ በወቅቱ የነበረበትን ደካማ ሕይወት ብቻ ሳይሆን፣ በሂደት ወደፊት መሆን የሚችለውንም ስላወቀ ነው በተደጋጋሚ ይቅርታውን የሰጠው። ኢየሱስ ጴጥሮስን ያየው፣ በወቅቱ ሆኖ የተገኘውን ሳይሆን፣ ወደ ፊት በሂደት ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን "ሙሉ መሰጠትን" ነው።

## 4. ሙሉ መሰጠት፣ ሕይወትን አሳልፎ መስጠትን ይጠይቃል

ኢየሱስ *"...ስለ እኔና ስለ ወንጌል ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያድናታል" ይላል (ማር. 8፡35)።* የሰው ሕይወት አንድ ቦታ አይቆምም። ቶሎ ያልፋል። ደቂቃ ወይም ሰከንድ ባለፈ ቁጥር፣ ወደ መጨረሻው እየተጠጋን ወይም እየተቃረብን መሆናችንን እናውቃለን። ደቂቃውን፣ ሰከንዱን አጠራቅመን ማስቀመጥ፣ ጊዜው እንዳይሄድ ማድረግ አንችልም። ማድረግ የምንችለው ጊዜያችንን ዘላለማዊ በሆነው ነገር ላይ ማሳለፍ ብቻ ነው። ሰማዕት ሆኖ የሞተው አሜሪካዊው ጂም ኤሊየት

- *"ሊያጣው የማይችለውን ነገር ለማትረፍ፣ ይዞ ሊያቆየው የማይችለውን የሚሰጥ፣ ሞኝ ሰው አይደለም"* አለ።[6]

[6] Harold E. Bauman. From the Mennonite Pulpit, Herald Press, Scottdale, PA. 1965.

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ስለ እርሱና ስለ ወንጌሉ ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው መስጠት እንዳለባቸው ነግሯቸዋል። ጂምስ ካልቨርት የተባለው ሚስዮናዊ እርሱና ሌሎች ሚስዮናውያን ወደ ፊጂ ደሴቶች ለመጓዝ ወደ መርከብ ሲገቡ፣ የመርከቡ ካፒቴን የጂምስ ካልቨርትን ሀሳብ ለማስለወጥ፣

- *"እነዚያ አረመኔዎች ዘንድ ሄደህ ሕይወትህንና አብረውህ ያሉትን ሰዎች ሕይወት ታጣለህ"* አለው። ጂምስ ካልቨርትም *"ገና ወደዚህ ስፍራ ከመምጣታችን በፊት ሞተናል"* አለው።

በሕይወቱ የመጀመሪያውን ስፍራ የማይሰጥ፣ ታማኝነቱን ለክርስቶስ የማይገልጥ፣ ክርስቶስን መከተል አይችልም። የአገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር፣ ነጻነታቸውን ለማስጠበቅ፣ የውጪ ወራሪዎችን ለመከላከል ብዙዎች ሕይወታቸውን ይሰጣሉ። ኢየሱስም ከዚያ የበለጠ እንጂ ያነሰ ነገር ከእኛ ከደቀ መዛሙርቱ አይጠብቅም። ምኞታችንን፣ ክብራችንን፣ ማዕረጋችንንና ዝናችንን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ማስረከብ አለብን።

## 5. ሙሉ መስጠት ሲኖረን፣ በእርሱና በቃሉ አናፍርም

ኢየሱስ *"በእኔና በቃሉ የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል" ይላል (ማር. 8፥38)።* ለጌታው ሙሉ መሰጠት ያለው አማኝ በጌታው አያፍርም። በክርስቶስ በኩል ስላገኘው ሕይወትና ስለ ክርስቶስ ከመመስከር ወደ ኋላ አይልም። በዓለም ውስጥ ታላቁን ጌታ የሚወክል ወይም የእርሱ አምባሳደር መሆኑን ስለሚያውቅ፣ ስለ እርሱ ለመናገር አያፍርም ወይም ወደ ኋላ አይልም። በ1945 ዓ.ም. ማርቲን ኒሞለር ከጀርመን እስር ቤት ሲወጣ፣ ጋዜጠኞች ትኩስ ዜና ከእርሱ ለማግኘት ይተናነቁ ነበር። የሰሙት እነርሱ የፈለጉትንና የጠበቁትን ዓይነት ዜና ሳይሆን፣ ስለ ክርስቶስ ነበር። በተለይ አንድ ጋዜጠኛ በጣም ተበሳጭቶ፣



- *"ስድስት ዓመት ሙሉ ናዚ ወህኒ ቤት ቆይቶ የሚያወራው ስለ ክርስቶስ ብቻ መሆኑ ያስደንቃል"* አለ።

የክርስቶስ ተከታዮች ለጌታቸው የተሰጠ ሕይወት ስላላቸው በእርሱና በቃሉ የማያፍሩ አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን በማስቀደማቸው ይቅርታ መጠየቅ እንደሌለባቸውም ያውቃሉ።

## 6. ሙሉ መሰጠት ያለው ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለ ነው፥

ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ደጋግመን ገልጸናል። ክርስቶስ የመስቀል ሞት ለምን እንደሞተ እናውቃለን። የሰው ልጅ በሰማይና በምድር መካከል የተሰቀለው ኃጢአት ሠርቶ ሳይሆን፣ ስለ ሰዎች ኃጢአት ሲል እንደሆነ እናውቃለን። በመስቀሉ ላይ ተንጠልጥሎ ስቃዩ ሲበዛበት *"አምላኬ! አምላኬ ለምን ተውከኝ?"* በማለት የጣር ድምጽ ጮኸ። በመጨረሻም *"ተፈጸመ!"* በማለት ራሱን ዝቅ፣ አንገቱን ስብር አድርጎ ለእግዚአብሔር አብ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ። አዎን! የመስቀል ሞት ለክርስቶስ ምን እንደሆነ እናውቃለን። ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ብሎ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በመጠኑም ቢሆን ገብቶናል። ጳውሎስ ክርስቶስ ሲሰቀል፣ አልነበረም፤ በመስቀል ላይ አልተንጠለጠለም፤ ታዲያ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" ሲል ምን ማለቱ ነው? ወደ ፊት ስለሚቀምሰው መከራ መናገሩ ነው ወይ?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ሲል ለማለት ያህል የተናገረው አይደለም። ትልቅ ምስጢር መግለጹ ነው። ጳውሎስ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ከማለት ደረጃ የደረሰው በአንድ ቀን ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ አልነበረም። ይሄ የመስቀል መንገድ ረጅምና አስቸጋሪ በመሆኑ ብዙዎቻችንን ያስፈራናል። በተለይ በአሁኑ ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች እንደ ጳውሎስ በድፍረት *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ከማለት

ደረጃ እንደርስ ይሆን? ልባችን፣ ምላሳችን፣ እግሮቻችን፣ እጆቻችን፣ ዓይኖቻችን፣ ጆሮቻችን ገና ያልተሰቀሉ በመሆናቸው "የተሰቀልን ክርስቲያኖች" ነን ብለን መናገር ብዙዎቻችንን ያሳፍረናል። *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ"* ማለት የሚችል ክርስቲያን የሚጓጓለትና የሚመኘው ምድራዊ ነገር ስለሌለው፣ ከማንም ጋር ስለ ሥልጣን፣ ወይም ስለ ቁሳቁሳዊ ነገር ብሎ አይታገልም።

*መስቀልን ሁልጊዜ የምናያይዘው ከሞት ጋር ነው?*

> *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" የሚል ክርስቲያን ለኃጢአት፣ ለአሮጌው ሕይወቱ፣ ለሰጋዊ ፍላጎቱና እንዲሁም ምኞቱ "ሞቼአለሁ" ማለቱ ነው።*

*ራሱን ከክርስቶስ ወገን በማድረግ፣ ኃጢአተኛውን ዓለምንና በውስጧ የያዘቻቸውን ሁሉ "ከእንግዲህ በእኔ ሕይወት ስፍራ የለሽም፤ ለአንቺ ሞቻለሁ" ማለቱ ነው።*

በዓለም ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ ክርስቲያኖች እያሉ ለምንድነው ዓለምን መለወጥ ያልቻሉበት ምክንያት ምን ይሆን? ከምክንያቶቹ መካከል አንደኛውና ትልቁ፣ ክርስቲያኖች ኢየሱስን መምሰል ስላቃተን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *"የእግዚአብሔርን ልብ ማን ሊያውቀው ይችላል? ሊመክረውስ የሚችል ማን ነው? ተብሎ እንደተጻፈው ነው። እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን"* ይላል (1 ቆሮ. 2፡16)። ሕጻን ልጅ ሆኜ ነው ወላጅ አባቴ የሞተው። አባቴ ከሞተ በኋላ አባቴን የሚያውቁት ሰዎች "አንተ የወተ ልጅ ነህ?" ብለው ይጠይቁኝ ነበር። አባቴን ስለምመስል አባቴን የሚያውቁት ሁሉ በቀላሉ የወተ ልጅ መሆኔን ያውቃሉ። ከአባቴ ጋር ኖሬ የእርሱን ጠባይ እያየሁ ባላድግም፣ ከእርሱ በመወለዴ፣ መልኬ ብቻ ሳይሆን ጠባዬም እርሱን እየመሰለ መጣ። እኔ ደግሞ የራሴ ልጆች ሲኖሩኝ፣ እኔነቴን በልጆቼ ላይ ማየት ጀመርኩ። በራሴ ሕይወት ውስጥ የማየው ባሕሪ ሁሉም የምወደው አይደለም። ስለዚህ የምወደውን እኔነቴን ልጆቼ እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ። የሚወደደውን ባሕሪዬን ልጆቼ



መያዝ ሲያቅታቸው ቅር ይለኛል። ጳውሎስ *"እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን"* ሲል፣ ክርስቶስን የሚመስል ባሕሪ አለን ማለቱ ነው።

- *አንድ ሚሲዮናዊ፣ "በሕይወቴ ፈጽሞ የማልረሳው፣ በቅርብ ጊዜ የቡዳ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ወጣት፣ 'ክርስቶስን ማመን እፈልግ ነበር፣ ነገር ግን በእርሱ አምናለሁ ከሚሉት ሰዎች መካከል አንድም እርሱን የሚመስል ሰው አላገኘሁም' ያለኝ ነው" አለ።*[7]

አማኝ ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለውም፣ በሙላት ኢየሱስን መምሰል አለበት። የመንፈስ ቅዱስ አንደኛው አገልግሎቱ፣ አማኞችን ክርስቶስን እንዲመስሉ ማድረግ ነው። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች "እግዚአብሔር ሆይ! በመንፈስ ቅዱስ ሙላኝ" ብለው ሲጸልዩ እንሰማለን። ለምን ይሆን መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላባቸው የሚጸልዩት? ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች *"የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ! ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪሳል ድረስ ስለ እናንተ እንደገና ምጥ ይዞኛል"* ሲል ጻፈላቸው (ገላት. 4፡19)። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ በመንፈስ ቅዱስ ቢሞላን ክርስቶስ በውስጣችን መኖሩን እርግጠኞች እንሆን ይሆን? ጳውሎስ *"እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም። ነገር ግን ክርስቶስ በውስጣችሁ ካለ፣ ሰውነታችሁ ከኃጢአት የተነሣ የሞተ ቢሆንም፣ መንፈሳችሁ ከጽድቅ የተነሣ ሕያው ነው"* ይላል (ሮሜ 8፡9-10)።

## 7. ሙሉ መሰጠት እስከ ሞት ድረስ ነው

ሞት ለእኔና ለእናንተ ይህን ያህል አዲስ ነገር አይደለም። ከተወለድንበትና ነፍስ ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ሞት መስማት

---

[7] Unknown Christian. How to Live the Victories Life, Zondervan Publishing House, Gran Rapids, Michigan.

ጆሯችን ሰልችቶታል። በቅርብ የምናውቃቸው፥ ከጎረቤታችን፣ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ሰዎች ሲሞቱ፥ እንዲሁም እናት፥ አባት፥ እህት፥ ወንድም ወይም የቅርብ ዘመዶች በሞት ከእኛ ተለይተውን ሲሄዱ አይተናል። በዚህ ምክንያት ልባችን በሀዘን ተሰብሮ ብዙ ዕንባ ያፈሰስንባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው። ለዚህ ነው "ሞት ለብዙዎቻችን እንግዳ ነገር አይደለም" ያልነው። በታሪክም ቢሆን የታላላቅ ሰዎችን አሟሟት እንብበናል። ለመፈጸም በተነሱበት ትልቅ ዓላማ ምክንያት ሕይወታቸውን በድፍረትና በቆራጥነት የሰጡ ወይም የሞቱ እንዳሉ እናውቃለን። ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፥ ለጥቁሮች እኩልነት ሲታገል ሕይወቱን እንዳጣ፥ እንዲሁም ማህተመ ጋንዲ ለሕንድ ነጻነት ሲታገል በሚጠሉት ሰዎች ጥይት ተመትቶ ሕይወቱ እንዳለፈ፥ እንዲሁም የእኛው የጥንት አባቶቻችን ለአገራቸው ነጻነት፥ አገራቸውን በጠላት ላለማስደፈር፥ የአገራቸውን ድንበር ላለማስነካት፥ ደማቸው እንደፈሰሰ፥ አጥንታቸው እንደተከሰከሰ እናውቃለን። ድፍረታቸውንና ቆራጥነታቸውን እናደንቃለን። ይሁን እንጂ፥ የከፈሉት መስዋዕት ከእኛ ደህንነት ጋር የተያያዘ አይደለም። ለደህንነታችን ሲል የመስቀል ሞት በመሞት ዕዳችንን የከፈለልን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ስለ ኢየሱስ ልደት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው በሁለቱ ወንጌሎች ብቻ ሲሆን፥ ስለ መስቀል ሞቱና ትንሳኤው ግን አራቱም ወንጌሎች ላይ፥ ይኸውም፥ በማቴዎስ፥ በማርቆስ፥ በሉቃስና በዮሐንስ ወንጌል ላይ ተጽፏል። ወደ ሞት እንዴት እንደሄደ፥ በምን ዓይነት መከራና ስቃይ ውስጥ እንዳለፈ ጥቃቅኑ ታሪክ ሁሉ ተጽፏል። ውስን በሆነው በእኔና በእናንተ አዕምሮ የሚመላለሱ ብዙ የማይገቡን፥ ጥያቄ የሆኑብን ብዙ ነገሮች አሉ። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው፥ ፍጹምና እንከን የሌለበት ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ የፈጠረው አምላክ በሰው እጅ እንዴት ይሞቷል? እውነተኛ የሆነው "መሲህ"፥ ራሱ አምላክ (እግዚአብሔር) የሆነው በሰው እጅ እንዴት መራራ የሆነ የመስቀል ሞት ይሞታል? ሰውን ለማዳን እግዚአብሔር የራሱን ልጅ መስዋዕት በማድረግ ፈንታ ሌላ መንገድ ለምን አልተ



ጠቀመም? መሞቱ አስፈላጊ ከሆነ፥ አሰቃቂና ጭካኔ በሞላበት የመስቀል ሞት ለምን ይሞታል? ሁሉን ማድረግ የሚችለው ጌታ "ደም ሳይፈስ ስርየት የለም" ለምን አለ? ወገኖቼ! ምስጢሩ ይሄ ነው። እግዚአብሔር በእጁ ለሠራው ሰው ያለውን ከፍተኛ ፍቅር መግለጽ የሚችለው ትልቅ ስጦታ በመስጠት እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። እንደ ዓይኑ ብሌን የሚወደውን ልጁን አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ፥ ሌላ የፍቅር መግለጫ ከየት ይገኛል? ለዚህ ነው በእኛ ምትክ እንዲሞት እግዚአብሔር ልጁን የሰጠን።

በስምንተኛው የክርስቲያኖች ስደት ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች፣ ለሰው አዕምሮ የሚዘገንኑ ጭካኔዎችን በክርስቲያኖች ላይ ይፈጽሙ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ለጌታቸው በነበራቸው ሙሉ መስጠት ክርስቲያኖች የሚደርስባቸው መከራ የተቀበሉት በሙሉ ጽናት ነው፥

- *ኡቲካ በሚባለው ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ሦስት መቶ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ተከታዮች በመሆናቸው ተይዘው፣ ከአንድ ትልቅ የሸክላ (ጡብ) መጥበሻ ከሆነው የእሳት ጉድጓድ ዙሪያ እንዲቆሙ አደረጓቸው። ለጣዖታቸው መስዋዕት ለማቅረብ ዕጣንና ከሰል አዘጋጁ፤ በጉድጓዱ ዙሪያ ያቆሟቸውን 3 መቶ ክርስቲያኖች "ጁፒተር" ለተባለው ጣዖታቸው የዕጣን መስዋዕት እንዲያቀርቡ አዘዟቸው። "እምቢ!" ቢሉ ግን እዚያ ትልቅ የእሳት ጉድጓድ ውስጥ እንደሚከተቱ ተነገራቸው። የሚያስደንቀው አንዳቸውም ሳያወላውሉ፣ ሁሉም "ለጣዖታችሁ መስዋዕት አናቀርብም" በማለታቸው፣ ከእሳት ጉድጓድ ውስጥ ሳይሞቱ ከነሕይወታቸው ተጥለው በእሳት ተቃጥለው ሞቱ። ይህን ሲያደርጉ፣ እያዘኑ፣ እያለቀሱ፣ እየተጸጸቱ ሳይሆን፣ ጌታቸውን እያከበሩና እያመሰገኑ ነበር።*

በዚህ ዓይነት ክርስትና ርካሽ የሆነ ሃይማኖት ሳይሆን፣ ዋጋ የሚያስከፍል እንደሆነ እንረዳለን። ምናልባት የእኔና የእናንተ እምነት

በዚህ ዓይነት አይፈተንም ይሆናል። እነርሱ የተሸከሙትን ዓይነት ትልቅ መስቀል አንሸከምም ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ሁላችንም የራሳችን የሆነ፣ አቅማችንን መዝኖ የሚያውቀው ጌታ በሚፈቅደው መጠን የተሰጠንን የራሳችንን መስቀል ለመሸከም ዝግጁዎች መሆን አለብን። በቅድስናና በመታዘዝ ሕይወት ውስጥ ሁልጊዜ መስቀል አለ። በክርስትና ሕይወታችሁ በጣም ተመችቷችሁ አንድም ጊዜ መስቀል መሸከማችሁ ካልተሰማችሁ፣ እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆናችሁ ያጠራጥራልና ራሳችሁን መርምሩ።

በተለያዩ የሮማ ግዛት ውስጥ፣ በተለያዩ የሮማ ንጉሠ ነገሥት አነሳሽነት የተካሄዱት አስር ታላላቅ የክርስቲያኖች ስደቶች ውስጥ፣ *ዘጠነኛው የተፈጸመው፣ ከ270 እስከ 275 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።* በዚህ ዘመን በሮም የነገሠው ንጉሥ፣ በጭካኔው ተወዳዳሪ *ያልነበረው አውሮሊያን* የተባለው ንጉሥ ነበር። ግዛቱን አስፋፍቶ፣ እንግሊዝን፣ ጎልን (ፈረንሳይን)፣ ስፔይን፣ ሲሪያንና ግብጽን ይገዛ ነበር።

በእነዚህ አምስት ዓመታት ውስጥ መጀመሪያ በሰማዕትነት ሕይወቱ ያለፈው ፍሊክስ የተባለው ሮም ውስጥ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው ነው። ይኸው የቤተ ክርስቲያን መሪ በ274 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) ራሱ በሰይፍ ታርዶ ሞተ። በዚህ በስደት ዘመን ክርስቲያኖችን ለሕይወታቸው ሳይሳሱ በእምነታቸው ጸንተው በመቆማቸው ወደ ክርስቶስ እምነት ስቦ የሚያመጣው፣ ድሆችንና ምስኪኖችን ብቻ ሳይሆን፣ በጣም የታወቁ ሀብታሞችንም ጭምር ነበር።

- *ከሮም 30 ማይልስ ያህል ራቅ ብሎ በሚገኝ አንድ ከተማ ወስጥ በጣም ሀብታም የነበረ፣ አጋፒተስ የተባለው ሰው፣ ያለውን ሀብትና ንብረት በሙሉ ሸጦ ለድሆች በማከፋፈሉ፣ ክርስቲያን ሳይሆን አይቀርም በማለት አንገቱ በሰይፍ ተቆርጦ ሞተ። ብዙም ሳይቆይ አውሮሊያን በራሱ ወታደሮች ተገደለ። ከእርሱ በኋላ የተለያዩ ንጉሦች አገሪቱን ተቆጣጠሯት። በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከስደቷ ለጥቂትም ጊዜ ቢሆን "እፎይ!" አለች።*



በተለያዩ የሮማ ግዛቶች ውስጥ፣ በተለያዩ የሮማ ንጉሠ ነገሥት አነሳሽነት የተካሄዱት አስር ታላላቅ የክርስቲያኖች ስደቶች ውስጥ፣ አስረኛውና የመጨረሻው የተፈጸመው፣ ከ284 እስከ 305 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በዚህ ዘመን ስደቱን ያንቀሳቅስ የነበረው ዲዮክሊቲያን የተባለው ንጉሥ ነበር። ይሄኛው የስደት ዘመን በእስከ ፊነቱ፣ ከዚህ በፊት የነበሩት ስደቶች ለዚህኛው ስደት መንደርደሪያ ናቸው ቢባል ትክክል ነው። ይኼኛው ከምንጊዜም የበለጠ በጣም የከፋ ስደት በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመበት ጊዜ ነው። *የዲዮክሊቲያን ዋና* ዓላማና ትልቁ ፍላጎት ቀደም ሲል ሮም ግዛት ውስጥ የነበረውን የጣዖት አምልኮት መልሶ ለማምጣት ነበር። ዲዮክሊቲያን በግዛቱ መጀመሪያ ላይ ለክርስቲያኖች ጥሩ አመለካከት ያለው ይመስል ነበር። ይሁን እንጂ፣ ብዙም ሳይቆይ ክርስቲያኖችን ማሰቃየት ጀመረ።

- *ሮም ከተማ ውስጥ ማርከስና ማርሲሊያነስ የተባሉ መንትዮች "ክርስቲያኖች ናቸው" ተብለው በአስተማሪያቸው አማካኝነት ተከሰው ቀረቡ። ወላጆቻቸው ጣዖት አምላኪዎች እንጂ፣ አማኞች አልነበሩም። እምነታቸውን ለማስለወጥና ጣዖት አምላኪዎች እንዲሆኑ ሲከራከሯቸው፣ ቤተሰቦቻቸው ሁሉ ወደ ክርስትና ሕይወት መምጣት ቻሉ። በእምነታቸው ምክንያት የሞት ፍርድ ከፈረዱባቸው በኋላ፣ እጆቻቸውን አስረው ከፍ አድርገው ቋሚ እንጨት ላይ አንጠለጠሏቸው። እንዲሁም እግሮቻቸውን ከቋሚ እንጨት ላይ በሚስማር አጣበቋቸው። በዚህ ዓይነት አንድ ቀንና አንድ ሌሊት ሙሉ ሰቅለው አቆዩዋቸው። በስቅላት ላይ እያሉ ጦር ወርውረው ይወጓቸው ነበር።*

ይህንን በመሰለ ስቃይና መከራ ውስጥ ቢያልፉም እነዚህ ሁለት ወጣቶች በእምነታቸው ጽኑ ሆነው በመቆማቸው፣

- *ይህንን ያየች የወህኒ ቤቱ አሰቃ ሚስት ልያ ተንክቶ ጊዜው አደገኛ መሆኑን ብታውቅም፣ ክርስቶስን ተቀብላ ክርስቲያን መሆኗን በድፍረት አወጀች። እርሷም ወዲያው ተይዛ ዛፍ ላይ*

*ካንጠለጠሏት በኋላ ከሥሯ እሳት አነደዱባት፤ ከእሳት የተረፈውን ሰውነቷን በቅርብ ከነበረው ወንዝ ውስጥ ወረወሩት።*

- *በ287 ዓ.ም. ሮም ውስጥ ኪንቲንና ሉሲያን የተባሉ ክርስቲያኖች፣ በዚህ ክርስቲያኖች እየታደኑ በሚሰቃዩበት ዘመን፣ ወንጌልን ለመስበክ ቆርጠው ተነሱ። እነዚህ ሥጋውያን በሆኑ ሰዎች ዕብዶች ቢያስመስላቸውም፣ የወንጌሉ ባለቤት ግን ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣቸዋል። ለጥቂት ጊዜ አንድ ላይ ሆነው ወንጌል ሰበኩ። ትንሽ ቆይተው ግን ሉሲያን ሌላ ከተማ ሄዶ ሲሰብክ ተይዞ ወዲያው ተገደለ።*
- *ኪንቲን ደግሞ ወደ ፒካርዲ ከተማ ሄዶ በኃይልና በሥልጣን ወንጌልን በድፍረትና በቆራጥነት ይሰብክ ነበር። ብዙም ሳይቆይ እርሱም ተይዞ ክርስቲያን በመሆኑ በሞት እንዲቀጣ ተፈረደበት። አሟሟቱ በጣም የሚዘገንን ነበር። እጆቹንና እግሮቹን በገመድ ጥፍር አድርገው ካሠሩ በኋላ፣ ገመዱን በሚሽከረከር ክብ ብረት ላይ በማሳለፍ፣ የአጥንቶቹ መገጣጠሚያዎቹ እስኪላቀቁ ድረስ በግራና በቀኝ ጎተቱት፤ ቀጥሎ በሽቦ ገረፉት፤ የፈላ ዘይት በላዩ ላይ አፈሰሱበት፤ ብብቱን በእሳት ለበለቡት። በዚህ ዓይነት እስኪደክማቸው ድረስ ካሰቃዩት በኋላ እስር ቤት ጥለውት በቁስሉ ምክንያት ከጥቂት ቀናት በኋላ ሞተ። በመጨረሻ ትልቅ ድንጋይ በላዩ ላይ አሥረው ወንዝ ውስጥ ወረወሩት።*

በዚህኛው የስደት ዘመን ኒኮሚዲያ በሚባለው በሮማ ግዛት ውስጥ ክርስቲያኖች ሁሉ ታድነው ከተያዙ በኋላ፣ ወህኒ ቤት ተጣሉ። ክርስቲያኖች ከፍተኛ ቅጣት እንዲያገኙ ብሎ ጋላሪየስ ማንም ሳያየው ተደብቆ ቤተ መንግሥቱን በእሳት ካቃጠለ በኋላ፣ ይህን ወንጀል የፈጸሙት ክርስቲያኖች ናቸው ብሎ በሀሰት ከሰሳቸው። ከዚህ በኋላ ትልቅ ስደት በክርስቲያኖች ላይ ተቀሰቀሰ። ይህ ስደት ለአስር ዓመት ያህል ቆየ። በዚህ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ በሺ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በእምነታ



ቸው ምክንያት በጭካኔ ተገደሉ። ሴት፣ ወንድ፣ ልጅ፣ ሽማግሌ ሳይሉ ሁሉንም ፈጁቸው። በዚያን ዘመን "ክርስቲያን" የሚል ስም በጣም የተጠላ ስለነበረ፣ ክርስቲያን መሆናቸው ከታወቀ፣ ምንም ዓይነት ምሕረት አይደረግላቸውም ነበር። ለሚደርሰው የተፈጥሮ አደጋ ሁሉ ምክንያት የሚያደርጉት ክርስቲያኖችን ነበር።

ክርስቲያኖችን የሚያሰቃዩበት የጭካኔ ሥራቸው ከሰው አዕምሮ በላይ ነበር። የብዙ ክርስቲያኖች ቤት በእሳት ይቃጠል ነበር። አምልጠው እንዳይወጡ በሩን በላያቸው ላይ ከቆለፉ በኋላ፣ ሕጻናትና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ፣ ቤታቸው ላይ እሳት በመለኮስ ከነቤታቸው ያቃጥሏቸው ነበር። ከባድ ድንጋይ አንገታቸው ላይ በገመድ አንጠልጥለው፣ ክርስቲያኖቹን በአንድነት በገመድ አስረው ባሕር ውስጥ ይከቷቸው ነበር። ግርፋትን፣ እሳትን፣ ሰይፍን፣ መስቀልን፣ መርዝንና፣ ረሀብን ክርስቲያኖችን በብዛት ገድሎ ለመጨረስ ይጠቀሙበት ነበር። ፊርጊያ ተብሎ በሚጠራው ከተማ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ክርስቲያኖች ስለነበሩ፣ ከተማዋም፣ ሕዝቡም በአንድ ጊዜ በእሳት እንዲወድሙ ተደረገ።

በመጨረሻው ክርስቲያኖችን መግደል ሲሰለቻቸው የብዙ ጠቅላይ ግዛት አገረ ገዢዎች ለንጉሠ ነገሥቱ በሮማ ግዛት ውስጥ ክርስቲያኖችን በዚህ ዓይነት መግደሉ ትክክል አይደለም በማለት አቤቱታ አቀረቡ። በዚህ ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች ከሞት አመለጡ። ይሁን እንጂ፣ በሚዘገንን ሁኔታ አካላዊ ጉድለት ያደርሱባቸው ነበር።

- *የብዙዎቹን ጆሮ ይቆርጡ፣ አፍንጫቸውን ይሰነጥቁ፣ ሁለቱን ወይም አንዱን ዓይኖቻቸውን ያወጡ ነበር። አጥንታቸውን ከሶኬቱ (ከመገናኛው) ማውጣት፣ የተለያየ የሰውነታቸውን ክፍል በእሳት ማቃጠል፣ ክርስቲያኖች ተለይተው የሚታወቁበት ምልክታቸው እንዲሆን አደረጉ። ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው የስደት ታሪኮች፣ ጥቂቶችን ምሳሌ እንዲሆኑን አቀረብናቸው እንጂ፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ክርስቲ*

ያኖች ምሕረት በሌለው፣ በጣም በሚዘገንን ሁኔታ አሰቃይ ተው እንደገደሏቸው ታሪክ ይመሰክራል።

- ሰባስቲያን የተባለ ክርስቲያን ሮም ከተማ ውስጥ የንጉሠ ነገሥቱ የዘብ ጠባቂ ነበር። ክርስቲያኖች በሚሰደዱበት ወቅት እምነቱን እንዲተው፣ ክርስቶስን ትቶ ጣዖትን እንዲያመልክ ተጠይቆ "እምቢ!" በማለቱ ንጉሡ ዲዮክልቲያን በቀስት ተወግቶ እንዲሞት ፈረደበት። ንጉሡ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እስኪሞት ድረስ በቀስት ተወጋ። ክርስቲያኖች ሬሳውን ወስደው እንዲቀብሩ ፈቃድ ጠይቀው ከወደቀበት አንስተው ወሰዱት። ነገር ግን ገና ያልሞተ መሆኑን ምልክት ሲያዩ፣ አንድ ስውር ቦታ ይዘውት ሄዱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከደረሰበት ጉዳት ድኖ በአዲስ ሕይወት መኖር ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀን ንጉሡ ታጅቦ ሲሄድ መንገድ ላይ አግኝቶት ክርስቲያኖችን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በማሳደዱ ፊት ለፊት በድፍረት ወቀሰው። ንጉሡም ሞቷል ብሎ ያሰበው ሰባስቲያንን በሕይወት ማየቱ አስደንቆት ወዲያውኑ እንዲያዝ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ተይዞ ከታሰረ በኋላ በዱላ ቀጥቅጠው ገደሉት። በዚህ ጊዜ ግን ሬሳውን ክርስቲያኖች እንዳያገኙት ቆሻሻ የሚተላለፍበት ቱቦ ውስጥ ጨመሩት። በዚህ ዓይነት የተጣለውን ሬሳ አንዲት ክርስቲያን እህት አግኝታ፣ ከዚያ አውጥታ፣ በካታኮምቡ ውስጥ ከሌሎች ሰማዕታት ሬሳ ጋር እንዲቀበር አደረገች።
- ቲሞቲ (ጢሞቲዎስ) የሮም ጠቅላይ ግዛት በነበረው በሞሪታኒያ ውስጥ በምትገኘዋ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዲያቆን ሆኖ የሚያገለግል ክርስቲያን ነበር። ሞራ የምትባለውን ክርስቲያን እህት ባገባ በጥቂት ሳምንት ውስጥ በክርስቲያኖች ላይ የተቀሰቀሰው ስደት ጀምሮ ቲሞቲ ክርስቲያን በመሆኑ ተይዞ ወህኒ ቤት ገባ። የሞሪታኒያ አገረ ገዢ የነበረው አርያኑስ የቤተ ክርስቲያኒቱን



ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠባቂ መሆኑን ስላወቀ፣ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲቃጠሉ ሰብስቦ እንዲያመጣ ትዕዛዝ ሰጠው። ቲሞቲ ለተሰጠው ትዕዛዝ ምላሽ ሲሰጥ፣ "የእግዚአብሔር ቃል በእሳት እንዲቃጠል ከምሰጥህ፣ ልጅ ቢኖረኝ፣ ልጄን እንድትገድለው መስጠት ይቀለኝ ነበር" በማለት ትዕዛዙን የማይቀበል መሆኑን ገለጸ። ይሄ መልስ እጅግ በጣም ስላስቆጣው፣ ቲሞቲ ተይዞ በእሳት በጋለ ብረት ወግተው ሁለቱን ዓይኖቹን እንዲያወጡ አርያኑስ ትዕዛዝ ሰጠ። በትዕዛዙ መሠረት ተፈጸመበት ዓይነ ስውር መሆኑን ሲያይ፣ "ዐይን ኖሮህ ማንበብ ስለማትችል፣ ከእንግዲህ በኋላ መጻሕፍቹ ዋጋ የላቸውም" አለው።

- ይሄም ሆኖ የቲሞቲ ቆራጥነቱና ድፍረቱ እጅግ በጣም ስላስቆጣው ተዘቅዝቆ እግሩ በገመድ እንዲንጠለጠል፣ ወደታች እንዲሟነው አንገቱ ላይ ክብደት ያለው ብረት እንዲታሠር፣ መናገር እንዳይችል አፉ ውስጥ ጨርቅ እንዲጠቀጠቅ ትዕዛዝ ሰጠ። ይህን ያደረገው መከራውና ጭንቀቱ ሲበዛበት ተሸንፎ እምነቱን ይተዋል፤ ጌታውን ይክዳል ብሎ በማሰብ ነበር። በቅርቡ ያገባት ሚስቱ ሞራ ይህን ሁሉ መከራ ሲቀበል ቆማ እንድታይ ተገዳ ነበር። ይህን ዓይነት ስቃይ ቆማ ከምታይ፣ ለእርሷ ሲል እምነቱን እንዲተው ለመነችው። እርሷ ላቀረበችለት ልመና መልስ ይሰጣል ብለው በማሰብ አፉ ውስጥ የተጠቀጠቀውን ጨርቅ አስወጡለት። ይሁን እንጂ፣ ከሀሳቧ ጋር በመስማማት ፋንታ፣ ይህን በማለቷ ትልቅ ስህተት እየሠራች መሆኑን ነገራት። እንዲሁም፣ ለክርስቶስና ለያዘው እምነት እስከ ሞት ድረስ ጸንቶ የሚቆም መሆኑን ግልጽ አድርጎ ነገራት። ይሄም ጥሩ ውጤት አስገኘ። ሚስቱ ሞራ የባሏን ድፍረትና ቆራጥነት አይታ በማወላወል ፈንታ፣ ከእርሱ ጋር በሞት አማካኝነት ወደ ሰማያዊ ክብር ለመሄድ ውሳኔዋን ገለጸች። እርሷንም፣

*አገረ ገዢው አርያንስ ሀሳቧን ለማስለወጥ ብሎ በጣም እንዲያሰቃዩዋት ትዕዛዝ ሰጠ። ማሰቃየት የሚችሉትን ያህል ካሰቃዩዋቸው በኋላ አሳባቸውን ማስለወጥ እንደማይችሉ ሲረዱ፣ ሁለቱንም ጎን ለጎን ሰቅለው ገደሏቸው።*

እነዚህ የክርስቶስ ጠላቶች ትልቁ ዓላማቸው ቤተ ክርስቲያንን ከዓለም ጠርጎ ለማጥፋት ነበር። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ስደቶችን በክርስቲያኖች ላይ ቢያነሳሱም ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፏት አልቻሉም። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እርሱ እንደ ገና መጥቶ እስኪወስዳት ድረስ በዓለም ውስጥ ጸንታ ትቆማለች። እግዚአብሔር የመከራን፣ የመስቀልን መንገድ ለምን እንደመረጠ፣ ውስን አዕምሮ ስላለን፣ ወይም ያለን መረዳት ትንሽ በመሆኑ፣ እኔና እናንተ ሙሉ በሙሉ ሊገባን አይችልም። ስለዚህ "እግዚአብሔር ሆይ! ክርስቲያኖች በዚህ ዓይነት እንዲሰቃዩ ለምን ትፈቅዳለህ? ለምን ዝም ትላለህ? ለምን አትበቀልላቸውም?" ብለን ብንጠይቅ፣ መልስ አናገኝም። በዚህ ዓይነት መንገድ እግዚአብሔርን የሞገተው ኢዮብ እንኳን ለጥያቄው የሚፈልገውን ዓይነት መልስ አላገኘም። ቢሆንም ቅሬታ በማሰማት ፈንታ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ *"እኔ እስከ አሁን ስለ አንተ የማውቀው ሰዎች የነገሩኝን በመስማት ብቻ ነበር፤ አሁን ግን በዐይኖቼ አየሁህ። ስለዚህ የተናገርሁት ነገር ሁሉ እኔኑ ራሴን አሳፍሮኛል፤ ከዚህም የተነሣ በዐመድና በትቢያ ላይ ተቀምጬ ንስሓ እገባለሁ"* አለ (ኢዮብ 42፥5-6)።

እኛም በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ እንድንጠይቅ የምፈልገው ጥያቄ "እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ለምን ዝም አለ?" የሚለውን ሳይሆን፣ እነዚህ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው እንዲሰጡ ይህን የመሰለ ድፍረትና ቆራጥነትን ማግኘት የቻሉት እንዴት ነው? ሞትን፣ መከራንና ስቃይን እንዳይፈሩ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድነው? የሚለውን ነው።

የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ቆርጠው በተነሱ የወንጌል ጠላቶች እጅ ተሰቃይተው ከሞቱት ውስጥ አንደኛው፣ ሐዋርያው ጳው



ሎስ ነው። የመጨረሻውን የሞት ጽዋ ከመቅመሱ በፊት የተናገረውን ንግግር እንስማ። *"እኔ ግን መሥዋዕት ለመሆን ተቃርቤአለሁ፤ ከዚህ ዓለም ተለይቼ የምሄድበት ጊዜም ደርሶአል፤ ጦርነትን በመልካም ተዋግቻለሁ፤ ሩጫን እስከ መጨረሻው ሮጫለሁ፤ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል፤ ይህንንም ለእኔ ብቻ ሳይሆን የእርሱን መገለጥ ለሚወድድ ሁሉ ይሰጣቸዋል"* አለ (2 ጢሞ. 4፥6-8)። ቀደም ሲል ራሱ ከአሳዳጆች አንዱ የነበረው ጳውሎስ፣ በደማስቆስ መንገድ ጌታ ካገኘው ጊዜ ጀምሮ፣ ያሳድደው ለነበረው ወንጌልና ጌታ መሰደድ እንዳለበት ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም።

መረዳት ብቻ ሳይሆን የተመደበለትን የመከራ ጽዋ እንደሚገባው ቀምሷል። ማንም ጳውሎስ የቀመሰውን ዓይነት የመከራ ጸዋ የቀመሰ የለም። ስላለፈበት የመከራ ሕይወት ሲናገር፣ *"...ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬአለሁ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ። አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ የወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ በጉዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቁትነት ተቆራምጃለሁ። ሌላውን ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው"* ይላል (2 ቆሮ. 11፥23-28)።

## 8. መስቀል የሙሉ መሰጠት ምልክት ነው

የክርስቶስ ለመሆናችን ተለይተን የምንታወቅበት ምልክታችን ምን ይሆን? የተትረፈረፈ የብልጽግና ሕይወት፣ ምቾት የበዛበት ኑሮ በመኖ

ራችን ይሆን? የክርስትና ሕይወት ምልክት ይሄ እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ (ለማሳየት) የሚሞክሩ አስተማሪዎች በአሁኑ ጊዜ፣ ከምንጊዜውም የበለጠ የበዙበት ዘመን ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ከሕይወታቸውና ከቤተ ክርስቲያናቸው መስቀልን ጨርሶ ለማጥፋት የሚሞክሩ ናቸው። የመስቀልን ሕይወት መለያ ምልክት አድርገው ከመቀበል ይልቅ፣ ብልጽግናንና ምቾትን የጥሩ ክርስቲያን ምልክት አድርገው ለመሳል የሚሞክሩ ናቸው። ያም ሆነ ይህ፣ ማንም ሊለውጠው የማይችለው አንድ መሠረታዊ የሆነ እውነት ማወቅ አለብን። ይኸውም፥

- *በጌታ ውስጥ እስከሆንን ድረስ፣ በቅድስና ሕይወታችንን ለመምራት ቁርጥ ውሳኔ እስካደረግን ድረስ፣ ከእርሱ ጋር በቅርብ እስከ ተራመድን ድረስ፣ እርሱ የቀመሰውን መከራና ስቃይ፣ እርሱ የጠጣውን መራራ ጽዋ፣ እርሱ የተሸከመውን ከባድ መስቀል መሸከም እንዳለብን ነው።*

ጠላታችን ዲያብሎስ ምስክርነታችን ተቀባይነት እንዳይኖረው፣ ያለንን ደስታ ገፍፎ ሕይወታችን በምሬት የተሞላ እንዲሆን ለማድረግ ምን ጊዜም ቢሆን የማይተኛልን መሆኑን ማወቅ አለብን። ይሄ የእኛን በጎነት የማይፈልገው ጠላት በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሞተውን፣ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ውስጥ ያስገባውን ሰው ለመታገል ጊዜውን እንደ ማያባክን እንወቅ። እንግዲህ እኔና እናንተ በኑሯችን ትግል ሲበዛብን፣ የክርስትና ሕይወት መኖር በጣም ከባድ፣ መንገዱም ጠባብ ሲሆንብን፣ በመከራ ስንታሽ ልባችን አይረበሽ፤ ቶሎ ተስፋ አንቁረጥ። የጌታ ለመሆናችን ምልክት (መለያ) መስቀላችን እንደ ሆነ አውቀን ደስ ይበለን። የአማኞች መለያችን፣ የመስቀል ሕይወት መኖራችን ስለሆነ፣ ምን ጊዜም ቢሆን በመስቀል ሕይወት አንፈር። ኢየሱስ ***"መስቀሉን የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም"*** በማለት በግልጽ ነግሮናል።

ክርስቶስን የምንመስለው ከእርሱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ሲኖረን፣ እንዲሁም ሕይወታችን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ የተሰጠ ሲሆን ነው።



እርሱን የምንመስለው እርሱ የተሸከመውን መስቀል በመሸከም ነው። ጳውሎስ *"...የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ" (ፊልጵ. 3፥11)* ያለው ለዚህ ነው። እርሱን መምሰል የምንችለው የተሰጠ ሕይወት ሲኖር ብቻ ነው። *የሙሉ መሰጠት (commitment)* ፍሬ ነገር ያለው በፍቅር ላይ ነው። ከወደድነው ራሳችንን ሙሉ በሙሉ መስጠት ወይም ማስረከብ ይህን ያህል አይከብደንም። ሁለት ወጣቶች ትዳር ለመመሥረት ወይም ባልና ሚስት ሆነው ለመኖር በካህኑ ፊት ቀርበው ቃል ኪዳን ሲለዋወጡ፣ *"ከዛሬ ጀምሮ ሕይወቴ ለአንተ/ለአንቺ የተሰጠ ነው። በሕይወቴ አንደኛ አንተ ነህ/አንቺ ነሽ፣ ከሞት በስተቀር የሚለየኝ ነገር የለም"* ማለታቸው ነው። ሙሉ መስጠት በሂደት እየተፈተነ ይመጣል። አንዳቸው ለሌላው እውነተኛ የሆነ መሰጠት ከሌለው ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲመጣ፣ የሚነፋፈቁ ፍቅረኞች ሊሰለቻቹ ይችላሉ።

ለእግዚአብሔርም ሙሉ መሰጠት ከሌለን፣ መስቀሉን ተሸክመን መሄድ አንችልም። ለእርሱ ሙሉ መሰጠት ካለን የሚያስከፍለንን ማንኛውንም ዓይነት ዋጋ ለመክፈል፣ እንዲሁም የመስቀሉን መራራ ጽዋ ለመጠጣት ወደ ኋላ አንልም። *"እግዚአብሔር ሆይ! ነፍሴ እስኪወጣ ድረስ እወድሃለሁ"* ማለት ብቻ በቂ አይደለም። መውደዳችን በተግባር መገለጽ አለበት። ኢየሱስ ይህንን እውነት ሲገልጽ፣

*"የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ" (ዮሐ. 14፥15)፣*

*"ትዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያውለው ይወደኛል" (ዮሐ. 14፥21)፣*

*"የሚወደኝ ቃሌን ይጠብቃል" (ዮሐ. 14፥25)* ይላል።

ኢየሱስ የንጉሦች ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ፣ ዩኒቨርስን የሚቆጣጠር እያንዳንዱ ሰው እርሱን እንዲከተለው ያዛል እንጂ ማንንም ተከተሉኝ ብሎ አይለምንም፤ ወይም ምርጫ አይሰጥም። ስለዚህ ትዕዛዙ የሚያባብል ሳይሆን ፊት ለፊትና ቀጥተኛ ነው። ሌሎች እንዲከተሉት ብሎ የሚያስተላልፈውን ትምህርት ደረጃውን ዝቅ፣ ጠባቡን መንገድ ሰፊ እያ

*ድርግም። "የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፤ እኔም ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝንም አባቴ ያከብረዋል" ይላል (ዮሐ. 12፥26)።*

*"ተከተለኝ"* የሚለውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ቀላል አይደለም። ለራስ መሞት ወይም ራስን መካድ ይጠይቃል። ክርስቶስ በሙሉ መሰጠት እንድናገለግለው ወይም እንድንከተለው ይፈልጋል እንጂ፣ ምክንያት እንድንሰጠው አይፈልግም። ለዚህ ነው ኢየሱስ፥

- *"ዕርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም" ያለው (ሉቃ. 9፥62)።*
- ኢየሱስ ሲጠራው *"መጀመሪያ አባቴን ልቅበር"* ያለውን ሰው፣ *"ሙታን ሙታናቸውን ይቅበሩ፤ አንተ ተከተለኝ" አለው (ማቴ. 8፥22)።*

ኢየሱስ *"ተከተሉኝ"* ብሎ የጠራቸው ሰዎች ትዕዛዙን ተቀብለው ሲከተሉት፣ ማንንም ሲያመሰግን አንሰማም። ኢየሱስ መጀመሪያ ላይ ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲመለምል፣ የጠራቸው ሁሉ፣ የዕለት ተግባራቸውን ጥለው ሙሉ በሙሉ ተከተሉት። ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በጀልባ ውስጥ ሆነው መረባቸውን ያበጁ ነበር። ኢየሱስ ሲጠራቸው፣ *"ወዲያውኑ ጀልባቸውንም ሆነ አባታቸውን ትተው ተከተሉት" (ማቴ. 4፥22)። ለራስ መሞት፣ ወይም "ሙሉ መሰጠት" የሌለበት ክርስትና ተጨባጭነት የሌለው ፍልስፍና ብቻ፣ ወይም ክርስቶስ የሌለበት ሐይማኖት ይሆናል።*

ሐዋርያው ጳውሎስ *"ለራሱ የሞተ"* መሆኑን ሲገልጽ፣ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው" ይላል (ገላ. 2፥20-21)።* እዚህ ላይ የሚያስደንቀውና እርስ በርሱ የሚቃረን የሚመስለው ነገር፣ ለራስ መሞት ትልቅ ነጻነትን የሚሰጥ መሆኑ ነው። "የሞተ ሰው" ስለ መብቱ አይጨነቅም፤ ወይም ሰዎች "ምን ይሉኝ ይሆን?" ብሎ አይሰጋም። ከተሰቀለው ክርስቶስ ጋር ሲገናኝ፣ በዓለም ውስጥ እንደ ትልቅ ነገር የሚፈለጉ ነገሮች ይኸውም ሀብት፣ ብልጽግና፣ እንዲሁም ምድራዊ ክብር ሁሉ ትርጉም የለሽ ሆነው ይጠፋሉ። የዚህን ምክንያት ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፣ *"የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑት ሰዎች ሥጋን ከፍትወቱና ከምኞቱ ጋር ሰቅለውታል" ይላል (ገላ. 5፥24)።* መስቀሉን የተሸከመ፣ ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለ ሰው፣ ስለ ነገው ወይም ስለ ወደፊቱ አይጨነቅም። ምክንያቱም የወደፊቱ በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። ለራሱ የሞተ ሰው ስለ እግዚአብሔር ክብር እንጂ፣ ስለ ራሱ ክብር አይጨነቅም።

*"ለራሱ የሞተ"* ሰው፣ ከራሱ የተላቀቀ ሰው በመሆኑ፣ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር የሚውል ነው። ለጌታ ኢየሱስ ያለው ሙሉ መሰጠት፣ በሚወስናቸው ውሳኔዎች ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያስደስትበትን ኃይልና ጸጋ ይሰጠዋል። ውሳኔው ሁሉ፣ የሚናገራቸው ቃላትና የሚያስባቸው ሀሳቦች ሁሉ ጤናማ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ናቸው። ጳውሎስ *"እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ ወይም ማናቸውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ" ሲል ይመክረናል (1 ቆሮ. 10፥31)። "ለራሱ መሞት"* ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ፍቅር እንዲኖረን ነጻ ያደርገናል። *"ለራሱ ያልሞተ"* ወይም ሙሉ መሰጠት የሌለው ሰው መስቀሉን መሸከም አይሆንለትም። መስቀሉን ካልተሸከመ ደግሞ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን አይችልም። ፍሬያማ ክርስቲያን ለመሆን፣ መጀመሪያ ለራሱ መሞትን ይጠይቃል። ኢየሱስ ይህን እውነት በምሳሌ ሲያስረዳ፣ *"እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት በመሬት ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ከሞተች ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል" ይላል (ዮሐ. 12፥24)።*

## 9. ራሱን የሰጠ ደቀ መዝሙር ደስተኛ ነው

ራሱን የሰጠ ደቀ መዝሙር ደስተኛ ነው። ራስን መስጠት ከመታዘዝ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ለኃያሉና ሁሉን ማድረግ በሚችለው ታላቅ ጌታ ላይ መተማመን ነው። የዘመኑን ቴክኖሎጂ እንደሚገባው መጠቀም አልችልም። ጊዜ ወስጄ ለመማርና የሚገባውን ያህል መለማመድ ጊዜ ስለሚጠይቅ፣ "ጊዜዬን ይሻማብኛል" ብዬ በመፍራት፣ የዘመኑን ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ችሎታዬ በጣም ውስን ነው። አለማወቄን ስለተቀበልኩት፣ የማውቅ መስዬ ለመታየት ምንም ጥረት አላደርግም። ይሄም የሆንኩትን ሆኜ ለመገኘት ሙሉ ነጻነት ሰጠኝ። ለምሳሌ፣ ኮምፒዩተሬን ለብዙ ዓመት ብጠቀምበት የሚገባውን ያህል ስለ ኮምፒዩተር አላውቅም። መሠረታዊ የሆነውን እንጂ፣ በሰፊው አላውቅም። አንድ ቦታ ችግር ቢያጋጥመኝ፣ ከእኔ የተሻለ ዕውቀት ያለው ሰው ካልረዳኝ፣ ቀጥ ብዬ እቆማለሁ። የእኔ ልጅ ሙሴ ከእኔ የተሻለ ዕውቀት ስላለው፣ የእርሱን ዕርዳታ ለመጠየቅ አላፍርም። እርሱ በኮምፒዩተር ዕውቀት ቢበልጠኝ፣ እኔ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ስለምበልጠው ዕርዳታ መጠየቅ አያሳፍረኝም።

ችግሬ ገብቶት ሊረዳኝ ሲመጣ፣ የማውቅ መስዬ ለመታየት ምንም ዓይነት ጥረት አላደርግም። አንዳንድ ሰዎች፣ ዕርዳታ እየፈለጉ እንኳን አለማወቃቸው እንዲታወቅባቸው አይፈልጉም። እኔ ይህን ዓይነት ችግር የለብኝም። "ስለ ኮምፒዩተር ደንቆሮ ነኝ፤ ብዙ አላውቅም" እለዋለሁ። እርሱም "ጊዜ ሰጥተህ ስላልተለማመድከው ነው እንጂ፣ እኔ ያወቅሁትን ማወቅ ያቅትሃል ብዬ አላምንም" ብሎ ያጽናናኛል። ሊረዳኝ ሲመጣ፣ ችግሬን ነግሬ ዝም በማለት ፈንታ፣ ይህንና ያንን እየነካሁ፣ "ይሄ እንዲህ ነው... እንዲያ ነው" እያልኩ፣ አዋቂ መስዬ ለመታየት ንግግር ባበዛበት፣ አባቱ ስለሆንኩ በአክብሮት ዝም ካላለኝ በስተቀር፣ ተናዶ "ችግሩን የምታውቅና መፍታት የምትችል ከሆነ ታዲያ ለምን ጠራኸኝ?" ማለቱ አይቀርም። ይህን እውነት በደንብ ስለማውቅ፣ ችግሩን ይፈታዋል ብዬ በማመን ለልጄ ለሙሴ ራሴን ሙሉ በሙሉ መስጠት አለብኝ። እራሴን ለሙሴ መስጠት (submit) ካልቻልኩ ዕርዳታ ማግኘት አልችልም።



የልጄን የሙሴን ዕርዳታ በማግኘቴ ደስ ብሎኝ፣ የሚሠራውን ለሚያውቀው ለልጄ ለሙሴ ራሴን እሰጣለሁ። ኢየሱስ እኔና እናንተን ደቀ መዝሙሩ እንድንሆን ሲጠራን በእርሱ ሙሉ እምነት ሊኖረን ይገባል። "ሸክማችሁ የከበደባችሁ እናንተ ደካሞች ሁሉ ወደ እኔ ኑ! እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ። ቀንበሬን በጫንቃችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህና ትሑት ነኝ፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። ቀንበሬ ልዝብ ነው፤ ሸክሜም ቀላል ነው" ይለናል (ማቴ. 11:28-30)። "ቀንበሬን በጫንቃችሁ ተሸከሙ" ማለት፣ "ራሳችሁን ለእኔ አስገዙ"፣ ወይም "ራሳችሁን በእኔ ሥልጣን ሥር አድርጉ" ማለት ነው።[8]

በመታዘዝና ራስን በመስጠት (submission) መካከል ልዩነት አለ። መኪናችንን ስናሽከረክር ከተወሰነው ፍጥነት በላይ እንዳንነዳ በጣም እንጠነቀቃለን። ሕጉ በሚፈቅደው መጠን የምንነዳው፣ ወይም ሕጉን የምንታዘዘው ብዙ ጊዜ ስለ ሕጉ ግድ ኖሮን ሳይሆን፣ ትራፊክ ፖሊስ አስቁሞ ትኬት ሰጥቶ ብዙ ብር እንዳይቀጣን ብለን ነው። ሕግ አስፈጻሚዎቹ ሕጉን አክብረን መታዘዛችንን እንጂ፣ ለምን እንደታዘዝን ምክንያታችንን ማወቅ አይፈልጉም፤ ግድ የላቸውም። መነሻ ምክንያታችንን (motive) ማወቅ አይፈልጉም። ክርስቶስ ግን የሚመለከተው ትዕዛዝ ማክበራችንን ብቻ አይደለም። ደቀ መዝሙሮቹ ከሆንን፣ ለእርሱ ራሳችንን የሰጠን እንድንሆን ይፈልጋል። ራሳችንን ለመስጠት ደግሞ በእርሱ ላይ የምንታመን መሆን አለብን። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ሳንሰጥ ልንታዘዝ እንችላለን። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ፈሪሳውያን ናቸው። የእግዚአብሔርን ሀሳብ ሳይረዱ፣ ትርጉሙ በትክክል ሳይገባቸው የሙሴን ሕግ ያከብራሉ፤ ለመታዘዝም ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። የተሰጠ ሕይወት ኖሯቸው የማይታዘዙ ሰዎች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እናያለን። ለዚህ ጥሩ ምሳሌያችን ጴጥሮስና ዮሐንስ ናቸው።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ሕይወታቸውን ለጌታ ሙሉ በሙሉ የሰጡ ደቀ መዛሙርት ናቸው። የሰው ሕግ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚጋጭ

---

[8] Dr. Keith Phillips. The Making of a Disciple, Fleming H. Revell Co., Old Tappan, New Jersey, c1960.

ሲሆን፣ ለሰው ሕግ እንታዘዝም አሉ። ጴጥሮስና ዮሐንስ በክርስቶስ ስም ሽባውን በመፈወሳቸው ምክንያት በከተማ ትልቅ ሁከት ተነስቶ የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች አስጠሯቸውና፣ የኢየሱስን ስም በመጥራት ከቶ እንዳይናገሩ ወይም እንዳያስተምሩ በጥብቅ አዘዟቸው። "ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፤ 'ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ተገቢ ነውን? እስቲ እናንተ ራሳችሁ ፍረዱ። እኛ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር አንቆጠብም" በማለት ትዕዛዛቸውን አልተቀበሉም (የሐዋ. 4፡18-20)። ይህንን ተናግረው ስለ ክርስቶስ መስብካቸውንና ማስተማራቸውን ቀጠሉ። እንዲያውም እግዚአብሔር ድፍረት እንዲሰጣቸው ጸለዩ። ለምድራዊ ባለሥልጣን አንታዘዝም ብለው ከሁሉ በላይ ሥልጣንና ኃይል ላለው እግዚአብሔር ራሳቸውን ሰጡ።

እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለብን ነገር ቢኖር፣ ዮሐንስና ጴጥሮስ ሳይደበቁ፣ እግዚአብሔርን በመተማመን፣ አለመታዘዛቸው ዋጋ እንደሚያስከፍላቸውም ቢያውቁ ስለ ክርስቶስ ተናገሩ። ለዓለም ባለሥልጣናት ባለመታዘዛቸው ምክንያት የሚያስቀጣቸው ቢሆንም፣ የእነርሱ አለመታዘዝ ለእግዚአብሔር ክብር የሚያስገኝለት ከሆነ፣ ቅጣቱን ለመቀበል ዝግጁ ነበሩ። ስለ ክርስቶስ ሲሰብኩ አንድ ሰው ያየናል ብለው ከፈሩና የበደለኛነት ስሜት የሚሰማቸው ቢሆን ኖሮ፣ ለእግዚአብሔር ሙሉ መሰጠት የላቸውም እንል ነበር። ደቀመዛሙርቱ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሲሉ በግልጽ ምድራዊ ባለሥልጣናትን ባይታዘዙ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆናቸው አያጠራጥርም። ዳንኤል ለተወሰነ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ የተከለከለ ቢሆንም፣ በመጸለዩ ምክንያት ምንም ዓይነት ቅጣት ቢደርስበትም፣ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነበር። "ዳንኤል ዐዋጁ ተፈርሞበት እንደጸና ባወቀ ጊዜ ወደሚኖርበት ሰገነት ወጣ፤ የሚኖርበትም ሰገነት በኢየሩሳሌም ትይዩ የተከፈቱ መስኮቶች ነበሩት፤ ከዚህ በፊት ያደርገው እንደነበር በጉልበቱ በመንበርከክ አምላኩን እያመሰገነ በቀን ሦስት ጊዜ ይጸልይ ነበር" (ዳን. 6፡10)። እውነተኛ ደቀ መዝሙር ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍለውም ጸንቶ ይቆማል።



## 10. የክርስቶስ ሥልጣን ተወዳዳሪ የለውም

ኢየሱስ፣ "ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፣ የራሱንም ሕይወት እንኳ ከእኔ አብልጦ የሚወድ ከሆነ የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም። የራሱን መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም" ይላል (ሉቃ. 14፡26-27)። ለክርስቶስ ራሳችንን ስንሰጥ ወይም ስናስገዛ፣ ከምድራዊ ባለሥልጣናት ጋር መጋጨታችን አይቀርም። ለክርስቶስ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ራስን መስጠት የሚችለው፣ ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታ ያደረገ ሰው ብቻ መሆን አለበት። እግዚአብሔርን መተማመን የሚለውን ሀሳብ ለመረዳት ብዙዎቻችን እንቸገራለን። ኢየሱስ "ከእናንተ ያለውን ሁሉ ያልተወ ማንም ሰው የእኔ ደቀ መዝሙር መሆን አይችልም" ይላል (ሉቃ. 14፡33)።

"ከእናንተ ያለውን ሁሉ ያልተወ" ሲል ምን ማለቱ ነው? የማንፈልገውን፣ የማንወደውን፣ የተረፈንን ሳይሆን፣ በጣም የምንወደውንና የምንሳሳለትን ነገር ሁሉ ያጠቃልላል። ሀብታችንን፣ እንደ ዐይናችን ብሌን የምንወዳቸውን ልጆቻችን ሁሉ መተው እንዳለብን ይናገራል። ለእግዚአብሔር ስንል መተው እንዳለብን ካላወቅን፣ አንዱን ለመውሰድ ቢፈልግ፣ ስብርብራችን ይወጣል። እግዚአብሔር ሥልጣንን ለሌሎች በመስጠት ወይም እንዲወክሉት በማድረግ ይገዛል። ደቀ መዛሙርቱን "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብና በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" አላቸው (ማቴ. 28፡18-19)። እንዲሁም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን አብን ይቀበላል" ይላል (ማቴ. 10፡40)። ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ሰጠው ሥልጣን ይናገራል። "ጌታ ስለ ሰጠን በጣም ብመካም አላፍርበትም፤ ምክንያቱም ይህ ሥልጣን የተሰጠን እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለም" ይላል (2 ቆሮ. 10፡8)። ጳውሎስ የተሰጠውን ሥልጣን ብዙ ጊዜ ሲጠቀምበት እናያለን። "ወንድሞች ሆይ!

*ሥራ ፈት ከሆነውና ከእኛ በተቀበላችሁት ትምህርት መሠረት ከማይኖር ክርስቲያን ሁሉ እንድትለዩ እናዝዛችኋለን" ይላል (2 ተሰ. 3፥6)።*

ሥልጣንን የምንቀበለው በመስጠት (submission) ነው። ማንኛውም ሰው ሥልጣኑን የሚጠቀመው ለባለሥልጣን ራሱን በሰጠው መጠን ነው። ያ ሮማዊ መቶ አለቃ፣ ኢየሱስ ቃል ብቻ ቢናገር ሎሌው እንደሚፈወስ ያውቅ ነበር። እምነቱ በክርስቶስ ላይ ከፍ ያለበትን ምክንያት ሲገልጽ፣ *"እኔም ራሴ ወደ አንተ ለመምጣት የበቃሁ ሰው አይደለሁም። ስለዚህ አንተ እዚያው ሆነህ በቃልህ ብታዝዝ አገልጋዬ ይድናል። እኔ ራሴ ለባለ ሥልጣኖች ታዛዥ ስሆን ከእኔ በታች የማዝዛቸው ወታደሮች አሉኝ። ስለዚህ አንዱን 'ሂድ' ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን 'ና' ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬንም 'ይህን አድርግ' ስለው ያደርጋል" አለው (ሉቃ. 7፥7-8)።* ይህ ሮማዊ ወታደር በባለሥልጣን የተወከለ ሰው ያለውን ኃይልና ሥልጣን ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። መጀመሪያ እርሱ ራሱ ለባለ ሥልጣን የተሰጠ ከሆነ፣ የሚያስተላልፈው ትዕዛዝ ፍጻሜ ያገኛል። እርሱን አለመታዘዝ ማለት የሮማን ንጉሠ ነገሥትን እንዳለመታዘዝ ይቆጠራል።



# 5

# በመስቀሉ፥ የእምነታችን ጽኑነት ይለካል

*"ወንድሞቼ ሆይ! ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት፤ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ"*
*(ያዕ. 1፥2)*

*በሰፊው ልንማረው የሚገባን፣ ገና ያልነካናቸው ብዙ መንፈሳዊ ትምህርቶች እያሉ፣ ደስታን የሚቀንሰውን፣ በሰው አዕምሮ ውስጥ ትልቅ ጥያቄ ሊፈጥር የሚችለውን፣ እንዲሁም ለመስማት የሚዘገንነውን የክርስቲያን ሰማዕታት ታሪክ ማቅረብ ለምን አስፈለገ? ምን ይጠቅማል? ደማ ደጉን ብቻ ለምን አናወራም"* በማለት አስተያየት የሚሰጡ አንዳንድ አማኞች እንደሚኖሩ እርግጠኞች ነን። በዘመናት ታሳቅ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ተራ ምዕመናን፣ አስተማሪዎች፣ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች፣ እንዲሁም ጎልማሶች በእምነታቸው ምክንያት በሰንሰለት ታስረው ከነፍሳቸው በእሳት ውስጥ የተቃጠሉ፣ በስቃያቸውና በመከራቸው የሌሎች መደሰቻና መዝናኛ ለመሆን ራሳቸውን አሳልፈው ስለ ሰጡት ቆራጥ ክርስቲያኖች የተለያዩ ታሪክ ጸሀፊዎች ለትምህርታችን እንዲሆን ታሪካቸውን ተርከዋል።

እኔም ይህን መጽሐፍ አዘጋጆቹ ለማቅረብ ስነሳ፣ ዋናው ዓላማዬ አንባቢዎቼን ያዝናናል ወይም ያስደስታል ብዬ ሳይሆን፣ የክርስትና እምነት ርካሽ ጸጋ፣ ያለዋጋ የመጣ፣ ወይም መስቀል የሌለበት ሳይሆን፣ ሕይወትን እስከ መስጠት ድረስ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን እንዳ'ንዘነጋው ለማድረግና ለመስቀሉ ጉዞ ራሳችንን የበለጠ እንድናዘጋጅ ለመምከር ነው። 2 ጢሞ. 3፥12 ላይ *"በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ"* ካለ፣ በአሁኑ ጊዜ እንደ ጥንቱ ስለ እምነታቸው በመከራ፣ በስደትና በእስራት ውስጥ የሚያልፉ አማኞች የማይኖሩት ለምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደምትሰደድና በመከራ ውስጥ እንደምታልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። እኛ በመከራ ውስጥ የማናልፍ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን እንድንደግፍ ዕድል እየሰጠን ስለሆነ፣ በሰጠን ዕድል ልንጠቀምበት ይገባል። በመከራና በስደት ውስጥ የሚያልፉት ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ እስራኤል ውስጥ የነበሩ የቀድሞ ነብያትም በልዩ ልዩ ፈተናና መከራ ውስጥ ያልፉ እንደነበረ፣ የዕብራውያንን መልዕክት የጻፈው ሰው ገልጾታል። *"አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፤ በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ። በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፤ እየተንገላቱ፣ እየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቆዳ ለብሰው ዞሩ። ዓለም ለእነርሱ አልተገባቸችውምና በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጉድጓዱ ተንከራተቱ"* ይላል (ዕብ. 11፥36-40)።

ይሄ እኛ ያለንበት ዘመን፣ *"ሰማዕትነት"*የሚለው ቃል ልዩ ትርጉም የያዘበት ዘመን ስለሆነ፣ እውነተኛውን፣ እውነተኛ ካልሆነው ለይተን ማወቅ ያስፈልገናል። *አሸባሪዎች (ቴሬሪስቶች)* መስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ፣ አይሮፕላን በመጥለፍ *"ወርልድ ትሬድ ሰንተር"* ላይ ከፍተኛ አደጋ አድርሰው ከ3 ሺ ሕዝብ በላይ በአንድ ጊዜ ያጠፉት ወጣቶች፣ አጥፍተው በመጥፋታቸው ራሳቸውን የሚያዩት እንደ *"ሰማዕታት"* አድርገው እንደ ሆነ የታወቀ ነው። ይህ



ብቻ ሳይሆን በየጊዜው በሬዲዮና በጋዜጣ የምንሰማው ዜና *"አጥፍቶ ማጥፋት"* በሚለው ፍልስፍናቸው፣ ቦምብ እያፈነዱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ራሳቸውን በማጥፋታቸው አሸባሪዎች ሳይሆን፣ "ሰማዕታት" ብለው ራሳቸውን እንደሚጠሩ የታወቀ ነው። እኛ ግን ሰማዕታት ስንል እንዲህ ዓይነቶቹን ማለታችን አይደለም።

## 1. ሰማዕት (Martyr) ማለት ምን ማለት ነው?

*"ሰማዕት"*የሚል ትርጉም የያዘው የእንግሊዝኛ ቃል፣ *(Martyr) (ማርተር)* ከላቲን የመጣ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ትርጉሙ *"ምስክር መሆን"* ማለት ነው። የቀድሞ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ክደው ከመኖር ይልቅ፣ *"ለሚያምኑትና ለተቀበሉት ሃይማኖት ምስክር"* ሆነው መሞትን የመረጡትን አማኞች ለመግለጽ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት ቃል ነው። አማኞች በወቅቱ የነበራቸው ሁለት ዓይነት ምርጫ ነበር።

- አንደኛው *"ክርስቶስን ክዶ በሕይወት መኖር"*ሲሆን፣
- ሁለተኛው ደግሞ *"ክርስቶስ ጌታ ነው በማለት መስክሮ መሞት"* ነበር። *"ክርስቶስን ክድቼ በሕይወት ከምኖር፣ ክርስቶስ ጌታ ነው ብዬ ብሞት ይሻለኛል"*የሚለውን ምርጫ በመምረጣቸው ሕይወታቸውን ያጡትን፣ እነዚያን *"ሰማዕታት"* ብለን እንጠራቸዋለን።

ሰማዕትነትን በትክክል ለመረዳት ግራ የሚያጋባን አንደኛው ምክንያት፣ በጥንት ዘመን አሳዳጆቹ ወይም ገዳዮቹ የክርስትና እምነት ጠላቶች ሳይሆኑ፣ ራሳቸውን "ክርስቲያን" ብለው የሚጠሩ በመሆናቸው ነው። ለምሳሌ፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ *የፕሮቴስታንት ተሀድሶ መሪዎችንና ተከታዮችን የሚያጠፉ፣ እንዲሁም ፕሮቴስታንቶች ደግሞ አናባፕቲስት ወይም ዳግም አጥማቂዎች ተብለው የሚጠሩትን የሚያሳድዱ መሆናቸው ነው።* ይሁን እንጂ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት የተቆረቆሩ በሚመስሉ ሰዎች ብዙዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።

የሰማዕታት ታሪክ የቀድሞ ክርስቲያኖችን ሕይወት ለማስታወስ ይረዳናል። የምናስታውሰውም ለበጎ እንጂ፣ ለክፉ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ከግብጽ ባርነት እንዴት ነጻ እንዳወጣቸው ለማስታወስ፣ የፋሲካን በዓል እንዲያከብሩ ትዕዛዝ ሰጥቷቸው ነበር። ይህም ማለት ለ400 ዓመት ያስጨነቋቸውንና የገዟቸውን ግብጻውያንን እንዲጠሉ፣ ልባቸው በግብጻውያን ላይ መራራ ሆኖ እንዲበቀሏቸው ሳይሆን፣ ታማኝና ኃያል የሆነው እግዚአብሔር እንዴት ከባርነት እንዳወጣቸው እንዲያስታውሱ ነበር። እኛም የሰማዕታትን የሕይወት ታሪክ የምናጠናው፣ ክርስቲያኖችን ያሳድዱ የነበሩትን ሰዎች ለመጥላትና ለመበቀል ሳይሆን፣ መከራቸውን ታግሰው ማለፍ የሚችሉበትን ጸጋና ኃይል ለክርስቲያኖች የሰጠውን ጌታ አስታውሰን ልባችን በምስጋና እንዲሞላ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ መከራ ሲያስታውስ፣ ትኩረት የሰጠው ክርስቶስን ባሳደዱት ሰዎች ላይ ሳይሆን፣ እስከ ሞት ድረስ ለእግዚአብ ሔር አብ ታዛዥ በሆነው ክርስቶስ ላይ ነበር። *"...እስከ ሞት ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ"* ይላል (ፊልጵ. 2፡8)። ትክክለኛ ያልሆነ ማስታወስ፣ ከዚህ በፊት የደረሰውን ጥቃትና በደልን እያስታወሱ ጥላቻንና በቀልን በልቡ ውስጥ እንዲፈጠር ያደርጋል። ትክ ክለኛ የሆነ ማስታወስ ግን መከራና ሞት፣ በክርስቶስ የሚገኘውን ድል ማንም ሊያጠፋው እንደማይችል የሰው ልብ እንዲያውቀው ያደርጋል።

## 2. የአማኞችን በመከራ ውስጥ ማለፍ መቀበል ለምን የቀተናል?

የሰማዕታትን ታሪክ መስማት ብዙዎች የማይፈልጉበት ምክንያት፣ መከራን በሚመለከት አሳብ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎችን በአዕምሯቸው ውስጥ ስለሚፈጥርባቸው ነው። ይኸውም *"ደጉ እግዚአብሔር እንዴት መከራ በሰዎች ሕይወት ውስጥ እንዲደርስ ይፈቅዳል? ወይም ያንን የመሰለ በደልና ግፍ የሚፈጽሙትን ጨካኝ የሆኑትን ሰዎች ለምን ዝም ብሎ ያልፋል"* በማለት እንዲጠይቁ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ነው። በምዕራቡ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ አማኞች ከመከራ ሁሉ ነጻ ሆነው እንዲኖሩ፣ በሦስተኛው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ግን በመከራ ውስጥ እንዲኖሩ የተበየነባቸው መስሎ የሚሰማቸው አሉ። ይሄ እውነት አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ መጠንቀቅ ያለብን ነገር ቢኖር፣ በመከራና በስደት ውስጥ የሚያልፉ ክርስቲያኖች ከሌሎች የበለጠ ቅዱሳን ወይም ብርቱ በመሆናቸው ነው ብለን እንዳናስብ ነው።

በመከራ ውስጥ ተፈትነው እንዲያልፉ እግዚአብሔር የሚፈቅደው በተወሰነው የዓለም ክፍል ውስጥ በሚኖሩት ሰዎች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሙሉ ልባቸው ክርስቶስን ለመከተል በወሰኑት አማኞች ሁሉ ላይ ነው። የሚያልፉበት የመከራና የስደት ሕይወት የሁሉም አንድ ዓይነት አይደለም። እዚህ ላይ መረዳት ያለብን እውነት ቢኖር፣ ማንኛውም አማኝ ሊያልፍበት ከሚችለው በላይ ይሆነ መከራ በሕይወቱ እንዲደርስበት ጌታ የማይፈቅድ መሆኑን ነው። አንዳንዶች እንደ እሳት በሚፋጅ፣ ሕይወታቸውን እስከ ማጣት በሚያደርስ ፈተናና መከራ ውስጥ ያልፋሉ። ሌሎች ደግሞ *"የክርስትያኖች መከራ ምንድነው?"* ብለው እስከሚጠይቁ ድረስ፣ ምንም ዓይነት ስደትም ሆነ መከራ አይደርስባቸውም። በእምነታቸው ምክንያት በስደትና በመከራ ውስጥ የሚያልፉት፣ ምንም ክፉ ነገር ያልደረሰባቸውን አማኞችን እየተመለከቱ "በሌሎች ላይ ምንም ሳይደርስ፣ ለምን ይሄ ሁሉ መከራ በእኔ ላይ ይደርሳል?" በማለት ከማዘንና ከማጉረምረም ይልቅ ደስ ሊላቸው እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ሐዋርያው ጴጥሮስ፣

⊃ *"አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል። እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው"* ይላል (1 ጴጥ. 1፡6-7)።

## 3. አማኞች እንደ ጥንቱ ዛሬም በመከራ ውስጥ ያልፋሉ

በእምነታቸው ምክንያት ሕይወታቸውን እስከማጣት ድረስ የደረሱ፣ በጥንት ዘመን የነበሩ አማኞች ብቻ ሳይሆኑ፣ በአሁኑ ዘመንም በከፍተኛ ስደት ውስጥ የሚያልፉ የክርስቶስ ተከታዮች እንዳሉ ማወቅ ይገባናል። ይሁን እንጂ፣ በእምነታቸው ምክንያት ስቃይን የሚቀምሱበት፣ ሕይወታቸውን የሚያጡበት መንገድ የአሁኖቹ ከጥንቶቹ ጋር አንድ ዓይነት ነው ማለት አይደለም። በአሁኑ ዘመን በእምነታቸው ምክንያት ከነፍሳቸው በአደባባይ በእሳት ተቃጥለው ሲሞቱ፣ ለአውሬዎች ተጥለው ስጋቸው ሲበጣጠስ፣ አጥንታቸው ሲሰባበር፣ በመጋዝ ሲሰነጠቁ፣ የፈላ እሬንጅ በላያቸው ላይ ፈስሶ እሳት ሲለኮስባቸው፣ በሰይፍ ሲቆራረጡ አናይም ይሆናል። ዓይነቱና መጠኑ የተለያየ ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ዘመን ስለ እምነታቸው መከራ የሚቀበሉ፣ ልዩ ልዩ ስደት፣ የሰው አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለው መከራ የሚደርስባቸው ክርስቲያኖች በዓለም ዙሪያ እንዳሉ የታወቀ ነው። በዚህኛው የትምህርት ክፍላችን በእኛ ዘመን የክርስቶስ ተከታዮች በመሆናቸው በመከራ ውስጥ ካለፉት አማኞች መካከል፣ ከእስልምና ሃይማኖት ወደ ክርስትን እምነት የመጣ አንድ አማኝ ያለፈበትን ስደት በአጭሩ እናቀርብላችኋለን።

ሰሜን አፍሪካ ለብዙ መቶ ዓመታት እስልምና አይሎ የሚታይበት ክፍል መሆኑን፣ በዚህ አካባቢ ክርስቲያን ሆኖ መኖር ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍል ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁ እንገምታለን። የአገሪቱ ሕዝብ መቶ በመቶ እስላም በሆነበት አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች በብዙ መከራና ስደት ውስጥ ያልፋሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው፣ ከእስልምና ወደ ክርስትና የመጣው የሞሮኮ ተወላጅ የሆነው አልጃባር ቡራኒ ነው። ኸርበርት ስክሎስበርግ የተባለው ክርስቲያን ጸሀፊ በጻፈው መጽሐፍ ያለፈበትን የስደት ጉዞ ራሱ አልጃባር ቡራኒ ሲተርክልን እንስማው። አልጃባር ቡራኒ ታሪኩን ሲገልጽ እንዲህ ይላል። "ተወልጄ ያደግሁት ሞሮኮ ነው። ወንጌልን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት በሚሲዮናውያን አማካኝነት ልጅ ሆኜ ነው። ሞሮኮ የእስላም ሃይማኖት ያየለበት አገር በመሆኑ ክርስቲያን ሆኖ ወይም የክርስቶስ ተከታይ ሆኖ መኖር ቀላል አይደለም። ማንም ሰው



እንደሚያውቀው ሞሮኳዊ ሆኖ መወለድ ማለት እስላም ሆኖ መወለድ ማለት ነው። ይህም ማለት እስልምናን እስላም ከሆኑ ወላጆች በመወለዳችን ምክንያት የተቀበልነው ነው። ሞሮኮ ውስጥ እየኖሩ በድፍረት "ክርስቲያን ነኝ" ብሎ በግልጽ መናገር ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነው። ሞሮኮ እያለሁ በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራና ስደት በእኔ ላይ አልደረሰብኝም። ምክንያቱም ክርስቲያን መሆኔን ለማንም ስላልተናገርኩ ነው።

ይኸው የሞሮኮው ተወላጅ አልጃባር ቡራኒ ታሪኩን በመቀጠል እንዲህ ይላል። "በበኩሌ ስደትን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀመስኩት ግብጽ አገር ሆኜ ነው። ሞሮኮ እያለሁ አንድ የውጪ አገር ሰው የሆነ ክርስቲያን ሰው ካይሮ ውስጥ አንድ ትልቅ መንፈሳዊ ስብሰባ እንደሚደረግ ነግሮኝ ስብሰባውን ለመካፈል፣ አስር ወንድሞችና እህቶች ወደ ካይሮ ሄድን። ከዚህ በፊት የማናውቀውን ብዙ ነገር ተማርን። ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአካል ተገኘሁ። ስለ ምስክርነት፣ ስለ ደቀ መዝሙርነትና በጠቅላላው ማንኛውም ክርስቲያን ማወቅ ስለሚገባው መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን ተማርኩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለም አቀፍ የሆነው የክርስቶስ አካል ክፍል መሆን ማለት ምን እንደ ሆነ ተረዳሁ። ኮንፍራንሱ እንዳለቀ፣ ከዚህ በፊት የጀመርኩትን ትምህርት ለመጨረስ ወደ ሞሮኮ ተመለስኩ። በዓመቱ መጨረሻ ላይ ጥቂት ጊዜ ስለ ነበረኝ፣ የበለጠ ስልጠና ለማግኘት ወደ ግብጽ ሄጄ ጥቂት ጊዜ አሌክሳንደሪያ ውስጥ አሳለፍኩ።

እኔና አንድ ክርስቲያን ወንድም ከሞሮኮ ተነስተን ግብጽ ስንደርስ፣ ከቱኒስያ ከመጡ ሁለት ወንድሞች ጋር አንድ አፓርታማ ውስጥ አብረን እየኖርን ስልጠና ይሰጠን ነበር። ይሄ ወቅት ለእኛ ልዩ የሆነ ደስታ ያገኘንበት ጊዜ ነበር። ችግር መፈጠር የጀመረው የመቆያ ጊዜያችንን ለማራዘም ቪዛ ለመጠየቅ ፖሊስ ጣቢያ በሄድን ጊዜ ነው። የእኛን አቋም የበለጠ ለመረዳት የተለያየ ጥያቄ መጠየቅ ጀመሩ። የመጣነው በቱሪስት ቪዛ እንጂ፣ ግብጽ ውስጥ ለመማር ወይም ለመሥራት ስላልሆነ እንዴት እንደምንኖር፣ ለአፓርትመንት የምንከፍለውን ገንዘብ ከየትና እንዴት እንደምናገኝ ጠየቁን። ከዚህም ሌላ ብዙ የተለያዩ ከባድ ጥያቄዎችን ጠየ

ቁን። የምናደርገው ነገር ሁሉ ሕጋዊ ቢሆንም፣ ባለስልጣኖች ግን በእኛ ላይ የነበራቸው ጥላቻ በግልጽ በፊታቸው ገጽታ ላይ ይታይ ነበር።

አንድ ቀን ማታ እነዚያ ከቱኒስያ የመጡት ሁለት ወንድሞቻችን በተለመደው ሰዓት ወደ ቤት ሳይመጡ ቀሩ። ብዙ ከጠበቅናቸው በኋላ የት እንዳሉ፣ ወይም የት እንደደረሱ የፕሮግራሙን ድሬክተር በስልክ መጠየቅ ፈለግን። ልክ ስልኩን አንስቼ ገና መነጋገር ስጀምር፣ የሲቪል ልብስ የለበሱ ሦስት ፖሊሶች የክፍላችንን በር በርግደው ገቡ። አንደኛው በኃይል ጮክ ብሎ፣ "ከማን ጋር ነው የምትነጋገረው?" ሲል ጠየቀኝ። እኔም ደንግጬ "ከጓደኛዬ ጋር ነው" አልኩት። ከቱኒስያ ከመጡት ወንድ ሞች መካከል አንደኛው አብሯቸው ነበር። በፊቱ ገጽታ ላይ ፍርሃትና ድንጋጤ ይታይበት ነበር። በብዙ ጥያቄዎች ቀኑን ሙሉ ሲያስጨንቁት እንደዋሉ በኋላ ሰማን። ክፍላችን ውስጥ ብዙ ነገር አገኙ። መንፈሳዊ መጽሐፍት፣ የስልጠናችንን ፕሮግራም የያዙ ልዩ ልዩ ወረቀቶችን አግኝ ተው፣ ሁሉንም ሰብስበው ሻንጣቸው ውስጥ ከትተው ይዘው ሄዱ።

ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት በጥያቄ እያጣደፉን ምንም ዓይነት እንቅ ልፍ አላስተኙንም። ሁለት ቀን ሙሉ ምንም ዓይነት ምግብ ስላልበላን በጣም ተርበን ነበር። በመጨረሻ ከእኛው በወሰዱት ገንዘብ፣ አንደኛው ፖሊስ ሳንድዊች ገዝቶልን መጣ። በአንድ ጊዜ ሦስት ወይም አራት ሰዎች ሆነው በጥያቄ ያስጨንቁን ነበር። ለጥያቄያቸው ሁሉ ተገቢውን መልስ እንሰጣቸው ስለ ነበረ፣ ማወቅ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ አወቁ። በሚቀጥለው ቀን ከመጽሐፍ ቅዱስ አስጠኚዬ ጋር ቀጠሮ ስለ ነበረኝ፣ ሊያነጋግረኝ ሲመጣ ፖሊሶች ይዘው ከእኛ ጋር አሠሩት። ጥያቄ ጠይቀ ውን መልሳችን ካላስደሰታቸው በጥፊ ይመቱን ነበር። አንዳንድ ጊዜ መልሱን አስቀድመው ይነግሩንና፣ ቀጥለው ጥያቄ ያቀርቡልናል። የጠበ ቁትን ዓይነት መልስ ካልሰጠናቸው በጥፊ ይመቱናል። ከፖሊሶቹ አንደ ኛው "ስለ ክርስቲያኖች ምን ታስባላችሁ?" ብሎ ሲጠይቀን፣ "ጥሩ ሰዎች ናቸው" የሚል መልስ ሰጠሁት። ቀጥሎ "እስላሞች መጥፎ ሰዎች ናቸው ማለታችሁ ነው?" በማለት በጥፊ መታኝ። መልሱን ቢያውቁትም እንዋሽ እንደሆን እኛን ለመፈተን ይጠይቁን ነበር። በጥያቄ በማስጨነቅ፣ በማሰ



ራብ፣ በመደብደብ ስነ-ልቦናችንን ለመሰባበር ከፍተኛ ጥረት አድር ገዋል።

*"ለምንድነው ግብጽ የመጣችሁት?" ... መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት ነው።*

*"መጽሐፍ ቅዱስ ለምን አገራችሁ አታጠኑም?" ...*

*"ምክንያቱም ስለማይፈቀድልን ነው..."*

*"መጽሐፍ ቅዱስን አገራችሁ ማጥናት ካልቻላችሁ፣ እኛም አገር ማጥናት አትችሉም... ለመሆኑ ግብጽ ውስጥ ምን ዓላማ አላችሁ?"*

*"የመጣንበት ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል በሰፊው ለመማር ነው"*

*"ተምራችሁ ምን ለማድረግ ነው? ካይሮ ውስጥ ያሉትን እስላሞችን ወደ ክርስትና እምነት ለመለወጥ ነው?"...*

*"አይደለም... ካይሮ ውስጥ ያሉ እኛ የምናውቃቸው ሰዎች ሁሉ ክርስቲያኖች ናቸው።"*

በዚህ ዓይነት የሚጠይቁት ጥያቄ ሁሉ በክርስትና እምነት ዙሪያ ብቻ ያተኮረ አልነበረም። ስለ ፖለቲካም ሆነ ስለ እስልምና እንዲሁም የተ ለያየ ጥያቄ ጠይቀውናል። እስልምናን የሚቃወም መጽሐፍ ሲያሳዩን፣ እኛም ክርስትናን የሚቃወም መጽሐፍ እንዳለ ነገርናቸው። መንፈሳ ችንና ስነ ልቦናችንን ለመሰበር እውነትነት በሌለው ነገር ይከሱንና በጥ ያቄ ይስጨንቁን ነበር። ልብሳችንን አውልቀን ራቁታችንን ፊታቸው እን ድንቆም በማድረግ ለሚያቀርቡልን ጥያቄ ሁሉ መልስ እንድንሰጣቸው ያስጨንቁን ነበር። *"እናንተ ሶዶማውያን ናችሁ፣ የእስላም ስም ይዛችሁ እንዴት ክርስቲያኖች መሆን ትችላላችሁ? ቤተሰባችሁን ያዋረዳችሁ፣ ተወልዳችሁ ያደጋችሁበትን ባሕል የተዋችሁ፣ አገራችሁን የከዳችሁ ናችሁ"* ይሉን ነበር። ግብጽን ለማጥፋት ከሚፈልጉ ሰዎች ገንዘብ ተቀ ፍሎን፣ ሁከትና ረብሻ በመፍጠር የእርስ በእርስ ጦርነት ለመፍጠር፣

ግብጽን ሌላዋ ሌባኖን ለማድረግ እንደመጣን አድርገው ይከሱን ነበር። ከጥያቄያቸው ቀጥሎ በእርግጫና በጥፊ ይደበድቡን ነበር።

የታሰርንበት ወህኒ ቤት ይዞታ ከመጠን በላይ መጥፎ ነበር። እጆቻችን በሰንሰለት እንደታሰሩ፣ ከብዙ እስረኞች ጋር ተጣብቀን፣ አንገታችንን ደፍተን አንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ታጉረን ነበር። በዚያ ውስጥ የነበረው መጥፎ ሽታ ያቅለሸልሻል። መጀመሪያ ላይ የታሰርነው ከፖሊስ ጣቢያው ምድር ቤት ካለው እስር ቤት ነበር። ሦስት ቀን ሙሉ ልዩ ልዩ ጥያቄ በመጠየቅ ከመረመሩን በኋላ፣ ከካይሮ ከተማ ወጣ ብሎ ከሚገኘው የፖለቲካ እስረኞች ከሚታሰሩበት፣ ቶራ ተብሎ ከሚጠራው ወህኒ ቤት ወሰዱን። ይሄ ወህኒ ቤት ፕሬዚደንት ሳዳትን የገደሉ አክራሪ እስላሞች የታሰሩበት፣ በጣም አደገኛና አስፈሪ የሆነ ወህኒ ቤት ነው። እነዚህ አክራሪ እስላሞች በክርስቲያኖች ላይ በተለይ ከእስልምና ወደ ክርስትና እምነት የመጡትን በጣም የሚጠሉ ሰዎች ናቸው። በዚህ ወህኒ ቤት መርማሪዎቹ በልዩ ልዩ ጥያቄ ከምንጊዜውም የበለጠ በማጠናከር ያስጨንቁን ነበር። በድርጊታቸውና እንዲሁም በፊታቸው ገጽታ ላይ በጣም እንደሚጠሉን በግልጽ ይታይ ነበር። እነርሱም በጣም የሚጠሉን መሆናቸውን በግልጽ ይነግሩን ነበር። ውስጥ እግራችን እስኪደማ ድረስ በዱላ ከቀጠቀጡን በኋላ ስቃያችንን ለማብዛት በባዶ እግራችን ጠጠር ላይ ያስሮጡን ነበር። በዚህ ዓይነት ከስቃያችን የተነሳ እግሮቻችን ሊፈነዱ የደረሱ ይመስለን ነበር። የጎድን አጥንቶታችንን እስኪሰባበር ድረስ በዱላ ይቀጠቅጡን ነበር። በአንድ ወገን ያለውን ጸጉራችንን ላጭተው፣ ሌላውን ወገን በመተው፣ መሳቂያና መቀለጃ በማድረግ መንፈሳችንን ለመስበር ይጥሩ ነበር።

ወህኒ ቤት ተጥለን ሁለት ወር ሙሉ በዚህ ዓይነት ስቃይ ውስጥ ስናልፍ፣ ካይሮ ውስጥ ያሉት ክርስቲያን ወንድሞቻችን የት እንደ ደረስን እንደማያውቁ መጨረሻ ላይ ተረዳን። መጨረሻ ላይ መጥፋታችንን ለፖሊስ ሪፖርት ሲያደርጉ፣ ወደ ሞሮኮ ተመልሰን መሄዳችንን ነገሯቸው። የወህኒ ቤቱ ባለሥልጣኖች፣ ደብዳቤ ጽፈን ወደ ውጪ እንድንልክ አልፈቀዱልንም ነበር። መጨረሻ ላይ ግን ከወህኒ ቤት ዘበኞች መካከል አንዱ ገንዘብ ከሰጠነው ደብዳቤያችንን ሊልክልን ፈቃደኛ እንደሆነ ነገረን።



ይሁን እንጂ፣ ወህኒ ቤት ስንገባ የነበረንን ገንዘብ በሙሉ ወስደውብን ስለነበረ የጠየቀንን ገንዘብ ልንሰጠው አልቻልንም። እግዚአብሔር ሲረዳን፣ ከእኛው ጋር ታስረው የነበሩ አንዳንድ ክርስቲያን ወንድሞች ገንዘብ አዋጥተው ስለሰጡን፣ ያንን ለዘበኛው ሰጥተን ደብዳቤያችን ተላከ። ውጪ የነበሩ ክርስቲያን ወንድሞቻችን በጻፍነው ደብዳቤ አማካኝነት ያለንበትን ሁኔታና የታሰርንበትን ወህኒ ቤት አወቁ።

ወህኒ ቤት ውስጥ የቀመስነው መከራ ቀላል አልነበረም። አየር በፍጹም በማይገባበት ወይም በታፈነ ትንሽ እስር ቤት ውስጥ፣ ትንኝና ዝንብ የወረረው፣ ብዙ እስረኞች በአንድ ላይ ታምቀን እንቀመጥ ነበር። ለሁለት ወራት ያህል ጺማችንን መላጨት፣ ጥርሳችንን መቦረሽ ወይም ገላችንን መታጠብ አልተፈቀደልንም ነበር። በቂ ምግብ አይሰጡንም ነበር። የሚሰጡን ትንሽ ሩዝና ባቄላ ነበር። እርሱም በትልና በትንኝ የተሞላ ነበር። እንኳን በልተን በዓይናችን ስናየውም ያቅለሸልሸን ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ ሳልበላ ቆየሁ። መጨረሻ ላይ ራሴን በሕይወት ለማቆየት የግድ መብላት ነበረብኝ። “ጌታ ሆይ! ይህን ምግብ ከነትሉና ከነትንኙ መብላት እንድችል እርዳኝ” ብዬ እያለቀስኩ ጸለይኩ። ትሉን በእጄ ለቅሜ ጨለማ ውስጥ ከወረወርኩ በኋላ ጨክኜ፣ ዓይኔን ጨፍኜ እንደምንም ብዬ በላሁ። እንድንጠጣ የሚሰጡን ውሃ ፍጹም የተበላሸና የገማ ነበር። ምርጫ ስላልነበረን የግድ ያንኑ መጠጣት ነበረብን። ውጪ መውጣት ስለማይፈቀድልን፣ ቀንና ማታ በጨለማ ውስጥ ጣራ ጣራውን እያየን ቁጭ ከማለት በስተቀር ምንም አናደርግም ነበር። ወህኒ ቤታችን ውስጥ ወንበርም ሆነ አልጋ ስለሌለ፣ የሚቀዘቅዝ ሲሚንቶ ላይ እንተኛ ነበር። አብረውን የታሰሩ አንዳንድ እስረኞች ወህኒ ቤት ሲገቡ ከተቀመጣላቸው ገንዘብ በማስወጣት፣ ከውጪ ምግብ እየተገዛላቸው ይበሉ ነበር። እኛ ግን እስልምናን በመተዋችን ዘበኞቹ እንደ እርኩስ ስለሚቆጥሩን እኛን ለመርዳት ፈቃደኞች አልነበሩም።

የወህኒ ቤቱ ሼኮች እኛን ወደ እስልምና እንደ ገና ለመለወጥ ያለመታከት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር። እኛ በነበርንበት ወህኒ ቤት ውስጥ ይህንን ሥራ እንዲሠራ የቀጠሩት “ማሙድ” የተባለው ሰው ከቁራን ብዙ

ጥቅሶችን እየጠቀሰ ሲያባብለን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ግን እውነት ያልሆነ
ውን ነገር ይጠቅስልን ነበር። አይሳካለት እንጂ ማሙድ እኛን ለመለወጥ
የተለያየ መንገድ ተጠቅሟል። አንዳንድ ጊዜ በኃይል ተቆጥቶ እየጮኸ
ይነግረናል፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ በጣም ለስለስ ብሎ በጨዋነት ሊያስተምረን
ይሞክር ነበር። አንድ ጊዜ ከቱኒስያ ከመጡት ሁለት ወንድሞች መካከል
አንዱን ወደ ክርስትና እምነት እንዴት እንደተለወጠ ሲጠይቀው፣ ሁላች
ንንም ገረመን። የተሰጠውን ዕድል በመጠቀም ወንድማችንም እንዴት
ክርስቲያን መሆን እንደቻለ ሲነግረው፣ በቁጣ ተሞልቶ ከአጠገቡ አባረ
ረው።

ይንን በመሰለ መራራ ሕይወት ውስጥ ስናልፍ፣ ውስጣችን በተስፋ
መቁረጥና በአዕምሮ ጭንቀት እየተሞላ መጣ። ቀስ በቀስም ወደ ሞት እየ
ተቃረብን መምጣታችን ተሰማን። ቀደም ሲል የነበረን ጽናትና ትዕግስት
ቀስ በቀስ እየላላ መምጣቱን ስንገነዘብ፣ በአንድ ላይ መጸለይና የመጽ
ሐፍ ቅዱስ ቃል በቃላችን የምናውቀውን ማለት ጀመርን። ይሄም አዕም
ሯችንን ለመጠበቅ ጥሩ መድኃኒት ሆነልን። ዕብ. 13፥5 ላይ ባለው ጥቅስ
ይኸውም፣ "...*እግዚአብሔር ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም*
በሚለው የተስፋ ቃል አዕምሯችንን ስናሳረፍ፣ በውስጣችን እየተጽናን
መጣን። ክርስቶስ የቀመሰውን መከራ በተመስጦ ሆነን በአዕምሯችን በማ
ሰላሰል፣ እንዲሁም የቀድሞ ክርስቲያኖች በመከራና በስቃይ ውስጥ ሲያ
ልፉ ደስ ይላቸው እንደነበረ ስናስብ ልባችን በደስታ ተሞልቶ በድፍረት
በአንድ ላይ መዘመር ጀመርን። እኛ ጮክ ብለን ስንዘምር ከእኛ ጋር ለመ
ፎካከር ሼኩ ጮክ ብሎ ቁራንን ያነብ ነበር።

በማማረር ፈንታ በደስታ መከራን መቀበል እንዳለብን እየተረዳን
ስንመጣ፣ የመንፈሳዊ ሕይወት አቋማችን፣ የሚሰማን የውስጥ ሰላም እየ
ታደሰ መጣ። ቀደም ሲል ስለደረሰብን መከራና ችግር ሁልጊዜ ራሳችንን
ወይም ሌሎችን ምክንያት እያደረግን እናማርር ነበር። የተሸናፊነት
ስሜት እየተሰማን ቁጭ ብለን ለራሳችን እናዝንና እናለቅስ ነበር። "ይሄ
ሁሉ መከራ የሚደርስብን ምን ክፉ ነገር አድርገን ነው" እያልን መከራ
ችንን እንቆጥርን እናማርር ነበር። በእግዚአብሔር ቃል መጽናናት ስንጀ



ምር ግን ራሳችንንና እንዲሁም ሌሎችን መውቀሳችንን አቁመን ስለ ክር
ስቶስ መከራ ልንቀበል እንደሚገባን ስንገነዘብ፣ ያለንበትን ሁኔታና እንዲ
ሁም እንድንበላ የሚሰጡንን የሚዘገንን ምግብ ጭምር በደስታ መቀበል
ቻልን። በዚያ ወህኒ ቤት ውስጥ ሦስት ወር ያህል እንደቆየን ከእስረኞች
መካከል አንዱ ክርስቲያን መሆኑን ተረዳን። ያ ሰው ከእኛ የተሻለ ነጻነት
ስለነበረው አንድ ቀን ተጨማሪ ምግብና አዲስ ኪዳን ይዞልን መጣ።
ቃሉን በማንበብ ብዙ ነገር እየተማርን ስንመጣ በሕይወታችን በጣም እየ
ተጽናናን መጣን። ውጪ ያሉት ክርስቲያን ወገኖቻችን መታሰራችንን
ሰምተው በኃይል ይጸልዩልን ጀመር። በዚህ ወቅት ወህኒ ቤት ስንገባ የለበ
ስነው ልብስ በላያችን ላይ የተቀዳደ መሆኑን፣ እንዲሁም በቂ የሚሆን
ምግብ እንደማናገኝ ሰምተው፣ ወገኖቻችን ልብስ፣ ተጨማሪ ምግብ ልከ
ውልን ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ አንዱም አልደረሰንም።

አንድ ቀን የወህኒ ቤት ጠባቂው ከታሰርንበት ክፍል ውስጥ አው
ጥቶ አንድ ሰፊ ክፍል ውስጥ አስገባን። እዚያ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ
ይጠብቀን የነበረ አንድ ሰው "እኔ እናንተን የምወክላችሁ የሕግ ጠበ
ቃችሁ ነኝ። ጀርመንና ፈረንሳይ ያሉት ወንድሞቻችሁ እናንተን እንድ
ወክላችሁ ቀጥረውኛል" በማለት ራሱን አስተዋወቀን። ጀርመንም ሆነ
ፈረንሳይ ማንንም ስለማናውቅ ነገሩ ጥርጣሬ ውስጥ ከተተን። መጠራ
ጠራችንን ተገንዝቦ በፈገግታ እርሱ እስላም እንጂ ክርስቲያን አለመሆኑን
ነገረን። ይሁን እንጂ፣ እኛን ለመወከል ሌሎች ጠበቃዎች የማይቀበሉ
ትን ኃላፊነት በመቀበሉ ብዙ ገንዘብ እንደተከፈለው ተረዳን። በአጭር
ጊዜ ውስጥ ከእስር ቤት እንደሚያስወጣን አረጋገጠልን።

ከሁለት ሳምንት በኋላ እኛና ሌሎች ሰባት ሰዎች ፍርድ ቤት ቀረ
ብን። ከዳኛው ፊት ለመቅረብ ተራችን ሲደርስ፣ ጉዳያችን በዝግ ችሎት
እንዲታይ ወደ ሌላ ክፍል ተወሰድን። አቃቤ ሕጉ የፈጸምነውን ወንጀል
ለዳኛው ሲገልጽ፣ "እስልምናን ሲሰድቡና ሲያቃልሉ፣ እንዲሁም እስላ
ሞችን ወደ ክርስትና እምነት ለመለወጥ ሲሞክሩ ተይዘዋል" በማለት የተ
ከሰስንበትን ምክንያት ተናገረ። ከእስልምና ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተ
ለወጥን መሆናችንን ለዳኛው ጨምሮ ገለጸ። የዋናው ጠበቃችን እረዳት

የሆነው ሰው፣ የቀረበብንን ክስ በመቃወም ያደረግነው ነገር ሁሉ ሕጋዊ መሆኑን ገለጸ። የተገኘብንም መጽሐፍ ሕጋዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የግብጽ አብያተ ክርስቲያናት መማክርት ጉባኤ የተቀበለው መሆኑን፣ አስፈላጊም ከሆነ ከጽሕፈት ቤቱ ይህንኑ የሚገልጽ ደብዳቤ ማቅረብ እንደሚችል ተናገረ።

በዚህ ወቅት ምንም ዓይነት ጥያቄ አልተጠየቅንም። ጉዳያችንን ለማቅረብና ለመስማት የወሰደው ጊዜ በጠቅላላው ከአምስት ወይም ከስድስት ደቂቃ አይበልጥም ነበር። ዳኛውም እስራታችን እንዲቀጥል ፈረደ። ይሄም ፍርድ ከምንጊዜውም የበለጠ ስብርብራችንን አወጣው። ይሁን እንጂ፣ በዚያ ሁኔታ ውስጥ የተማርነው ነገር ቢኖር፣ በጠበቃችን ላይ ሳይሆን በጌታ ላይ ብቻ መታመን እንደነበረብን ነው። ከዚህ በኋላ የእስር ቤት ሁኔታችን በመጠኑም ቢሆን የተሻሻለ ሆነልን። በቀን ውስጥ ስድስት ሰዓት ያህል ከክፍላችን ውጪ እንድንወጣ፣ ገላችንን እንድንታጠብ፣ ጥርሳችንን እንድንቦርሽ ጠበቃችን አስፈቀደልን። በዚሁ መሠረት ጠበቃችን ፒጃማ፣ ምግብ አመጣልን። ለሚያስፈልገን ነገር እንድንጠቀምበት ገንዘብ ለወህኒ ቤቱ ኃላፊዎች ሰጠልን። ከዚህ በኋላ የወህኒ ቤት ጠባቂዎችም የምንጠይቀውን ነገር ገዝተው ያመጡልን ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ፍርድ ቤት ቀረብን። ጠበቃችንም ከነበርንበት ክፍል መጥቶ "እነዚያ ከዳተኞች የትኞቹ ናቸው?" ብሎ ሲጠይቅ፣ እኛ መሆናችንን ምልክት ሰጠነው። እስልምና ትክክል ነው ብለን ከተናገርን ወዲያውኑ ከእስር ቤት መውጣት እንደምንችል ነገረን። እኛ ግን ፈቃደኞች አለመሆናችንን ገልጸንለት እስራታችን ቀጠለ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ ፍርድ ቤት ቀረብን። በአሁኑ ወቅት ሌሎች እስረኞች በሌሉበት፣ ወይም በዝግ ችሎታ፣ ጠበቃችን ባለበት፣ ከሌላ ዳኛ ፊት እንድንቀርብ ሆነ። አቃቤ ሕጉ የተከሰስንበትን ምክንያት በጽሁፍ አቀረበ። አቃቤ ሕጉ ስለ እኛ ብዙ ክፉ ነገር በመናገር ዳኛውን ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት አደረገ። ኃይለኛ ሁከት ቀስቃሾች እንደ ሆንን፣ በሌባኖን ላይ በደረሰው ዓይነት ሁኔታ ግብጽን ለማጥፋት የመጣን ወንጀለኞች እንደሆንን አድርጎ አቀረበን። አቃቤ ሕጉ ላቀረበብን ክስ



ጠበቃችን ሁለት ፍሬ ሀሳቦችን ጠቀሰ። አንደኛው፣ ሰው ሁሉ፣ የውጪ አገር ሰዎችንም ጭምር የፈለጉትን ሃይማኖት የማምለክ ነጻነት ሊኖራቸው እንደሚገባ በተደረገው ዓለም አቀፍ ስምምነት ግብጽም የፈረመች በመሆኗ፣ ያንንም ስምምነት ማክበር እንዳለባት፣ ሁለተኛ ግብጽ ይህን የፈረመችበትን ስምምነት እንደማታከብር ዓለም የሚያውቅ መሆኑን ነው። ይህም አባባል እውነት እንደሆነ የፈረንሳይ ጋዜጣ ላይ የተጻፈውን ጽሁፍ አነበበ። እንዲሁም የሃይማኖት ነጻነት ለሕዝቡ መሰጠት እንዳለበት የሚደግፈውን የግብጽን፣ የቱኒሲያንና የሞሮኮን ሕገ መንግሥት አነበበላቸው። ጠበቃው የራሱ እምነት እስልምና እንደሆነ፣ እኛ የተቀበልነውን እምነት እንደማይቀበል፣ ያም ሆኖ የእርሱ አቋም በእኛ ላይ ሊያስፈርድብን የሚችል እንዳልሆነ ተናገረ።

አቃቤ ሕጉ ሃይማኖቱን የካደ በሞት መቀጣት አለበት የሚለውን የእስላምን ሕግ ጠቀሰ። ጠበቃችንም ቁራን ይህንን እንደማይል ተናገረ። በሞት መቀጣት ያለባቸው ግብዞች እንደሆኑ፣ እነርሱም ከነበሩት ሃይማኖት ወደ እስልምና ከተለወጡ በኋላ እንደ ገና ቀድሞ ወደነበሩበት እምነት የተለወጡትን እንደሆነ ገለጸ። ስለዚህ፣ በየትኛውም ሕግ፣ በዓለም አቀፉ፣ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትም ሆነ በእስላም ሕግ መሠረት እነዚህ ሰዎች ያለአግባብ የታሰሩ ናቸው ብሎ በግልጽ ተናገረ። በተጨማሪም ፖሊሶች ያለአግባብ፣ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ እንዳሰቃዩዋቸው ገለጸ። ይሄም ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ የግብጽን ስምና ዝና እንዳበላሸ ተናገረ።

ይህንን ኃይለኛ ንግግር ሲሰማ ዳኛው በጣም ተረበሸ። ይሁን እንጂ፣ በጠበቃችን መታመን እንደሌለብን መንፈሳችን ይመሰክርልን ነበር። ዳኛው ከአማካሪዎቹ ጋር ለመነጋገር እኛንና ጠበቃችንን አስወጣን። ጥቂት ቆይቶ አንድ ሰው መጥቶ ለጠበቃችን አንድ ወረቀት ሰጠው። በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ቃል ሲያነብ ፊቱ ሲጠቁር አይተን መልካም ዜና የሚያበስር እንዳልሆነ ተረዳን። እንደጠረጠርነው ፍርዱ የሚለው፣ ሌላ መመሪያ ወይም (ትዕዛዝ) እስኪወጣ ድረስ ወህኒ ቤት እንድንቆይ የሚያዝ ነበር። እጆቻችን በሰንሰለት እንደታሰሩ እንደ ገና

ወህኒ ቤት ተጣልን። የወህኒ ቤቱ ጠባቂዎች ይገፈትሩንና ያዋርዱን ነበር። አንደኛው በኃይል ጮኾ "ከአጠገቤ በፍጥነት ሂዱ! አለበለዚያ ተኩሼ እገድላችኋለሁ" አለን።

በዚህ ሁሉ ውስጥ በጌታ ያለን እምነት ከምንጊዜውም የበለጠ የበረታ ነበር። ወህኒ ቤት ውስጥ ትንሽ ተሻሽሎ የነበረው ሁኔታችን ከዚህ በኋላ የበለጠ የከፋ ሆነብን። ለሽንት ካልሆነ በስተቀር ወደ ውጪ እንዳንወጣ ተደረገ። ከውጪ ምግብ የሚመጣልን ቆመ። ያንን የተላ ሩዝና ባቄላ እንድንበላ ተገደድን። በዚህ ውስጥ አንድ እንደ በረከት የቆጠርነው ነገር ሆነልን። ይኸውም ቀድሞ የነበረው ሼክ ወደ ሌላ ወህኒ ቤት ስለተዘዋወረ፣ ያ ሰው ያሳየን የነበረው ጥላቻና ፋታ የማይሰጥ ሰበካው የቀረልን መሆኑ ነው። የግብጽን ሕግ መሠረት በማድረግ ምንም ያህል ሙከራ ብናደርግ ነጻነታችንን ማግኘት አልቻልንም። የወህኒ ቤት ቆይታችን እየረዘመ ሲመጣ፣ ሁኔታችን በውጪው ዓለም እየተሰማ መጣ። የግብጽ መንግሥት ነጻነታችንን መስጠት እንዳለበት ዓለም አቀፍ የሆነ ግፊት በደብዳቤ ከየስፍራው ይመጣለት ነበር። ሁለት የአሜሪካ የኮንግሬስ አባሎች ዋሽንግተን ላለው የግብጽ አምባሳደር ደብዳቤ ጻፉለት። ከዚህ በኋላ ጉዳዩ ከፍርድ ቤት እጅ ወጥቶ በግብጽ መንግሥት እጅ ላይ ወደቀ። ይህ የውጪው ግፊት የእኛን ሁኔታ ለወጠው። የወህኒ ቤቱ ጠባቂ መጥቶ ከታሰርንበት ክፍል አውጥቶ በአስቸኳይ ከአገር እንድንወጣ ወደሚመለከተው የመንግሥት አካል አስተላለፈን።

ይሁን እንጂ፣ የእኛ ችግር እዚያ ላይ እንዳላበቃ ተገነዘብን። በዚህ ሁኔታ ወደ ሞሮኮና ወደ ቱኒስያ ብንመለስ ምን እንደሚደርስብን መረዳት ከባድ አልሆነብንም። በእነዚህ አገሮች ውስጥ እንደ ግብጽ የክርስቲያኖች ሕብረት አምላካቸውን ለማምለክ ነጻነት እንደሌላቸው እናውቃለን። ስለዚህ ወደ አገራችን ብንመለስ፣ ቀለል ካለ እሳት ወጥተን፣ ወደ ኃይለኛው እሳት መግባታችን እንደሆነ ተረዳን። ከወዳጆቻችን አንዱ ዘንድ ስልክ እንድንደውል እንዲፈቅድልን የወህኒ ቤት ዘበኛውን ጠየቅ ነው። በዚያ ሁኔታ እኛን ሊቀበለን ፈቃደኛ የሆነ አገር ለማግኘት ብዙ ሞክረን አልተሳካልንም። በመጨረሻ አንድ ቀን የት እንደምንሄድ ሳናውቅ ወደ



ካይሮ ኤርፖርት ተወሰደን። የት ሊወስዱን ነው ብለን ስናስብ ምንም ነገር ሳይነግሩን ፈረንሳይ አይሮፕላን ውስጥ አስገቡን። እጆቻችን በሰንሰለት እንደታሰረ መቀመጫው ላይ ገፍተው አስቀመጡን። ወዲያው የታሰርንበትን ሰንሰለት ከእጃችን ላይ ፈትተው ወደ አዲሱ ቤታችን፣ ይኸውም ወደ ፈረንሳይ አገር አመራን።

በግብጽ አስከፊ በሆነው ወህኒ ቤት በቆየንበት ጊዜ፣ በብዙ መከራ ውስጥ ብናልፍም፣ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚጠቅመንን ሰፊ ትምህርት ተምረንበታል። "ለምን ይሄ በእኛ ደረሰ!" ብለን አናማርርም። በመከራችን ውስጥ ጽናት የሆነልን፣ ትዕግሥትን የሰጠን፣ በስጋዊ ዓይናችን አንየው እንጂ፣ በወቅቱ አንረዳው እንጂ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደ ነበረ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ነን። በመከራችን ወቅት እንዴት መጸለይ እንዳለብን፣ እንዲሁም ጸሎት ለነፍሳችን ምግብ እንደ ሆነ ተምረናል። ወህኒ ቤት እንድንጣልና ያን ሁሉ መከራ እንድንቀምስ ያደረጉንን ሰዎች በመጥላት ፈንታ መውደድና እንዲሁም ይቅርታ መስጠት እንዳለብን ተምረናል። ወህኒ ቤት በተጣልንበት ወቅት፣ በሰዎች ቁጥጥር ውስጥ የዋልን፣ ነጻነት የሌለን እስረኞች ብንሆንም፣ ጌታ ኢየሱስ ከኃጢአት ባርነት ነጻ ያወጣን ነጻ ሕዝቦች መሆናችንን አልተጠራጠርንም። የምንበላው የዕለት ምግብ የሌለን ብንሆንም፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለጸጋ መሆናችንን አወቅን።

መከራ፣ ስደት፣ እስራትI በመጨረሻም ሞት የሚለውን ቃል የዘመኑ ክርስቲያኖች ስንሰማ ያስደነግጠናል። ባለን ጥበብና ዘዴ ከእነዚህ አስፈሪ ነገሮች ሸሽተን መኖር እንፈልጋለን። የመስቀሉ ምስጢር የገባው ጳውሎስ ግን የልቡን ፍላጎትና ምኞት ሲገልጽ፣ *"...የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንደመሰለው እመኛለሁ..."* ይላል (ፊልጵ. 3፥11)። ጳውሎስ ይህን ለመናገር ያህል የተናገረው ሳይሆን፣ ከልቡ የተጨመቀ እውነት ነው። በሕይወቱም አስመስክሯል።

## 4. የሁላችንም የእምነታችን ጽኑነት በመከራ ይፈተናል

የእኔና የእናንተ የእምነታችን ጽኑነት እንደ ሌሎች ከሃነፍሳችን በእሳት መቃጠል፣ በሰይፍ በመታረድ፣ በዘይት ውስጥ በመቀቀል፣ በአውሬዎች ተበጣጥሶ በመጣል፣ በመጋዝ ለሁለት በመሰንጠቅ፣ በወህኒ ቤት ለረጅም ጊዜ ተጥለን በብዙ ስቃይ ውስጥ በማለፍ ላይፈተን ይችላል። የክርስትና ሕይወትን በተደላደለና በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ መኖር የሚሞክሩ የብልጽግና ወንጌል አስተማሪዎች፣ ያለመስቀል የክርስትና ሕይወትን መኖር ይቻላል ብለው ያስተምሩ እንጂ፣ እውነተኛ ክርስቲያኖች ከሆንን ከመስቀል ሕይወት ውጪ መኖር እንደማንችል ማወቅ ይገባናል። እርግጥ ነው፣ የሁላችንም መስቀል እኩል አይደለም። በዓይነቱና በመጠኑ ይለያያል። መስቀላችን ስለ ሌላው ሰው በጎነት ስንል የሚደርስብን መጠላት፣ መገፋት ወይም በድህነት መሰቃየትና መንሳቆል ሊሆን ይችላል። እርግጠኛ መሆን ያለብን ነገር ቢኖር፣ እግዚአብሔር ከአቅማችን በላይ የሆነ መስቀል የማያሸክመን መሆኑ ነው። ሁላችንም የራሳችን መስቀል ካለን፣ የተሸከምነው መስቀል ትልቅ ከመሰለን፣ ያንን የሰጠን "መሸከም ትችላላችሁ" ማለቱ ስለሆነ፣ ይህን ያህል የታመነብንን አምላክ ሳናጉረመርም መስቀላችንን ተሸክመን በደስታ ልንከተለው ይገባል። የተሸከምነው መስቀል ካሰብን ደግሞ፣ እርሱ ያልሰጠንን ሌላ መስቀል ተሸክመን ለመሄድ አንሞክር። ይህ ከሆነ ያለአግባብ ራሳችንን እንጎዳለን።

መስቀል እኔና እናንተ በራሳችን ኃጢአት የምንቀምሰው የመከራ ጽዋ አይደለም። ቀደም ሲል እንደገለጸነው፦

- *አንድ አማኝ ክርስቶስን በመከተሉ፣ ፍጹም ታዛዥ በመሆኑ፣ ሕይወቱን በቅድሳና በመምራቱ ምክንያት የሚደርስበት ሰቃይ ያ መስቀል ነው።*
- *በመታዘዝ ጎዳና ላይ ሁልጊዜ መስቀል አለ።*

"መስቀል ወይም መከራ አጋጥሞኝ አያውቅም" የሚል ክርስቲያን ቢኖር፣ ያ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን መሆኑ ያጠራጥራል። መስቀልን



በመሸከም ውስጥ ምን እንዳለ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፣ *"ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ የሚለው ቃል ለሚጠፉት ሰዎች እንደ ሞኝነት ይቆጠራል፤ ለምንድን ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው"* ይላል (1 ቆሮ. 1፥18-25)። የመስቀሉ ኃይል ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለጌታ እንድንሰጥ ያስችለናል። ራሱን በሞት ለሰጠ አምላክ ራስን መስጠት አያስቸግርም። የመስቀሉ ኃይል ለአምላካችን ታማኞች እንድንሆን ኃይልን ይሰጠናል። የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው አማኞች ለሞተላቸው አምላክ በእሳት ተቃጥለዋል፤ በዘይት ተቀቅለዋል፤ በአውሬዎች ተበልተዋል፤ በመጋዝ ተሰንጥቀዋል። ያንን መራር የሞት ጽዋ ለመጠጣት ኃይልን ያገኙት የመስቀሉ ትርጉም ስለገባቸው ነው። ዛሬ ወንጌል ለእኔና ለእናንተ ሊደርሰን የቻለው ብዙዎች በታማኝነት ዋጋ ስለከፈሉበት እንደሆነ ደጋግመን ገልጸናል። እኛም የብዙዎች ደም የፈሰሰበትን፣ ብዙ ዋጋ የተከፈለበትን ወንጌል ተቀብለን፣ ለሚቀጥለው ትውልድ በተራችን ዋጋ ከፍለን ልናስተላልፍ ይገባል። ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን። አሜን!

# 6

# በመስቀሉ፥ ታዛዥነታችን ይረጋገጣል

*“የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ”*
*(ዕብ. 5፥8)*

*“...እስከ ሞት ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ”*
*(ፊልጵ. 2፥8)*

ደቀ መዝሙርነትን ከሚገልጹ ነገሮች መካከል አንደኛው ታዛዥነት ነው። ደቀ መዝሙሩ እየመረጠ ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ ለመምህሩ ፍጹም ታዛዥ መሆን አለበት። ሰው እግዚአብሔርን የሚታዘዘው ዩኒቨርስን የፈጠረ ኃያል ጌታ በመሆኑና እንዲሁም ስላሳየው ምሕረትና ቸርነቱ ምስጋናውን የሚገልጽበት በመሆኑ ነው። ኢየሱስ፣

➔ *“ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ”* ይላል (ዮሐ. 14፡15)።

ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር ተግባራዊ የሚያደርጉት፣ ቃሉን የሚታዘዙት ብቻ ናቸው። ሳይታዘዙት *“እንወድሃለን”* ቢሉት፣ ፍቅራቸው እውነትነት ያለው አይደለም። ንስሀ ገብተን ስንከተለው፣ ለእርሱ ያለንን ፍቅር ማሳየታችን ነው። የውሃ ጥምቀት ስንወስድ *“ለራሳችን መሞታችን”* ማሳየታችን፣ እንዲሁም ክርስቶስን የሕይወታችን ጌታ ማድረጋችን ነው።



ይህን ዓይነቱ ታዛዥነት የደረስንበትን መንፈሳዊ ዕድገት የሚያመለክት ነው። ይሄም እስከ ሞት ድረስ መታዘዝ እንዳለብን የሚያሳይ ሲሆን፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣

➔ *“ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል” ይላል (ሮሜ 6፥3-4)።*

የክርስትና ሕይወት አማኝ በሕይወቱ በሂደት መታዘዝን እየተለማመደ የሚያድግበት ሕይወት ነው።

ወታደርነት፣ ሙሉ መታዘዝ ያለበት ሕይወት እንደሆነ የታወቀ ነው። ተራ ወታደሮች ለሃምሳ አለቃው የሚያሳዩት ሙሉ መታዘዝ የሚያስደንቅ ነው። ሌሊት አስነስቶ “ሩጡ!” ሲላቸው፣ ይሮጣሉ። “ተቀመጡ!” ሲላቸው ይቀመጣሉ። “ሽንት ቤት አጽዱ” ሲላቸው፣ ያጸዳሉ። ትዕዛዙን ለመፈጸም ማመንታት፣ መከራከር፣ “እምቢ!” ማለት አይችሉም። የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ወዲያው መፈጸም አለባቸው። ተራ ወታደሮች ሃምሣ አለቃውን የሚታዘዙት፣ እርሱ የመቶ አለቃውን በመታዘዙ ነው። መታዘዝና ትዕዛዙን መቀበል ከተራ ወታደሩ እስከ ጄኔራሉ ድረስ የሚደርስ ነው። ተራ ወታደሩ የሃምሣ አለቃውን ትዕዛዝ “ዕምቢ!” ቢል፣ የጄኔራሉን ትዕዛዝ “ዕምቢ!” እንዳለ ይቆጠራል። ይሄም ከፍተኛ ቅጣት ያስከትላል። በጦርነትም ሆነ በሰላም ጊዜ ደህንነታቸው ሊጠበቅ የሚችለው በመታዘዛቸው ነው። የማይታዘዘውን ወታደር ጦር ሜዳ መውሰድ በራሱም ሆነ በሌሎች ወታደሮች ላይ አደጋ እንዲደርስ መፍቀድ ይሆናል።

በውትድርና ዓለም ውስጥ ወታደሩ አለቃውን የሚታዘዝበት ምክንያት ብዙ ጊዜ ከፍርሃት የተነሳ ሲሆን፣ ክርስቲያን ግን ጌታውን የሚታዘዝበት ምክንያት ከፍቅር የተነሳ ነው። የክርስቲያኖች የመንፈሳዊ ዕድገት የተመሠረተው በመታዘዝ ውስጥ ነው። ያም መሆን የሚችለው በአማ

ኞች ሙሉ የመሰጠት ሕይወትና በቃሉ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። ኢየሱስ፣

➔ *"...ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው" አለ (ሉቃ. 11፡28)።*

ፈቃዱን ሳያዉቁ እግዚአብሔርን መታዘዝ ትልቅ ድፍረትን የሚይጠይቅ ነው። ምን ማድረግ እንዳለባቸው በትክክል ሳንነግራቸው፣ ልጆቻችንን *"ያዘዝናችሁን አልፈጸማችሁም"* ብለን ብንቀጣቸው፣ ትክክል ስላልሆንን በማስቆጣት እናስመርራቸዋለን (ኤፌ. 6፡4)። እግዚአብሔር ግን እንደ ሰው ፍርደ ገምድል አይደለም። በቃሉ ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለብን በግልጽ አስቀምጦልናል። ኢየሱስ *"በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፣ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል" ይላል (ዮሐ. 8፡31)።* የእኛ ኃላፊነት ቃሉን በጥንቃቄ መመርመር ነው።

## 1. በመከራ ውስጥ መታዘዝን እንማራለን

ክርስቶስን ማወቅና በመከራው እርሱን መምሰል፣ መታዘዝን መማር ነው። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ያነበብነው ዕብ. 5፡8 ላይ *"...የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ"* ይላል። *"የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም መታዘዝን ይማራል፤ የሚማረውም በመከራ ውስጥ ነው"* የሚለው ሀሳብ ለብዙዎቻችን አዕምሮ በጣም ተልቆብን ግራ መጋባታችን አይቀርም። መታዘዝን መማር ያለበት የማይታዘዝ ሰው ብቻ መሆን አለበት ብለን ስለምናስብ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ታዛዥ ስለሆነ፣ መታዘዝን መማር አያስፈልገውም" ማለታችን አይቀርም። ነገር ግን በመታዘዙ ላይ የሚጠበቅበት ነገር ወይም ኃላፊነቱ እየጨመረ ሲመጣ፣ መታዘዝ ምን እንደሆነ ሙሉ መረዳትን ይሰጣል። በመምሕሩና በተማሪው መካከል የተቀራረበ ግንኙነት ሲኖር፣ መታዘዝን ቀላል ያደርገዋል።



- *"ክርስቲያን ደቀ መዝሙርነት፣ በክርስቶስና በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያለውን ሞዴል የያዘ፣ በመምሕሩና በተማሪው መካከል ያለ ቅርብ ግንኙነት ሲሆን፣ መምሕሩ በክርስቶስ ውስጥ ያገኘውን ሙሉ ሕይወት በተማሪው ሕይወት ውስጥ በመፍጠር፣ ተማሪውም ራሳቸውን ማባዛት የሚችሉትን ሌሎች ሰዎችን ማፍራት እንዲችል ማብቃት ነው።"*[9]

አለመታዘዝ የሰውን ኃጢአተኛነት ይገልጻል። ይኸውም፣ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል ፈንታ የራሳችንን መንገድ እንከተላለን። እግዚአብሔር "መንገዱ ይሄ ነውና በዚህ ሂዱ" ሲለን፣ ፊታችንን ወደዚያ አቅጣጫ እንመልሳለን። ኢየሱስ ለእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ራሱን ሙሉ በሙሉ በመስጠት *"መታዘዝን"* አስተማረን። ፍጹም የሆነ መታዘዝን ያሳየው እርሱ ብቻ ነው። ኢየሱስ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር አብን፣ *"የእኔ ሳይሆን፣ የአንተ ፈቃድ ይሁን"* አለ። ይህን ማለት ቀላል አይደለም። ከዚያ የበለጠ ከባድ የሚሆነው ደግሞ ማድረጉ ነው። በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል፣ በፈቃዱና በፈቃዳችን መካከል በሚኖረው ትግል፣ ፈቃዱን እስክንፈጽም ድረስ መከራው ይቀጥላል።

የመጀመሪያው ሰው፣ አዳም ባለመታዘዙ ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት አበላሸ። በሁለተኛው አዳም፣ ይኸውም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ታዛዥ መሆን፣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የፈረሰ ግንኙነት እንደ ገና ተሠራ። የማይታዘዘው ኃጢአተኛው ሰው፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ። ክርስቶስ ታዛዥ በመሆን፣ እኛንም ታዛዥ እንድንሆን ረዳን። በመከራ ውስጥ የምንማረው ታዛዥነት፣ ፈቃዳችንና ሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እስኪመስል ድረስ በሂደት የምንማረው ነው። በክርስቶስ መከራ ውስጥ ኅብረት ሲኖረን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ሙሉ ታዛዥነት እንደርሳለን። ስለዚህ እኔና እናንተ ከመከራና ከስቃይ ሸሽተን ለመኖር ራሳችንን ስንደብቅ፣ ስለ እምነታችን ስንል ዋጋ ለመክፈል እምቢ ስንል፣

[9] Dr. Keith Philips. The Making of a Disciple, Fleming H. Revell Co. Old Tappan, New Jersey, 1968.

እግዚአብሔርን በሙሉ መታዘዝ ውስጥ የሚገኘውን እውነተኛ ዕውቀት፣ እውነተኛ የሆነውን መንፈሳዊ ዕድገት እንፈልግም ማለታችን ይሆናል።

ለእግዚአብሔር ታዛዥ ሆነው በመቆም፣ በመከራቸው ክርስቶስን የመሰሉ፣ እርሱ የቀመሰውን መከራ የቀመሱ፣ እርሱ የሞተውን ዓይነት ሞት የሞቱ፣ እውነተኛ የእምነት አርበኞች በዓለም ዙሪያ ይገኛሉ። የሃይማኖት ነጻነት ባለበት አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች፣ ምንም ዓይነት መከራና ስደት በእነርሱም ሆነ በሌሎች ላይ ሲደርስ አይተው ስለማያውቁ፣ የሃይማኖት ነጻነት የሌለበት፣ ኃይለኛ የፖለቲካ ትዕዕኖ ባለበት አገር ውስጥ ክርስቲያን ሆኖ መኖር፣ ባመኑት ነገር ጸንቶ መቆም ምን ዓይነት ድፍረትና ቆራጥ መንፈስ እንደሚጠይቅ መረዳት አይሆንላቸውም።

## 2. ጌታውን በመታዘዙ ምክንያት በመከራ ውስጥ ያለፈ

*የሃይማኖት ነጻነት ከሌለባቸው ብዙ አገሮች መካከል አንደኛው ኔፓል ነው። የኔፖል አገር ተወላጆች የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ፣ ሃይማኖታቸውን ቢለውጡ፣ የሐገሪቱን ሕግ እንደጣሱ በመቆጠር ፍርድ ቤት ቀርበው በእስራት ይቀጣሉ። ወደ ክርስትና ሕይወት የመጡ አማኞች፣ የፈለጉትን ለማመን ነጻነት ሊኖራቸው ሲገባ፣ በአገራቸው ውስጥ ነጻነት በማጣት በእምነታቸው ምክንያት ከፍተኛ ስደትና መከራ ይደርስባቸዋል።*

*ጌታቸውን በመታዘዛቸው ምክንያት በከፍተኛ መከራና ስደት ውስጥ ካለፉት የእምነት አርበኞች መካከል አንደኛው ፕሬም የተባለው የኔፓል ተወላጅ ሲሆን፣ አንዳንዶች "የኔፓሉ ሐዋርያ" ብለው ይጠሩታል። ይህ ሰው የያዘውን እምነት አልለቅም በማለቱ አሥራ አራት ጊዜ በተለያዩ ወህኒ ቤቶች ውስጥ ታስሮ ብዙ ስቃይ የደረሰበት ሰው ነው። መጀመሪያ መታሠር የጀመረው፣ አምስት ወንዶችንና አራት ሴቶችን ወደ ክርስትና እምነት አምጥቶ በውሃ ካጠመቃቸው በኋላ ነው። እነዚህ ከእስልምና ወደ ክርስትና የመጡ ዘጠኝ አማኞች፣ "ሃይማኖታችሁን*



*ለውጣችኋል" በመባል ከእርሱ ጋር ወህኒ ቤት ተጣሉ። እነርሱ በአንድ ዓመት እሥራት ተቀጥተው ሲለቀቁ፣ ወንድማችን ፕሬም ግን እነዚያን ሰዎች ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ አድርገሃል በመባል ስድስት ዓመት ታሠረ።*

*የኔፓል ወህኒ ቤት በአስከፊነቱ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ነው። ብዙ እስረኞች በየቀኑ ስለሚሞቱ፣ አንዳንዶች "የሞት ወህኒ ቤት" የሚል የቅጽል ስም ሰጥተውት ነበር። ወህኒ ቤቱ ዓየር ማስገቢያም ሆነ ማስወጫ የሌለው፣ የታፈነ፣ በቂ መጸዳጃ የሌለው፣ አካባቢው ጽዳት የጎደለው ሲሆን፣ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ከ25 እስከ ሰላሳ የሚሆኑ እስረኞች እንደ ሠርዲን ተጠቅጥቀው ይኖራሉ። ሽታው እጅግ በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ አዲስ እስረኞች በገቡ በማማሽ ሰዓት ውስጥ ራሳቸውን ስተው መሬት ላይ ይወድቃሉ። በክረምት ወራት ብርዱን፣ በበጋ ወራት ሙቀቱን፣ ብርቱ ነው የተባለው ሰው እንኳን ታግሶ ሊወጣው የሚችል አይደለም። ትንኙ፣ ዝንቡ፣ ተባዩ ፍጹም ሌላ ነው። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ዓይጦች ከመኖራቸው የተነሳ እስረኞቹ ሲተኙ አውራ ጣታቸውን እየነከሱ ኢያስተኟቸውም ነበር። በዚህ ምክንያት ነው ጤናማ ሆነው የገቡ እስረኞች በአጭር ጊዜ ውስጥ እየሞቱ ሬሳቸው እየተጫነ የሚወጣው። የሚያስደንቀው ግን እነዚያ ክርስቲያን በመሆናቸው ምክንያት አንድ ዓመት የታሠሩት ዘጠኙ ክርስቲያኖች በዚህ እስር ቤት ውስጥ ከሞት አምልጠው ከነህይወታቸው የወጡ መሆናቸው ነው። አንድ ዓመት ታስረው ሲፈቱ ከሳሾቻቸው እንደ ጠበቁት የክርስትና እምነታቸውን በመተው ፈንታ የበለጠ ጠንካራ ክርስቲያኖች ሆነው ወጡ። ያለፉበት መከራ የመንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ አሳደገላቸው እንጂ፣ ከተቀበሉት እምነት አላራቃቸውም።*

*በመጀመሪያው ወህኒ ቤት በወንድማችን ፕሬም ላይ የጠበቁትን ዓይነት የመንፈስ ስብራት ስላላዩ፣ እጅግ በጣም የከፋ ነው ወደ ሚባለው ወህኒ ቤት ወስደው አሰሩት። ሌሎችን እስረኞች በእም*

ኑቱ ይበርዛችዋል ብለው በመፍራት፣ ምንም ዓይነት ብርሃን በማይገባበት ጨለማ በሆነ ክፍል ውስጥ ለብቻው አስረው አስቀመጡት። ይህን ያደረጉት በአጭር ጊዜ ውስጥ አዕምሮውን ይስታል ብለው በማሰብ ነበር። ይሁን እንጂ፣ የጠበቁትን ዓይነት ውጤት ባለማየታቸው፣ የወህኒ ቤቱ ኃላፊዎች ኃይሉንና ጽናቱን የሚያገኘው ከየት ነው በማለት በመደነቅ ይጠይቁ ነበር። ለብቻው የታሰረበት ክፍል በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ፣ ከመቀመጥ በስተቀር መቆም ወይም መሬት ተዘርግቶ መንጠራራት እንኳን አይችልም ነበር። ምግቡን አብስሎ መብላት ስለማይችል ሌሎች እስረኞች በበሩ ሥር ምግብ እያቀበሉት ይመገብ ስለ ነበር፣ እንደጠበቁት ቶሎ ሳይሞት ቀረ። የውስጥ ልብሱን ቅማል ወሮት ሲበላው፣ እጆቹ በሰንሰለት በመታሠራቸው ምክንያት የበላውን ቦታ እንኳን ማከክ አይችልም ነበር። የታሠረበት ሠንሠለት ቁርጭምጭሚቱን እየበላ ሥጋውን ልጦ አጥንቱ ይታይ ነበር። በክረምቱ ወራት በብርድ እየደነዘዘ ብዙ ጊዜ ለሞት የተቃረበበት ጊዜ ነበር። ለብቻው ጨለማ ክፍል ውስጥ ቢታሠርም አሁንም እነርሱ እንደጠበቁትና እንዳሰቡት አዕምሮውን አልሳተም። ከአንዱ ወህኒ ቤት ክፉ ነው ወደሚሉት ወደ ሌላው ወህኒ ቤት ያንከራትቱት ነበር። ይሁን እንጂ፣ በሄደበት ወህኒ ቤት ሁሉ፣ ለወህኒ ቤት ዘበኞችና ለእስረኞች ስለ ጌታ ኢየሱስ ይመሰክር ነበር።

"ለጌታው ምን ዓይነት ኃይለኛ ፍቅር ቢኖረው ነው፣ ሳያማርር ስለ አዳኝነቱ የሚመሰክረው" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ከሳሾቹ ምንም ማድረግ ሲያቅታቸው መጨረሻ ላይ ፈቱት። ሲፈታም "ሁለተኛ አልመሰክርም፤ ስለ ክርስቶስ አልናገርም" ብሎ ቃል ገብቶ ሳይሆን፣

- ❖ "መመስከሬን አላቆምም፤ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ የማደራጀው በድብቅ ወይም በስውር ሳይሆን፣ በግልጽ ነው" ብሎ ተናግሮ ነው። ይህን ሲል መልሰው አሰሩት። "ክርስቲያን ሆኖ ዝም ማለት እንዴት ይቻላል? እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን እንዴት በድብቅ ወይም በስውር ትኖራለች? ክርስቶስ



ለእኛ የሞተው በግልጽ እንጂ በድብቅ ወይም በስውር አይደለም። ከመስቀል ሞት ለማምለጥ ሲል ራሱን አልደበቀም። ስለዚህ እኛም ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለንም ስለ እርሱ በድፍረት መናገር አለብን" ይል ነበር።

ለመሆኑ የዚህን ሰው ቆራጥነትና ድፍረት፣ እንዲሁም ለአምላኩ ያለውን ታማኝነት ስናይና ስንሰማ ምን ይሰማን ይሆን? እኔና እናንተ ጥቂት በጎ ያልሆነ ነገር በሕይወታችን ሲደርስብን የምናሰማው እሮሮ፣ ማጉረምረም፣ በውስጣችን የሚሰማን የተስፋ መቁረጥ ስሜት አያሳፍረንም? ይህን ያህል ዋጋ እየከፈሉ ያስተላለፉልንን ወንጌል፣ እኛም በተራችን ዋጋ ከፍለን ለሌሎች ማስተላለፍ ሲገባን ሥጋዊ ጥቅም ወይም ትርፍ ማግኛ፣ ጸጋውን ርካሽ ስናደርገው አያሳፍረንም?

## 3. ክርስቶስ የቀመሰውን መከራ ለመቅመስ መመኘት ሞኝነት ነው?

ማንኛውም ሰው መልካም ነው ብሎ የሚያስበውን ነገር ለማግኘት ይመኛል። ባለጸጋ ለመሆን፣ በሥራው ላይ ሹመት ወይም ሥልጣን ለማግኘት፣ ያማረና የጣፈጠ ትዳር ይዞ ደስ ብሎት መኖርን ይመኛል። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በጎ ነገሮችን ለማግኘት መመኘት የሰው ሁሉ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። ራሳችንን ካላመመን፣ ወይም አዕምሯችንን ካልሳትን በስተቀር "በሥቃይና በመከራ ውስጥ ለማለፍ እመኛለሁ፤ በመከራ ያለፈ ሰው የቀመሰውን ዓይነት መከራ ለመቅመስ እመኛለሁ" ብለን አንልም። ይሁን እንጂ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክቱ "በስቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱ እርሱን እንድመስል እመኛለሁ" በማለት የልቡን ፍላጎት ገለጸ። ጳውሎስ ይህን የተናገረው ለማለት ያህል ሳይሆን፣ ወይም አዕምሮውን ስቶ፣ የሚናገረውን ሳያውቅ ዝም ብሎ የተናገረው ሳይሆን፣ የሚለውን አውቆ፣ ጤናማ የሆነ አዕምሮውን ተጠቅሞ፣ እንደሚገባው ከልቡ አስቦበት የተናገረው ነው። ይህን ያለው "በመሰቃየት ውስጥ ደህንነት ይገኛል" ብሎ አስቦ እንዳልሆነ

እናውቃለን። ጳውሎስ *"በሥቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱ እርሱን እንድመስል እመኛለሁ"* ሲል፣ በልቡ ውስጥ የሚቃጠለውን ፍላጎቱን መግለጹ ነው። በሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው ይሄንኑ ለመፈጸም ነው።

## 4. ጳውሎስ ክርስቶስን በመከራው ሊመስለው ተመኘ

ጳውሎስ "ክርስቶስን እንዳውቅ" ሲል፣ በታሪክ ማኅደር የተዘረዘረውን የክርስቶስን የሕይወት ታሪክ ማውቅ ማለቱ አይደለም። ማወቅ የሚፈልገው የክርስቶስን የሕይወት ታሪክ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም፣ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን እያሰረ ወህኒ ቤት በሚጥልበት ወቅት፣ ክርስቲያኖችን በሚያሳድድበትም ጊዜ የክርስቶስን ታሪክ በደንብ ያውቅ ነበር። ከእርሱ ጋር እውነተኛ ግንኙነት ስላልነበረው፣ እውነተኛ አማኝ እንደሚያውቀው ግን ከልቡ አያውቀውም ነበር። ለዚህ ነው *"ሳዖል! ሳዖል! ለምን ታሳድደኛለህ?"* ብሎ ሲጠይቀው፣ *"ጌታ ሆይ! ማን ነህ?"* ብሎ መልሶ የጠየቀው። በደማስቆ መንገድ ጌታን ፊት ለፊት ከማግኘቱ በፊት ኢየሱስን በታሪኩ ብቻ ያውቀው ነበር። ጳውሎስ *"ክርስቶስን አውቅ ዘንድ..."* በማለት የተመኘው ግን ይህን ዓይነቱን ዕውቀት ማለቱ አይደለም።

ጳውሎስ የሚለውን ዓይነት ዕውቀት ለማግኘት የሚቻለው ታሪኩን በማንበብ ሳይሆን፣ እርሱ ራሱ በሕይወታችን ውስጥ እንዲኖር በመፍቀድ ብቻ ነው። የዚህ ዕውቀት ውጤት የሞቱንና የትንሳኤውን ኃይል መረዳት ነው። ከእርሱ ጋር ሞተን በአዲስ ሕይወት ከእርሱ ጋር እንነሳለን። ጳውሎስ ክርስቶስን እንዳውቅ ሲል፣ እንደኛው በውስጡ ተወልዶ አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ተፈጥሮ፣ አዲስ መንፈስ እንዲኖረው መፈለጉን ነው። ጳውሎስ "ክርስቶስን አውቅ ዘንድ" ብሎ በተናገረበት ጊዜ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ አውቆታል። በደማስቆ መንገድ ክርስቶስን ፊት ለፊት ተገናኝቶት ያወቀውና እንደ አዳኙ የተቀበለው ቢሆንም፣ በዚያ ብቻ ረክቶ መቀመጥ የሚፈልግ ሰው አልነበረም። ሙሉ በሙሉ ለክርስ



ቶስ የተሰጠ፣ ክርስቶስ በእርሱ ሕይወት ውስጥ እንዲኖር፣ የክርስቶስ ምስል በሕይወቱ እንዲቀረጽ በጣም የሚፈልግ ሰው ስለ ነበር፣ በጥልቀት ሊያውቀው እንደሚፈልግ ምኞቱን ገለጸ። ይህ የጳውሎስ ብቻ ሳይሆን፣ የሁላችንም ፍላጎትና ጥማት ሊሆን ይገባል።

ስለዚህ ጳውሎስ *"ክርስቶስን አውቅ ዘንድ፣ በትንሳኤውም እመስለው ዘንድ"* ማለቱ ይህን ያህል አይደንቀንም። ምክንያቱም ይህን ዓይነቱን ዕውቀት ሁላችንም የምንፈልገው በመሆኑ፣ ይህን ነገር መናፈቅና መመኘት እንግዳ አይሆንብንም። ከዚህ የበለጠ እንግዳ የሚሆንብን፣ በቀላሉ የማይገባን፣ ማመን የሚያስቸግረን ግን ሌላ ነገር አለ። ይኸውም በመከራው ክርስቶስን ለመምሰል መፈለግ ወይም መመኘት ነው። ለመሆኑ ጳውሎስ የክርስቶስን መከራ ለመካፈል፣ በመከራውም እርሱን መምሰል ለምን ፈለገ? ክርስቶስን በጥልቀት ማወቅ እንዲሁ የሚገኝ ሳይሆን፣ በመከራ ውስጥ በማለፍ የሚገኝ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። በመከራው መምሰል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በነፍሱ ውስጥ የሚሰማውን የስቃይ ስሜት፣ ውስጣዊ ሀዘኑን፣ ስለ ሌሎች ኃጢአት ሲል መቆርቆሩንና መድማቱን ተካፋይ ለመሆን ፈቃደኛ መሆን ነው።

ጳውሎስ በዚህ ዓይነት የመከራው ተካፋይ በመሆኑ ክርስቶስ ይሰማው የነበረውን ዓይነት ስሜት ነበረው። ለዚህ ነው፣

❖ *"ለወገኖቼ ስል ስለ ወንድሞቼ እኔ ራሴ የተረገምሁና ከክርስቶስም ተለይቼ የተጣልሁ እንድሆን እንኳ እወድ ነበር"* ያለው (ሮሜ 9:3)።

የዓለም አዳኝ የሆነው ክርስቶስ ስለ ዓለም በኃጢአት መጥፋት ምክንያት የሚሰማውን ስሜት መግለጹ ነው። ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር መከራ መቀበልና መሞት ሲል የክርስቶስ መሞት ሁሉን ነገር አያሟላም ወይም በቂ አይደለም ማለቱ አይደለም። ነገር ግን፣ ጳውሎስ የክርስትና ሕይወት ልምምድን ምንጊዜም ቢሆን ከመስቀሉ ለይቶት ስለማያውቅ ነው። ጳውሎስ ለወንጌሉ ሲል ከክርስቶስ ጋር መከራ መቀበሉን እንደ ክብርና እንደ ትልቅ ዕድል እንደ ቆጠረው፣ እኛም እንደ ትልቅ ክብርና ዕድል ልንቆ

ጥረው ይገባል። ክርስቶስ ያደረገልንን ትልቅ ነገር በጥልቀት ለመረዳት የመከራው ተካፋይ ከመሆን የበለጠ ሌላ የተሻለ መንገድ የለም።

ከክርስቶስ ጋር መከራ መቀበል ሕይወታችን ክርስቶስን እንዲመስል ይቀርጸዋል። ከላይ ያየነው ስለ ሌላው መጥፋት በመጨነቅ፣ በመንፈስ ከክርስቶስ ጋር የምንለማመደው መከራና ስቃይ ነው። በስሜትና በሥጋችን የምንለማመደው መከራና ስቃይስ ይኖር ይሆን? በመከራ ውስጥ የሚገኘውን በጎ ነገር ጳውሎስ ሲገልጽ፣

- *"...በመከራችንም ሐሴት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን። ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣ የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን፣ ይህም ተስፋ ለዕፍረት አይደርገንም፤ እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና"* (ሮሜ 5፥3-5) ይላል።

ጳውሎስ *"በመከራችንም ሐሴት እናደርጋለን"* ሲል፣ *ይህን የሚለው እውነት ከልቡ ነው ወይ?"* ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እርግጥ ነው በህመማቸው ደስ የሚላቸው፣ ህመማቸውን ከመጠን በላይ የሚያጋንኑ፣ በህመማቸው ምክንያት የሌሎችን እንክብካቤ ለማግኘት የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ሁልጊዜ ስለ ህመማቸው ማውራት፣ "አመመኝ፣ ቆረጠኝ" ማለት ደስ የሚላቸው አሉ። የህመም ስሜት ካልተሰማቸው "ምን ሆንኩ?" በማለት የሚደነግጡም ሰዎች እንደማይጠፉ እርግጠኞች ነን። አንዳንድ ሰዎች ሆስፒታል ሄደው ሲመለሱ የሚበሳጩና የሚያዝኑ አሉ። *"የምርመራው ውጤት የከፋ ሆነ እንዴ? የሚያሳስብ ነገር ገጠማችሁ ወይ?"* ተብለው ሲጠየቁ፣ በመበሳጨት "ሀኪሙ ምንም ዓይነት በሽታ የለብህም፤ ...ፍጹም ጤነኛ ነህ አለኝ" ይላሉ። አንዳንድ ሰዎች በሥጋቸው ጤነኛ ሆነው በአዕምሯቸው የታመሙ፣ በራሳቸው ላይ የህመም ስሜት የሚያመጡም አሉ። ጳውሎስ "በመከራችን ሐሴት እናደርጋለን" ሲል፣ ከላይ የገለጽናቸውን ዓይነት ሰዎች ባህሪ ኖሮት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ወይም ዝም ብሎ ለመናገር ሲል የተናገረው፣ የቃላት ጨዋታ አይደለም።



- ጳውሎስ የራሱን የመከራና የስቃይ ድርሻ ተቀብሏል። *"...ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ በጉዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። ብዙ ጥሬአለሁ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቁትነት ተቆራምጃለሁ..."* ይላል (2 ቆሮ. 11፥23-27)።

በዚህ ሁሉ መከራና ስቃይ ውስጥ አልፎ፣ እንዴት ሌላ መከራና ስቃይ ይመኛል? ብለን አሁንም መጠየቃችን አይቀርም። ጳውሎስ ያለፈበት የመከራ ሕይወት፣ የቀመሰው የመከራ ጽዋ ወደ ጌታው የበለጠ አስጠጋው እንጂ መራራ አላደረገውም። የመከራውና የስቃዩ ብዛት የክርስትና ሕይወት ልምምዱን አላናጋውም፤ ወይም ደስታውን አልገፈፈበትም። እግዚአብሔር በሕይወቱ ያቀደውን ዓላማ አልደመሰሰበትም። ነገር ግን መከራው እምነቱን ያጠነከረለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ክርስቶስን በመታዘዙ ምክንያት መከራ መቀበሉን እንደ ዕድል ቆጠረው። ጳውሎስ አርቆ መመልከት የሚችል ሰው ነበር። ከመከራውና ከስቃዩ ባሻገር አርቆ ተመለከተ እንጂ፣ በወቅቱ የሚያልፍበትን የመከራ ልምምድ፣ እየቀመሰ ያለውን መራራ ጽዋ አልተመለከተም። መከራውንና ስቃዩን ሳይሆን፣ በመጨረሻ የሚያገኘውን ውጤት ትኩር ብሎ ተመለከተ። *"...ትዕግሥት፣ ጽናት፣ የተፈተነ ባሕርይ..."* ያለው ሰው ሆነ። ይሄም በወቅቱ የሚያልፍበት መከራና ስቃይ እንዳይሰማው፣ እንዲሁም ለሕይወቱ ጥሩ ትርጉም ሊሰጠው ቻለ።

ለመሆኑ መከራ ለእኔና ለእናንተ ይህን ዓይነቱን ውጤት ያስገኝልን ይሆን? ለዚህ ወሳኙ የእኔና የእናንተ ሁኔታ ነው። መከራና ስቃይን የምን ቀበለው በደስታ ነው ወይስ እያጉረመረምንና እየተበሳጨን ነው? በዚህ ዓይነት ከሆነ፣ ልባችን መራራ ይሆናል። "ለምን ይሄ ሁሉ መከራ በእኔ ላይ ይደርሳል? ሌሎች እኔ በማልፍበት ሁኔታ ለምን አያልፉም?" በማለት የምንበሳጭ፣ የምናኮርፍና የምናምጽ ከሆነ፣ ውጤቱ አሁን እየቀመስን ካለነው መከራና ስቃይ የበለጠ የከፋ ይሆናል። በመከራችን እንሠራበታለን፣ ወይም እንሰበርበታለን። ምርጫው አሁንም የራሳችን ነው። ጳውሎስ በመከራው የተደሰተበት ምክንያት አለው። ምክንያቱን ሲገልጽ፣

❖ *"...በመከራችንም ሐሴት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን። ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣ የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን፣ ይህም ተስፋ ለዕፍረት አይዳርገንም፤ እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና" (ሮሜ 5፡3-5)* አለ።

መከራ ፍጹም የሆነ ሥራውን በሕይወታችን እንዲፈጽም ከፈቀድንለት፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ያላየነውን አዲስ ነገር ይፈጥራል። ሕይወትን በጥልቀት እንድናውቅ፣ የመጨረሻውን ዕጣ ፋንታችንን እንድናውቅ ያደርገናል።

ዕውቀት መጽሐፍትን በማንበብ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ይገኛል፤ ጥበብ ግን በሕይወት ልምምድ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው። በመከራ ውስጥ በማለፍ የምናገኘው መረዳት ግን ምንጊዜም የማይረሳ ነው። በመከራና በስቃይ ውስጥ ስናልፍ ኃይልን የምናገኘው፣ ከውስጣዊው ሕይወታችን ነው። በመከራና በፈተና ውስጥ ስናልፍ ኃይል የሚሆነን፣ ብዙዎቻችን መኖሩን የማናውቀው የሚያግዘን ልዩ ኃይል አለልን። በመከራና በስቃይ ውስጥ ያለፉትን በተከታታይ ታሪካቸውን ሰምተን በትዕግሥታቸውና በቆራጥነታቸው የተደነቅንባቸውን ሰማዕታት ሆነው ያለፉትን የእምነት አርበኞችን፣ "ይህን ሁሉ መከራና ስቃይ እንዴት



*ታግሳችሁ ማለፍ ቻላችሁ?"* ብለን ብንጠይቃቸው፣ ኃይሉን ከየት እንዳገኙት ስለሚያውቁ፣ *"ብዙዎች ስላልደረሱበት መኖሩን የማያውቁት የተሰወረ ኃይል አለ። ያ ኃይል በመከራችንና በስቃያችን ወቅት ጉልበትና ብርታትን ይሆነናል"* ማለታቸው አይቀርም።

ከክርስቶስ የምናገኘው ኃይል ሊያቆመን የሚችለው፣ ኃያል የሆነው ጌታ ሙሉ በሙሉ በሕይወታችን ውስጥ ሲኖር ነው። በመከራችን ውስጥ ጸንተን ስንቆም፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን መሆናችን ይሰማናል። ከዚህ በፊት ያልተረዳነውን አዲስ መረዳት እናገኛለን። እንደ ቀድሞው ጥልቀት በሌለው መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ እየተፍገመገምን በመውደቅና በመነሳት ሕይወት ውስጥ አንኖርም። ዛፍን፣ ብርቱ "ዛፍ" የሚያደርገው፣ በተለያየ የዓየር ጠባይ ውስጥ ካለፈ በኋላ ነው። ልክ እንደ ዚሁ ሰውም ብርቱ የሚሆነው በተለያየ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ካለፈ በኋላ ነው። በመከራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተለማምዶ ማለፍ የክርስቶስ ገጸ ባሕሪ እንዲቀረጽብን ያደርጋል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለዚህ እውነት ሲመሰክር፣

❖ *"በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ፣ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ መልሶ ያበረታችኋል፤ አጽንቶም ያቆማችኋል"* ይላል (1 ጴጥ. 51)።

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ለመንፈሳዊ ልጁ ለጢሞቴዎስ የክርስትና እምነት ቀላል እንደሆነ፣ ትግል እንደሌለበት አድርጎ አላስተማረውም። በእኔ የደረሰውን ብነግረው ፈርቶ ይሸሻል ብሎ በማሰብ፣ የክርስትና ሕይወትን ቀለል አድርጎ አላስተማረውም። አስቀድሞ በማወቅ እንዲጠነቀቅ ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ እንዲኖርበትም ጭምር ነው። እርሱ ባለፈበት መንገድ እንደሚያልፍ፣ እርሱ የቀመሰውን የመከራ ጽዋ እንደሚቀምስ በማሳሰብ በሕይወቱ የደረሰበት መከራና ስደት አንድም ሳያስቀር ዘርዝሮ ገለጸለት።

❖ *"አንተ ግን አካሄዴን፣ ዓላማዬን፣ እምነቴን፣ ትዕግሥቴን፣ ፍቅሬንና ጽናቴን ሁሉ ታውቃለህ። ስደቴን መከራዬን በአንጾኪያና*

*በኢቆንዮን፣ በልስጥራንም የደረሰብኝን ሁሉ፣ የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ ጌታ ግን ከእነዚህ ሁሉ አዳነኝ። በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ"*(2 ጢሞ. 3፡10-12) አለው።

ጳውሎስ "በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" ሲል፣ ከእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ውጪ የሚኖሩ፣ ወንጌልን የሚሸቃቅጡ፣ ጥቅሙን እንጂ ዋጋ መክፈል የማይፈልጉ፣ ከመታዘዝና ከቅድስና ሕይወት ውጪ የሚኖሩ፣ መከራና ስደት አይደርስባቸውም ማለት ነው። በመታዘዝ ሕይወት ውስጥ ሁልጊዜ መከራና ስደት አለ። የክርስትና ሕይወት፣ *"የእኔ ጌታ እያንቀባረረ ያኖረኛል"*የሚባልበት እምነት አይደለም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ ብዙዎቻችን በትግል እንጂ ተንቀባረን ስላልኖርን ክርስቲያን መሆናችን ያጠራጥረን ነበር። ወይም እግዚአብሔርን *"አንዳንዶቹን ታንቀባርራለህ! ሌሎቻችንን ግን በመከራ ውስጥ ታሳልፈናለህ። በዚህ ዓይነት ታዳላለህ"* እንለው ነበር። ወደ መንግሥቱ ሲጠራንም፣ *"ኑና ሙቱልኝ! መስቀሉን ተሸክማችሁ ተከተሉኝ"* እንጂ፣ *"ኑ! እንቀባርሬ አኖራችኋለሁ፤ የአበባ ምንጣፍ አንጥፍላችኋለሁ፤ ምንም የማይጎድላችሁ ባለጸጋዎች አደርጋችኋለሁ"*አላለንም። እስካሁን በሕይወታችን እንዳየነው፣ መጀመሪያ ስንመጣ ከተነገረን ውጪ ሆኖ አላገኘ ነውም።

## 5. በመታዘዛቸው በመስቀል ሕይወት ውስጥ ያለፉ

እግዚአብሔር በዓለም ዙሪያ ቆራጥ የሆኑ፣ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው የሰጡ የእምነት አርበኞች አሉት። ከብዙዎቹ መካከል አንደኛው የሮማንያ ተወላጅ የሆነው *ጆሴፍ ትሰን* የተባለው የጌታ አገልጋይ ነው። *ጆሴፍ ትሰን* በሮማንያ አገር የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነበር። ለቀደመው የኮሚኒስት መንግሥት በጣም አደገኛና አስቸጋሪ ሰው ሆኖ ይታይ ነበር። በዚህ ምክንያት የሚወስደውን እርምጃ፣ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ሁሉ በጥንቃቄ ይከታተሉ ነበር። የሮማንያ



ተወላጆችም ሆኑ የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው፣ በ1973 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) የሮማንያ መንግሥት ባለሥልጣናት ሕገ መንግሥታቸው ከሚፈቅደው ውጪ የሃይማኖት ነጻነትን ከሕዝቡ በኃይል እየገፈፉ እንደሆነ አንድ በአንድ በመዘርዘር በሰፊው በጽሁፍ አሳትሞ አውጥቶ ነበር። ይህን በማድረጉ የእዚህ ክርስቲያን አገልጋይ ጀብደኛነት የመንግሥቱን ባለሥልጣናትን በኃይል አስቆጥቶ ነበር። ለረጅም ጊዜ በማስፈራራትና በማሳደድ፣ ወህኒ ቤት ከተው በማስጨነቅ መንፈሱን ለመስበር ቆርጠው ተነሱ።

ይህን የስደት እንቅስቃሴያቸውን በ1974 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ሲጀምሩ፣ ስድስት የመንግሥቱ ባለሥልጣናት *ጆሴፍ ትሰን "የአገሪቱን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ፕሮፖጋንዳ አሰራጭቷል"* በማለት ክስ አቀረቡበት። የበቀል እርምጃቸውን ከመውሰዳቸው በፊት፣ *"በጽሁፍ ያወጣሁት ዝርዝር መግለጫ ስህተት ነው"* ብሎ እንዲያስተባብል ጠየቁት። የተጠየቀውን ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆኑን ሲያውቁ፣ መንፈሱን ሰብረው ጸጥ ለማሰኘት፣ ልዩ ልዩ ከፉ እርምጃዎችን በእርሱ ላይ ለመውሰድ ቆርጠው ተነሱ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የደረሰበትን ሲገልጽ፣ *"ለስድስት ወር ያህል አስረው፣ በሳምንት አምስት ቀን፣ አንዳንድ ጊዜ በቀን አስር ሰዓት ሙሉ በተለያየ መንገድ እየመረመሩ ያስጨንቁኝ ነበር። መርማሪው የራሱ የሆነ የምርመራ ዘዴ ወይም መሣሪያ ነበረው። ይኸውም፣ መጥፎ ቋንቋ መጠቀም፣ ማስፈራራት፣ በተንኮል የተሞላ እርምጃ በእኔ ላይ መውሰድ፣ የሀሰት ክስ በማቅረብ፣ እንዲሁም ከአግባብ ውጪ የሆነ ኃይልን በመጠቀም ነበር። ሁልጊዜ ለምርመራ ከፊታቸው በምቀርብበት ወቅት፣ እነዚህ እነርሱ የሚጠቀሙባቸው መንገዶች ሁሉ የሰይጣን መሣሪያዎች ስለ ሆኑ፣ እኔ በበኩሌ በጠላቴ በሰይጣን መሣሪያ መጠቀም እንደሌለብኝ፣ እነርሱ ከሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ይልቅ፣ በጌታዬ መሣሪያ ይኸውም፣ በእግዚአብሔር መታመን፣ በፍቅር፣ በደስታና በእውነት መምላት፣ እንዲሁም ራሴን መስዋዕት አድርጌ ማቅረብ እንዳለብኝ ተረድቼ ነበር።*

አንድ ቀን ጆሴፍ ትሶን እየደበደቡ ሲመረምሩት፣ በአካባቢው ያለው ሕዝብ ሁሉ እንዲሰማ ብሎ በኃይል ይጮኽ ነበር። ይህን ያደረገበት ምክንያት መብቱ እንዴት እንደተገፈፈና እንዲሁም ምን ዓይነት በደል እንደተፈጸመበት ሌሎች ሰምተው ምስክሮች እንዲሆኑ በማሰብ ነበር። በሚቀጥለው ጊዜ መርማሪው ፊት ሲቀርብ፣ እንደዚያ በኃይል በመጮኹ መርማሪውን ይቅርታ ጠየቀው። ለምን ይቅርታ እንደጠየቀው ግራ ተጋብቶ ለነበረው መርማሪ ምክንያቱን ሲያስረዳው፣ የተደበደበው ክርስቶስ ወደ መስቀል ሞት በሄደበት በመጨረሻው ሳምንት፣ "ቅዱስ ሳምንት" ተብሎ በሚጠራው ሳምንት ውስጥ ነበር። ይቅርታ ለምን መጠየቅ እንዳስፈለገው ሲገልጽ፣

- ❖ *"አዳኝ የሆነው ጌታ ኢየሱስ በተሰቃየበት ቅዱስ ሳምንት፣ መከራ ከመቀበል የበለጠ ለክርስቲያን ሌላ መልካም ዕድል የለም። በዚያን ጊዜ ስትደበድበኝ ትልቅ ክብር እየሰጠኸኝ ነበር። ይህን በማድረግህ ስለ ጮኽኩብህ በጣም አዝናለሁ። ነገር ግን ይህን የመሰለ ትልቅ ዕድል ስለ ሰጠኸኝ ላመሰግንህ ይገባ ነበር። ከማክሰኞ ቀን ጀምሮ ለአንተና ለቤተሰብህ በጣም አጥብቄ እየጸለይኩልህ ነበር" አለው።*

ከዚህ የከፋ መከራና ሞት ይደርስብሃል ብለው ሲያስፈራሩት፣ ለጠላቶቹ የሚሰጠውን መልስ አዘጋጅቶ ስለ ነበር እንዲህ አላቸው።

- ❖ *"የእናንተ ትልቁ መሣሪያችሁ መግደል ነው። የእኔ ደግሞ ትልቁ መሳሪያዬ ሌላ ነገር ሳይሆን መሞት ነው። ይሄ ሁኔታ የሚሠራው በዚህ ዓይነት ነው። በቴፕ የተቀዳው ስብከቴ በመላው አገሪቷ ውስጥ እንደተበተነ ታውቃላችሁ። ብትገድሉኝ፣ እነዚህ ተዘጋጅተው የተበተኑት መልዕክቶቼ ከደሜ ጋር ተቀላቅለው በየስፍራው የበለጠ ይረጫሉ። በስብከቴ ምክንያት እንደገደላችሁኝ ዓለም ሁሉ ያውቃል። እንድታውቁልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር፣ መልዕክቴ (ስብከቴ) በሕይወት እያለሁ ከሰበኩት ስብከት 10 ጊዜ የሚበልጥ ኃይለኛ ጩኸት የሚ*



*ያሰማ መሆኑ ነው። ብትገድሉኝ ከፍተኛ ድል በማግኘቴ እጅግ በጣም ደስ ይለኛል" አለው።*

በ1981 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ጆሴፍ ትሶን ከአገሩ ተሰዶ በባዕድ አገር በመኖር መልዕክት እያዘጋጀ ወደ አገሩ ወደ ሮማንያ በመላክ ጌታውን ያገለግል ነበር። አሁን ያለበትን ሁኔታ ባላውቅም እርግጠኛ ነኝ፣ የኮሚኒስት አገዛዝ (አስተዳደር) ከወደቀ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ በነጻነት ወንጌልን እንደሚሰብክ።

የእኔና የእናንተ የክርስትና ሕይወት ዕድገት የሚለካው አንዳንዶች እንደሚያስቡት ተመችቶን በምንኖረው ኑሮ፣ ባለን ሀብትና ብልጽግና ሳይሆን፣ በምንኖረው የመስቀል ሕይወት ነው። *የተሰቀለ ሕይወት ሳንኖር፣ ትንሳኤ ያለው ሕይወት መኖር አንችልም።* ይህን ዓይነቱን አባባል የማይኖሩ ሰዎች ይህን አባባል መቀበል ከባድ እንደሚሆንባቸው የታወቀ ነው። የተሰቀለ ሕይወት የኖረው ሐዋርያው ጳውሎስ፣

- *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው"* ይላል (ገላት. 2፡20)።

በሥቃዩ ተካፋይ መሆን፣ በሞቱ እርሱን መምሰል የምንችለው፣ የተሰቀለ ሕይወት ሲኖረን ብቻ ነው። ያልተሰቀለ ሕይወት ያላቸው ሰዎች ከክርስቶስ ጋር መከራ መቀበል አይችሉም። ታሪካቸውን በተከታታይ የሰማናቸው ሰማዕታት ሁሉ፣ በሰው አዕምሮ ይቻላል ተብሎ የማይገመተውን ሁሉ ታግሰው ማለፍ የቻሉት፣ የተሰቀለ ሕይወት ያላቸው በመሆናቸው ብቻ ነው። የተሰቀለ ሕይወት ካለን፣ እንዴ ሞተናልና *"ስደት ይደርስብኝ ይሆን? ወህኒ ቤት እጣል ይሆን? በሰይፍ እታረድ ይሆን?"* ብለን አንፈራም፤ ስጋትም አይኖርብንም። የተሰቀለ ሕይወት ከሌለን ግን፣ እውነቱን ልንገራችሁ፣ ምንም ዓይነት መከራና ስደት ስለማይደር ስብን ልንፈራ አይገባም። ለዚህ ነው አንዳንዶች የክርስትና ሕይወት ቀላል ነው የሚሉት።

ሐዋርያው ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" ሲል፣ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ ጳውሎስ በዚያ አካባቢ ስላልነበረ፣ በመስቀል ላይ ከክርስቶስ ጋር እንዳልተንጠለጠለ እናውቃለን። ታዲያ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ' ሲል ምን ማለቱ ነው?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ስቅላት ማለት ሞት ነው። ስቅላት ሞት ከሆነ፣ ለኃጢአት፣ ለአሮጌው እኛነታችን፣ ለሥጋዊው ፍትወታችን፣ እንዲሁም ለአሮጌው ምኞታችን ሞተናል ማለት ነው። ከሆነ፣ በነዚህ ነገሮች ላይ ክርስቶስን መስለናል ማለት ነው። ለእነዚህ ነገሮች ከሞትን በእኛ ሕይወት ውስጥ ኃይል አይኖራቸውም ማለት ነው። ሞተ የምንለው ሰው፣ የሚሞተው የተወሰነው የሰውነት ክፉሉ ብቻ ሳይሆን፣ ጠቅላላ የሰውነቱ ክፍሎች በሙሉ ነው። እግራችን የተሰቀለ ከሆነ፣ እግራችን እግዚአብሔርን ወደማያከብር ሥፍራ ይዞን አይሄድም። ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀልን፣ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ለማድረስ እግሮቻችን የክርስቶስን ፈለግ ተከትለው ይሄዳሉ። እንዴ ተሰቅለን ሞተናልና ይህንንም ስናደርግ መከራና ስደት ይደርስብናል ብለን አንፈራም። ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀልን፣ እጆቻችንም ከክርስቶስ እጆች ጋር ተሰቅለዋልና እጆቻችን መከራ ለመቀበል እንጂ፣ ክፉ ነገር ለማድረግ የተዘረጉ አይደሉም።

አንድ የጥንት ወታደር ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ የውሃ ጥምቀት ለመውሰድ ወሰነ። ሊያጠምቀው የተዘጋጀውን መጋቢ እንዲህ አለው። "ከአንዱ እጄ በስተቀር የተቀረውን ሰውነቴን በሙሉ ውሃ ውስጥ ልታጠልቅ ትችላለህ" አለው። መጋቢው ግን "የውሃ ጥምቀት መውሰድ ከፈለግህ፣ ከክርስቶስ ጋር የተቀበርክ መሆን ስለሚያስፈልግህ፣ መላው ሰውነትህ፣ እጅህም ጭምር ውሃ ውስጥ መጥለቅ ወይም መቀበር አለበት" አለው። ያም ጦረኛ፣ "የለም አይሆንም! ይሄኛው እጄ ጠላቶቼን የምዋጋበት ስለሆነ፣ ለክርስቶስ መስጠት አልፈልግም" አለ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ልክ እንደዚህ ወታደር ናቸው። መላ ሕይወታቸውን ለጌታ በመስጠት ፈንታ የተወሰነውን ክፍል ብቻ ለመስጠት ይፈልጋሉ። ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀልን ግን መላው ሰውነታችን ለእርሱ



የተሰጠ ወይም የሞተ መሆን አለበት። በ1ኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ወደ አሜሪካ የመጣ አንድ ስዊድናዊ በውትድርና ለማገልገል ፈቃደኛ ሆኖ ቀረበ። "አንተ የአሜሪካ ተወላጅ ወይም ዜግነት ስሌለህ፣ ከወታደርነት ግዳጅ ነጻ ነህ! መሄድ ትችላለህ" ተባለ። ያ ሰው ግን "አይሆንም! አሜሪካ የመጣሁት በከፊል ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ አሜሪካ ለመኖር ስለሆነ፣ አሜሪካ የምትፈልገኝ ከሆነ፣ ግዳጄን ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ" አለ። ዛሬም እኔና እናንተ በክርስቶስ ውስጥ ከሆንን፣ ለክርስቲያናዊ ግዳጅ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ የሰጠን መሆን አለብን። ከክርስቶስ ጋር መሞት፣ ከክርስቶስ ጋር መሰቀል አለብን።

በዓለም ዙሪያ ቆራጥ የሆኑ፣ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው ከሰጡ የእምነት አርበኞች መካከል ሌላው ጊሮላም ሳቮናሮላ የተባለ ሰው ነው። ይህ የእምነት አርበኛ፣ የክርስትናን እምነትን በሚጠሉ በውጪ ጠላቶቹ ሳይሆን፣ በራሱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሰቃይቶ የሞተ ነው። እነዚህ የጊሮላም ሳቮናሮላ አሳዳጆች፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን "ግብዞች፣ የእፉኝትና የእባብ ልጆች" ብሎ ይጠራቸው የነበሩትን ፈሪሳውያንን የሚመስሉ መሪዎች ናቸው። ሳቮናሮላ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ጣሊያናዊ የተሀድሶ መሪ ሲሆን፣ የህክምና ትምህርቱን ጥሎ ጌታን ለማገልገል የወጣ ሰው ነበር። በጣም ኃይለኛና የሚደነቅ የመስበክ ስጦታ የነበረው ታዋቂ አስተማሪ ነበር። በጣም ተወዳጅ ሰው ስለ ነበረ፣ የፍሎረንስ የፖለቲካ መሪ እስከ መሆን የደረሰበት ጊዜ ነበር። በሥልጣን ላይ በነበረበት ዘመን ድሆች የሚረዱበት የበጎ አድራጎት ድርጅት ያቋቋመ፣ በከተማው ውስጥ የነበረውን የሞራል ውድቀት ለመለወጥ የታገለ፣ ከቆራጥነቱና ከደፋርነት የተነሳ፣ ጳጳሱን "ሀሰተኛ ነብይ ነው" ብሎ የተናገረ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ፣ የአገልግሎቱ ዘመን በአጭሩ ተቀጨ። ከወዳጆቹ ይልቅ ጠላቶቹ ኃይለኞች ሆነው ተገኙ።

ሳቮናሮላ የመጨረሻውን መልዕክት ለረጅም ዘመን ብዙዎችን ባስተማረበት በቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ውስጥ አደረገ። ስብከቱን እንደ ጨረሰ፣ ስለ እውነት ሲል ለመሞት ዝግጁ መሆኑን ገልጾ ሕይወቱን ለጌታ በአደራ አሳልፎ ሰጠ። ወዲያው ወታደሮች ለፍርድ ሊያቀርቡት

ይዘውት ሄዱ። ለብዙ ዘመን ያገለገላቸው ተከታዮቹ ከደውት ሸሹ። ከቤተ ክርስቲያን አውጥተው ሲወስዱት፣ ከዚህ በፊት ያደንቁት የነበሩት ሁሉ ድንጋይ እየወረወሩ ራስ ራሱን ይቀጠቅጡት ነበር። ጭካኔ በሞላበት ሁኔታ በእርግጫ ይረግጡት ነበር። እርሱን ቶሎ መግደል በቂ ቅጣት አይሆንም ብለው ስላሰቡ ነፍሱ ከሥጋው እስከ ተለየችበት ጊዜ ድረስ መከራውንና ስቃዩን ለማብዛት በልዩ ልዩ መንገድ ያሰቃዩት ነበር። በጳጳሱ ሙሉ ፈቃድና ትዕዛዝ መሠረት፣ ከሳሾቹ በገመድ አሥረው ረጅም ከሆነው ጣራው ላይ ካንጠለጠሉት በኋላ፣ ሲሚንቶ ወለል ላይ ወደታች ይጥሉት ነበር። በዚህ ዓይነት አንድ ወር ሙሉ ካሰቃዩት በኋላ እውነትነት የሌለው ክስ መስርተው የሞት ፍርድ ፈረዱበት። የመጨረሻ ንግግሩ፥

- *"ጌታ ሆይ! በደል የሌለብህ ፍጹም አምላክ ሆነህ ስለ እኔ ኃጢአት ስትል ከሞትህ፣ እኔስ ይህን የማይረባ አካል (ሰውነት) ከፍቅር የተነሳ ልሰጥህ አይገባምን?" የሚል ነበር።*

ስለ እምነታቸው ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ፣ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ እኔና እንደ እናንተ ተራ የሆኑ አማኞችም ጭምር ናቸው። ገና ኖረን ስላልጨረስን በመንገዳችን ምን እንደሚያጋጥመን አናውቅም። ዛሬ እንደ ጥንቶቹ ከነነፍሳችን በእሳት ባንቃጠልም፣ በመጋዝ ባንሰነጠቅም፣ ወህኒ ቤት ውስጥ ባንበሰብስም፣ ሁላችንም የራሳችን የሆነ መስቀል አለን። ያለመስቀል የክርስትና ሕይወት መኖር ስለማንችል፣ ትንሽም ሆነ ትልቅ፣ እንደ አቅማችን የሚሰጠንን መስቀል ተሸክመን፣ ከእኛ በፊት ቀድሞ መስቀሉን የተሸከመውን ጌታ ተከትለን እስከ መጨረሻው እንድንዘልቅ እግዚአብሔር ለሁላችንም ጸጋውንና ጽናቱን ይስጠን።



# 7

# ኃይል አለ በመስቀሉ

*"..ውጫዊ ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ ውስጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፣ ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል"*
*(2 ቆሮ. 4:16-17)*

*"አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፣ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፣ በድንጋይ ተወገሩ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፣ እየተንሳቀሉ፣ እየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቆዳ ለብሰው ዞሩ፣ ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጉድጓዱ ተንከራተቱ"*
*(ዕብ. 11:36-38)*

ጳውሎስ *"ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ የሚለው ቃል ለሚጠፉት ሰዎች እንደ ሞኝነት ይቆጠራል፣ ለምንድን ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው" ይላል (1 ቆሮ. 1:18)* ሲል ምን ማለቱ ነው? ከመስቀል ውጪ ለሚኖሩት ወይም ለማያምኑት የክርስቶስ መስቀል ሞኝነት መስሎ ይታያል፣ የመስቀል ሕይወት ተሳታፊ ለሆኑት ግን ኃይል እንደሆነ የታወቀ ነው። የመጀመሪያው መስቀል ተሸካሚ፣ ወይም ፈቅዶ ራሱን ለሞት አሳልፎ የሰጠ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በመስቀል ላይ መራራ የሆነውን የሞት

ጽዋ የጠጣውም ኃጢአት ተገኝቶበት ሳይሆን፣ ሰውን ከዘላለም ሞት ለማዳን ነው። በዚህ ዓይነት ራሱን በሞት አሳልፎ ለሰጠው አምላክ ራስን መስጠት ያስቸግረን ይሆን? እነዚህ ከላይ ታሪካቸውን የሰማናቸው ሰማዕታትን ስናስብ፣ *"ይሄን ሁሉ ታላቅ መከራ እንዴት ማለፍ ቻሉ? በእነርሱ ላይ የደረሰው መከራ በእኛ ላይ ቢደርስ፣ ከአቅማችን በላይ ሆኖ እንከደው ይሆን?"* ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የራሳችንን አቅም ስንመዝን፣ በመከራ ውስጥ ለማለፍ እንደማንችል እናውቃለን። ይሁን እንጂ፣ መዘንጋት የሌለብን ነገር ቢኖር፣ የመስቀሉ ኃይል ለአምላካችን ታማኞች ሆነን እንድንቆም ኃይልን የሚሰጠን መሆኑ ነው። በመከራ ውስጥ ስናልፍ የጌታ መገኘት ስላለ፣ ታግሰን የምንቆምበትን ጸጋ ያበዛልናል።

የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው የጥንት የእምነት አርበኞች ለሞተላቸው አምላክ በእሳት ተቃጥለዋል፣ በዘይት ተቀቅለዋል፣ በአውሬዎች ተበልተዋል፣ በመጋዝ ተሰንጥቀዋል። በሰይፍ ተወግተዋል። ያንን መራር የሞት ጽዋ ለመጠጣት ጉልበት ያገኙት የመስቀሉ ትርጉም በትክክል ስለገባቸው እንደሆነ ከዚህ በፊት ገልጸናል። እኛም የእነርሱን ዓይነት የመከራ ጽዋ አንጠጣ እንጂ፣ የራሳችን የሆነ መጠጣት ያለብን የመከራ ጽዋ አለን። እኔና እናንተ ትልቅ መሸነፍ በሕይወታችን ሊደርስብን የሚችለው፣ የክርስትና ሕይወት መስቀል፣ መከራ የሌበት ሕይወት መስሎን ራሳችንን እንደሚገባው ሳናዘጋጅ የቀረን እንደሆን ነው። ዛሬ ወንጌል ለእኔና ለእናንተ ሊደርሰን የቻለው ብዙዎች በታማኝነት ዋጋ የከፈሉበት ሲሆን፣ እኛም የብዙዎች ደም የፈሰሰበትን፣ ብዙ ዋጋ የተከፈለበትን ወንጌል ተቀብለን፣ በተራችን ዋጋ ከፍለን ወንጌሉ ላልደረሳቸው እንድናስተላልፍ ተጠርተናል።

### 1. የመስቀሉ ኃይል ታማኞች እንድንሆን ጽናትን ይሰጠናል

የመስቀሉ ኃይል ራሳችንን ለጌታ እንድናስረክብ ያስችለናል። ራሱን በሞት ለሰጠ አምላክ፣ ራስን መስጠት አያስቸግርም። ፍቅር የማያሸንፈው ኃይል የለም። ክርስቶስ በፍቅሩ እንጂ፣ በጉልበት ማንንም



አላሸነፈም። የመስቀሉ ፍቅር ያለንን ሁሉ እንድንሰጥ፣ ዋጋ የሚያስከፍልም ቢሆን ለመክፈል፣ ኃይልና ጉልበትን ይሰጠናል። ክርስቶስን ከመስቀሉ እንዲወርድ የሚያደርጉ ብዙ ግፊቶች ደርሰውበታል። ይሁን እንጂ፣ ካለው ፍቅር የተነሳ የመጨረሻውን የሞት ጽዋ ከመጠጣት ወደ ኋላ አላለም። የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው አማኞች ለሞተላቸው አምላክ በእሳት ተቃጥለዋል፣ በዘይት ተቀቅለዋል፣ በአውሬዎች ተበጣጥሰዋል፣ በመጋዝ ተሰንጥቀዋል። እኛስ በትንሽ ነገር አኩርፈን፣ ተቀይመን እጃችንን ቆልፈን እንቀመጥ ይሆን? ያንን መራራ የሞት ጽዋ ለመጠጣት ኃይል የሰጣቸው ሌላ ነገር ሳይሆን፣ በመስቀሉ ላይ ያረፈው ጌታ ስለ እነርሱ ሲል እንደሆነ በትክክል ስለገባቸው ነው። ጥንት ስለ ወንጌል ከፍተኛ ዋጋ ከከፈሉ፣ በልዩ ልዩ ስደት ውስጥ ካለፉት አማኞች መካከል የስኮትላንድ ክርስቲያኖች ይገኙበታል። የሁሉንም ታሪክ በሰፊው ለማቅረብ ጊዜና ቦታ ስለማይበቃን፣ ለትምህርታችን እንዲሆን፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ልምምዳቸው ጎልተው ከሚታዩት መካከል የአንድ የሦቱን ሰማዕታት ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናል።

በተሀድሶ ዘመን ማርቲን ሉተር፣ ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር በእምነት ባለመስማማቱ ምክንያት በተፈጠረው ግጭት፣ እንዲሁም በወቅቱ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን እምነት በመቃወም ያስተምር የነበረው ትምህርት፣ ጠቅላላ አውሮፓን በኃይል የነካ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነበር። ያ ዘመን ለቤተክርስቲያን የተሀድሶ ዘመን ነበር። ማርቲን ሉተር ጽድቅ በእምነት እንጂ በሥራ አለመሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሰ ያስተማረው ትምህርት የብዙዎችን ልብ የማረከ፣ እንዲሁም እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲመረምሩ ያደረገ ነው። ያ ብቻ ሳይሆን፣ ትምህርቱ የሃይማኖት መሪዎችን በጣም ያስቆጣ በመሆኑ፣ ብዙዎች በመከራ፣ በስደት፣ በሞት ሸለቆ ውስጥ ያለፉበት ዘመን ነው። በዚያን ወቅት እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉትና ጥማት ከነበራቸው ሰዎች መካከል አንደኛው የስኮትላንዱ ተወላጅ *ፓትሪክ ሃሚልተን* የተባለው ሰው ነው። ፓትሪክ ሃሚልተንና ሦስቱ ጓደኞቹ የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ለመመርመር

በማሰብ ጀርመን በሚገኘው ማርበርግ ዩኒቨርሲቲ ገቡ። ይሄ አውሮፓ ውስጥ የመጀመሪያው የፕሮቴስታንት ዩኒቨርሲቲ ነው። ፓትሪክ ሃሚልተንና ጓደኞቹ በዚያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተማሪዎች በነበሩበት ወቅት ነው ከማርቲን ሉተር ጋር በቅርብ የተዋወቁት። እነዚህ የስኮትላንድ ወጣቶች በማርቲን ሉተር አስተምሮትና በሚጽፏቸው ጽሁፎች ተስበው ነው የሮማ ካቶሊክን እምነት ትተው ወደ ፕሮቴስታንት እምነት የመጡት።

ፓትሪክ ሃሚልተን፣ ከማርቲን ሉተር ስለ ክርስትና እምነትና እንዲሁም ስለ ቅድስና ሕይወት እውነተኛ የሆነ ትምህርትና እውነተኛ የሆነ መረዳት ካገኘ በኋላ፣ የራሱን ሕዝብ፣ ይኸውም እስኮትላንድን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት፣ በትክክለኛው መንገድ እግዚአብሔር አብንና ወልድን እንዲያውቁ ለማስተማር ሦስቱን ጓደኞቹን ይዞ በአስቸኳይ ወደ ትውልድ አገሩ፣ ወደ ስኮትላንድ ተመለሰ። ነገር ግን ልክ ስኮትላንድ እንደ ገባ የቅዱስ እንድሪያስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ካህን፣ ጄምስ ቢተን፣ ፓትሪክ ሃሚልተን ስለሚያስተምረው ልዩ ትምህርት ሰምተው በአስቸኳይ እርሳቸው ዘንድ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጡ። ፓትሪክ ሃሚልተንም ጳጳሳቱ ስለሚያስተምሩት ትምህርት የተቃውሞውን ቃል እንዲያቀርብ ዕድል የሚሰጡት መስሎት ምንም ሳያመነታ ደስ ብሎት ቀረበ። ይሁን እንጂ፣ እንደ ጠበቀው ዓይነት አልሆነለትም። አጭር የሆነ ምርመራ ካደረጉለት በኋላ፣ ሊቀ ካህኑ ጄምስ ቢተን የመጨረሻውን ውሳኔ እስኪሰጡት ድረስ ወህኒ ቤት እንዲቆይ ትዕዛዝ ሰጡ። በትዕዛዛቸው መሠረት በጣም ቆሻሻ ከሆነ ሥፍራ ሌሊቱን እንዲያሳልፍ ካደረጉ በኋላ፣ ጊዜ ሳይፈጁ በማግስቱ ጥዋት ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግለት በጳጳሳቱ ፊት አቀረቡት።

የተከሰሰባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር ጽፈው አነበቡለት። የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት ምክንያት ከሆኑት፣ ወንጀል ብለው ያቀረቧቸው፥ *"በካቶሊክ እምነት ተቀባይነት ያለውን የምናናን ሕይወት ይቃወማል... ...የሞቱት ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ ወይም ወደ ሲዖል ከመግባታቸው በፊት የሚቆዩበት ጊዜያዊ ማረፊያ መኖሩን፣ ...እንዲያማልዱ ለቅዱሳን መጸለይን፣ ...ለሞቱት ሰዎች መጸለይን፣ የካቶሊክ ሃይማኖት*



*የተቀበለውን ቁርባንና እንዲሁም የጳጳሳትን ፍጹምነት አያምንም፤ እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች በመቃወም በአደባባይ አስተምሯል"* የሚል ነበር። የክሱ ምክንያት ከተነበበለት በኋላ፣ በመቃወም ፈንታ የቀረበበት ክስ ሁሉ ትክክል ነው ብሎ ተስማማ። በዚህ ምክንያት ከነነፍሱ በአደባባይ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ወዲያው ተፈረደበት። ጠባብ የሆነ አስተያየት የነበራቸው ሊቀ ካህን ጄምስ ቢተን ፍርዳቸውን ካስተላለፉ በኋላ፣ በዚያኑ ቀን ከሰዓት በኋላ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ ከነሕይወቱ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ትዕዛዝ ሰጡ። ፓትሪክ ሃሚልተን ከነነፍሱ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ወደ ተወሰነበት ስፍራ ሲደርስ፣ በእሳት ተቃጥሎ ሲሞት ለማየት ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ አየ። ይሁን እንጂ፣ በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ፓትሪክ ሃሚልተንን አስፈራርተው የተቀበለውን እምነት ክዶ ወደ ቀድሞው እምነቱ ሊመልሱት አስበው ይሆናል እንጂ እውነትም፣ ከነነፍሱ በእሳት በማቃጠል የሞት ፍርድ ሊፈጽሙበት ነው ብለው አላመኑም ነበር። ነገር ግን እንዳሰቡት እንዳልሆነ ለመረዳት ይህን ያህል ጊዜ አልፈጀባቸውም።

ፓትሪክ ሃሚልተንን በእንጨት ላይ ሰቅለው ከነነፍሱ ለማቃጠል ክምር እንጨት ካለበት አደባባይ አምጥተው አቆሙት። እርሱም በዚያ ስፍራ ለጥቂት ጊዜ ተንበርክኮ ከልቡ ጸለየ። ጸሎቱን እንደ ጨረሰ፣ ከቆመው እንጨት ጋር በሰንሰለት ጥፍር አድርገው አሰሩት። ዙሪያውን ጭራሮ ቆለሉ። በሁለቱም ብብቶቹ ውስጥ ባሩድ (ፈንጂ) ካደረጉ በኋላ በቆመው እንጨትና በተከመረው ጭራሮው ላይ እሳት ለኮሱበት። የሚገርመው ነገር ቢኖር ጭራሮው በኃይል ሲነድ ለበለበው እንጂ፣ በብብቶቹ ሥር ያኖሯቸው ባሩዶች (ፈንጂዎች) ያልፈነዱ መሆናቸውና ሌላ ጉዳት ያልደረሰበት መሆኑ ነው። በዚህ ጊዜ ተጨማሪ ባሩዶች (ፈንጂዎች) አምጥተው ከጭራሮው እሳት ለኮሱት፤ አሁንም ባሩዶቹ አልፈነዱም። ነገር ግን ጭራሮ በፓትሪክ ሃሚልተን ዙሪያ በኃይል እንዲነዱ አደረጉ።

እሳቱ ዙሪያውን በኃይል ሲነድ፣ ፓትሪክ ሃሚልተን በእሳቱ ውስጥ ሆኖ *"ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ነፍሴን ተቀበላት! ይህ ዓለም (ግዛት) በጨለማ የተሞላ የሚሆነው እስከ መቼ ነው? የእነዚህን ሰዎች ጭካኔና አምባገነን*

ነትን የምትታገሰው እስከ መቼና እስከ ምን ድረስ ነው?" ብሎ በኃይል ጮኸ። ፓትሪክ ሃሚልተን በኃይል በሚነደው እሳት ውስጥ ከነነፍሱ በመቃጠል በብዙ ስቃይ ውስጥ ቢያልፍም፣ መከራውን የተቀበለው፣ አንድ እውነተኛ ክርስቲያን ሊኖረው በሚገባው ድፍረትና ጽናት ነው። በዚያ ስፍራ ተገኝተው የፓትሪክ ሃሚልተንን ስቃይ በዓይናቸው ያዩ ክርስቲያኖች ሁሉ፣ ሰማዕት ሆኖ ሕይወቱ ሲያልፍ እግዚአብሔር ጸጋውን ምን ያህል እንዳበዛለት ምስክሮች ሆነዋል። ይሄም የመጀመሪያ የጭካኔ ሥራ የተፈጸመው በአየርላንድ ውስጥ በ1527 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ነው።

ስለ እምነቱ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለው ሁለተኛው አማኝ፣ *ሄንሪ ፎርስት* የተባለው አማኝ ነው። ፓትሪክ ሃሚልተን ከሞተ ከሁለት ዓመት በኋላ ይኸውም በ1529 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ሄንሪ ፎርስት የተባለ ሰው፣ በፓትሪክ ሃሚልተን ላይ የተፈጸውመው የጭካኔ ሥራ አስፈርቶት ጸጥ በማለት ፈንታ፣ ፓትሪክ ሃሚልተን ሰማዕት እንደሆነና ያስተማረውም ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆን በግልጽ ማስተማር ጀመረ። ሊቀ ካህኑ ጄምስ ቢተን ይህንን ሲሰሙ፣ በአስቸኳይ ተይዞ ወህኒ ቤት እንዲጣል ትዕዛዝ ሰጡ። *ሄንሪ ፎርስትን* እየተከታተለ የሚሰብከውንና የሚያስተምረውን ትምህርት ሰምቶ ሪፖርት እንዲያደርግ አንድ የካቶሊክ መነኩሴ ተመድቦ ነበር። ይህም ሰው የተላከው፣ *ሄንሪ ፎርስት* እምነቱን ሳይደብቅ በግልጽ ይናገራል ብለው ስላመኑ ነው። ልክ እንዳሰቡት ሄንሪ ፎርስት፣ በግልጽ ፓትሪክ ሃሚልተን መልካም ሰው እንደ ነበረና ያስተማረውም ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ እንዳልነበረ በግልጽ ይናገር ነበር። እንዲሰልል የተላከው መነኩሴ ለሊቀ ካህኑ ለጄምስ ቢተን ይህንኑ ሪፖርት አደረገ። ይህንኑ እንደ መረጃ በማቅረብ ሄንሪ ፎርስት እንደ ከሃዲ ወይም መናፍቅ ተቆጥሮ ከነነፍሱ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈረደበት።

ሄንሪ ፎርስት በጣም የታወቀ፣ በሕዝብ ዘንድ በጣም የተደነቀና የተወደደ መንፈሳዊ ሰው በመሆኑ በአደባባይ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት እንዳይሉ ሕዝቡን ስለፈሩ በምን ዓይነት ሁኔታ መገደል እንዳለበት አማካሪዎቹ እንዲመክሩበት ተደረገ። የሊቀ ካህኑ የቅርብ አገልጋይ የሆነ ሰው፣



ወህኒ ቤት ውስጥ ማንም ሰው ሳያይ በድብቅ መገደል አለበት። ፓትሪክ ሃሚልተን በአደባባይ በእሳት ተቃጥሎ ሲሞት፣ የእሳቱ ጪስ እውነቱን በመሸፈን ፈንታ፣ ከተጠበቀው በላይ የሕዝቡን ልብ ይነካና ሕዝቡ የበለጠ ይቀሰቀስ ይሆናል ብለው በመፍራትና በማሰብ፣ ያንን በመሰለ ሁኔታ ሄንሪ ፎርስት እንደ ሌሎቹ ሰማዕታት በአደባባይ ከነነፍሱ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት አላደረጉም። ሊቀ ካህኑ ጄምስ ቢተን አገልጋዩ የሰጠውን ምክርና አስተያየት ተቀብሎ ወህኒ ቤት ውስጥ በትራስ አፍነው ገደሉት። በዚህ ዓይነት ሄንሪ ፎርስት ሰማዕት ሆኖ አለፈ።

በስኮትላንድ፣ በእውነተኛ ክርስቲያኖች ላይ የተቀጣጠለው የስደት እሳት በዚህ አላበቃም። ስለ እምነቱ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለው ሦስተኛው የእምነት አርበኛ *ስትራተር* የተባለው ሰው ነው። በ1534 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) *ዴቪድ ስትራተንና ኖርማን ጎርሊ* የተባሉ ክርስቲያኖች ስለ ወንጌሉ እውነት ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው። ጎርሊ የታሰረው፣ የሙታን ጊዜያዊ ማረፊያ (ፐርገቶሪ) የለም፣ ጳጳሱ ሐሰተኛ ክርስቶስ ነው፣ እንዲሁም ጳጳሱ በስኮትላንድ ውስጥ ሕጋዊ መብት የለውም ብሎ ተናግሯል በማለት ነው። *ስትራተን* አሳ አጥማጅ የነበረ ሲሆን፣ የቀረበበትም ክስ *ከኖርማን ጎርሊ* ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። *ጎርሊና ስትራተን* ተይዘው በቁጥጥር ወይም በእስር ላይ ከዋሉ በኋላ፣ ሁለቱም መናፍቅ ተብለው ከነሕይወታቸው በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ ተፈረደባቸው። በፍርዱ መሠረት፣ በኤደንበርግና በሊት ከተማ መካከል ከአንድ ሰፊ ሳር ሜዳ ላይ፣ ብዙ ሕዝብ ባለበት አካባቢ እንዲሞቱ ተወሰነ። ይህ ስፍራ የተመረጠበት ዋና ምክንያት በዚያ አካባቢ ያለው ሕዝብ *ጎርሊና ስትራተን* የሚያምኑትን ዓይነት እምነት ቢይዙ፣ እነርሱም በእሳት ተቃጥለው በሞቱበት ዓይነትና ሁኔታ የሚሞቱ መሆናቸውን ለማስጠንቀቅና በሕዝቡ ላይ ፍርሃትን ለመጨመር ነበር።

ይሁን እንጂ፣ በእነዚህ ሁለት ሰማዕታት ላይም ሆነ ሁኔታውን በሚመለከቱት አማኞች ገጽታ ላይ የሚነበብ ምንም ዓይነት ፍርሃት አልነበረም። እነዚህ ሰማዕታት ኃያሉ ጌታና አዳኝ፣ አንድ ቀን በክብር ተሞልተው ዘለዓለማዊውን ሕይወት ለመኖር ትንሳኤ እንደሚያገኙ በማ

ወቅና በማመን፣ በደስታና በድፍረት ተሞልተው ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥተው ጊዜያዊ የሆነውን የሞት ጽዋ ቀመሱ። ይሄም ሁኔታ ብዙዎቹን ዝም በማሰኘት ፈንታ፣ የበለጠ ድፍረትን ሰጣቸው። ብዙዎች ላመኑበትና ለተቀበሉት እውነት ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው ለመስጠት ወደ ኋላ እንዲሉ አላደረጋቸውም።

ስለ እምነቱ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለው አራተኛው አማኝ *ጆርጅ ዊሻርት* የተባለው ሰው ነው። በ1543 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) *ጆርጅ ዊሻርት*፣ የስኮትላንድ ተወላጅ፣ የካቶሊክ ቄስ የነበረውን *ታዋቂውን ጆን ናክስን* ወደ ትክክለኛ እምነት *ያመጣ*፣ የካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ምሁር የነበረው *ታላቅ* የእምነት አርበኛ የቀመሰው ሞትና ስቃይ ነው። *ጆርጅ ዊሻርት*፣ ረጅምና በጣም ደስ የሚል ቁመና የነበረው፣ በጣም ጨዋ፣ ትሁት፣ ሰው በቀላሉ ሊቀርበው የሚችል፣ ለድሆች ቸርነትን የሚያሳይ፣ ሌሎችን ለመርዳት ሲል በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ የሚኖር፣ ማስተማር የሚወድና እንዲሁም ከማንኛውም ነገር የበለጠ እግዚአብሔርን በጣም የሚወድ ሰው ነበር። *መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት* (ዲስፕሊን) የነበረው፣ ጊዜውን በጾምና በጸሎት የሚያሳልፍ፣ የተረፈውን ሳይሆን ካለው ጥቂት ነገር ምንንም ለሌላቸው ድሆች የሚያካፍል በርህራሄ የተሞላ ሰው ነበር።

*መጽሐፍ ቅዱስን* ጠለቅ ብሎ ከልቡ ስለሚያስተምር፣ ኃይለኛ ሰው ነው ብለው በማሰብ፣ የሚያስተምረውን በማጥላላት ሊገድሉት ምክንያት የሚፈልጉለ አንዳንድ ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ ለማሰብ ከአዕምሮ በላይ በሆነ ሁኔታ ጌታ ይከላከልለት ነበር። ብዙ ጊዜ ሌላውን ለመጉዳት ያላቸውን ዝንባሌ፣ እንዲሁም በልባቸው ውስጥ ያለውን ክፉ አሳብ በኃይልና በስልጣን ተሞልቶ ከነገራቸው በኋላ፣ ወደ መልካሙ ሕይወት እንዲመለሱ ያሳስባቸው ነበር። የሚያስደንቀው አንዳንዶቹ ትምህርቱንና ምክሩን ከሰሙ በኋላ፣ ስለሚያስተምረው ትምህርትና የእምነት አቋም ደስ ይሰኙበት ነበር። ያ ብቻ ሳይሆን፣ ትምህርቱን ሰምተው የተቀበሉት ሰዎች፣ በግል ሕይወታቸውም ውስጥ ስላገኙት ለውጥ ደስ ይላቸው ነበር። የተሀድሶን ትምህርት በመስበኩና በማስተማሩ ግን ቅር የሚሰኙበት አንዳንድ ሰዎች ነበሩ።



በ1944 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ለአገሩ ተወላጆች እውነተኛውን ወንጌል ለመስበክ የነበረው ጥማት እየጨመረ ሲመጣ፣ *ካምብሪጅን* ትቶ ወደ አገሩ፣ ወደ እስኮትላንድ ተመለሰ። በስኮትላንድ ማስተማሩን ሲጀምር ትኩረት የሰጠው ሐዋርያው ጳውሎስ በጻፈው በሮሜ መልዕክት ላይ፣ ማርቲን ሉተር ከሰላሳ ዓመት በፊት ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ መሆኑን በመተንተን ባስተማረው ክፍል ላይ ነበር። ያስተምር የነበረውም በነጻነትና ጸጋ በተሞላበት ሁኔታ ስለ ነበረ ጳጳሳቱ ብዙ ተከታይ ያገኛል በለው ስለፈሩ፣ ሁኔታው በጣም እያሰጋቸው መጣ። ለሁለት ዓመት ያህል *ጆርጅ ዊሻርት* ስኮትላንድ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ድረስ እየዞረ ሲሰብክና ሲያስተምር፣ የሮማ ካቶሊክ ቄሶች ትምህርቱን ለማስቆም በማሰብ ሊገድሉት ሞክረው ብዙ ጊዜ ከሞት አምልጧል።

አንድ ጊዜ ደቡብ ስኮትላንድ ውስጥ ቸነፈር መግባቱን ሰምቶ በስጋቸውና እንዲሁም በነፍሳቸው የታመሙትን ለመርዳት በአስቸኳይ በሄደበት ጊዜ ሕዝቡ የተቀበለው በደስታና በሙሉ ልብ ነበር። ያንን ስፍራ ትቶ ወደ መጣበት ከመመለሱ በፊት፣ በሊቀ ካህኑ በዴቪድ ቢተን የተቀሰቀሰ፣ *ጆን ዊተን* የተባለው የካቶሊክ ቄስ ሊገድለው ሞክሮ ነበር። ጆን ዊተን በለበሰው ካባ ውስጥ ጆርጅ ዊሽአርትን የሚወጋበት ጩቤ ይዞ ከመድረኩ ትንሽ ራቅ ብሎ፣ ሰብኮ ሲጨርስ ከሚቀመጥበት ስፍራ ሆኖ ይጠብቀው ነበር። ዊሻርት ግን ያ ሰው በለበሰው ካባ ውስጥ ጩቤ መያዙን አውቆ፣ "የእኔ ወንድም፣ ምንድነው የምትፈልገው?" ብሎ ከጠየቀው በኋላ፣ የያዘውን ጩቤ ከእጁ ፈልቅቆ ወሰደበት። ያም የካቶሊክ ቄስ ደንግጦ በጉልበቱ ተንበርክኮ፣ የመጣው እርሱን ሊገድል እንደነበረ ተናዞ ይቅርታ እንዲያደርግለት ለመነው። ውጪ ሆነው ሁኔታውን ይመለከቱ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች፣ ያንን ክፉና ተንኮለኛውን ሰው እንዲበቀሉት ለእነርሱ አሳልፈው እንዲሰጧቸው ጠየቁ። በጣም ከመናደዳቸው የተነሳ አጥሩን ጥሰው በመግባት ሊወስዱት ትንሽ ነበር የቀራቸው። *ዊሽአርት* ግን እጁን ይዞ *"ይህን ሰው ለመጉዳት የሚሞክር ሰው እኔን መጉዳት ነው፤ ይህ ሰው እኔን ምንም አልጎዳኝም። ወደፊት የበለጠ እንድጠነቀቅ*

*ግን ብዙ ትምህርት ሰጥቶኛል"* አላቸው። በዚህ ዓይነት ሕዝቡን ካረጋጋ በኋላ፣ ሊገድለው የመጣውን ያን የካቶሊክ ቄስ በሰላም አሰናበተው።

*ዊሻርት* ወደነበረበት ወደ ሞንትሮስ ከተማ ከተመለሰ በኋላ፣ በካቶሊክ እምነት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ካርዲናል ቢተን፣ ከሌላ ሰው የተጻፈ አስመስለው የውሸት ደብዳቤ ጽፈው ላኩለት። ደብዳቤውም፣ "አንድ በጣም የታመመ፣ ለሞት የተቃረበ ሰው አለና በአስቸኳይ መጥተህ እንድትረዳው" የሚል ነበር። አንድ ማይል ያህል ራቅ ብሎ፣ ካርዲናል ቢተን፣ 60 የሚሆኑ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች መንገድ ላይ አድፍጠው በመጠበቅ እንዲገድሉት ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር። ነገር ግን ዊሻርትና በጣም የቅርቡ የሆኑ ሰዎች ጥቂት ከተጓዙ በኋላ፣ ድንገት ጉዞውን መቀጠል እንደሌለባቸው ከውስጡ ልዩ የሆነ ስሜት ተሰማውና አብረውት ይጓዙ ለነበሩት ሰዎች፣ *"ጉዞዬን እንዳልቀጥል እግዚአብሔር ከልክሎኛል፤ መንገዳችን ላይ ሊጎዱኝ ያደፈጡ ሰዎች አሉ። ጥቂቶቻችሁ ቀድማችሁ በመሄድ በመንገዳችን ላይ ሊያጠቁን ያደፈጡ ሰዎች መኖር አለመኖራቸው ተመልከቱና ንገሩኝ"* አላቸው። ጥቂት ከሄዱ በኋላ *በካርዲናል ቢተን* የተደራጁ ጦር የታጠቁ ሰዎች መኖራቸውን ተመልክተው ይህንኑ ለዊሻርት ነገሩት። ዊሻርትም "አንድ ቀን በዚህ ደም በተጠማ ሰው ሕይወቴ እንደሚያልፍ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ፣ ሕይወቴ የሚያልፈው በአደባባይ ሕዝብ በግልጽ እያየኝ እንጂ፣ በደፈጣ አይደለም" አለ።

ብዙ ሳይቆይ *በ1546 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ዊሻርት* ደቡብ ስኮትላንድ ውስጥ መሆኑን ካርዲናል ቢተን ሰምተው የዚያን ክፍል አገረ ገዢ *ዊሻርትን* በቁጥጥሩ ሥር እንዲያውለው ጠየቁ። አገረ ገዢው ደስ ባይለውም፣ ወይም ከፈቃዱ ውጪ ቢሆንም፣ ካርዲናል ቢተንን ለማስደሰት ሲል፣ *ዊሻርትን* ይዞ ወህኒ ቤት አስገባው። ከዚያም ወደ *ኤደንበርግ* ተወስዶ ቅዱስ አንድሪው ጥንታዊ ሕንጻ ውስጥ እንዲታሰር አደረገ። በሚቀጥለው ቀን የመናፍቃውያንን ትምህርት ያስተምራል በማለት ተከሶ ከጳጳሳቱ ፊት እንዲቀርብና መልስ እንዲሰጥ ተደረገ። በዚያን ቀን ጥዋት፣ *ካርዲናል ቢተን* እውነተኛውን ወንጌል የሚሰብከውን ሰው የሚ



ያጅቡ ሳይሆን ጦር ሜዳ ሊሄዱ የተዘጋጁ የሚመስሉ መቶ ሰዎችን የወታደር ትጥቅ ይዘው እንዲያጅቡት አደረጉ። ይሄን ዓይነት አጀብ አስከትለውም ቢሆን፣ *ዊሻርትን* የሚወዱትና የሚያደንቁት ሰዎች ከእጃችን ነጥቀው ይወስዱት ይሆናል ብለው በጣም ይፈሩ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ጸጥ ብሎ ምንም ሳያወላውል ሄደላቸው።

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ *ካርዲናሉ* ፊት እንደ ቆመ፣ *ዳን ጆን ዊንሪሚ* የተባለው ሰው መድረኩ ላይ ወጥቶ ስለ መናፍቃውያንና ስለ መናፍቅ ትምህርት ሰበከ። ስብከቱን ሲጨርስ፣ *ጆን ላንደር* የተባለው ሌላ ሰው 18 ዓይነት ክስ በዊሻርት ላይ ዘርዝሮ አቀረበ። ክሱም የእርግማን፣ የስድብና የማስፈራራት ቋንቋ የተቀላቀለበት ነበር። የክሱን ዝርዝር መግለጫ ሲያነብ፣ ላቡ እስኪንጠባጠብ ድረስ በኃይለኛ ቁጣ ውስጥ ነበር። የተመሠረተበትን ክስ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ፣ "አንተ ከሃዲ፣ ቃልህን የማትጠብቅ፣ ሌባ፣ ለእነዚህ ለተከሰስክባቸው ነገሮች የምትሰጠው መልስ ምንድነው? ለእነዚህ ክሶች ለእያንዳንዳቸው በቂ መረጃና ምስክር አለኝ" በማለት ጮክ ብሎ ተናገረው።

*ዊሻርትም* በጉልበቱ ተንበርክኮ ከጸለየ በኋላ በጨዋና በረጋ መንፈስ ሆኖ፣ የክርስቶስ ውበት በሕይወቱ እየታየበት፣ "እናንተ በእኔ ላይ ለመፍረድ የተቀመጣችሁ ሰዎች፣ የግል እምነቴንና ያስተማርኩትን ትምህርት በትክክል ለማወቅ ከፈለጋችሁ ሰው የነገራችሁን ሳይሆን፣ ከእኔው ከራሴ ማዳመጥ ይገባችኋል። መከላከያዬን እንዳቀርብ የመናገር ዕድል ብትሰጡኝ፣ እናንተ ነፍሳችሁን እንዳታጡ፣ እኔም በሀሰት ክስ እንዳልሞት ሁለታችንንም ይረዳን ነበር። ለእናንተ በጎነት፣ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን፣ የእኔም ሕይወት ያለአግባብ እንዳይጠፋ፣ እናንተ ለመፍረድ የተቀመጣችሁ ዳኞች፣ ምን እንደማምን ወይም እምነቴ ምን እንደሆን እኔው ራሴ ስናገር በቀና ልብ ሆናችሁ በጥሞና አዳምጡኝ" አላቸው። በዚህን ጊዜ ቄሱ ላንደር በኃይል ጮክ ብሎ *"አንተ መናፍቃዊ፣ ከሃዲ፣ ሌባ! አንተ እንድትሰብክ ሕጉ አይፈቅድልህም። ከቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ሳታገኝ በራስህ ሥልጣን ለመስበክና ለማስተማር የምትሞክር ሰው ነህ"* አለው። በዚህ ጊዜ ዊሻርት ምን ለማድረግ እንዳሰቡ

ተገንዝቦ ደጋግሞ አቤቱታውን ቢያቀርብም ሰሚ ስላላገኘ፣ መከራብና ምንም ጥቅም እንደሌለው ተረዳ። በቀረበበት በ18ቱም ክሶች ከሃዲ (መናፍቅ) ነው ተብሎ፣ በስቅላትና በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈረደበት።

በእሳት ተቃጥሎ በሚሞትበት ቀን፣ ጥዋት ካርዲናሉ ሁለት ቄሶችን ወደ ወህኒ ቤት ላኩ። ጥቁር የናይለን ጨርቅ ኮት ካለበሱት በኋላ በተለያዩ የሰውነቱ ክፍሎቹ ላይ ፈንጂዎችን አሰሩበት። እጆቹን ወደ ኋላ አዙረው ጥፍር አድርገው አሰሩት። እንዲሁም በብረት ሰንሰለት ወገቡን ካሰሩ በኋላ በአንገቱ ላይ ያሰሩትን ገመድ እየሳቡ ወደሚሰቀልበትና በእሳት ወደሚቃጠልበት ስፍራ እንደ ከብት እየነዱ ወሰዱት። የዊሻርት ብዙ ወዳጆችና ደጋፊዎቹ የሞት ቅጣቱን ያደናቅፉ ይሆናል ብለው በመፍራት *ካርዲናል ቢተን፣ ዊሻርት* በእሳት ተቃጥሎ እስኪሚሞትበት ጊዜ ድረስ *መሣሪያ የታጠቁ ብዙ ሰዎች ዙሪያውን አሰልፈው ነበር። ወደ መሰቀያው* ሲወስዱት ከቄሶቹ አንዱ እየቀለደበት *"ዊሻርት! ከልጇ ጋር እንድታማልድህ ወደ እመቤታችን ጸልይ"* አለው።

ዊሻርትም፣ *"ወንድሞቼ እባካችሁን አቁሙ! እሳቱ የሚፈትነኝ ፈተና ይበቃኛልና በሌላ ፈተና አትፈትኑኝ!"* አላቸው። ዊሻርት ለመቃጠል ከተከመረው እንጨት አጠገብ በጉልበቱ ተንበርክኮ *"አንተ የዓለም አዳኝ የሆንከው ጌታ ሆይ! ልዩ ምሕረትህን በእኔ ላይ አድርግ። በሰማይ የምትኖር አባቴ ሆይ! ነፍሴን በቅዱሱ እጅህ ላይ አኖራለሁ"* ብሎ ከጸለየ በኋላ እንደ ገና ለከሳሾቹ *"የሰማዩ አባቴ ሆይ! በሀሰት የከሰሱኝን ሰዎች ሁሉ ይቅር እንድትላቸው እለምንሃለሁ"። እኔ በሙሉ ልቤ ይቅር ብያቸዋለሁ። ክርስቶስ ሆይ! አለማወቃቸው እንዳያስፈርድባቸው ይቅር እንድትላቸው እጠይቅሃለሁ"* ብሎ ከልቡ ጸለየ።

ይህን ብሎ ከጸለየ በኋላ በዚያ ስፍራ ተሰብስቦ ወደ ነበረው ሕዝብ ፊቱና አዙሮ እንዲህ ሲል ጮክ ብሎ ተናገረ። *"ስለ ቃሉና፣ ስለ እውነተኛ ወንጌል በእግዚአብሔር ለተሰጠኝ ጸጋ ዛሬ በሰዎች እጅ መከራን እቀበላለሁ። መከራውንም የምቀበለው በሀዘን ሳይሆን በደስታ ልብ ነው። የተላከሁትም ስለ ክርስቶስ ስል መከራን እንድቀበል ነው። ቀረብ ብላችሁ የፊቴን ገጽታ ብታዩ፣ ይህንን በኃይል የሚነደውን እሳት በመፍራት የፊቴ ቀለም ሲለዋወጥ አታዩም። ከደስታ በስተቀር ምንም ዓይነት ፍርሃት በውስጤ የለም። ዛሬ ማታ ከአዳኜ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እራት እንደምበላ አውቃለሁ'* አላቸው። በዚህ ዓይነት የብዙዎቹን ልብ የሚነካ ንግግር ሲያደርግ፣ ስቅላቱን የሚያስፈጽመው ሰው በዊሻርት እግር ሥር ተንበርክኮ *"የእኔ ጌታ እባክሀን ይቅር በለኝ፤ እኔ አንተ እንድትሞት አልፈረድኩብሀም፤ ከበደሉ ንጹህ ነኝ"* አለው። ይህን ሲለው *ዊሻርት ያንን ሰው፣ "የእኔ ወንድም በሙሉ ልቤ ይቅር ብዬሃለሁ። ይቅርታ እንዳደረግሁልህ ይሄ ማረጋገጫ ይሁንልህ። አንተ ሥራህን ሥራ"* ብሎት እቅፍ አድርጎ ጉንጩን ሳመው።

*ዊሻርት ተፈርዶበት መስቀያ* እንጨቱ ላይ ከሰቀሉት በኋላ ከሥሩ የተከመረውን እንጨት ለኮሱት። በኃይል የሚነደው እሳት ሰውነቱን አቃጥሎ ፍጹም አመድ እስኪሆን ድረስ ለረጅም ጊዜ ተሰቅሎ ቆየ። በዚህ ዓይነት ስቃይ ሲሞት የሚያዩ ሰዎች፣ ዕንባቸውን መቆጣጠር እስከሚያቅታቸው ድረስ ያለቅሱ ነበር። ንጹህ ሰው በማሰቃየታቸው ጳጳሳቱን ይሰድቡና ይረግሙ ነበር። በዚህ ዓይነት በጣም የተቆጣው ሕዝብ በቁጣ በመነሳሳት፣ የዚህ ግፍ ምክንያት የሆነውን ካርዲናሉን ገድለው በኃይል ህንጻውንና ንብረቱን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በቁጥጥራቸው ሥር እንዳደረጉት የሰማዕታት ታሪክ ይመሰክራል።

ወንጌሉን ለመስበክ በከተማም ሆነ ከከተማ ውጪ በምድርም ሆነ በባሕር ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወር ሕይወቱን ለማጥፋት የሚፈልጉ ነበሩ። እነዚያ ጠላቶቹ አይሁዳውያን፣ አሕዛብ ወይም ሐሰተኛ ወንድሞች ይሁኑ፣ እያንዳንዳቸው ሕይወቱን ለማጥፋት የሚፈልጉበት የራሳቸው የሆነ ምክንያት ነበራቸው። ብዙ ሰዓት ያለመታከት፣ ያለ ዕንቅልፍ፣ ያለ ምግብ ብዙ ይሠራ ነበር። በተጨማሪ ለተከላቸው አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት በመናፍቃውያን ሀሰተኛ ትምህርት ምክንያት ይከፋፈሉ ይሆናሉ ብሎ በመፍራት ይጨነቅ ነበር። በመጨረሻ በእምነቱ ምክንያት ሮም ውስጥ የሞትን ጽዋ በመቅመስ ከፍተኛውን ዋጋ (መስዋዕት) ከፈለ።

የጳውሎስ የሐዋርያነት ሕይወት የመከራና የጭንቀት ሕይወት ነው። ያለፈበትን የመከራ ሕይወት ሲዘረዝር፣ *"...በብዙ ትዕግስት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በመታሰር፣ በሁከት፣ በሥራ ብዛት፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመራብ፣ በንጽሕና፣ በዕውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር፣ በእውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኃይል፣ በቀኝና በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመያዝ፣ በክብርና በውርደት፣ በመመስገንና በመሰደብ ኖረናል፤ ደግሞም እውነተኞች ስንሆን ሐሰተኞች ተብለናል፤ የታወቅን ስንሆን እንዳልታወቅን ሆነናል፤ሞተዋል ስንባል እንሆ በሕይወት አለን፤ ብንደበደብም አልተገደልንም"* (2 ቆሮ. 6፥4-9) አለ።

## 2. የመስቀሉ ኃይል ኃጢአትን "እምቢ" እንድንል ያስችለናል

ዮሴፍ ከእግዚአብሔር ብዙ በጎ ነገር ስለተቀበለ፣ በጶጢፋር ሚስት አማካኝነት ኃጢአት እንዲሠራ ግብዣ ሲቀርብለት፣ ግብዣውን መቀበል "እምቢ!" አለ።"እምቢ ያለው ሰዎች ያዩናል፣ ጶጢፋር ይመጣል፣ ችግር ላይ እወድቃለሁ" ብሎ በማለት ሳይሆን፣ በጎ ያደረገለትን ጌታውን፣ የራሴ ያልሆነውን በመውሰድ እንዴት አስቀይመዋለሁ በማለት ነው። "እምቢ!" ያለውም "በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?" በማለት ነው (ዘፍ. 39፥10)። ዳዊት ኦርዮንን አስገድሎ፣ ሚስቱን ነጥቆ ከወሰደ በኋላ ኃጢአቱ ሲገለጽ ያሰማው የንስሀ ጩኸት፣ "እኔ ያመጽሁት በአንተ ላይ ነው፤ የበደልሁትም አንተን ብቻ ነው" የሚል ነበር (መዝ. 51፥1)። ኃጢአት ሲሠራ የበደለው ያከበረውን፣ ከበግ እረኛነት አንስቶ ንጉሥ ያደረገውን አምላኩን እንደሆነ ተረድቷል። ፍቅሩ ኃጢአት እንዳይሠራ ግድ ሊለው ይገባ ነበር።እኛም ኃጢአት ስንሠራ፣ የክርስቶስን ቁስል በሚስማር እንደገና መንጎጣችን መሆኑን ስናውቅ፣ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ያሳየን ፍቅር ትዝ ብሎን፣ "ስለ እኔ ሲል የሞተውን ጌታ ለምን አስቀይማለሁ?" በማለት ኃጢአትን እምቢ እንላለን።



"የክርስቶስ መስቀል ለእኛ የእግዚአብሔር ኃይል" የሚሆነው እንዴት ነው? የክርስቶስ መስቀል ኃጢአትን "እምቢ!" እንድንል የሚያስችለንን ኃይል ይሰጠናል። ኃጢአት ስንሠራ የክርስቶስን ቁስል እንደገና በሚስማር መውጋታችን መሆኑን ስለምናውቅ፥ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የከፈለንልን፥ ያሳየን ፍቅር ትዝ ይለንና "ስለ እኔ ሲል የሞተውን ጌታ ኃጢአትን በመሥራት ለምን አስቀይማለሁ? ለምንስ ቁስሉን በሚስማር እየደጋገምኩ እወጋለሁ?" በማለት ኃጢአትን "እምቢ!" እንላለን። የመስቀሉ ኃይል ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለጌታ እንድንሰጥ ያስችለናል። ራሱን በሞት አሳልፎ ለሰጠ አምላክ፥ ራስን መስጠት አያስቸግርም። ፍቅር የማያሸንፈው ኃይል ምንም የለም፤ ክርስቶስ በፍቅሩ እንጂ፥ በጉልበትና በኃይል አላሸነፈም። የመስቀሉ ኃይል ለአምላካችን ታማኞች እንድንሆን ኃይልን ይሰጠናል። ክርስቶስን ከመስቀል እንዲወርድ የሚያደርጉት ብዙ ግፊቶች ደርሰውበታል። ይሁን እንጂ፥ የመጨረሻውን የሞት ጽዋ ከመጠጣት ወደ ኋላ አላለም። የመስቀሉ ፍቅር በደንብ የገባቸው አማኞች ለሞተላቸው አምላክ በእሳት ተቃጥለው፥ በዘይት ተቀቅለው፥ በአውሬዎች ተበጣጥሰው፥ በመጋዝ ተሰንጥቀው ሞተ ዋል። ዛሬ ወንጌል ለእኔና ለእናንተ ሊደርስ የቻለው እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ በመሆናቸው ነው።

## 3. የመስቀሉ ኃይል የበደሉንን ይቅር እንድንል ያስችለናል

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ ለገረፉት፣ የሾህ አክሊል ለደፉበት፣ በጦር ጎኑን ለወጉት፣ ልብሱን ገፈው ዕጣ ለተጣጣሉበት *"የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"* ሲል ጸለየላቸው። ከልብ የወጣ፣ ሙሉ ይቅርታ ያለበት የልብ ጩኸት ነው። ይቅርታ መስጠት ከባድ ነው። የመስቀሉ ኃይል ግን ለበደሉን ይቅርታ እንድንሰጥ ያስችለናል። የመስቀሉ ትርጉም የገባው እስጢፋኖስ እውነትን በመናገሩ ምክንያት በድንጋይ ሲወገር፣ ለሚወግሩት ሰዎች "የሚያደርጉትን አያውቁምና

ይቅር በላቸው" ብሎ ከልቡ ጸለየ። እስጢፋኖስ ለወገሩት ይቅርታ መስ ጠቱ ባያድነውም፤ ልቡ ተፈትቶ የክብር ሞት ሞተ። በውስጣችን የበቀ ለውን መራራ ሥር ሳናስወግድ አንሙት። የመስቀሉ ኃይል የበደሉንን ይቅር እንድንል ኃይልን ይሰጠናል።

*የመስቀሉ መንገድ የእርቅ መንገድ ነው። ጳውሎስ "ነገር ግን እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ ክርስቶስ በእኛ ምትክ ሞቶአል፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ያስረዳል። እንግዲህ የጸደቅነው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሆነ ይበልጡንም ከእግዚአብሔር ቁጣ የምንድነው በእርሱ አማካይነት ነው። ምክንያቱም እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን ሳለ በልጁ ሞት ከእግዚ አብሔር ጋር ታርቀናል፤ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅን በኋላ በሕያው ልጁ አማካይነት ይበልጡን እንድናለን"* (ሮሜ 5፥8-11) ይላል። ጳውሎስ በኤፌሶን 2፥12-14 ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካ ኝነት ስለሚገኘው እርቅ፣ በጣም ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል። *"አሁን ግን እናንተ ከዚህ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁት፣ በኢየሱስ ክርስ ቶስ ሆናችሁ በእርሱ ደም ቀርባችኋል። ሁለቱን የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰና ሁለቱን አይሁዳውያንንና አሕዛብን አንድ ያደረገ ሰላማችን ክርስቶስ ነው"* ይላል። በክርስቶስ መስቀል የታረቅነው በሦስት አቅ ጣጫ ነው። ይኸውም፣

አንደኛ መስቀሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያስታርቀናል። ከሰዎች ጋር ለይቶን የነበረው ግድግዳ በመስቀሉ አማካኝነት ይፈርሳል። የክር ስቶስን ፍቅር በሕይወታችን መለማመድ ስንጀምር፣ ሁለተኛ፤ ከእግዚ አብሔር ጋር፤ እንዲሁም ሦስተኛ ከራሳችንም ጋር የታረቅን እንሆ ናለን። በተጨማሪ የማስታረቅ ሥጦታን እንዲምስጠን ጳውሎስ ይናገ ራል። *"ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ አዲስ ሆኖአል። ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ አማ ካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን"* ይላል (2 ቆሮ. 5፥18-19)። የክርስቶስ ፍቅር በሕይወታችን ሲፈስ፣ ከሌሎች ጋር የሚኖረን ጦርነት ያበቃል። የቤዛነት ውጤት ለእግዚአ



ብሔርና ለሌሎች ፍቅርን ይሰጣል። ክርስትና የእርቅ ሕይወት ነው። የእርቅ ውጤት ከእግዚአብሔር ጋር፣ ከራሳችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሰላምን መፍጠር ነው።

በቅርቡ አንድ ክርስቲያን ወንድም "አለ" የተባለውን ነገር ሰምቼ፣ አንዳንዶቻችን ራሳችንን "ክርስቲያኖች" ብለን ብንጠራም፣ የክርስትና መንገድ በደንብ ያልገባን መሆናችንን አሳየኝ። በምክንያት ተጋጭተው ለሁለት ከተከፈለው ሕብረት ውስጥ፣ ከአንደኛው ወገን ያሉት፣ "ብንለያይም እንጣላ!" በማለት የእርቅ እጃቸውን ዘረጉ። በሌ ላው ወገን ካሉት መሪዎቹ መካከል አንዱ "ከእነርሱ ጋር ከመታረቅ በገመድ ታንቄ ብሞት ይሻለኛል" እንዳለ ሰምቼ፣ በመገረም "እውነ ትም ይህቺ ናት ክርስትና!" ብዬ አልኩ።

የመስቀሉ ኃይል በውስጣችን መራራ ሥር እንዳይበቅል እራሳ ችንን እንድንጠብቅ ይረዳናል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ በሚሰቃይበት ወቅት ለገረፉት፣ የሾህ አክሊል ለደፉበት፣ በጦር ጎኑን ለወጉት፣ ልብሱን ገፍፈው በልብሱ ዕጣ ለተጣጣሉበት፣ "ይሰቀል" ብለው ለጮኹት፣ በጥፊ ለመቱት፣ ምራቃቸውን ለተፉበት፣ *"የሚያደ ርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"* ሲል ጸለየላቸው። ይህን ዓይነቱ ፀሎት ከልብ የወጣ ሙሉ ይቅርታ ያለበት እውነተኛ የሆነ የልብ ጩኸት ነው። ይቅርታ መስጠት ከባድ ነው። ይሁን እንጂ፣ የመስ ቀሉ ኃይል ለበደሉን ይቅርታን እንድንሰጥ ያስችለናል። የመስቀሉ ትርጉም በደንብ የገባው እስጢፋኖስ እውነትን በመናገሩ ምክንያት በድንጋይ ለሚወግሩት ሰዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ እንደ ጸለየው "የሚያደርጉትን አያውቁምን ይቅር በላቸው" ብሎ ጸለየ። እስጢፋኖስ በወቅቱ በድንጋይ ለሚወግሩት ይቅርት መስጠቱ ከሞት ባያድነውም፣ ልቡ ተፈትቶ እንደ ጌታው "የክብር ሞት" ሞተ።

በእምነታቸው ምክንያት በመከራ፤ በስደት፤ በልዩ ልዩ ፈተና ውስጥ ያለፉ፤ ስለ እምነታቸው ዋጋ የከፈሉ በሐዋርያት ዘመን የነበሩ አማኞች ብቻ ሳይሆኑ፤ በየዘመናቱ የእምነት አርበኞች መጥተው አልፈ

ዋል። የሚያልፉበት ፈተና፣ የሚቀምሱት የመከራ ጽዋ፣ የሚሰደዱበት የስደት ዓይነት የተለየ ይሁን እንጂ፣ በእኛም ዘመን እውነተኛ የሆኑ የእምነት አርበኞች አሉ። እንደ ጥንቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ በአሁኑም ጊዜ እየተሰደደች ናት። እውነትን ይዛ እስከ ቆመች ድረስ፣ የወንጌሉን ቃል በእውነትና በግልጽ እስካወጀች ድረስ፣ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ በስደት ውስጥ ታልፋለች። ዛሬም ስለ እምነታቸው በየዕለቱ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ብዙዎች አሉ። ያፈሰሱት ደም፣ የከፈሉት ዋጋ እንዲሁ ተሸፍኖ ወይም ተረስቶ የሚያልፍ ሳይሆን፣ አንድ ቀን በጌታ ፊት ቀርበው የሰማዕትነት ዘውድን እንደሚያሰጣቸው ግልጽ ነው።

የእነዚህ ሰማዕታት ጩኸት ውስጣችንን እንዲቀሰቅስ፣ ድፍረት፣ እምነት፣ ቆራጥነትና እንዲሁም ለጌታቸው ያላቸው እውነተኛ ፍቅር እንደ ተላላፊ በሽታ እኛንም እንዲነካን፣ የእነርሱን ፈለግ ተከትለን ድርሻችንን እንድንፈጽም ኃይልን እንዲሰጠን የሁላችንም ጸሎት ይሁን። ከመጀመሪያው ሰማዕት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መጥተው ያለፉት የእምነት አርበኞች በሕይወታቸው ተወዳድረው፣ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለው ያስተላለፉልንን ወንጌል፣ እኛም በምድራዊ ሀብት ሳንሸቃቅጠውና ማትረፍያ ሳናደርገው፣ እነርሱ የከፈሉትን ዓይነት ዋጋ ከፍለን ለሌሎች ማስተላለፍ እንድንችል እግዚአብሔር ለሁላችንም ጸጋውን ያብዛልን።

## 4. የመስቀሉ ኃይል የማይወደደውን መውደድ ያስችለናል

በመስቀሉ ኃይል አለ። ኢየሱስን የመስቀል ሞት እንዲሞት ያደረገው ለሰው ልጅ ካለው ብርቱ ፍቅር የተነሳ ነው። ለእኛ ያሳየው ፍቅር ምን ዓይነት እንደሆነ ሲገልጽ፣ *"ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም"* አለ (ዮሐ. 15፡13)። ሐዋርያ ዮሐንስ ደግሞ ክርስቶስ እንዴት እንደወደደን ሲገልጽ፣ *"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና፣ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል"* አለ (1 ዮሐ. 3፡16)።



የማፍቀር ኃይልንና ፈቃድን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው። መኖር ሲደክመንና ሲሰለቸን፣ በመከራ ውስጥ ስናልፍ፣ ስሜታችን ሲጎዳ ከምንጊዜውም የበለጠ የሚወደንን እንፈልጋለን እንጂ ሌላውን የምንወድበት አቅም አይኖረንም።

የማይወደደውን ለመውደድ የእኛን ፈቃድ ይጠይቃል። መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ፍቅራችንንም በሥራ ለመግለጽ እርምጃ መውሰድ አለብን። ፍቅራችንን ለማይገባው ሰው ለመስጠት ውስጣችን "እምቢ!" ሲለን፣ ምንም ሳናስቀር እንድንሰጥ የሚያስችለን የመስቀሉ ኃይል ነው። የጎዱን፣ ያጠቁን፣ የገፉን፣ ስማችንን በጭቃ የለወሱትን፣ መውደድ በሰው ኃይል ስለማይቻል፣ እነርሱን የምንወድበት ኃይልን የምናገኘው የመስቀሉ ኃይል ሲገባን ነው። *"እግዚአብሔር ሆይ! "እከሌን መውደድ አልችልም" ስንል፣ ነፍስህን እስከ መስጠት ድረስ የወደድከኝን ጌታ መውደድ አልችልም፤ ለአንተ በቂ ፍቅር የለኝም"* ማለታችን እንደሆነ የተገነዘብነው አንመስልም።

እርሱ የፍቅር አምላክ ስለሆነ፣ ፍቅር የሚጀምረው በእግዚአብሔር ፍቅር ስንሞላ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር በሰው ሕይወት ውስጥ ሲፈስ፣ የሰውን ሕይወት ይለውጣል፣ የክርስትናን ባህሪ በውስጣችን ይቀርጻል። ፍቅር ከአምላክ ነው፤ ፍቅሩን የመቀበልና የመስጠት ችሎታ ሰጥቶናል። ፍቅር ብድራትን አይጠብቅም፤ የምንወደው ሰው መልሶ እንዲወደን፣ በጎ ያደረግንለት ሰው መልሶ በጎ እንዲያደርግልን መጠበቅ የሁላችንም ፍላጎት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶቻችንን፣ ክፉ የሚያደርጉብንን እንድንወድ ሲያዘን ከእነርሱ ምንም በጎ ነገር ሳንጠብቅ ነው። ኢየሱስ *"እናንተ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም ነገርም አድርጉላቸው፤ ብድራችን ይመለስልናል ብላችሁ ተስፋ ሳታደርጉ አበድሩ፤ ይህን ብታደርጉ ዋጋችሁ ትልቅ ይሆናል፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጆችም ትሆናላችሁ፤ እርሱ ለውለታቢሶችና ለክፉዎች እንኳ ሳይቀር ቸር ነው። የሰማይ አባታችሁ መሐሪ እንደሆነ እናንተም እንዲሁ መሐሪዎች ሁኑ"* ይለናል (ሉቃ. 6፡35-36)።

## 5. የመስቀሉ ኃይል ልባችንን በርህራሄ ይሞላል

ኢየሱስ በሰማይና በምድር መካከል ተንጠልጥሎ፣ እጆቹና እግሮቹ በሚስማር ተጠርቅቀው፣ ጎኑ በጦር ተወግቶ፣ በጭንቀትና በስቃይ እያለ፣ ዐይኖቹን ከራሱ መከራ ላይ አንስቶ ሌሎቹን በርህራሄ ዐይን የማየት አቅም ነበረው። ከመስቀሉ ላይ ሆኖ ወደታች ሲመለከት፣ በሀዘን ልቧ የተሞደሸውን እናቱን አይቶ፣ ይወደው የነበረውን ዮሐንስን "እነሆ እናትህ..."፣ እንዲሁም እናቱን ወደ ዮሐንስ እያመለከተ፣ "...አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ" አላት። ኢየሱስ ይህን በተናገረበት ወቅት እያንዳንዱ የራሱ የሆነ ሀዘን፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት እንደነበረው ያውቃል። ኢየሱስ በዚያ ወቅት ሊያስተላልፈው የሞከረው መልዕክት፣ እያንዳንዱ የራሱን ጭንቀትና ፍርሃትን ትቶ ስለሌላው እንዲያስብ ለማድረግ ነበር።

የክርስቶስ ተከታዮች በዚህ ወቅት አመለካከታቸው በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነበር። ይኸውም ዓይናቸው ያረፈው በመስቀሉ ላይ በተንጠለጠለው ክርስቶስ ላይ ብቻ ነበር። ኢየሱስ ለማስተማር የፈለገው አምልኮታቸው የተሟላ እንዲሆን፣ ወደ ላይ ብቻ ሳይሆን ወደ ጎንም መመልከት እንዳለባቸው ነው። አማኞች ከአማላካቸው ጋር ድንቅ የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል። ሲያመልኩ፣ ሲጸልዩ፣ ሲያገለግሉ፣ አሥራታቸውን ሲከፍሉ፣ ሌላ ነው። ነገር ግን አጠገባቸው ካለው ወንድማቸው (እህታቸው) ጋር ያላቸው ግንኙነት የተቀራረበ አይደለም። ስለ ወንድማቸው ልባቸው ርህሩህ አይደለም። ኢየሱስ ከርህራሄው የተነሳ የራሱን መከራ ፈጽሞ ረሳ።

እርግጥ ነው እኔና እናንተ ርህራሄን ለብሰን አንወለድም። በተፈጥሯችን ግን ርሁሩህ እንድንሆን የሚያስችል ኃይል ሁላችንም አለን። በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠርን፣ ባህሪው በውስጣችን አለ። መስቀሉን በመሸከም ክርስቶስን የምንመስል ከሆነ፣ በርህራሄውም እንመስለዋለን። በርህራሄ ስንሞላ በጭንቀት፣ በችግርና በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን በምላሳችን ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለመርዳት እጆቻችንን ለመዘርጋት የሚያስችል ኃይል ይኖረናል። ስለ ወንድሞቻችን በጎ የሆነውን እንድናስብ፣ እንድ



ንጨነቅ፣ ለበጎ ሥራ እጆቻችንን እንድናነሳ ያደርገናል። መስቀሉን የመሸከም አቅም ሲኖረን፣ ርህራሄ ልናሳየው፣ ፍቅራችንን ልንሰጠው የምንችለው፣ በኑሮው የተጨነቀ፣ ውስጡ የቆሰለና የደማ ማን ነው?" በማለት ርህራሄ የምናሳየውን ሰው እንፈልጋለን።

# 8

# ያለመስቀል ዘውድ የለም

*"በእግዚአብሔር ታመን፤ በርታ! ተስፋ አትቁረጥ፤ በእግዚአብሔር ታመን" (መዝ. 27፡14)*

*"መ*ስቀል አጋጥሞኝ አያውቅም...ለእኔ የክርስትና ሕይወት ቀላል ነው..."* የሚል ክርስቲያን ቢኖር፣ ያ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን መሆኑ ያጠራጥረናል። የሁላችንም መስቀል አንድ ዓይነትና እኩል አይደለም። እንደ አቅማችን ይለያያል። በበኩሌ ክርስትና ቀሎኝ አያውቅም። *"መንገዱ ጠባብ"* ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይሁን እንጂ፣ ከምንችለው በላይ በትከሻችን ላይ ጭኖ አይገድለንም። መንፈሳዊ ሞት የምንሞተው መስቀል በመሸከማችን ሳይሆን፣ መስቀል የሌለበት ሕይወት ለመኖር ስንሞክር ብቻ ነው። መስቀላችን ትልቅ ሆኖ ከተሰማን፣ በማጉረምረም ፈንታ *"ምን ያህል ቢታመንብኝ ነው?"* በማለት ደስ ሊለን ይገባል። ካሰብን ደግሞ እርሱ ያልሰጠንን መስቀል ተሸክመን ለመሄድ ብንሞክር፣ ያለአግባብ ራሳችንን እንጎዳለን እንጂ የበለጠ ሽልማት አያስገኝልንም።



### 1. መፍራት ያለብን መስቀል የሌለበትን ሕይወት መኖርን ነው

የመከራችንን ትክክለኛውን ምክንያት ብናውቅም ባናውቅም ከሚደርስብን መከራ፣ ችግርና ፈተና ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ትምህርት እናገኝበታለን። ጳውሎስ በመከራ ውስጥ ስለሚገኘው ጥቅም ሲገልጽ፣ እንዲህ አለ፥

- *"የምሕረት አባትና የመጽናናት ሁሉ አምላክ ለሆነውና እንዲሁም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ለሆነው አምላክ ምስጋና ይሁን። እኛ ከእግዚአብሔር በምናገኘው መጽናናት በመከራ ላይ ያሉትን ሁሉ ማጽናናት እንድንችል፣ እግዚአብሔር እኛን በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል። የክርስቶስን መከራ በብዛት እንደምንካፈላችን መጠን፣ እንዲሁም በክርስቶስ አማካይነት መጽናናትን በብዛት እናገኛለን። እኛ መከራ ስንቀበል እናንተ መጽናናትና ደኅንነት ታገኛላችሁ፤ እኛ ስንጽናና ደግሞ እናንተም እኛ የምንቀበለውን መከራ በትዕግሥት ተቀብላችሁ ትጽናናላችሁ"* ይላል (2 ቆሮ. 1፡3-6)።

እንዲሁም ሐዋርያው ጴጥሮስ በሕይወታችን ልዩ ልዩ መከራ እንዲደርስ እግዚአብሔር ለምን እንደሚፈቅድ ሲገልጽ፣

- *"ይህ ፈተና የደረሰባችሁ የእምነታችሁን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ነው፤ የሚጠፋ ወርቅ እንኳ በእሳት ይፈተናል፤ ከወርቅ ይልቅ የከበረ እምነታችሁ እንደዚሁ መፈተን አለበት፤ ይህም የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን ያስገኝላችኋል"* ይላል (1 ጴጥ. 1፡7)።

በሕይወቱ ውስጥ የሚያጋጥመውን አስቸጋሪ ሁኔታ ተቀብሎ ለዕድገቱ የሚጠቀምበት አማኝ የተባረከ ነው። ከበጎ ነገር ብቻ ሳይሆን ከክፉ ነገር ውስጥም ለመማር ፈቃደኛ የሆነ ሰው ከመከራው ብዙ ትምህርትን ያገኛል። አንዳንድ መከራ በሕይወታችን ሲደርስ፣ መጽ

ናኛ የሚሆነን ክፍል ከቃሉ ይሰጠናል። የተሀድሶ እንቅስቃሴ መሪ የነበረው ማርቲን ሉተር፣

- *"በመከራ ውስጥ ባላልፍ ኖሮ ስለ እግዚአብሔር ቃል በቂ የሆነ መረዳት አይኖረኝም"* ነበር አለ።

እግዚአብሔር ሊያስተምረን የሚፈልገውን ነገር ጎልቶ እንዲታየንና የበለጠ እንዲጠቅመን ያደርግልናል። ወደ መንፈሳዊ ዕድገት የሚያደርሰን ዲሲፕሊን መደረጉ ብቻ ሳይሆን፣ ከቃሉ የምናገኘው ትምህርት ጭምር ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን፣

- *"አምላክህ እግዚአብሔር የሰጠሀን ትእዛዝ ስለ መጠበቅህ በልብህ ያለውን አሳብ ያውቅ ዘንድ አንተን ለመፈተን በዚህ በረሓ አርባ ዓመት ሙሉ በመከራ ውስጥ በማሳለፍ እንዴት እንደመራህ አስታውስ። በረሀብ እንድትሠቃይ አደረገህ ቀጥሎም አንተም ሆነህ የቀድሞ አባቶችህ የማታውቁትን መና አበላህ ይህንንም ማድረጉ ሰው ሕይወቱ ተጠብቆለት መኖር የሚችለው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አለመሆኑን ሊያስተምርህ ነው። በእነዚህም አርባ ዓመታት ውስጥ ልብስህ አላለቀም፤ ከጉዞም የተነሣ እግርህ አላበጠም። አባት ልጆቹን በመገሠጽ እየቀጣ በሥነ ሥርዓት እንደሚያሠለጥን፣ አምላክህ እግዚአብሔርም አንተን እየገሠጸና እየቀጣ በሥነ ሥርዓት ያሠለጠነህ መሆኑን አስታውስ"* ይላቸዋል (ዘዳ. 8፡2-5)።

እግዚአብሔር በሕይወታችን መከራ እንዲደርስ ለምን እንደ ፈቀደ፣ ምክንያቱን ብናውቀውም ባናውቀውም፣ *"በመከራ ውስጥ እንድናልፍ የፈቀደው ጥሩ ምክንያት ቢኖረው ነው"* ብለን አምነን መቀበል አለብን። አልፎ አልፎ ምድራዊ አባት ልጆቹን የሚቀጣበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፣ የሚሰጣቸው ቅጣት ከእነርሱ አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነውን ነው። ሰማያዊ አባታችን የሆነውም እግዚአብሔ



ርም ከአቅማችን በላይ መስቀል አያሸክመንም። *ከመስቀል ውጪ መኖር፣ ዲሲፕሊን የሌለው ሕይወት መኖር ነው።*

## 2. መስቀሉ የቅድስናው ተካፋዮች ያደርገናል

መስቀሉን ስንሸከም በመከራና በስቃይ ውስጥ እናልፋለን። እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ እንድናልፍ የሚፈቅደው፣ የቅድስናው ተካፋዮች ሆነን እንድናድግ ስለሚፈልግ ነው። የሥጋ አባቶቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው እንደሚቀጡን ሁሉ እግዚአብሔርም አልፎ አልፎ ይቀጣናል። የሚቀጣበት ምክንያት ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ፣

- *"...እርሱ ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለጥቅማችን ይቀጣናል"* ይላል (ዕብ. 12፡10)።

*"መከራና ስቃይ ከቅድስና ጋር ምን ግንኙነት አለው?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በመከራ ውስጥ ስናልፍ፣*

*መከራ ከምንጊዜውም የበለጠ ኃጢአተኛው ተፈጥሯችን ምን ያህል የተበላሸ እንደሆነ አጉልቶ ያሳየናል። ሁሉ ነገር መልካም በሚሆንልን ጊዜ ግን በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ኃጢአት እንደሚገባው አጥርተን ማየት አንችልም። መከራ ሲገጥመን በሕይወታችን ያለው ኃጢአት ይታየንና ከእግዚአብሔር ምሕረትን እንድንጠይቅ ያደርገናል።*

በመከራና በስቃይ ውስጥ በማሳለፍ እግዚአብሔር ዲሲፕሊን እንድንሆን የሚፈቅድበት ምክንያት ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ሥር የሰደደ እንዲሆን ነው። በመከራ ውስጥ በኃያሉ እግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ዝቅ አድርገን ራሳችንን እንድናስገዛ፣ በጥበቡ እንድንታመን፣ በፍቅሩ እንድንጽናና ነው። ኢዮብ ምዕራፍ 42፡5 ላይ *"እስካሁን ስለ አንተ የማውቀው ሰዎች የነገሩኝን በመስማት ብቻ ነበር፤ አሁን ግን በዐይኖቼ አየሁህ"* እንዳለው እኛም እዚያ ደረጃ ላይ

ስንደርስ እንዲሁ እንላለን። እግዚአብሔርን በታሪኩ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት መፍጠር ያስችለናል።

በመከራችን ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ የሆነ ሕብረት መፍጠር ያስችለናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዮስ አማኞች በጻፈው መልዕክቱ በመከራው ኢየሱስን መምሰል እንደሚመኝ ገልጿል (ፊልጵ. 3፥10)። *"ክርስቶስን ለማወቅ"* ሲል፣ ተራ ዕውቀት ሳይሆን እጅግ በጣም የተቀራረበ ግላዊ የሆነ ግንኙነት ማለቱ ነው። ብዙዎቻችን ክርስቶስን በብዙ መንገድ ልንመስለው እንመኛለን፤ በመከራው ግን ጳውሎስ እንደሚለው ለመምሰል አንዳንዶቻችን እርግጠኞች አይደለንም። ክርስቶስን በማወቅ ለማደግ ብንፈልግ ግን፣ የግድ በመከራው ልንመስለው ፈቃደኞች እንሆናለን። እንዲሁም የትንሣኤውን ኃይል ለማወቅ በሞቱ እርሱን መምሰል እንፈቅዳለን። ጳውሎስ የቀመሰው መከራ ስለ ወንጌል መሰደድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ መከራዎችን አይቷል። ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ካረፈበት ጊዜ ጀምሮ ብዙዎች መስቀላቸውን እንደሚገባው የተሸከሙ በዘመናት መጥተው እንዳለፉ በሰፊው ተመልክተናል። እኛም የእነርሱን አርአያ ተከትለን መስቀላችንን እንደሚገባው ተሸክመን ማለፍ አለብን።

ጌታ የሚወደውን የሚገስጽ ወይም የሚቀጣ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይሄ እውነት ተግባራዊ ሲሆን የምናየው በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ውስጥ ይኖሩ በነበሩ አማኞች ሕይወት ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ዘመን ባለነው አማኞች ሕይወትም ጭምር ይታያል። ዲሲፕሊን ፍቅር ከሞላበት፣ ስለ ልጆቹ መንፈሳዊ ዕድገትና በጎነት ከሚያስብና ከሚጨነቅ አባት የሚመጣ እንደሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ልጆቹን ዲሲፕሊን ከሚያደርግባቸው መሣሪያዎች መካከል አንደኛው፣ በመከራና በችግር ውስጥ እንዲያልፉ በመፍቀድ ነው። ይሄም በፍቅር የተሞላ መሆኑን፣ ፍቅሩንና ጥንቃቄውን እንጂ መጥላቱን የሚያመለክት አይደለም። የዕብራውያንን መልዕክት የጻፈው ሰው፣



- *"ልጄ ሆይ! የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አታቃልል፤ በቀጣህም ጊዜ ተስፋ አትቁረጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚወደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጅ አድርጎ የሚያየውንም ይቀጣል"* ይላል (ዕብ. 12፥5-6)።

የፍቅሩ ምልክት ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ እንዳናቃልል፣ ሲቀጣንም ተስፋ እንዳንቆርጥ ጸሀፊው ይመክረናል። "አታቃልል" ሲል፣ ዋጋ የሌለው፣ የማይጠቅም አድርግህ አትመልከት ማለቱ ነው። መፍራት ያለብን ቅጣቱን ሳይሆን፣ በመከራችን ውስጥ የእግዚአብሔርን እጅ ማየት ሲያቅተን ነው። በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ስናልፍ፣ ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን አምነን በመቀበል ፈንታ፣ እንዲሁ እንደ አጋጣሚ በእኛ ላይ የደረሰብን አድርገን ከተመለከትነው፣ ለጥቅማችን የመጣ መሆኑን መቀበል ያቅተናል። እንዲሁም የምናልፍበት የመከራ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር አሳብ ወይም ዓላማ ምን እንደሆነ ስለማንረዳ፣ በራሳችን ጥረት ከመከራችን መውጣት የምንችልበትን መንገድ ለማግኘት ብዙ ትግል ውስጥ እንገባለን።

በሕይወታችን የሚደርሱ አንዳንድ መከራውችና ችግሮች፣ እንዳጋጣሚ የሚፈጠሩ ሳይሆኑ የእግዚአብሔር የእጆቹ ሥራዎች እንደሆኑ ወይም ከእርሱ የሚመጡ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ሥፍራ ይናገራል።

- *"እስቲ የእግዚአብሔርን አሠራር አስተውል! እግዚአብሔር ያጣመመውን ሰው እንዴት ሊያቃናው ይችላል? ሁሉ ነገር በሠመረልህ ጊዜ ደስ ይበልህ፤ መከራም በሚመጣ ጊዜ ይህን አስታውስ፤ እግዚአብሔር ሁለቱንም ነገሮች ማለትም ደስታንና መከራን የሚልክበት ጊዜ ይኖራል፤ የትኛው ቀድሞ እንደሚመጣ ለማወቅ ግን ከቶ አትችልም"* (መክብብ 7፥13-14)።

አንዳንድ ክርስቲያኖች የፍቅር አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ከላይ የሰማነውን መከራንና ችግርን ያመጣል ብለው ማመን የሚያቅታቸው አሉ። መቀበል ያቅታቸው እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣

- *ሁልጊዜ ተፈጻሚነት ማግኘት የሚችል እግዚአብሔር የፈቀደው ነገር ብቻ ነው፤ ምክንያቱም መልካምም ሆነ ክፉ ሁሉ ነገር የሚፈጸመው በእርሱ ትእዛዝ ነው"* ይላል (ሰቆቃው 3፡37-38)።

ስለዚህ በመከራና በችግር ውስጥ ስናልፍ፣ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት ለይተን እንወቅ እንጂ፣ ቅጣቱን ችላ ብለን አንለፍ።

## 3. ኢየሱስ መስቀሉን አልሸሸም

ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የታቀደው የእግዚአብሔር ዓላማ የሚፈጸምበት ጊዜ ሲደርስ፥ ኢየሱስ የሚጠብቀው ሞት እንደሆነ ቢያውቅም፥ እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱ "ተው አትሂድ! የሃይማኖት መሪዎች ይገድሉሃል" ብለው ቢያስጠነቅቁትም፥ ኢየሱስ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳቀና መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ኢየሩሳሌምም የገባው ተደብቆ ሳይሆን፥ በብዙ ሕዝብ ታጅቦ በክብርና በዕልልታ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ውርንጫውን ወደ ኢየሱስ አመጡት፥ ልብሶቻቸውንም በላዩ ጣል አድርገው ኢየሱስን በውርንጫው ላይ አስቀመጡት። ሰዎችም እርሱ በሚሄድበት መንገድ ላይ ልብሶቻቸውን ያነጥፉ ነበር። በደብረ ዘይት ተራራ ቁልቁል ወደሚወስደው መንገድ በተቃረበ ጊዜ፥ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆነ ደቀ መዛሙርት፥ ስላዩት ታምራት ሁሉ ደስ እያላቸው ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ጀመር። በጌታ ስም የሚመጣው ንጉሥ በሰማይ ሰላም፥ በአርያምም ክብር ይሁን!"* ይሉ ነበር (የሉቃ. 19፥35-38)።



ጥንት ነቢያት ሊያስተላልፉት የሚፈልጉትን መልዕክት ሕዝቡ መረዳት ሲያቅተው፥ ወይም ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፥ ድራማ የሚመስል፥ የሕዝቡን ዓይንና ልብ መሳብ የሚችል አንዳንድ ለዓይን ጎልቶ የሚታዩ ነገሮችን ያደርጉ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ኤርምያስን አንድ ያልተለመደ ነገር እንዲያደርግ አዞት ነበር። ይኸውም፥

- *"ሄደህ ከተልባ እግር የተሠራ መቀነት ግዛ፤ ወገብህንም ታጠቅበት፤ ነገር ግን ውሃ አታስነካው አለኝ። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ መቀነቱን ገዛሁ፤ ወገቤንም ታጠቅሁበት"* ይላል (ኤር. 13፥1-2)።
- እንዲሁም ሕዝቅኤልን *"አንተ በግራ ጎንህ ተኛ የእስራኤልም ቤት ኃጢአት በአንተ ላይ ይሁን፤ በዚህ ጎንህ በተኛህበት ቀን ቁጥር ኃጢአታቸውን ትሸከማለህ። እነርሱ ኃጢአት በደረጉባቸው ዓመታት መጠን የቀን ቁጥር መድቤብሃለሁ። ስለዚህ 390 ቀን የእስራኤልን ቤት ኃጢአት ትሸከማለህ"* አለው (ሕዝ. 4፤4-5)።

ኤርምያስና ሕዝቅኤል እግዚአብሔር "አድርጉ" ያላቸውን ነገር በማድረግ ለሕዝቡ ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን መልዕክት አስተላለፉ። ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ውርንጭላ ሲገባ፥ ልክ ከላይ እንዳየነው ኤርምያስና ሕዝቅኤል አልሰማ ያለውን ሕዝብ መልዕክቱ በግልጽ እንዲገባው እንዳደረጉት፥ ከእግዚአብሔር የተላከው መሲህ እርሱ እንደሆነ ለማሳየት ኢየሱስ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲገባ ሆነ። በዚህ ዓይነት ኢየሱስ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም ሲገባ፥ ከብዙ ዓመት በፊት በነቢዩ ዘካርያስ የተተነበየው ትንቢት በማያጠራጥር ሁኔታ እንደተፈጸመ፥ እውነተኛው መሲህ፥ በእግዚአብሔር የተቀባው ንጉሥ እርሱ መሆኑን ለሚቀበለው ሁሉ ገለጸ። ይሁን እንጂ፥ በሕይወታቸው በማንገስ ፈንታ በእንጨት ላይ አንጠለጠሉት።

ከላይ ባየነው ሁኔታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ፥ እንዲሁ ሳይታሰብበት ድንገት የሆነ ነገር ሳይሆን፥ አስቀድሞ የታቀደ መሆኑን አውቀናል። ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ በጨለማ፥ ተደብቆ፥ ማንም ሳያየው ሹልክ ብሎ ሳይሆን፥ ጉዞው ወደ መስቀል እንደሚያደርሰው እያወቀ በድፍረትና በቆራጥነትና በግልጽ እንደ ሄደ እናውቃለን። በዚህ ጊዜ *"የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን ኢየሱስን ይይዙት ዘንድ የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው እንዲጠቁም ትእዛዝ ሰጥተው ነበር"* (የዮሐ. 11፥57)። ኢየሱስ በልቡ ፍርሃት ቢኖር ኖሮ፥ በካህናት አለቆች የሚፈለግ መሆኑን እያወቀ፥ ሹልክ ብሎ ወይም ተደብቆ እንጂ በሕዝብ ታጅቦ በግልጽ ኢየሩሳሌም አይገባም ነበር። ከገባም በኋላ ከማይታወቅበት ሥፍራ ተደብቆ መቆየት ይችል ነበር።

ነገር ግን ሕዝብ ሁሉ በሚያየው ሁኔታ፥ ትይንታዊ በሆነ መልክ በብዙ ሺ ሕዝብ ታጅቦ ኢየሩሳሌም ገባ። እርሱን ይዞ ለመጣ ዋጋ ይከፈለዋል ተብሎ ማስታወቂያ የወጣ መሆኑን እያወቀ፥ በግልጽ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም በድፍረት መግባቱ፥ ብዙዎቹን፥ ደቀ መዛሙርቱንም ሳይቀር ሳያስደንቃቸው እንዳልቀረ እንገምታለን። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ኢየሩሳሌም ሲገባ፥ በነብዩ በዘካርያስ የተተነበየው ትንቢት ፍጻሜ አገኘ።

- *"አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ! እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ! እልል በዪ፤ እነሆ ጻድቁና አዳኙ ንጉሥሽ ትሁት ሆኖ በአህያ ላይ ተቀምጦ በአህያ ግልገል፥ በውርንጫዋ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ ይመጣል"* ይላል (ዘካር. 9፥9)።

በጥንት ዘመን ነገሥታት ለጦርነት ሲመጡ፥ ፈረስ እየጋለቡ ነው። ለሰላም ሲመጡ ግን በአህያ ላይ እየጋለቡ ነበር። ኢየሱስ ግን በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እጁን ዘርግቶ "አሁንስ እንደ ንጉሣችሁ አድርጋችሁ አትቀበሉኝምን?" በማለት የፍቅር ጥሪ ማሰማቱ ነበር። ይሁን እንጂ



የተቀበለው ሰው አልነበረም። እንዲያውም ይባስ ብለው በእንጨት ላይ አንጠልጥለው ገደሉት።

ኢየሱስ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ቁጥራቸው እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ሰዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው *"በጌታ ስም የሚመጣው ንጉሥ፥ በሰማይ ሰላም፥ በአርያምም ክብር ይሁን"* እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። ሕዝቡ ኢየሱስን ሲያከብሩና ሲያመሰግኑ ያዩ የነበሩት ፈሪሳውያን ሁኔታው በጣም ስላበሳጫቸው ኢየሱስን *"መምህር ሆይ! ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው እንጂ አሉት"* (የሉቃ. 19፥39)። ኢየሱስም "እነርሱ ዝም ቢሉ፥ ድንጋዮች ይጮኻሉ" አላቸው። ፈሪሳውያን ኢየሱስን የሚያመሰግነውን ሕዝብ እያዩ በመደነቅ "ዓለም በሙሉ እየተከተለው እኮ ነው" አሉ። በዚያን ወቅት ፋሲካን ለማክበር በኢየሩሳሌም ቁጥሩ ከመቶ ሺ የማያንስ ሕዝብ በመሰብሰቡ፥ ለንጉሡ የሚገባውን ዙፋን ለመስጠት ዓለም ሁሉ የተሰበሰበ ይመስል ነበር። ይሁን እንጂ፥ የሚገባውን የንጉሥነት ዙፋኑን በመስጠት ፈንታ የሰጡት የመስቀልን ሞት ነበር።

ይህን ያህል ሕዝብ መሰብሰቡ የሚያስደንቅ አይደለም። በጎ ነገር ሲያደርግ ያዩት፥ ከእርሱ በጎ ነገር የተቀበሉት፥ ሊከተሉት የሚፈልጉ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። ቢታንያ ውስጥ አልአዛርን ከሞት ሲያስነሳ ያዩትና ያደነቁት፥ ገሊላ ውስጥ በደምብ የሚያውቁት የገሊላ ሰዎች፥ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ ያጠገባቸው ቁጥራቸው ከአምስት ሺ የሚበልጥ ሕዝብ፥ ከእርሱ ፈውስን ያገኙ ዓይነ ሥውሮች፥ ደንቆሮዎችና ዲዳዎች፥ አንካሶችና ሽባዎች፥ እንዲሁም ሕጻናት ሳይቀሩ ሊያከብሩት እንደተገኙ እናምናለን። ኢየሱስ ይህን የመሰለ ታላቅ አቀባበል ይደረግለት እንጂ፥ ከአደጋ ነጻ አልነበረም። ይህን ያህል ሕዝብ ወደራሱ መሳቡ ያስደነገጣቸውና ያስፈራቸው የሃይማኖት መሪዎች ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። ለፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም የተሰበሰበው ሕዝብ፥ በኢየሱስ ምክንያት ሁከት ይነሳ ይሆናል በሚል ፍርሃት፥ ሮማውያን ወታደሮች ጸጥታውን ለመጠበቅ በሥፍ

ራው ተገኝተው ነበር። የሰላሙ አለቃ፥ የሁከት ምክንያት ይሆናል ተብሎ መታሰቡ በጣም ያሳዝናል።

ሮማውያን ጥንት በድል አድራጊነት ዋና ከተማቸው ሮም ሲገቡ የሚደረገው ሰልፍ ልዩ ነበር። የጦሩ መሪ ወይም ጄኔራል በወርቅ ሠረገላ፥ ግርማ ሞገስ ባላቸው ፈረሰኞች ታጅቦ ከፊት ለፊት ቀድሞ ይሄዳል። ከእርሱ በኋላ በሠራዊቱ ውስጥ ባለ ከፍተኛ ማዕረጎች ከጠላት የማረኳቸውን ሀብትና ንብረት ይዘው ያልፋሉ። በመጨረሻው ሕዝቡ እንዲያያቸው በጦርነት የማረኳቸው ሰዎች በሰንሰለት ታሥረው እንዲያልፉ ይደረጋል። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ግን ከላይ ባየነው ዓይነት ሁኔታ አልነበረም። እየጋለበ የገባው በፈረስ ላይ ሆን በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ነው። በጦርነት የማረከውን ምርኮ ለማሳየት ሳይሆን ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ለመስጠት ነው። የታጀበው ከፍተኛ ማዕረግ ባላቸው ወታደሮች ሳይሆን በሽባዎችና በአንካሶች፥ በዓይነ ሥውሮች፥ በልጆች፥ ከገሊላና ከቢታንያ የመጡ ተራ ሰዎች እንደ ነበረ ተመልክተናል። ጸጥታ ለማስከበር በቦታው የተገኙት የሮም ወታደሮችና ባለሥልጣኖች ሕዝቡ "ሆሳዕና" እያለ የሚጮኹለትን ሰው ሲያዩ፥ የመጣው በወርቅ ሠረገላ ተቀምጦ፥ በሚያማምሩ ፈረሰኞችና ፈረሶች ታጅቦ ሳይሆን፥ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ነው። ያቺም የአህያ ውርንጭላ የራሱ ሳትሆን በተውሶ የተገኘች ነች። የፉከራ ድምጽ እያሰማ ሳይሆን እያለቀሰ በመሆኑ ናቁት። እርግጥ ነው ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የገባው በታላቅ ክብር ነው። ይሁን እንጂ፥ ሮማውያን በጠበቁት ዓይነት ክብር አልነበረም። እንዲህ ዓይነቱ ምን ዓይነት ንጉሥ ነው? በማለት ብዙዎቹን እንዳጠያየቀ እርግጠኞች ነን።

ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት እንደ ገባ አራቱም ወንጌሎች ታሪኩን ጽፈዋል። ብዙ ሰዎች በየመንገዱ ተሰልፈው ልብሳቸውን መንገድ ላይ እያነጠፉ በታላቅ ዕልልታ ተቀብለውታል። *"በጌታ ስም የሚመጣው ንጉሥ፥ በሰማይ ሰላም፥ በአርያምም ክብር ይሁን"* በማለት ዘምረውለታል። ኢየሱስን በዚህ ዓይነት የተቀበ



ለው ሕዝብ ትንሽ ቆይቶ በአንድ ድምጽ "ይሰቀል!" ብለው ሲጮሁበት ይሰማል። ምን ይሆን የሕዝቡን ሀሳብ በአንድ ጊዜ እንዲህ ያስለወጠው? ሕዝቡ ይሰቀል ብሎ በአንድ ድምጽ ሲጮኽ፥ ዓለም ሁሉ በእርሱ ላይ የሞት ፍርድ ለመፍረድ የተነሳ ይመስል ነበር። ለዚህ ነው ፈሪሳውያንና የሃይማኖት መሪዎች *"..አታዩም ዓለም ሁሉ ሲፈርድበት..."* ያሉት።

በዚያን ጊዜ "ፋሲካን" ለማክበር ከልዩ ልዩ አገር በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ በኢየሩሳሌም ተሰብስቦ ነበር። የዓለም ንጉሥ የሆነው "ዙፋኑ ይገባኛል" ብሎ በኃይል ለመውሰድ የመጣ ይመስላል። ውስን አዕምሮ ላለን፥ ለእኔና ለእናንተ ሁኔታው ፈጽሞ አይገባም። ከሳምንት በፊት ልብሳቸውን እያወለቁ ያነጠፉለት፥ "ሆሳዕና" እያሉ የዘመሩለትን ሰው ዛሬ "ስቀለው!" ብለው መጮኻቸው ግራ ያጋባል። ያ የእነርሱ ባሕሪ ብቻ ሳይሆን፥ በዘመኑ ያለነው ሰዎችም ባሕሪ ነው። ዛሬ አድንቀን ነገ አሳንሰን እናወራለን። ዛሬ ስመን፥ ነገ እንነክሳለን። ዛሬ የአበባ ጉንጉን አስታቅፈን ነገ ድንጋይ እንወረውራለን። የሚገርመው እንዲህ ዓይነት ባሕሪ ያለንን፥ ፍጹም የሚወደድ ባሕሪ የሌለን እኔና እናንተን መውደዱ ነው።

ስለ እምነታቸው ዋጋ የከፈሉትን ሰማዕታት ታሪክ ስንሰማ፣ ያየንባቸውን ድፍረትና ሙሉ መሰጠት ማድነቃችን አይቀርም። በሌላ በኩል ደግሞ *"በርህራሄ የተሞላው አምላክ ክርስቲያኖች ይህን ያህል ሲሰቃዩና በመከራ ውስጥ ሲያልፉ እያየ እንዴት መጨከን ቻለ? የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንዳልነበረች ለማድረግ የሚታገሉትን፣ እንዲሁም አማኞችን ከምድር ገጽታ ፈጽሞ ለማጥፋት ጥረት የሚያደርጉትን የቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ጠላቶች የሆኑትን እግዚአብሔር ሳይበቀላቸው ለምን ዝም ይላል?"* የሚለው ጥያቄ በውስጣችን መፈጠሩ እንደማይቀር ግልጽ ነው። "ለምን?...ለምን?" የሚለውን ጥያቄ የምንጠይቅ እኛ ብቻ ሳንሆን፣ ጥንትም ቢሆን፣ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችም እግዚአብሔርን ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ ጠይቀውታል። ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ኢዮብ ሲሆን፣

ሌላው ኤርምያስ ነው። ኤርምያስ በአካባቢው የሚፈጸመውን ክፉ ሥራ ከተመለከተ በኋላ፣

- *"እግዚአብሔር ሆይ! ክስ መሥርቼ ከአንተ ጋር ብከራከር፣ አንተ ሁልጊዜ እውነተኛ ሆነህ ትገኛለህ፤ ይሁን እንጂ ስለ ትክክለኛ ፍትሕ አንተን መጠየቅ አለብኝ፤ ክፉዎች የሚበለጽጉት ስለምን ድን ነው? አታላዮችስ ሁሉ ነገር የሚሳካላቸው ስለምንድን ነው? ይልቁንም አንተ ስለተከልሃቸው ሥር ሰድደዋል፤ አድገውም ፍሬ ያፈራሉ፤ በአፋቸው ያከብሩሃል፤ ልባቸው ግን ከአንተ የራቀ ነው። እግዚአብሔር ሆይ! እኔን ግን ታውቀኛለህ፤ ምን እንደ ምሠራና ከልቤም እንደምወድህ ታያለህ..."* ይላል (ኤርም. 12፥1-3) አለ።

## 4. ከመስቀሉ በፊት ዘውድ ለመጫን ለሚፈልጉ ትምህርት ሰጠ

ለሚከዳው ጴጥሮስ፥ ለሚሸጠው ይሁዳ አስቆሮቱ፥ በመከራው ወቅት ጥለውት ለሚሸሹት ደቀ መዛሙርቱ፥ ራሳቸውን አይተው እር ምጃቸውን እንዲያስተካከሉ እስከ መጨረሻው ድረስ በቂ ጊዜና ዕድል ሰጥቷቸው፣ የመጨረሻውንም ዕራት አብሯቸው ቀርቦ ነበር።

- *"ሰዓቱ በደረሰ ጊዜ ኢየሱስ ከሐዋርያቱ ጋር በማእድ ተቀ መጠ፤ እንዲህም አላቸው፤ መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን ፋሲካ አብሬያችሁ ለመብላት በጣም ስመኝ ነበር! እላችኋለሁ በእግዚአብሔር መንግሥት የዚህ ትርጉም እስኪፈጸም ድረስ ይህን ፋሲካ ዳግመኛ አልበላም። ጽዋውን ተቀብሎ ካመሰገነ በኋላ እንዲህ አላቸው፤ እንካችሁ ሁላችሁ ከዚህ ተካፈሉ፤ እላ ችኋለሁና ከአሁን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት እስከ ምትመጣ ድረስ ከዚህ ወይን ፍሬ አልጠጣም። እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም ሰጣቸውና ይህ ስለ እናንተ የሚ*



*ሰጥ ሥጋዬ ነው፥ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ"* (የሉቃ. 22፥16-19)።

በዚህ ዓይነት ኢየሱስ የመጨረሻውን እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከበላ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በሕይወታቸው መለማመድ ያቃታ ቸውን አንድ ትልቅ ትምህርት ለማስተማር ተነሳ። ይኸውም *"ከእራት ተነሳ፤ መጎናጸፊያውን አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ። ከዚያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታ ጠቀው ፎጣ ያብስ ነበር"* ይላል (የዮሐ. 13፥4-5)። የክብር እንግዳ የነ በረው ኢየሱስ፥ የራሱን ደቀ መዛሙርት እግር ለማጠብ መነሳቱ፥ ብዙ ዎችን ሳያስደንቅ እንዳልቀረ እናምናለን። ንጉሥ የሆነው ጌታ እግር ለማጠብ መነሳቱ፥ ሰው ውስን በሆነው አዕምሮ ሊገምተው ከሚችለው በላይ ነው። በዚያን ዘመን እግር ማጠብ እንደ አነስተኛና ዝቅተኛ ተግባር ይገመት ስለነበረ ነው ጴጥሮስ ኢየሱስን *"የእኔን እግር አንተ አታጥብም"* ብሎ እምቢ ያለው። ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ መነሳቱ፣ የሃይማኖት ሥርዓት ለመፈጸም ሳይሆን፣ ለደቀ መዛሙርቱ ከፍተኛ ትምህርት ለማስተላለፍ ፈልጎ ነው።

የኢየሱስን አስደናቂ ድርጊት ደቀ መዛሙርቱ ከማየታቸው በፊት በሁሉም አዕምሮ ውስጥ ይመላለስ የነበረው፥ በክርስቶስ መንግ ሥት ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ እንዴት እንደሚይዙ፥ ከያዙ በኋላም ለረጅም ጊዜ ይዘው የሚዘልቁበትን መንገድ ያስቡ ነበር። ነገር ግን እዚህ ላይ ከሁሉም በላይ የሆነው፥ መምህርና ጌታ የሆነው፥ ከነበረበት ከፍተኛ ደረጃ ተነስቶ ወደ ምድር ዝቅ ብሎ የተከታዮቹን እግር ማጠቡ ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ሳያስገርማቸው እንዳልቀረ እንገም ታለን። በዚህ ተግባሩ ብቻ ኢየሱስ የዓለምን ሥርዓትና ደንብ ግልብ ጥብጡን እንዳወጣ እንገነዘባለን። የእርሱ ደንብ *"ከፍ ለማለት ዝቅ፥ ዝቅ ለማለት ከፍ ማለትን"* እንደሚጠይቅ አሳያቸው። ሁኔታው የተለ መደ ስላልነበረ ደቀ መዛሙርቱን ሳያስደነግጣቸው አልቀረም። ኢየ ሱስ በተግባር ካሳያቸው በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፥

- *“ያደረግሁላችሁን ታስተውሉላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና። እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ኋለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል። እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ”* አላቸው (የዮሐ. 13፥13-15)።

## 5. መስቀሉን እንድንሸከም ጸጋውን ያበዛልናል

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ጌቴሴማኔ የሄዱት ሊገድሉት ከሚፈልጉት ሰዎች ለመሸሽ ወይም ለመደበቅ አልነበረም። በብዙ ሺ ሕዝብ ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው፥ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የታቀደው የእግዚአብሔር ዓላማ በእርሱ ሕይወት የሚፈጸምበት የመጨረሻው ሰዓት የተቃረበ መሆኑን አውቆ ነው። ኢየሱስ ሞት እንደሚጠብቀው እያወቀ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው፥ ተገዶ ሳይሆን በራሱ ፈቃድ ነው። የሚጠብቀውን የመስቀል ሞት መታገስ የሚችልበትን ኃይል እንዲሰጠው፥ ከአባቱ ጋር በጸሎት ለማሳለፍ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሦስቱን ይዞ ወደ ጌቴሴማኔ ሄደ። ደቀ መዛሙርቱ ግን በእንቅልፍ ስለተሸነፉ አብረውት በጸሎት ሊተጉ አልቻሉም። ኢየሱስ ግን የሚደርስበትን አስቀድሞ ያውቅ ስለ ነበረ፥ መንፈሱ በኃይል ይጨነቅበት ነበር።

ማቴዎስ፥ ኢየሱስ በወቅቱ የተሰማውን ስሜት ሲገልጽ፥ *“ይተክዝና ይጨነቅ ነበር”* (የማቴ. 26፥37) ይላል። እንዲሁም ማርቆስ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ጽፏል። *“ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዝናለች…”* ይላል። ይህን ብሏቸው ለብቻው ለመጸለይ ትንሽ ራቅ ብሎ ሄደ። ደቀ መዛሙርቱን ትቷቸው የሄደው፥ እንዲተኙ ሳይሆን በጸሎት እንዲተጉ ካሳሰባቸው በኋላ ነው። ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ለመጸለይ ብቻውን የሚሆንበት ጊዜ እንደነበረ እናስታውሳለን። ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ



ሲሄዱ ማዕበል አጋጥሟቸው የተጨነቁት፥ ኢየሱስ ከእነርሱ ተለይቶ ለብቻው ለመጸለይ በቆየበት ወቅት እንደነበረ እናስታውሳለን። በጌቴሴማኔ ውስጥ ግን ብቻውን ሆኖ በመጸለይ ፈንታ፥ ደቀ መዛሙርቱ አብረውት እንዲቆዩና በጸሎት እንዲያግዙት ሲጠይቃቸው እናያለን። ሊጠጣው የተዘጋጀለት የመከራ ጽዋ በጣም ከባድ መሆኑን ስላወቀ፥ የደቀ መዛሙርቱን የጸሎት ድጋፍ ከምንጊዜውም የበለጠ ስለፈለገ ነው።

እኔና እናንተም ብቻችንን መሆን የማንፈልግበት፥ ከአጠገባችን ሰው እንዳይጠፋ የምንፈልግበት ጊዜ አለ። ይኸውም፥ በሕመም አልጋ ላይ ስንሆን፥ ለምሳሌ የቀዶ ጥገና ሕክምና ለመውሰድ ስንዘጋጅ፥ በዓለም የተወሰነልንን ጊዜ ጨርሰን ለመሄድ ጥቂት ቀናት እንደቀረን ስናውቅ፥ ወይም ያልጠበቅነው ነገር በሕይወታችን ደርሶ በታላቅ መከራ ውስጥ ስናልፍ፥ ቅርባችን ናቸው የምንላቸው ሰዎች አጠገባችን ሆነው እንዲያጽናኑንና እንዲያበረታቱን፥ ዕንባችንን እንዲያብሱልን እንፈልጋለን። የሚያዝኑልን፥ የሚያጽናኑንና፥ “አይዟችሁ!” የሚሉን ሰዎች እንፈልጋለን። ለብቻ ሆኖ መሰቃየት ከማንኛውም ክፉ ነገር የበለጠ የከፋ እንደሆነ ይታወቃል። ከየትኛውም ቅጣት የበለጠ አስከፊ የሚሆነው፥ እንዲቀጣ የተፈረደበትን ሰው አንድ ክፍል ውስጥ፥ ከሰው ሁሉ ተገልሎ ወይም ተዘግቶበት ለብቻው እንዲቀመጥ ሲደረግ ነው። ብቸኝነት በጣም ከባድ ነው። አዕምሮን ያስታል። የከፋ እንደሆነ ብቸኝነት ከሕይወት ይልቅ መሞትን ያስመርጣል። የክርስቶስን ስቃይ የበለጠ የከፋ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንደኛው በወቅቱ የተሰማው ብቸኝነት እንደነበረ ግልጽ ነው።

ኢየሱስ በጌቴሴማኔ የተሰማው ብቸኝነት ከላይ ከገለጽነው ሁኔታ የበለጠ የከፋ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ብቻውን እንዲታገል ትተውት ዕንቅልፋቸውን ተኙ። ስለ መከራውና ስለሚሰማው ጭንቀት ደቀ መዛሙርቱ ግድ የሌላቸው በመሆናቸው ምክንያት፥ ኢየሱስ ስሜቱ ምን ያህል እንደተጎዳና ብቸኝነት እንዴት እንደተሰማው ከመ

ናገር ወደ ኋላ አላለም። *"እናንተ ሰዎች፣ ከእኔ ጋር ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታችሁን?"* (የማቴ. 26፥40) አላቸው። ኢየሱስ ለብቻው ከአባቱ ጋር ለመሆን ያልፈለገበት ጊዜ ቢኖር፤ ይሄ በጌቴሴማኔ በቆየበት ጊዜ ብቻ ነው። ኢየሱስ ከጭንቀቱ የተነሳ *"አባቴ ሆይ! ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፤ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን"* ብሎ ወደ አባቱ ጸለየ (የማቴ. 26፥39)። ኢየሱስ ይህን ጸሎት የጸለየው ዝም ብሎ ሳይሆን በትልቅ ጭንቀት ውስጥ ሆኖ ነው። *"ኢጅግ ተጨንቆም በብርቱ ይጸልይ ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነበር"* ይላል (የሉቃ. 22፥44)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ አብረውት እንዲሆኑ የፈለገበት ጊዜ ቢኖር፣ ይህን በመሰለ ጭንቀት ውስጥ በነበረበት ወቅት፣ በጌቴሴማኔ ብቻ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ከምንጊዜውም የበለጠ በሚፈልጋቸው ወቅት፣ ከሥጋ ድካም የተነሳ በጸሎት አብረውት ሊተጉ አልቻሉም። አጠገቡ ሆኖ እንደ ደም የሚንጠባጠበውን ላቡን ከፊቱ ላይ የሚጠርግለት ሰው አልነበረውም። መላእክቶች ተሰልፈው የሚያገለግሉት ጌታ ዛሬ አጠገቡ የሚቆም ሰው ማጣቱ እንዴት ያሳዝናል?

በጌቴሴማኔ ውስጥ ኢየሱስ ያን ያህል ከፍተኛ ጭንቀት እንዲሰማው ያደረገው ምክንያት ምን ይሆን? የሚደርስበትን ስቃይና ሞትን በማሰብና በመፍራት ይሆን? እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ ኢየሱስ "ፍጹም አምላክ" ብቻ ሳይሆን፣ "ፍጹም ሰውም" መሆኑን ነው። አምላክ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ መከራው ሊሰማው አይችልም ብለን እንደመድም ነበር። በጌቴሴማኔ ሲጨነቅ የምናየው፣ እንደ እኔና እንደ እናንተ ፍጹም ሰው ሆኖ ነው። ኢየሱስ የተጨነቀበት ሌላው ምክንያት በእግዚአብሔር የተተወ በመሆኑም ጭምር ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ጽዋው ከእርሱ እንዲያልፍ ጠይቋል። ይሁን እንጂ፣ ክርስቶስ ከጸለያቸው ጸሎቶች ሁሉ መልስ ያላገኘበት ጊዜ ቢኖር፣ በየጌቴሴማኔ የጸለየው ጸሎት ነው።

የመከራ ጽዋውን ጠጣው እንጂ ሳይጠጣው አላለፈም። የኢየሱስን መከራ የበለጠ ከባድ ያደረገበት ምክንያት ዓለም ንቆ የተወው



በመሆኑ ሳይሆን፣ የራሱ የሆኑት ደቀ መዛሙርቱም ጥለውት መሸሻቸው ነው። በጌቴሴማኒ የጸሎት ትግል ውስጥ እያለ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ እግዚአብሔርም ራሱ የተወው መስሎ የተሰማው ጊዜ ነበር። *"አባት ሆይ! ፈቃድህ ከሆነ ይሄ ጽዋ ከእኔ ይለፍ"* ብሎ እንደ ጸለየው ቢያልፍ ኖሮ የመስቀሉ ታሪክ ምን ይሆን ነበር? ከአባቱ ፈቃድ ውጪ ኢየሱስ የራሱ ፈቃድ እንዲፈጸም ቢፈልግ ኖሮ፣ በሺ የሚቆጠሩ መላእክት ከሰማይ ወርደው እርሱን በመደገፍ ይዋጉለት ነበር። ከሰማይ መላእክት መጥተው ቢዋጉለት፣ ያለምንም ትግል ሰይጣንን አንድ ጊዜ በኃይል በመውጋት ብቻ ድልን ያገኝ ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ቤተ ክርስቲያንና እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አይኖርም ነበር። በጠቅላላው የሰው የደህንነት ታሪክ እዚያ ላይ ያበቃ ነበር። ኢየሱስ መስዋዕት መሆን አያስፈልገውም ነበር። የመስቀሉ ስቃይና ሞት ሕዝቡን የሚበኝበት የደህንነት መንገድ መሆኑ ይቀር ነበር።

የመስቀሉ ስቃይ፣ ጌታ የሚጠጣው መራራ ጽዋው የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣበት ዋናው ምክንያት ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ራሱን ስለ እኛ ሲል አሳልፎ ለመስጠት ነው። በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ የምናየው፣ "ጠላቶቹን የሚወድ፣ ጽድቁ ከፈሪሳውያን ጽድቅ የሚበልጥ፣ ኃብታም መሆን ሲችል ድህነትን የሚመርጥ፣ የለበሰውን ገፎ ለሌላው የሚሰጥ፣ ለሚያሰቃዩት የሚጸልይ" ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መስቀሉ የእግዚአብሔር መንግሥት እንቅፋት ወይም መሰናክል ሳይሆን፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርስ ነው። ኢየሱስ በጌቴሴማኔ ብዙ ከታገለና ከጸለየ በኋላ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለአባቱ ፈቃድ አሳልፎ ሰጠ። የተወሰነው ጊዜ ሲደርስ፣ የተኙትን ደቀ መዛሙርት ከእንቅልፋቸው ቀስቅሶ፣ "የሰው ልጅ አሳልፎ የሚሰጥበት ጊዜ ደርሷል" ካላቸው በኋላ ሊገሉት ወደሚፈልጉት ሰዎች በድፍረትና በቆራጥነት አመራ።

## 6. በመስቀል መከራ ውስጥ እንድናልፍ ጌታ ለምን ይፈቅዳል?

መከራ ሁለት ዓይነት ውጤት አለው። ይኸውም፣ በአግባቡ የሚጠቀሙበት ከሆነ፣ መንፈስ ጠንካራ አድርጎ ይሠራቸዋል። በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ግን ይሰብራቸዋል ወይም እንዳልነበረ አድርጎ ያጠፉቸዋል። *"ለምን ይሄ በእኔ ደረሰ?"* በማለት ውስጣቸው በቁጣ የተሞላ ይሆናል። ቁጣቸውም በሰው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔርም ላይ ይሆናል። *"ይሄን ዓይነት መከራ ሲደርስብኝ ለምን ዝም አልክ?"* በማለት ቦክስ ጨብጠው በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ቃል መናገር ይጀምራሉ። አንዳንዶች መከራው ጠበቅ ሲልባቸው በእግዚአብሔር ላይ ያኮርፉና ከሕይወታቸው ሊያስወጡት ይሞክራሉ። ነብዩ ኤርምያስ ሕይወቱ በብዙ መከራ፣ ስደትና ጭንቀት የተሞላ ሰው እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ጋር ሙግት የገጠመው፣ *"እኔ ያንተን ጦርነት እየተዋጋሁ፣ ትዕዛዝህን እየፈጸምኩ ትርፌ ለቅሶና ዕንባ ብቻ የሆነው ለምንድን ነው?"* በማለት ነው። ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር *"ለምን?"* ለሚለው ጥያቄያችን መልስ የመስጠት ግዴታ የለበትም። ሰው በኑሮ ሂደት ውስጥ እንዲረዳው ያደርጋል እንጂ፣ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር፣ ለምን እንደሚያደርግ ተፈጣሪ ለሆነው ሰው ገለጻ የመስጠት ግዴታ እንደሌለበት ብዙዎቻችን የተረዳነው አንመስልም። ኢዮብም ጠይቆ የሚፈልገውን ዓይነት መልስ አላገኘም። ይሁን እንጂ፣ በመከራ ውስጥ እንደሚገባው ታሽቶ ካለፈ በኋላ፣ *"ከቀድሞ ይልቅ አሁን ማንነትህን በትክክል አውቄአለሁ! ገብቶኛል! ተረድቻለሁ!"* እንዳለ እናስታውሳለን።

ከላይ የጠቀስናቸውን ሰማዕታት የሚዘገንና የሚያስደንቅ ታሪክ ስንሰማ፣ የተለያየ ጥያቄ በአዕምሯችን እንደሚመላለስ እርግጠኞች ነን። እግዚአብሔር የሕይወትን መንገድ ለምን ጠባብና አስቸጋሪ አደረገው? የክርስትና መንገድ የመስቀል ጉዞ ያለበት ለምን ሆነ? የእግዚአብሔር ወዳጆች በመከራ ውስጥ፣ በዕንባ ሸለቆ፣ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለምን ያልፋሉ? እርግጥ ነው! እነዚህን ለመሳሰሉ አንዳንድ ጥያቄዎቻችን መልስ



ልናገኝላቸው እንችላለን። ለአንዳንዶቹ ግን አጥጋቢ የሆነ መልስ የምናገኘው እንደ ጸሀይ ከሚያበራው ሰማያዊ ቤታችን ስንደርስ ብቻ ነው።

በመከራ፣ በፈተና፣ በዕንባ፣ ጨለማ በበዛበት ሕይወት፣ በስቃይና በመከራ ውስጥ ለምን እንደምናልፍ በከፊል የምናውቃቸውን መልሶች ከዚህ ቀጥሎ እንዘረዝራለን።

*1ኛ፣ መከራ እግዚአብሔርን እንድናከብር ያስችለናል።*

በአግባቡ ወይም በትክክል ከተጠቀምንበት መከራ እግዚአብሔርን እንድናከብር ያስችለናል። መከራ ባለአደራ መሆን ስለሆነ ልንቀበለው ይገባል። ለተለያዩ ነገሮች ባለአደራ መሆን ምን እንደሆነ ይገባናል። ለማስተማር አደራ የተጣለበት ሰው፣ ከእርሱ በላይ ለሆነ ሰው ተጠያቂነት አለው። የመዘመር ስጦታ ያለው፣ ስለ ስጦታው ተጠያቂነት አለበት። ገንዘብ ያለው፣ ገንዘቡን ለሰጠው ጌታ ባለአደራ ነው። ከእግዚአብሔር ለተሰጠን ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ፣ ስጦታውን ለሰዎች ጥቅም፣ እግዚአብሔርን ለማክበር እንድናውለው ለሰጪው ተጠያቂዎች ነን። የመከራም ባለአደራነት አለ። መከራ በምንም ዓይነት ወደ እኛ ይምጣ፣ ከእግዚአብሔር እንደመጣ አድርገን ልንቀበለው፣ ልንሸከመው፣ በውስጡ ልናልፍ፣ ለስሙ ክብር ልናውለው ይገባል። ኢዮብ እግዚአብሔር በቅድስና ሕይወቱ ያደነቀው እንደ እሳት በሚያቃጥል ፈተና ውስጥ እንዳለፈ እናውቃለን።

አንድ ቀን ሰይጣን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው። *"አንተ ቅድስናውን ያደነቅህለት፣ ያንተ ወዳጅ የሆነው ኢዮብ፣ ቅዱስ የሆነበት ምክንያት እንዲሁ ይመስልሃል? ሁሉን ነገር አሟልተህ ስለሰጠኸው ነው። አሁን ያለውን ሁሉ እንድወስድበት ብትፈቅድልኝ፣ ከአንተ ጋር መቆም እንደማይችል፣ ፍጹም እንደሚክዳህ አሳይህ ነበር"* አለው። እግዚአብሔርም "እንዳትገድለው እንጂ የፈቀድከውን እንድታደርግበት ፈቅጄልሃለሁ" አለው። ሰይጣንም በተሰጠው ፈቃድ መሠረት የኢዮብን ሕይወት በልዩ ልዩ መከራ ማመስ ጀመረ። ይሁን እንጂ፣ ኢዮብ እግዚአብሔርን

በመካድ ፈንታ፣ *"ዕራቁቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጣሁ፤ ዕራቁቴንም እሄዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔር ነሳ፤ የእግዚአብሔር ስም ብሩክ ይሁን"* አለ (ኢዮብ 1፡21)። የኢዮብ መከራ በዚህ ብቻ አላበቃም። ጤንነቱ ተወስዶ በታላቅ መከራ ውስጥ አለፈ። ያም ሆኖ ኢዮብ "ቢገድለኝም እንኳን በእርሱ እታመናለሁ" አለ። ከዚህ ሁሉ መከራና ስቃይ በኋላ ቀድሞ ከነበረው የበለጠ ሰጥቶ መልሶ አከበረው። ስለዚህ መከራን በትክክሉ ከተጠቀምንበት እግዚአብሔር በመከራችን ይከብራል። ወደ ሕይወታችን መከራ ሲመጣ እንዴት ማስተናገድ እንዳለብን ማወቅ አለብን። ምንም ዓይነት መከራ ቢሆን፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ ይምጣ፣ ክርስቲያኖች የተሰጠንን መከራ በአግባቡ መያዝ ካልቻልን እግዚአብሔርን ልናከብረውና ልናስከብረው አንችልም።

*2ኛ፣ መከራ እግዚአብሔር ጸጋውን የሚያሳይበት ምክንያት ይሆናል፦*

መከራ፣ ድቅድቅ ጨለማ፣ ዕንባ በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ለምን ይደርሳል? እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት ውስጥ ጸጋውን ለመግለጽ ወይም ለማሳየት ዕድል ይሰጣል። ይህም ማለት ታላቅ የሆነውን ሥራ ለመሥራት በር ይከፍትለታል። የሕግ ሙያ ለመማር ብዙ ዓመት ትምህርት ቤት ያሳለፈ ወጣት፣ የተማረውን በሥራ ለመተርጎም በተለያየ ምክንያት የሚጋጩ ሰዎች ያስፈልጉታል። እንዲሁም በህክምና ሙያ ብዙ ዓመት ያጠፋው ወጣት ትምህርቱን በተግባር ላይ ለማዋል የታመሙ ሰዎች መኖር አለባቸው። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔርም ምሕረቱን፣ ቸርነቱን፣ ጸጋውን ለአማኞች ለማሳየት፣ አማኞች በመከራ፣ በስቃይና በዕንባ ውስጥ ማለፍ አለባቸው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ታላቅ ጸጋ ማየት ያስቻለው "የሥጋው መውጊያ እሾኽ" ስለ ተሰጠው ነው። ያ ለስጋው መውጊያ እንዲሆን የተሰጠው እሾህ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ጸጋ እንዲያይበት ዕድል ሰጠው።



*3ኛ፣ በመከራ ውስጥ ካለፍን፣ በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን መርዳት እንድንችል የበለጠ ያዘጋጀናል።*

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑ ሌሎችን መርዳት እንዲችሉ፣ በመከራ ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግ አስቀድሞ ያሰለጥናቸዋል። በመከራ ውስጥ ከማለፍ የበለጠ ሌላ የተሻለ አስተማሪ አይኖርም። በሕይወታችን ከተማርናቸው ትምህርቶች ውስጥ ፈጽሞ የማንረሳቸው፣ በመከራ ውስጥ በማለፍ የተማርናቸው ትምህርቶች ናቸው። ጳውሎስ፣ *"እኛ ራሳችን ከእግዚአብሔር በተቀበልነው መጽናናት በመከራ ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣ እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናል"* ይላል (2 ቆሮ. 1፡4)። መከራ ውስጥ ያለውን ሰው፣ በመከራ ውስጥ ያላለፈ ሰው ሊያጽናናው ከባድ ይሆንበታል። በመከራ ውስጥ ያለፈው ግን፣ *"አንተ ባለፍከበት ሕይወት አልፌአለሁ... የሚሰማህ ስሜት ይገባኛል"* ቢለው፣ ያ የተጎዳ ሰው፣ ያንን ሰው መቀበል ይቀለዋል። በዓለም ውስጥ ያለው ትልቁ በረከት የሚመጣው በጣም ጥልቅ ከሆነ ሀዘን፣ ፈተናና ዕንባ ውስጥ ነው። ወደ መንግሥተ ሰማይም እንኳን መግባት የሚቻለው በመስቀሉ መንገድ ብቻ ነው። ከክርስቶስ መስቀል ውጪ ወደ አብ የሚያደርስ ሌላ መንገድ የለም።

*4ኛ፣ መከራ፣ ገጸ ባሕሪያችንን ይሠራል፦*

መከራ፣ ፈተና፣ ዕንባ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚደርስበት ሌላው ምክንያት ገጸ ባሕሪያችንን ለመሥራት ነው። ገጸ ባሕሪያችን እንዲገነባ ከባድ ይሁን እንጂ፣ በዲስፕሊን ውስጥ ማለፍ አለብን። እግዚአብሔር ስለ ውጪያዊ ሕይወታችን ሳይሆን፣ ስለ ውስጣዊ ሕይወታችን ያስባል። እንዲያስተምረን፣ እንዲያነጻን፣ የምንስማማ እንዲያደርገን፣ እግዚአብሔር በእርሱ ፊት እንድንሆን የሚፈልገውን ዓይነት እንድንሆን፣ አሁንም አሁንም፣ እግዚአብሔር በሚያሳልፈን ዲሲፕሊን ውስጥ ማለፍ አለብን። በመከራ ውስጥ ማለፍ ያለውን መልካም ነገር

የተረዳው ዳዊት፣ *"ሥርዐትህን እማር ዘንድ በመከራ ውስጥ ማለፌ መልካም ሆነልኝ"* አለ (መዝ. 119፡71)።

*5ኛ፣ መከራ በእግዚአብሔር እንድንታመን ያበረታታናል፦*

መከራ ሲመጣብን ምን ማድረግ አለብን? ኢሳያስ 50፡10 ላይ *"ከእናንተ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ የባሪያውንም ቃል የሚሰማ ማን ነው? ያ ሰው በጨለማ የሚሄድ ከሆነና ብርሃንም ከሌለው፣ በእግዚአብሔር ይታመን፤ በአምላኩም ይደገፍ"* ይላል። አንዳንዶቻችን አልፎ አልፎ በታላቅ መከራ ውስጥ ማለፋችን አይቀርም። በዚያን ጊዜ በሚያስተማምነው ጌታ በመታመን በእርሱ እንጽና።

በአሁኑ ዘመን በአንዳንድ ክርስቲያኖች አካባቢ፣ መንፈሳዊ ሕይወት የማያቋርጥ ደስታ፣ ሰላምና ምድራዊ ብልጽግና የሞላበት ሕይወት ብቻ እንደሆነ አድርገው ያምናሉ። ደህንነትን ሲያገኙና በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ፣ ከችግርና ከመከራ ሁሉ ወዲያው ነጻ እንደሚሆኑ ያስባሉ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ከዚያ አልፈው አማኝ ሆኖ በተአምር የተሞላ ሕይወት ከሌለው በእምነቱ የሳተ መሆን አለበት ብለው ያምናሉ። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ሁልጊዜ ደስታ፣ ሁልጊዜ መዝናናት፣ ከመከራና ከመስቀል ሕይወት ነጻ የሆነ፣ ሁልጊዜ ፈንጠዝያ ብቻ የሞላበት ነው ብለው ያስባሉ። ማንም መታመም የለበትም፤ ከታመመ ግን ወዲያ መፈወስ አለበት፤ ገንዘብ ቢያስፈልገው፣ ሰማይ ተከፍቶ የሚያስፈልገውን ያህል እግዚአብሔር ያዘንብለታል ብለው ያምናሉ። በብልጽግና ሕይወት ካልኖረ ግን፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ልክ ስላልሆነ ነው ወይም አንድ ነገር ቢጎድለው ነው ይላሉ። እርግጥ ነው እግዚአብሔር ቸርነቱንና በተአምር የተሞላ አምላክ መሆኑን ለማሳየት አንዳንድ ጊዜ ለብዙዎች በሰፊው የሚሰጥበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፣ የክርስትና ሕይወት ሁል ጊዜ ደስታ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት ብቻ ሳይሆን መከራና ስቃይም እንዳለበት መረዳት ያስፈልጋል።



ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኃዋርያው ጳውሎስ ነው። ስለ ወንጌሉ ሲል፣ ይሆናል ብሎ ማመን ወይም መገመት እስቸጋሪ እስከሚሆንብን ድረስ በብዙ መከራና ስቃይ ውስጥ እንዳለፈ እናውቃለን። እኔና እናንተ ምንም ዓይነት ወንጀል ሳንሠራ ቆዳችንና ሥጋችንን በጭቆ በሚገባ ጅራፍ አንዴ ብንገረፍ፣ ሥጋዊው አካላችንን ብቻ ሳይሆን ስሜታችንን ጭምር እስከ መጨረሻው ድረስ ሰንካላ አድርጎ እንደሚያስቀረን እንገምታለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን አንዴ ብቻ ሳይሆን አምስት ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ወቅት 39 ጅራፍ በሰውነቱ ላይ ሲያርፍ፣ ከላይ ያለውን ቆዳውን ብቻ ሳይሆን ሥጋውን እንደበጣጠሰው እርግጠኞች ነን። መከራውና ስቃዩ ያ ብቻ አይደለም። በሮማውያን ባለሥልጣናት ሦስት ጊዜ የጀርባው አጥንት እስኪሰባበር ድረስ በዱላ ተደብድቧል። አንድ ጊዜ በልስጥራ ከተማ ውስጥ እርሱን ለማጥቃት በተሰበሰበ ሕዝብ ተከብቦ፣ በድንጋይ ከወገሩት በኋላ መሬት ለመሬት እየጎተቱ ሞቷል ብለው ጥለውት ሄደዋል። ለመሆኑ በድንጋይ መደብደብ (መወገር) በእኛ ላይ ቢደርስ፣ ምን ያህሉን ታግሰን ማለፍ እንችል ይሆን? ስቃዩን በመፍራት የሚወረወርብን አንዱ ትልቅ ድንጋይ ራሳችን ላይ አርፎ በአንድ ጊዜ ከመከራችን እንዲገላግለን መጸለያችን አይቀርም። ጸሎታችን መልስ ሳያገኝ ቀርቶ በድንጋይ ተቀጥቅጠን ቀስ በቀስ ብንሞት እንዴት ከባድ ይሆንብን ነበር! ሐዋርያው ጳውሎስ ከባድ ወንጀል ፈጽሞ ሳይሆን ክርስቲያን በመሆኑ፣ የምሥራቹን ቃል በመስበኩ ብቻ፣ በብዙ መከራና ስቃይ ውስጥ እንዳለፈ እናውቃለን። ገላትያ 6፡17 ላይ ሐዋርያነቱን በሚጠራጠሩ አንዳንድ ሰዎች ተቆጥቶ *"እኔ የኢየሱስን ምልክት በሥጋዬ ተሸክሜ አለሁና ከእንግዲህ ወዲህ ማንም አያስቸግረኝ"* ለምን እንዳለ ይገባናል።

ለጥቂት ወራት ታስረው የወጡ ሰዎች፣ እስራት ምን እንደሆነ፣ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ለብቻ መቆየት በስሜትና በአዕምሮ ላይ ምን ያህል ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያስከትል ከልምምዳቸው ይመሰክራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን በእምነቱ ምክንያት በተለያየ ጊዜ በሮማውያን ወህኒ ቤቶች ብዙ ጊዜ አሳልፏል። እነዚህ ጳውሎስ ያሳለፈባቸው ወህኒ ቤቶች በዘመኑ የወህኒ ቤት ሁኔታዎች ጋር ስናስተያየው በጣም የሚዘ

ግንን ነበር። እንደ በረዶ የሚቀዘቅዝ፣ ንጽህና የሌለው፣ የጤና ቀውስ የሚያመጣ ነበር። እጅና እግርን በሰንሰለት ታስሮ ለረጅም ጊዜ መቆየት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መገመት አያስቸግረንም። ጳውሎስ ራሱን "የክርስቶስ እስረኛ የሆንኩ" ብሎ ሲጠራ፣ በመበሳጨትና ተስፋ በመቁረጥ ሳይሆን፣ እንደ ታላቅ ክብር በመቁጠር ነበር። ከዚህ ሁሉ በላይ ጳውሎስ ተፈጥሮ በሚያመጣው አደጋ ብዙ የተሰቃየ ሰው ነበር። ያ ብቻ ሳይሆን በሚያሳፍር በሽታ ውስጥ ያልፍ እንደ ነበር እናውቃለን። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ጳውሎስ "የስጋዬ መውጊያ እሾህ ተሰጠኝ" ያለውን፣ አንድ ዓይነት የዓይን ህመም፣ እንዲሁም የሚጥል በሽታ ሳይኖርበት አይቀርም ብለው የሚገምቱ አሉ። በተጨማሪ በሜዲትራንያን ባሕር ሦስት ጊዜ ያህል የመርከብ መገልበጥ አደጋ ደርሶበታል። ወንጌልን ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ሲሰብክ በመንገዱ ላይ በሰውም ሆነ በተፈጥሮ ምክንያት በብዙ ጉዳት ውስጥ አልፏል። ያለውን ለመንጠቅ ብቻ ሳይሆን ሕይወቱንም ጭምር ሊያጠፉ የሚያደፍጡ ወንበዴዎች በሚንዝቡት ስፍራ ሁሉ ያጋጥሙት ነበር።

## 7. መስቀላችንን እስከ መጨረሻው እንሸከም ይሆን?

እንዲህ ዓይነቱን ጌታ አሳልፎ መስጠት፣ እንዲህ ዓይነቱን ጌታ መካድና መሸሽ እንዴት ያሳዝናል? *እርሱም ገና እየተናገረ ሳለ፣ ብዙ ሰዎች መጡ፤ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ የተባለውም ሰው ይመራቸው ነበር፤ ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ተጠጋ። ኢየሱስ ግን ይሁዳ ሆይ! የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጠዋለህን አለው"* (የሉቃ. 22፤47-48)። ይሁዳ ፍጹም ተወዳዳሪ የሌለው ከሀዲ ነው። ከእግዚአብሔር ሕብረት ወጥቶ ከሰይጣን ጋር የተባበረ ሰው ነው። ይሁዳ ከሕይወቱ እግዚአብሔርን በማስወጣቱ፣ በሰይጣን ቁጥጥር ውስጥ በመዋሉ፣ ክርስቶስን ለጠላቶቹ አሳልፎ ለመስጠት ተነሳ። ለመጨረሻው እራት እንደተሰበሰቡ ኢየሱስ አንድ አስደንጋጭ የሆነ ንግግር ተናገረ። በመንፈሱ ታውኮ *"እውነት እላችኋለሁ፤ ከእናንተ አንዱ*



*እኔን አሳልፎ ይሰጣል ሲል በግልጽ ተናገረ"* (የዮሐ. 13፤21)። ይህን ሲል ይሁዳም እዚያው ስለ ነበር ሰምቷል። "ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል" ሲል፣ ሌሎች ደቀ መዛሙርቱ እንደጠየቁት ይሁዳም "እኔ እሆን?" ብሎ ጠይቋል። ደቀ መዛሙርት ይህንን ሲሉ በራሳቸው ላይ እምነት እንዳልነበራቸው ያሳያል። ኢየሱስ ይህን ዓይነቱን አስደንጋጭ ነገር ከተናገረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ይሁዳ አስቆሮቱ ከመካከላቸው ቀስ ብሎ ወጥቶ ሄደ። ይሁዳ ቀስ ብሎ ሲወጣ፣ ጌታን አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ ነው ብሎ የተጠራጠረ ሰው ከመካከላቸው አልነበረም። በወቅቱ ገንዘብ ያዥ ስለነበረ ምናልባት ለድሆች አንዳንድ ነገር ለመግዛት የሄደ ሳይመስላቸው እንዳልቀረ እንገምታለን። የይሁዳ ዓላማ ግን ያ አልነበረም።

በዚያን ዘመን ወላጆች ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ፣ "ይሁዳ" የሚለውን ስም መስጠት የተለመደ ነበር። ይሁዳ አስቆሮቱ ጌታውን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ግን፣ ማንም ወላጅ ልጁን "ይሁዳ" ወይም ከሀዲ ብሎ መጥራት አይፈልግም። ይሁዳ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን የቻለው፣ እውነተኛ ማንነቱ ሳይታወቅ ሾልኮ በመግባት ሳይሆን፣ ኢየሱስ ራሱ ሌሎችን ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ እንደጠራቸው፣ እርሱም በዚያው ዓይነት መንገድ የተጠራ ነው። ገንዘብ ያዥ መሆን የቻለው ዝም ብሎ ሳይሆን፣ ሌሎች በእርሱ ላይ ከፍተኛ እምነት ስለነበራቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። በመጨረሻውም እራት ላይ የተቀመጠው በክብር ቦታ፣ ይኸውም ከክርስቶስ አጠገብ እንደነበረ እናውቃለን። ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት እንዲመቸው በመካከላቸው ተደብቆ የገባ ሰው አልነበረም። እንግዲያውስ ይሁዳ የእግዚአብሔርን ልጅ እንዴት አሳልፎ መስጠት ቻለ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እዚህ ላይ መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር፣ የከዳው ይሁዳ አስቆሮቱ ብቻ አለመሆኑን ነው። የተቀሩት ደቀ መዛሙርቱ በመከራው ጊዜ፣ ከኢየሱስ አጠገብ መገኘት በሚገባቸው ጊዜ ጥለውት የሸሹ መሆናቸውን፣ እንዲሁም ለክርስቶስ በጣም ቅርብ የነበረው ጴጥ

ሮስም "የምትሉትን ሰው በፍጹም አላውቀውም" ብሎ የካደው መሆ
ኑን እናውቃለን።

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሦስት ዓመት ትኩል አብሯቸው
በቆየበት ዘመን፥ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚሞት፥ ከሞት በሦስተ
ኛው ቀን እንዴት እንደሚነሳ የነገራቸውን፥ እንዴት ሊረሱት ቻሉ?
ረስተውት ካልሆነ ደግሞ እንዴት ማመን አቃታቸው? ብለን መጠየ
ቃችን አይቀርም። የይሁዳ አስቆሮቱ ጌታውን መካድ ከሌሎቹ የተለየ
ይሁን እንጂ፥ ይህን ያህል ከእነርሱ ክህደት በጣም የራቀ አልነበረም።
አንዳንዶቹ የገንዘብ ፍቅር ያሰከረው እንደሆነ አድርገው ያቀርቡ
ታል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን "ሰይጣን ገባበት" ነው የሚለው። በይሁዳ
ሕይወት ውስጥ "ሰይጣን የገባበት" ያለፈቃዱ እንዲሁ ሳይሆን፥ ሰይጣ
ንን ወደ ልቡ ለማስገባትና ለማስተናገድ ፈቃደኛ በመሆኑ ነው።
ኢየሱስ የሚመሠርተው የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ዙፋን የሚያ
ስጠጋ ብቻ ሳይሆን ወደ መስቀል የሚያደርስም መሆኑን ደቀ መዛሙ
ርቱ እየተረዱ ሲመጡ፥ ኢየሱስን እየሸሹት ሄዱ። ኢየሱስን በመካ
ዳት የታወቀው "ይሁዳ" ይሁን እንጂ፥ ኢየሱስን በመካድ የመጀመ
ሪያውም ሆነ የመጨረሻው አይደለም። ክርስቲያኖች በተሰደዱባቸው
ጊዜያት በታሪክ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ስለ እምነታቸው ሲሉ በቆራ
ጥነት ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ስለሰጡት ሰዎች ነው። ይሁን
እንጂ፥ ከሞት ለማምለጥ ሲሉ እምነታቸውን የካዱም መኖራቸውን
መዘንጋት የለብንም። ሁላችንም እንደ ይሁዳ አስቆሮቱ፥ እንደ ጴጥ
ሮስና እንደተቀሩት ደቀ መዛሙርት ጌታችንን የመካዳት ዝንባሌ እን
ዳለን መዘንጋት የለብንም። ምን ያህል ጊዜ ጌታችንን በልባችን፥ በም
ንኖረው ኑሮና በምንሰጠው አገልግሎት ሸሽተን እንደኖርን፥ እንደ
ካዳነው እኛ ብንዘነጋ የተከዳው ጌታ አይዘነጋውም። በጸጋው እየደ
ጋገመ ዕድል ባይሰጠን ኖሮ፥ እንደ ይሁዳ አስቆሮቱ ገና ድሮ ጠፍ
ተን በቀረን ነበር።

የኢየሱስ ነገር ብዙዎችን የሚያስደንቀው ለከዱት ሰዎች እንኳን
ፍቅሩ የማይለወጥ መሆኑ ነው። ይሁዳ አስቆሮቱ ኢየሱስን ሊገድሉ



የሚፈልጉትን ሰዎች እየመራ ሲመጣ፥ "ወዳጄ" ብሎ እንደጠራው እና
ውቃለን። ሌሎችም ደቀ መዛሙርት ጥለውት የሸሹ ቢሆኑም፥ ለእነ
ርሱ የነበረው ፍቅር አልተለወጠም። የራሱ ሕዝብ በስቅላት እንዲቀጣ
ለሮማውያን አሳልፈው ቢሰጡትም፥ "ስቀሉት! ስቀሉት!" እያሉ ቢጮ
ኹም፣ ከፍቅሩ የተነሳ ራቁቱን በሰማይና በምድር መካከል በተንጠለ
ጠለበት ወቅት፥ *"አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር
በላቸው"* ብሎ ጸለየላቸው። በክርስቶስ መስቀል አካባቢ፥ ወይም በመስ
ቀሉ ታሪክ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ይሁዳ አስቆሮቱና ጴጥሮስ
ናቸው። ሁለቱም ከክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መካከል ከፍተኛ ደረጃ
የነበራቸው ነበሩ። ሁለቱም ጌታ ያደርጋቸውን ተአምራት በቅርብ
ሆነው አይተዋል። ሁለቱም በፍርሃት፥ በድንጋጤና በተስፋ መቁረጥ
ውስጥ አልፈዋል። የክርስቶስ ሁኔታ እየከፋ ሲመጣ፥ ሁለቱም ጌታቸ
ውን ካዱት። ሁለቱም ጌታቸውን በመካዳቸው ከልባቸው አዝነዋል።

ጴጥሮስና ይሁዳ በብዙ ነገር ይመሳሰሉ እንጂ የሚለዩበት አንድ
ትልቅ ነገር ነበር። ይኸውም፥ ይሁዳ አስቆሮቱ በወሰደው እርምጃ፥
ጌታውን በመካዱና አሳልፎ በመስጠቱ በጣም ቢያዝንም፥ ሀዘኑ ንስሀ
ወደ መግባት አላመጣውም። "ላደረግሁት በደል ይገባኛል" ብሎ
በራሱ ላይ ስለ ፈረደ፥ ራሱን በገመድ አንጠልጥሎ ገደለ። በታሪክ
ውስጥ ዓለም የማይረሳው፥ ተወዳዳሪ የሌለው ከሃዲ ሆነ። ኢየሱስ ሊሰ
ጠው የሚችለውን ይቅርታ መቀበል እምቢ ብሎ ሞተ። ጴጥሮስ ግን፥
ጌታውን በመካዱ አዝኗል፤ ተዋርዷል፤ ነገር ግን የክርስቶስን የጸጋና
የይቅርታ መልዕክት ልቡን ከፍቶ በመቀበሉ፥ ይቅርታን አገኘ።
ከኢየሱስ ምሕረትና ይቅርታን የተቀበለ ጴጥሮስ፥ በኢየሩሳሌም
ውስጥ በነበረው ከፍተኛ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ዘመን፥ የብዙ
ዎች መዳን ምክንያት ሆነ። ጴጥሮስ በጸጸትና በዕንባ ሸለቆ ውስጥ
ካለፈ በኋላ፥ እስከ መጨረሻው ድረስ ለጌታው ታማኝ ሆኖ እንደ
ቆመ፥ ጌታው የቀመሰውን ዓይነት የሞት ጽዋ እስኪቀምስ ድረስ፥ ከጌ
ታው አጠገብ አንድም ጊዜ ቢሆን ወደ ኋላ ዞር አላለም። ያገኘውን
ሁለተኛ ዕድል እንደሚገባው ተጠቀመበት።

የታወቀው የስኮትላንዱ ጆርጅ ማትሰን በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሊገኝ ስለሚችለው ድል ሲናገር እንዲህ አለ።

"ነፍሴ ሆይ! ደክሞሽ፣ ከሰውነት ውጪ ሆነሽ በደረትሽ የተዘረረሽበትን ቦታ አላይም አትበይ። በሕይወታቸው ዕድሳት ያገኙበት ቦታ ምን ዓይነት ቦታ እንደነበረ እንዲናገሩ ወደዚህ ዓለም መጥተው ያለፉትን ታላላቅ ሰዎችን ጠይቂ! እውነተኛ ልምምዳቸው፣ እኔ ያለፍኩበትን ዓይነት ምቾት የሌለበት ሥፍራ መሆኑን ይነግሩሻል።

- አብርሃምን ብትጠይቂው፣ "የመስዋዕት በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል" ያለበት ሞሪያ ተራራ ላይ እንደሆነ ይነግርሻል።
- ዮሴፍን ብትጠይቂው ያለበደሉ የታሠረበት ጨለማ ቤት መሆኑንን ይነግርሻል።
- ሙሴን ብትጠይቂው፣ የበግ ጠባቂ ሆኖ በየሜካው የሮጠበት ጊዜ መሆኑን ይነግርሻል።
- ሩትን ብትጠይቂያት፣ ከጥዋት እስከ ማታ በእርሻዎች ውስጥ በመቃረም የደከመችበት ጊዜ መሆኑ ትነግርሻለች።
- ዳዊትን ብትጠይቂው አብዛኛው መዝሙሮች የሌሊት ዝማሬዎች እንደሆኑ ይነግርሻል።
- ኢዮብን ብትጠይቂው፣ እግዚአብሔር በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ መልስ እንደሰጠው ይነግርሻል።
- ጴጥሮስን ብትጠይቂው፣ በገሊላ ባሕር ራሱን ዝቅ አድርጎ በሰጠበት ጊዜ መሆኑን ይነግርሻል።
- ዮሐንስን ብትጠይቂው፣ ለብቻው በጳጥሞስ ደሴት የነበረበት ጊዜ እንደሆነ ይነግርሻል።



- ጳውሎስን ብትጠይቂው፣ ታላቅ የመንፈስ ሥራ በሕይወቱ የጀመረው በደማስቆስ መንገድ በኃይለኛ ብርሃን ተመትቶ ማየት ባልቻለበት ወቅት መሆኑን ይነግርሻል።
- የሰውን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ብትጠይቂው፣ በጌቴሴማኔ የደም ላብ እያላበው "ፈቃድህ ከሆነ ይህን ጽዋ ልጠጣው" ብሎ በቃተተበት ጊዜ እንደሆነ ይነግርሻል።

ስለዚህ ነፍሴ ሆይ! የአበባ ጉንጉንሽ በጌቴሴማኔ ነው። በብቸኝነትሽ ሰዓት ትከብሪአለሽ። በጭንቀትሽ ጊዜ ደስ ይልሻል። ዝማሬ ከውስጥሽ ፈንቅሎ የሚወጣው ምድረ በዳነት በሚሰማሽ ጊዜ ነው" አለ።

አደጋ፣ ጨለማ፣ መሸነፍ፣ ሞት ከፊታችን ሲሆን፥ ወደ ጌታ የምናሰማው የተስፋ መቁረጥ ጩኸት፣ እንደሚያድነን፣ ሕይወታችንን በብርሃንና በድል እንደሚሞላን እንወቅ።"

# በመታዘዝ ውስጥ መስቀል አለ (ማጠቃለያ ሃሳብ)

*"ሥጋን ከመግደል አልፈው ነፍስን መግደል የማይችሉትን ሰዎች አትፍሩ..."*
**(ማቴ. 10፡28)**

*ሕ*ይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ካስረከብን፣ ያለማወላውልና ያለማመንታት ለፈቃዱ ራሳችንን ካስገዛን፣ ያልጠበቅነውን ዓይነት ዋጋ ሊያስከፍለን ይችላል። ታዛዥነታችን እውነተኛና ከምንም ነገር ጋር የተያያዘ ካልሆነ፣ *"ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍለኝም ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ"* ካልን፣ መታዘዛችን በመስቀል ሕይወት ውስጥ ሊያሳልፈን ይችላል። ለዚህ ነው *"በመታዘዝ ውስጥ ሁልጊዜ መስቀል አለ"* የሚባለው። ራስን ለእግዚአብሔር ማስረከብ ማለት የግል ምኞትን መተው ብቻ ሳይሆን፣ እስከ ሞት ድረስ ራስን አሳልፎ መስጠትን የሚጠይቅ ነው። አንዳንዶቻችን ስለ ክርስቶስ ስንል የመስቀል ሞትን አንቀምስም ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ዓላማና ፈቃድ ለመፈጸም አስፈላጊ ከሆነ፣ ሕይወታችንን እንኳን አሳልፈን እስከ መስጠት ድረስ ሊያደርሰን ይችላል። ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍለን ቢሆንም እንኳን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ከመሆን የተሻለ ሌላ በጎና አስተማማኝ የሆነ ስፍራ በዓለም ላይ የለም። ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት፣ ኢየሱስ በጌቴሴማኔ የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ሆኖ ሲጸልይ፣ የደም ላብ ያላበው፣ እግዚአብሔር አብን *"እንደ ፈቃድህ ይሁን"* ሲል፣ የሚያስከፍ ለውን ዋጋ፣ የሚቀምሰውን የመስቀል ሞት አስቀድሞ ስላወቀ ነው።



በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መኖር ሰላምና ደስታ ያለበት ቢሆንም፣ ዋጋ ሳያስከፍል እንዲሁ የሚገኝ አለመሆኑን ማወቅ አለብን። እንደ ዲትሪች ባንሆፈር አነጋገር *"ኢየሱስ የጠራን፣ በሕይወታችን ተወራርደን እንድንሞትለት ነው።"* በዘመናት ብዙዎች የተሰጣቸውን መስቀል በታማኝነትና በቆራጥነት የተሸከሙት፣ ብድራታቸውን ትኩር ብለው በመመልከታቸው ነው። አስቴር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍላት እንደሚችል ብታውቅም፣ ራሷን መስዋዕት አድርጋ ለመስጠት ዝግጁ ነበረች። ለዚህ ነው *"...በሕግ የተከለከለ ቢሆንም ደፍሬ ወደ ንጉሡ ዘንድ እገባለሁ፤ ይህን በማድረጌ ብሞትም ልሙት" ያለችው (አስቴር 4፡16)።* በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ታሪካቸውን እንዳነበብነው፣ በእምነታቸው ጸንተው በመቆማቸው ሁሉም በተለያየ መንገድ የሞትን ጽዋ ቀምሰው ያለፉ ናቸው። እነዚህ ሰማዕታት ስደትን፣ መከራንና እንዲሁም በመጨረሻ ሞትን የቀመሱት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመኖር ምርጫቸውን ያደረጉ በመሆናቸው ነው።

አንዳንድ የዘመኑ ክርስቲያኖች ስለ እምነታችን ዋጋ ለመክፈል ፈሪዎች የሆንነው ለምን ይሆን? የክርስትና ሕይወት መስቀል የሌለበት፣ ሳቅና ፈንጠዝያ ብቻ የሞላበት፣ የምንፈልገውን ሁሉ የምናገኝበት መስሎ እንዲታየን የሆነበት ምክንያት ምን ይሆን? የምቾት ኑሯችን ገጸ-ባሕሪያችንን ደካማ አድርጎት ይሆን? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያየናቸው የእምነት አርበኞች የቀመሱትን መከራና መራራ የሞት ጽዋ ስንመለከት፣ የክርስትና እምነት ምንም ዓይነት ዋጋ የማያስከፍል፣ ርካሽ ሃይማኖት እንዳልሆነ እናረጋግጣለን። ክርስትናን ያለምርጫችን ተገደን የተቀበልነው እምነት አይሁን እንጂ፣ የአመንነው አጥብቀን ለመያዝ፣ መንፈሳዊ ጉዟችንን በመልካም ለመጨረስ፣ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍለን ማወቅ አለብን።

ያለመስቀል ክርስትና ስለሌለ፣ ከመስቀል ሸሽተን መኖር አንችልም። ከሁሉም የበለጠ የሚያሳዝነው ግን፣ አንዳንዶች "በመታዘዝ ውስጥ መስቀል እንዳለ" ባለማወቅ፣ ከመከራና ከችግር ነጻ ሆኖ መኖርን፣ እንደ በረከት አድርገው የሚቆጥሩ መኖራቸው ነው። በድፍረትና በቆራጥነት

ሕይወታቸውን የመሩትን፣ ስለ እምነታቸው ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉትን የእምነት አርበኞች ምሳሌ እንዲሆኑን የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ሰው ታሪካቸውን በዝርዝር ጽፎታል። *"...የተሰጣቸውን ተስፋ አገኙ፤ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፤ የእሳትን ኃይል አጠፉ፤ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፤ ከደካማነት ወደ ብርቱነት ተለወጡ፤ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፤ የወራሪ ጦችን ወታደሮች አባረሩ፤ ...ሌሎችም የበለጠ ትንሣኤ ለማግኘት አስበው ልዩ ልዩ ሥቃይ ተቀበሉ፤ ከእስራት ነፃ መሆንንም እምቢ አሉ። ሌሎች መዘባበቻ ሆነው ተገረፉ፤ ሌሎች በእግር ብረት ታስረው ወደ ወህኒ ቤት ተጣሉ፤ በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ተሰነጠቁ፤ በሰይፍ ተገደሉ፤ የበግና የፍየል ቆዳ ለብሰው ተንከራተቱ፤ ድኾችና ስደተኞች ሆነው ተንገላቱ፤ በበረሓ፣ በተራራ፣ በምድር ውስጥ ባሉ ዋሻዎችና ፈፋዎች ዞሩ..." (ዕብ. 11፡33-38) ይላል።*

እነዚህን በመከራ ውስጥ ያለፉትን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያደነቃቸውን ታላላቅ የእምነት አርበኞችን የዘመኑ "የብልጽግና ወንጌል አስተማሪዎች"፣ *"በመከራ ውስጥ ያለፉት እምነት ስለሌላቸው ነው"* በማለት እንደ ደካማ ክርስቲያኖች አድርገው እንደሚቆጥሯቸው እርግጠኞች ነን። እነዚህ መስቀል የሌለበት የክርስትና ሕይወት ለመኖር የሚሞክሩ፣ እግዚአብሔርን የሚያከብሩት ኃያል አምላክ በመሆኑ ሳይሆን፣ "አገኘን፣ ሆንልን" በሚሉት ምድራዊ ነገር ላይ ተመሥርተው ነው። የሚፈልጉትን ምድራዊ ነገር ካላገኙ፣ እግዚአብሔርን ያልሆነውን እንደ ሆነ አድርገው ይስሉታል። ለዚህ ነው መስቀል የሌለበትን የክርስትና ሕይወት እንደ በረከት የሚቆጥሩት።

መስቀል መሸከም በጥንት ዘመን ለነበሩት አማኞች ብቻ እንደሆነ፣ በአሁኑ ዘመን ያለነውን ክርስቲያኖች የማይመለከተን አድርገው የሚያስቡ ክርስቲያኖች እንዳሉ የታወቀ ነው። ስለ እምነታቸው የታረዱ ሰማዕታት ታሪክ የሚዘገንናቸው፣ ፈጽሞ መስማት የማይፈልጉ ናቸው። እርግጥ ነው ሁላችንም በተመሳሳይ መከራና ስደት ውስጥ ላናልፍ እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ ያለመስቀል ደቀ መዝሙር መሆን ስለማንችል፣ ሁላችንም የራሳችን የሆነ መስቀል አለን። ቢሆንም እግዚአብሔር



ልንሸከመው የማንችለው፣ ከአቅማችን በላይ የሆነ መስቀል እንደማያሸክመን ማወቅ አለብን። ከባድ እንኳን ቢሆን፣ ለመሸከም የሚያስችለንን ጸጋ አብሮ የሚሰጠን መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

ኢየሱስ *"የገዛ ራሱን መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ሰው የእኔ ሊሆን አይገባውም" (ማቴ. 10፡38) ይላል።* የራሳችን መስቀል ካለን፣ ኢየሱስ ምን እንድናደርግ ነው የጠየቀን? መስቀላችንን እንድንጎትተው ሳይሆን፣ እንድንሸከመው ነው። መስቀላችን ከጌታ የተሰጠን እንጂ፣ እኛ ራሳችን የምንፈጥረው፣ ወይም እኛ መርጠን የምንሸከመው አይደለም። መስቀላችንን መሸከም ያለብን በደስታ እንጂ፣ በእልህ ወይም እየተነጫነጭንና እያጉረመረምን አይደለም። በፍርሃት ሳይሆን በድፍረት ተሞልተን የምንሸከመው ነው። መስቀላችንን የምንሸከመው ለዘላለም ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ስለሆነ፣ በትዕግሥት እስከ መጨረሻው ልንሸከመው ይገባል። መስቀላችን በሰው እጅ የተሠራ ተራ መስቀል ሳይሆን፣ የተቀደሰ ሸክም፣ ከክርስቶስ ጋር የሚያቀራርበንና የሚያያይዘን ሸክም ነው።

*መስቀሉን እንድንሸከም ጌታችን ያዘዘን ለምን ይሆን?*

*መስቀሉን ሳንሸከም ደቀ መዝሙር መሆን ስለማንችል፣*

*የክርስቶስ ፍቅር ግድ ስለሚለን፣*

*እርሱ ራሱ ስለተሸከመው፣*

*የምንሸከምበትን ጸጋ ስለሚሰጠን፣*

*መስቀሉን ሳንሸከም አክሊል ልናገኝ ስለማንችል ነው።*

ክርስቶስ *"መስቀል ተሸክማችሁ በዚህ ሂዱ!"* ሲለን ብቻችንን፣ እርሱ ባልሄደበት፣ እርሱ ባልተራመደበት መንገድ እንድንሄድ አይደለም። በመንገዳችን ላይ እግሮቻችንን የሚያቆስል ነገር ቢያጋጥመን፣ ከእኛ በፊት የኢየሱስንም እግሮች ያቆሰሉና ያደሙ መሆናቸውን አንዘንጋ።

- *አልፎ አልፎ መንገዳችን ጨለማ ቢሆንብን፣ ኢየሱስም ከዚያ በከፋ ጨለማ ውስጥ አልፏል።*
- *በመንገዳችን ላይ ከፍተኛ ውጊያ ቢያጋጥመን፣ ኢየሱስም በዚያ ትግል ውስጥ አልፏል።*
- *መስቀሉን ለመሸከም ከባድ ቢሆንብን፣ እርሱ ከተሸከመው መስቀል ጋር ስናስተያየው፣ እኛ የተሸከምነው መስቀል ቀላል እንደሆነ እንረዳለን።*
- *መንገዱ ከባድና በጣም አስቸጋሪ ቢሆንብን፣ ከክርስቶስ ጋር እስካገናኘን ድረስ እንወደዋለን እንጂ አንጠላውም።*
- *ኢየሱስን መከተል ማለት ከእርሱ ጋር ሕብረት መፍጠር ነው። ኢየሱስ "የገዛ ራሱን መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ሰው የእኔ ሊሆን አይገባውም" ስላለ፣ ያለመስቀል የእርሱ መሆን አንችልም። ከእርሱ ጋር ሕብረት በመፍጠር የሚገኘው ደስታ በቃላት ልንገልጸው ከምንችለው በላይ ነው። ክርስቶስ መስቀሉን እንድንሸከም ሲጠራን፣ "የፍቅሬ ተካፋይ ሁኑ" ማለቱ እንደሆነ እንወቅ።*

*ጌታ ሆይ! መስቀልህን ተሸክመን እንድንከተልህ እርዳን። አሜን!*



## ዋቢ ጽሁፎች

## Bibliography

*Bauman, Harold E. From the Mennonite Pulpit, Herald Press, Scottdale, PA. 1965.*

*Bonhoeffer, Dietrich. The Cost of Discipleship, The Macmillan co. New York c1959.*

*King, Marie Gentert Ed. Foxes Book of Martyrs, A Jove Book, New York, NY 1968.*

*Ogilvie, Lloyd John. Conversation with God, Harvest House Publishers, Eugene, Oregon, 1992.*

*Philips, Keiths. The Making of a Disciple, Fleming H. Revell Co., Old Tappan, New Jersey, c1960.*

*Smith, Gerald B. ed. Men Who Met God, Christian Publications, Camp Hill, PA, 1986.*

*Theodore W. Engstrom, Theodore W. ed. Great Sermon by Great American Preachers, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI.*

*Unknown Christian. How to Live the Victories Life, Zondervan Publishing House, Gran Rapids, Michigan.*

*Warren, Kay. Say Yes to God, Zondorvan, Grand Rapids, Michigan, 2007.*